# የኢማን ምጥቀት መለኪያዎች

## ወቅፍ ዘካና አገልግሎት

በዑስማን ኑሪ ቶፕባሽ
Osman Nuri TOPBAS

ትርጉም:- ሐድያ መሀመድ
አርታዒ:- ሐሰን ታጁ

አሳታሚ:- አልበያን ሊሚትድ

# የኢማን ምጥቀት

# መለኪያዎች

*ስልክ ቁጥር ፡- 0913878788 ወይም 0911199822*
*አዲስ አበባ ኢትዮጵያ*

የአሳታሚው መብት በሕግ
የተጠበቀ ነው።
All rights are reserved
አንደኛ እትም ጥር 2003

AFKAD 4

*Addis Ababa Ethiopia*

First Edition Jan.2011

# ማውጫ


**ርእስ** **ገጽ**

**ምዕራፍ አንድ ....... 6**

**እምነትን በሙሉ ፍቅርና ስሜት ማራመድ ....... 6**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 9**

**ምዕራፍ ሁለት ....... 37**

**ኢኽላስ (ፍጹምነት) ....... 37**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 40**

**ምዕራፍ ሶስት ....... 55**

**ተቅዋ ....... 55**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 60**

**ምዕራፍ አራት ....... 69**

**ተውባና እስቲግፋር ....... 69**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 74**

**ምእራፍ አምስት ....... 83**

**አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) መታዘዝ ....... 83**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 84**

**ምዕራፍ ስድስት ....... 97**

**በአምልኮ ጥንቁቅ መሆን ....... 97**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 98**

**ሀ- ነዋፊል (ሱና) የአምልኮ ተግባራት ....... 110**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 112**

**ለ- ሶላትን በጀማዓ (በኅብረት) መስገድ ....... 120**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 122**

**ሐ- የሌሊት ሶላት (ተሃጁድ) ....... 136**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች ....... 141**

**መ. ሶላትና ዱዓ (ፀሎት) ....... 150**

| ርእስ | ገጽ |
|---|---|


**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች........................................152**

**ሠ- ትህትና (ተዋዱዕ) እና ኹሹዕ.....................................167**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች........................................169**

**ምዕራፍ ሰባት.......................................................177**

**ከቅዱስ ቁርዓን ጋር መተሳሰር.......................................177**

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች........................................181**

**ምዕራፍ ስምንት.....................................................194**

**ዚክር ማድረግና ሰለዋት ማውረድ**..................................194

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች**........................................200

**ምዕራፍ ዘጠኝ**.......................................................212

**ለሞትና ለመጪው ዓለም መዘጋጀት**..................................212

**የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች**........................................216

# ምዕራፍ አንድ

# እምነትን በሙሉ ፍቅርና ስሜት ማራመድ

እምነት የአእምሮ ብርሃን ነው። የሕሊና መወልወያ መሣሪያ ነው። ልብን ማለስለሻ ቅባት ነው። አላፊና ጠፊ ከሆነችው ከዚህችኛዋ ዓለም ወደ ቀጣዩ ዓለም በስኬትና በደስታ ለመጓዝ ልባዊ እምነት ወሳኝ ነው። የእምነት ብርሃን የተነፈገች ነፍስ መጨረሻዋ ውርደት እንጂ ሌላ አይደለም።

የሰው ልጆች በምድር ላይ ሕልውና አግኝተው መኖር ከጀመሩ አንስቶ ያለ እምነት እንዳይባዝኑና እንዳይዋትቱ መለኮታዊ አመራርና ነቢያት በየዘመናቱ ሲላኩላቸው ቆይተዋል። የአላህ ወዳጆች በእነዚህ ሁለት መመሪያዎች እየታገዙ የሕይወታቸውን ቅኝት ሲያስተካክሉና ሲመላለሱ ኖረዋል፤ እየኖሩም ነው። በታሪክ ዘመናት ሁሉ ነቢያት፣ ቅዱሳንና ሷሊሆች ለግሳፄ የሚያመች የሆነን ታላቅ ምሳሌ ለየኖሩበት ማኅበረሰብ እየተው አልፈዋል።

እምነት ሲባል ከመለኮት የሚሰጥ የሆነ ምርጥ ፀጋ ነው። በምድር ላይ የሰው ልጅ ፈተናዎች ያጋጥሙታል። አንድ አማኝ በመከራና በፈተና ጊዜያቶች የሚያሳየው ትእግስትና የአላህን ፍርድ ወድዶ መቀበሉ በመጪው ዓለም ለሚያገኘው ታላቅ የሆነ ሽልማት እንደሚከፍለው ቤዛ ይቆጠራል። የአለማት ጌታ አላህ ባሮቹ የሚከፍሉትን ይህን መስዋእት እንደታላቅና እምነታቸውን ከፍ የሚያደርጉበት አጋጣሚ በማየት ከፍ ያለ ግምት ይሰጠዋል።

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ ٱشۡتَرَىٰ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ أَنفُسَهُمۡ وَأَمۡوَٰلَهُم بِأَنَّ لَهُمُ ﴾ التوبة: ١١١

*"አላህ ከምእመናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለእነርሱ ብቻ ያላቸው በመሆን ገዛቸው። (አት-ተውባ፡ 111)*

ይህ የቁርአን አንቀጽ ለዚህ እውነታ ትክክለኛ ማሳያ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው እምነቱን የተሟላ ለማድረግ ሕይወቱን፣ ገንዘቡንና ንብረቱን በአላህ መንገድ ላይ መሰዋት ይጠበቅበታል ማለት ነው። ይህንን ማድረጉ የአላህን ውዴታ ለማግኘት ወሳኝ ነው።

በሕይወት አውድ ላይ አማኞች የሚያጋጥማቸውን ፈተናና ትግል በጽናት ተቋቁመው በአላህና በመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) መንገድ ላይ በመሆን ፍፃሜያቸውን በዚሁ ረክተው እንዲያሳርጉ ይጠበቅባቸዋል።

እያንዳንዱ አማኝ የሆነ ሰው የልቅና ባለቤት የሆነውን አላህን ውዴታ ለማግኘት ብዙ ዋጋዎችን የመክፈል ግዴታ አለበት። አንድ ሰው ያልለፋበትንና ምንም ዋጋ ያላወጣበትን ነገር የራሱ ለማድረግ በመጣሩ ግዜውን ያለአግባብ ከማባከን ውጪ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም።

በእምነት ደረጃዎች ወደ ላይ ከፍ ለማለት መልካም ሥራዎችን አብዝቶ መሥራት ላይ የግድ መሆኑን ማወቁ ጥበብ ነው። መልካም ሥራ ማለት ደግሞ ጥሩ ሥነ-ምግባር፣ እውነተኛ ንያ (እሳቤ) እና አላህን የሚያስደስት የሆነ ንግግርና ድርጊት እንጂ ሌላ አይደለም። ለዚህም ነው በቁርአንና በነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ.) ሐዲሶች እምነትና መልካም ተግባር ተቆራኝተው በብዛት የሚጠቀሱት። እምነት ሲባል እንዲሁ ደረቅ የሆኑ ሃቆችን በነባቤ ቃል ማነብነብ ሳይሆን ሃቅን መረዳት፣ ከዚያም በልብ ውስጥ አምኖ መቀበል፣ እንዲሁም በስብእና ላይ በማንፀባረቅ መግለጽ ነው።

እምነት ከአምልኮ ይልቅ ከፍ ያለ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው። አላህን እንደሚገባውና እርሱ እንደሚፈልገው አድርጎ ማምለክ የሚቻለው እምነት ሲኖር ነው። አምልኮትን ለማከናወን የሚያስፈልጉን ጊዜያት ከቀን ውስጥ የተወሰኑ ናቸው። ለምሳሌ ሶላትን ብንወስድ የሚሰገደው በቀን ውስጥ ለአምስት ጊዜያት ያክል ብቻ ነው። እምነትን ካየን ግን በእያንዳንዷ ቅጽበት በልባችንና በስብእናችን ውስጥ የሚያድርና የሚገለጽ ረቂቅ ነገር ነው። ለዚህም ነው ልባችንን ከሚያደንዙና ግዴለሽ እንድንሆን ከሚያደርጉ ኃጢአቶች ሁልጊዜም መራቅና መጠንቀቅ

የሚኖርብን፡፡ እንዲሁም እምነታችን እንዲያብብና እንዲያፈራ በየጊዜው መልካም ምግባራትን እየፈፀምን መንከባከብ አለብን፡፡ (ይህም ልክ እንደ መንፈሳዊ ጋሻ ነው ማለት ነው፡፡)

የእምነትን ጌጥ በልቡ ማኖር ለአንድ አማኝ ሰው ከምንም በላይ ታላቅ የሆነ ሃብቱ ነው፡፡ ሰይጣን በቁርአን እንደተጠቀሰው ሁልጊዜም የእኛ የሰው ልጆች ጠላት ነው፡፡ ስለሆነም የእርሱ የምንጊዜም ጥረት በአማኝ ሰው ልብ ውስጥ የሚገኝን የእምነት ጌጥ መስረቅና በእርኩስ ሃሳብና ምኞት መሙላት ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ የተለያዩና ብዛት ያላቸው ዘዴዎችንና ሹክሹክታዎችን ይጠቀማል፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَلَمْ أَعْهَدْ إِلَيْكُمْ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ أَن لَّا تَعْبُدُواْ ٱلشَّيْطَٰنَ ۖ إِنَّهُۥ لَكُمْ عَدُوٌّ مُّبِينٌ ﴿٦٠﴾ وَأَنِ ٱعْبُدُونِى ۚ هَٰذَا صِرَٰطٌ مُّسْتَقِيمٌ ﴿٦١﴾ وَلَقَدْ أَضَلَّ مِنكُمْ جِبِلًّا كَثِيرًا ۖ أَفَلَمْ تَكُونُواْ تَعْقِلُونَ ﴿٦٢﴾ ﴾ يس: ٦٠ - ٦٢

*“የአደም ልጆች ሆይ! ሰይጣንን አትገዙ፡፡ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና፤ በማለት ወደእናንተ አላዘዝኩምን? ተገዙኝም ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው (በማለትም)፡፡ ከእናንተም ብዙን ፍጡር በእርግጥ አሳስቷል፤ የምታውቁም አልነበራችሁምን?” (ያሲን:60-62)*

ከዚህ ሁኔታ የምንወስደው ተግሳጽ ሁልጊዜም ቢሆን ልባችንን የመጠበቅና የመንከባከብ ወሳኝ ትግል ማድረግ ያለብን መሆኑን ነው፡፡ ልባችንን መጠበቅ ከቻልን ሁልጊዜም በእምነት የጋለና በጐ ምግባራትን ለመከወን የተነሳሳ ይሆናል፡፡ በመልካም ሥራ ላይ ዘውታሪ በመሆንም የማይናወጽ አቋም ይኖረናል፡፡ የእምነታችን ጌጥ እንዲጎላና ይበልጥ እንዲደምቅ የአላህን ታላቅነት ማወጅና በጐ ምግባራትን ማብዛት እንዲሁም አላህን ዘወትር ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ አላህን ማስታወስ ማለት የአላህን ስሞች፣ ባሕሪያትና አጠቃላይ በፍጥረተ ዓለም ውስጥ የሚያደርገውን ማስተናበር ወዘተ እያሰቡ እርሱን ማውሳትና ስሙን ከፍ ከፍ ማድረግ ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ልብ (ቀልብ) ከገፍላ (ግዴለሽነትና)

ከጭንቀት ትላቀቃለች፡፡ እንዲሁም የእምነትን ጥፍጥና ታጣጥማለች፡፡ ፍፁም ሰላምና መረጋጋትም ይሰፍንባታል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱذۡكُر رَّبَّكَ فِي نَفۡسِكَ تَضَرُّعٗا وَخِيفَةٗ وَدُونَ ٱلۡجَهۡرِ مِنَ ٱلۡقَوۡلِ بِٱلۡغُدُوِّ وَٱلۡأٓصَالِ وَلَا تَكُن مِّنَ ٱلۡغَٰفِلِينَ ٢٠٥ ﴾ الأعراف: ٢٠٥

*"ጌታህንም በምስጢር ተዋድቀህና ፈርተህ ከጩኸት በታችም በሆነ ቃል በጧትም በማታም አውሳው፡፡ ከዘንጊዎቹም አትሁን፡፡" (አል-አዕራፍ፡ 205)*

አላህን በማስታወስና ፈቃዱን በመሙላት የምጥቀት ደረጃ ላይ የደረሱ ባሪያዎቹ በዚህ ዓለም ላይ የሚገጥማቸውን ችግርና መከራ አሳንሰው ነው የሚያዩት፡፡ ምክንያቱም በሞት፣ በቀብር ውስጥና በዚያኛው ዓለም ያለውን መከራ ከዚህችኛዋ ዓለም መከራ ጋር ሲያነጻጽሩት የዚህችኛዋ ዓለም መከራ እዚህ ግባ የሚባል ሆኖ ስለማያገኙት ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ካንፀባረቋቸው ሥፍር ቁጥር የሌላቸው የሰናይ ምግባራት መገለጫዎች መካከል ትእግስትን፣ ይቅርባይነትን፣ ጽናትን፣ አርቆ አስተዋይነትን፣ መስዋእትነትን የሚመለከቱ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እናያለን፡፡ እንዲሁም በእርሳቸው እነፃ ከታላቅ የስብእና ቁንጮ ላይ የደረሱ ተከታዮቻቸውን የእምነት ትሩፋቶችም እንቃኛለን -በአላህ ፈቃድ፡፡

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ገና የ12 አመት ታዳጊ እያሉ በሂራ የሚባል አንድ መነኩሴ እንዲህ አላቸው፡-

"አንተ የምወድህ ልጅ! በአል-ላትና በኡዛ ይሁንብህ የምጠይቅህን መልስልኝ፡፡" በዚህ ጊዜ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡- "በላትና በኡዛ ስም ምንም ነገር እንዳደርግ አትጠይቀኝ፡፡ በአላህ ይሁንብኝ!

እነዚህን ሁለት ጣኦታት የምጠላና የምጸየፈውን ያህል ሌላ ነገር አልጠላም።”

በዚያ የእድሜ ደረጃቸው ላይ ሆነው እንኳን የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ራሳቸውን ከጣኦታት ምን ያህል ያርቁ እንደነበር መገንዘብ አይከብድም። በኋለኞቹ ዘመናት እድሜያቸው 40 ከሆነ በኋላ የነቢይነት ተልእኳቸውን ሲጀምሩ ቀድሞ በፊጥራ (ተፈጥሮ) ይፀየፏቸው የነበሩ ጣኦታትን በመለከታዊ ብርሃን በመታገዝ በግልጽ ማውገዝና ሕዝብን ማስተማር ዋነኛ ዓላማቸው ሆነ።

በፈርኦን ጊዜ የነበሩ አስማተኞች የነቢዩላህ ሙሣን (ዐ.ሰ.) ተዓምር ካስተዋሉ በኋላ የእርሱን አምላክነት በማስተባበላቸው ሊሸከሙት የሚከብድ መከራ ሊቀበሉ ግድ ሆነ። ይሁን እንጂ እነርሱ ይህንን መከራ ከእምነታቸው ጽናት በመነጨ ድፍረት ፊት ለፊት ተጋፈጡት እንጂ ወደ ኋላ አላፈገፈጉም። እንዲህ ነበር ፈርኦንን ያሉት፡-

﴿ قَالُوا۟ لَن نُّؤۡثِرَكَ عَلَىٰ مَا جَآءَنَا مِنَ ٱلۡبَيِّنَٰتِ وَٱلَّذِي فَطَرَنَاۖ فَٱقۡضِ مَآ أَنتَ قَاضٍۖ إِنَّمَا تَقۡضِي هَٰذِهِ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَآ ﴿٧٢﴾ ﴾ طه: ٧٢

*“ከመጡልን ተአምራቶችና ከዚያም ከፈጠረን (አምላክ) ፈጽሞ አንመርጥህም። አንተም የምትፈርደውን ፍረድ። የምትፈርደው በዚህች በአነስተኛይቱ ሕይወት ብቻ ነው አሉ።” (ጣሃ:72)*

ፈርኦንም የእነዚያን ሰዎች እጆችና እግሮች እያፈራረቀ (ማለትም ቀኝ እጅና ግራ እግር ወይም ግራ እጅና ቀኝ እግር) ቆረጠ። በዘንባባ ግንዶች ላይ ከመሰቀላቸው በፊትም የቀራቸውን እጆች ወደ ሰማይ ከፍ አድርገው በጌታቸው ፊት ፍጹም በመተናነስ እንዲህ አሉ፡-

﴿ رَبَّنَآ أَفۡرِغۡ عَلَيۡنَا صَبۡرٗا وَتَوَفَّنَا مُسۡلِمِينَ ﴿١٢٦﴾ ﴾ الأعراف: ١٢٦

*“...ጌታችን ሆይ! በእኛ ላይ ትእግስትን አፍስስ። ሙስሊሞችም ሆነን ግደለን።” (አል-አዕራፍ:126)*

ኃያሉን ጌታቸውን እንዲያስጠጋቸው ተማፀኑት፡፡ ከዚያም ሰማእት (ሸሂድ) ሆነው ወደርሱ በመሄድ እስከፍርዱ ቀን ድረስ በመደሰቻ ገነት ውስጥ ይቆያሉ፡፡

የኢየሱስን ትምህርት በቀጥታ ተከትለው አላህን ሲያመልኩ የኖሩ የጥንቶቹ ሰዎች በሰርከስ ትርዒት ማሳያ በታዎች ላይ ለአንበሳ እየተጣሉ (እየተሰጡ) በታላቅ ስሜትና ፍቅር ሸሂድ (ሰማእት) ሆነዋል፡፡

በሰማእታት መዝገብ ውስጥ ስማቸው በክብር ያረፈው ሌሎቹ ጀግኖች ደግሞ የየመን አሃዳዊ ክርስቲያኖች ሲሆኑ በቁርአን አስሃቡል-ኡኽዱድ (የጉድቡ ወይም ጉድጓዱ ባለቤቶች) በመባል ይታወቃሉ፡፡ የመንንና አካባቢዋን በዘመኑ ይገዛ የነበረው ዙነዋስ የተባለ የሂሚዮር ሥርወ-መንግስት ንጉስ በ3ኛው መቶ (ዓ.ል) የነጅራን አሃዳዊ ክርስቲያኖችን ኃይማኖታቸውን ለማስቀየር ይኽ ነው የማይባል የቁም ስቅል አድርሶባቸዋል፡፡ ይህንን ተቋቁመው በኃይማኖታቸው በመጽናታቸው ከነሕይወታቸው የእሳት ጉድጓዶች ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሃያ ሺህ የሚሆኑ ሰዎች እንደሞቱ ይነገራል፡፡ ሆኖም ግን እነዚያ ጨቋኞችና ከሃዲያን በመሆናቸው የአላህን ኃይማኖት በግልጽ ሲቃወሙና ተከታዮቹንም ይህን በመሰለ የቁም ስቃይ አበሳቸውን ሲያሳዩዋቸው የቆዩት ዙነዋስና ተከታዮቹ በዚህች በቅርቢቱ ዓለም ለስኬት አልታደሉም፡፡ በመጪውም ዓለም ወደተጋጋመችው የጀሃነም እሳት ይመለሳሉ፡፡ ማለቂያ ለሌለው ዘመንም አካላዊና ሕሊናዊ ፍዳቸውን ያያሉ፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُتِلَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡأُخۡدُودِ ٤ ٱلنَّارِ ذَاتِ ٱلۡوَقُودِ ٥ ﴾ البروج: ٤ - ٥

*“የጉድቡ ባለቤቶች ተረገሙ፡፡ የማገዶ ባለቤት የሆነችው እሳት (ባለቤቶች) ፡፡” (አል-ቡሩጅ፡ 4-5)*

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባ የነበረችው ሱመያ በዚያ በተባረከ የኢስላም የመጀመሪያ ወቅት ለኃይማኖቷ ብላ ነፍሷን ስለከፈለችና በቁረይሽ ከሃዲያን ስለተገደለች የመጀመሪያዋ እንስት ሰማእት (ሸሂድ) ለመሆን

ታድላለች፡፡ ሱመያ (ረ.ዐ.) አማኝ ከመሆኗ በፊት ሰውነቷን እሾህ ሲቧጥጠው እንኳን እጅግ ትፈራና ትደነግጥ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ልቧ በእምነት ካጌጠና አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ከምንምና ከማንም በላይ ከወደደች በኋላ ከሃዲያኑ ያዘጋጁትን የጋለ ብረት ተቋቁማለች፡፡ ኃይማኖቷንም ለድርድር አላቀረበችም፡፡ ባለቤቷ ያሲርም ምንም እንኳን በእድሜ የገፋና ደካማ ቢሆንም በትእግስትና በታላቅ ጽናት ነበር ሞቱን የተቀበለው፡፡ በመጨረሻም ለታላቅ ስኬት በመታደሉ ሰማእት (ሸሂድ) ለመሆን በቃ፡፡ የያሲር ቤተሰቦች በእርግጥም የኢስላም የመጀመሪያዎቹ ሰማእታት ናቸው፡፡ ለታላቁ ፀጋ የሚከፈለውን ውድ ዋጋ ከፍለው ምኞታቸውን ያገኙ ጀግኖች ነበሩ፡፡

ቢላል (ረ.ዐ.) በሚደርስበት መከራ ደሙ እንደውሃ ቢንጠባጠብና ከሰውነቱ ላይ ደርቆ ቢደድርም ፍንክች የሚል አልነበረም፡፡ አረመኔና እንስሳዊ ተፈጥሮ በነበራቸው አጋሪ ሰዎች የቱንም ያህል መከራና ግፍ ቢፈፀምበት አሃድ! አሃድ! አሃድ! ከማለት ውጪ አንዳችም ቃል አይናገርም ነበር፡፡ በዚያ ሁሉ የስቃይ ዶፍ ውስጥ አላህን የመገናኘት ጣፋጭ ደስታ ከሰማይ እንደሚወርድ ጠል ልቡን ሲያረሰርሰው ይሰማው ነበር፡፡

ኡመር (ረ.ዐ.) በኸሊፋነታቸው ጊዜ ከመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች አንዱ የሆነውን ኸባብ ኢብን አረት (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ጠየቁት፡-

“በአላህ መንገድ ላይ ሆነህ ከደረሰብህ ስቃይ የተወሰነውን ልታጫውተን ትችላለህ?”

ኸባብ እንዲህ አለ፡-

“የምእመናን አዛዥ ሆይ! ጀርባዬን መመልከት ይችላሉ፡፡”

ኡመር (ረ.ዐ.) የኸባብን ጀርባ ካስተዋሉ በኋላ በጣም ተሳቀቁ፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡- “በሕይወቴ ሁሉ እንዲህ ዓይነት ግፍ የተፈፀመበት ጀርባ አይቼ አላውቅም፡፡”

ኸባብ (ረ.ዐ.) ንግግሩን ቀጠለ ፡-

“ከሃዲያኑ እሳት ያነዱና ልብሴን እንዳወልቅ ካደረጉ በኋላ በጀርባዬ እሳቱ ላይ ያስተኙኛል፡፡ በመጨረሻም እሳቱ ከቆዳዬ ሥር እየቀለጠ በሚወጣው የፈሳሽ እንጥብጣቢ ይጠፋል፡፡”

ከሃዲያኑ የጋለ ብረትና ድንጋይ በመቆንጠጫ እየያዙ በኸባብ (ረ.ዐ.) ጀርባ ላይ ያደርጉበት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም ከሥቃዩ የተነሣ ብዙውን ጊዜ አቅሉን ይስት ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን እነርሱ የሚፈልጉትን የክህደት ቃል ፈጽሞ ከአንደበቱ አውጥቶላቸው አያውቅም፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የአላህና የመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ውዴታ የደረሰበትን ምድራዊ መከራ ሁሉ እንዲቋቋም ጽናትን ይሰጠው ስለነበር ነው፡፡

ኸባብ እንዲህ ይላል፡-

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በካዕባ ጥላ ሥር መጐናፀፊያቸውን ተንተርሰው ሳሉ፡- ‹‹ከአላህ እርዳታ ለምን አይጠይቁልንም? ለምንስ አይፀልዩልንም?›› ብለን ስሞታ አቀረብን፡፡ እርሳቸውም እንዲህ አሉን፡-

“ከእናንተ በፊት ባለፉት ሕዝቦች ዘመን አንድ አማኝ ሰው ይያዝና ጉድጓድ ተቆፍሮለት እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ከዚያም መጋዝ ይመጣና ከራሱ ላይ ተደርጐ ለሁለት ይሰነጠቃል፡፡ ሥጋው ከአንጥንቱ በብረት ሜንጦ ይላጋል፡፡ ይህ ሁሉ ከኃይማኖቱ አይመልሰውም ነበር፡፡ በአላህ እምላለሁ! አንድ ተጓዥ ከሰንአ እስከ ሐድረመውት ከአላህ በጎቹን ተኩላ እንዳያገኝበት ካልሆነ በስተቀር ሌላ የሚፈራው ነገር ሳይኖር እስከሚጓዝ ድረስ አላህ ይህን ተልእኮ ከግቡ ያደርሳል፡፡ ዳሩ ግን እናንተ ትቻኮላላችሁ፡፡” (ቡኻሪ የዘገቡት)

የኢስላም ጠላቶች ሱሃይብን (ረ.ዐ.) አቅሉን እስኪስት ድረስ ነበር የሚደበድቡት፡፡ ይህ ድብደባም ሱሃይብ (ረ.ዐ.) ወደ መዲና እስኪሰደድ ድረስ አልተቋረጠም ነበር፡፡ በመጨረሻም ተሳካለትና ወደ መዲና የሚወስደውን ጉዞ ብቻውን ተያያዘው፡፡ ሆኖም ግን ከመካውያን አጋሪዎች የተወሰኑት ይከተሉት ስለነበር ከደረሱበት በኋላ እንዲህ አሉት፡-

“ወደ መካ ስትመጣ ድሃና ያጣህ የነጣህ ደካማ ሰው ነበርክ፡፡ በመካከላችን ሆነህ ብዙ ሃብት ሰበሰብክ፡፡ አሁን ደግሞ ሃብትህን ጭነህ ያለችግር ልትኮበልል ታስባለህን? በአላህ ይሁንብን! እንዲህ እንዲሆን አንፈቅድም፡፡”

ሱሃይብ (ረ.ዐ.) በዚህ ጊዜ ፈጠን ብሎ ከመጓጓዣው እንስሳ ላይ በመውረድ ከኮረጆው ላይ ጥቂት የቀስት ፍላጻዎችን አወጣና እንዲህ አላቸው፡-

“የቁረይሽ ሰዎች ሆይ! ተወዳዳሪ የሌለኝ ዓላሚ ቀስተኛ መሆኔን ታውቃላችሁ፡፡ በአላህ ይሁንብኝ ልትጠጉኝ ከሞከራችሁ እነዚህን ሁሉ ቀስቶች አንድ በአንድ አስወነጭፋቸዋለሁ፡፡ አረሮቹ ሲያልቁብኝም ሰይፌን ከሰገባው አወጣለሁ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ወደእኔ ልትጠጉ እንደማትችሉ ታውቃላችሁ፡፡ ለመሆኑ ሃብቴን ያስቀመጥኩበትን ቦታ ብነግራችሁ ወደፈለግኩት እንድሄድ መንገዱን ትለቁልኛላችሁን?”

ይህንን ንግግር የሰሙት አጋሪዎች በዚህ ሃሳብ እንደሚስማሙ ገለጹ፡፡ ከዚያ በኋላ ሱሃይብ ሃብቱን የት የት ቦታ ላይ እንዳስቀመጠው ሲነግራቸው መንገዱን ለቀቁለት፡፡ ከረቢኡል አወል ወር አጋማሽ በኋላ ነበር መዲና አቅራቢያ ከሚገኘው ቁባ ከተባለው መንደር የደረሰው፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጋርም እንደገና ተገናኙ፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዳዩትም ፈገግ ብለው እንዲህ አሉት፡- “ሱሃይብ አሸነፈ! ሱሃይብ አሸነፈ! አባ ያህያ ሆይ! ገቢያህ በእርግጥ ትርፋማ ነበር፡፡ ገቢያህ ትርፋማ ነበር፡፡”

የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ የወረደው በዚህ ክስተት ምክንያት እንደሆነ ዘገባዎች ያስረዳሉ፡-

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَشۡرِي نَفۡسَهُ ٱبۡتِغَآءَ مَرۡضَاتِ ٱللَّهِۚ وَٱللَّهُ رَءُوفُۢ بِٱلۡعِبَادِ ٢٠٧ ﴾ البقرة: ٢٠٧

*“ከሰዎችም ውስጥ የአላህን ውዴታ ለመፈለግ ነፍሱን የሚሸጥ ሰው አልለ። አላህም ለባሮቹ በጣም ሩህሩህ ነው።” (አል-በቀራህ፡207)*

ዚኒራ (ረ.ዐ.) ሌላዋ ሴት ሶሃባ ስትሆን በቁረይሽ ከሃዲያን ብዙ ስቃይን ቀምሳለች። አቡ ጃህል ባደረሰባት ግርፋት የዓይኗን ብርሃን እስከማጣትም ደርሳለች።

አቡ ጃህል የአይኗን መጥፋት ካስተዋለ በኋላ እንዲህ አለ፡- “ላትና ዑዛ እንዳሳወሩሽ አየሽን?” ዚኒራ (ረ.ዐ.) ግን እንዲህ በማለት መለሰች፡-

“በአላህ ይሁንብኝ! እነርሱ አይደሉም አይኔን ያጠፉት። ላትና ዑዛ ጥቅምም ሆነ አንዳች ጉዳት ሊያመጡ አይችሉም። አላህ ግን የዓይን ብርሃኔን ሊመልስልኝ ቻይ ነው!”

ሲነጋ በዘላለማዊ የመንፈስ ጨለማ የተጋረዱት አጋሪዎች በአላህ እዝነት የዚኒራ የዓይን ብርሃን ተመልሶላት ሲመለከቱ እጅግ ተደነቁ።

ብዙ ቀደምት ሙስሊሞች የከሃዲያኑን ግፍ ቀምሰዋል። ከእነዚህ ታዋቂ የሆኑ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች መካከል አሚር ቢን ፉሃይራ፣ አቡ ፉካሂያ፣ ሚቅዳድ ቢን አምር፣ ኡሙ ኡበይስ፣ ሉበይና ሃቱን፣ ናህዲዮ ሃቱንና ሴት ልጇ እጅግ ለግምት የሚያስቸግር ግፍና መከራን የተቀበሉ ናቸው። ከሃዲያኑ እግሮቻቸውን በሰንሰለት አስረው ራቁታቸውን እንደሆኑ የቀኑ ሙቀት እጅግ ኃይለኛ በሆነበት ሰዓት መሬት ለመሬት ይጐትቷቸው ነበር። እንዲሁም ቋጥኝ ድንጋዮችን በደረታቸው ወይም በጀርባቸው ላይ ይጭኑባቸዋል። ይህንን ግፍ በማከታተል ሲፈጽሙባቸውም ከስቃዩ ብዛት ብዙውን ጊዜ ሕሊናቸውን ስለሚስቱ ምን እንደተናገሩ እንኳን አያውቁም ነበር። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የክህደት ቃልን እስኪናገሩ ወይም ሞተው እስኪገላገሉ ድረስ ስቃያቸውን ያራዝሙባቸው ነበር።

እንደዚያም ሆኖ እነዚህ የተባረኩ የኢስላም የበኩር ልጆች በዚያ ሊሸከሙት በሚከብድ ስቃይ ውስጥ ሆነው እንኳን እምነታቸውን ከብክለት ጠብቀው መቆየት ችለዋል። እነርሱ በንብረታቸውና

በሕይወታቸው በከፈሉት መስዋእትነት ምክንያት ይህ መለኮታዊ ፀጋ ለእኛ ሊደርስ በቅቷል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው እነርሱ የኢስላምን ኃይማኖት ታላቅ ዋጋ በሚገባ መገንዘብ ስለቻሉ ነበር፡፡ በእርግጥም በሁለቱም ሃገር መለኮታዊ ሞገስ የሚያስገኘውን በር እንዴት ማስከፈት እንደሚቻል ያውቁበት ነበር፡፡ ፈራሽና በስባሽ የሆነው ስጋቸውን የተሸከመችው ነፍሳቸው እንደማንኛውም ፍጡር አካላቸውን ተለይታ ብትሄድም፤ እነርሱ ግን በዚህ ቀን ይቋረጣል ወይም ያልቃል የማይባል በሆነ የፈጣሪ ፀጋ እየተንበሻበሹ ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ ከልባቸው አምነው ይተገብሩት ነበር፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٢ ﴾ آل عمران:
١٠٢

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት፡፡ እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጂ አትሙቱ፡፡” (አሊ-ዒምራን፡ 102)*

ሰዕድ ኢብን አቢ-ወቃስ (ረ.ዐ.) እናቱን የሚወድና የሚታዘዝ ልጅ ነበር፡፡ ኢስላምን በተቀበለ ጊዜ እናቱ እንዲህ አለችው፡-

“ሰዓድ ሆይ! ምንድን ነው ያደረግከው ነገር? ይህን አዲስ ሃይማኖት ካልተውክ ምግብ አልበላም ውሃም አልጠጣም፡፡ በመጨረሻ ላይ መሞቴ አይቀርም፡፡ ከዚያ በኋላ ‘እናቱን የገደለው ልጅ’ እየተባልክ የአገር መዘባበቻ ትሆናለህ፡፡”

ሰዕድ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መለሰላት “እባክሽ እናቴ ይህን ኃይማኖቴን ለምንም ነገር ብዬ አልተወውም፡፡” ይህን የሰማችው እናቱ ለሁለት ቀናትና ሌሊቶች ምንም ነገር ባለመቅመሷ ተዳከመች፡፡ እጅግ የሚወዳት እናቱን እልህ ለመስበር በማሰብ ሰዕድ ቆራጥ በሆነ አቋም እንዲህ አላት፡-

“የምወድሽ እናቴ! አንድ ነገር ልታውቂ ይገባሻል፡፡ አንቺ ያሉሽ ነፍሶች መቶ ቢሆኑና በየተራ ብትሞቺ እንኳን ይህን ኃይማኖቴ ፈጽሞ አልተውም…”

የልጇን የአቋም ጽናት የተመለከተችው እናት የእልህ ጉዞዋን በማቆም ምግብ መውሰድ ጀመረች፡፡ ከዚህ ክስተት በኋላ ነበር የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ የወረደው፡-

﴿ وَوَصَّيۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ بِوَٰلِدَيۡهِ حَمَلَتۡهُ أُمُّهُۥ وَهۡنًا عَلَىٰ وَهۡنٖ وَفِصَٰلُهُۥ فِي عَامَيۡنِ أَنِ ٱشۡكُرۡ
لِي وَلِوَٰلِدَيۡكَ إِلَيَّ ٱلۡمَصِيرُ ١٤ وَإِن جَٰهَدَاكَ عَلَىٰٓ أَن تُشۡرِكَ بِي مَا لَيۡسَ لَكَ بِهِۦ عِلۡمٞ فَلَا
تُطِعۡهُمَاۖ وَصَاحِبۡهُمَا فِي ٱلدُّنۡيَا مَعۡرُوفٗاۖ وَٱتَّبِعۡ سَبِيلَ مَنۡ أَنَابَ إِلَيَّۚ ثُمَّ إِلَيَّ مَرۡجِعُكُمۡ
فَأُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ١٥ ﴾ لقمان: ١٤ - ١٥

*“ሰውንም በወላጆቹ (በጐ እንዲያደርግ) በጥብቅ አዘዝነው፡፡ እናቱም ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው፡፡ ጡት መጣያውም በሁለት ዓመት ውስጥ ነው፡፡ ለእኔም ለወላጆችህም አመስግን በማለት (አዘዝነው)፡፡ መመለሻውም ወደኔ ነው፡፡ ለአንተ በእርሱ እውቀት የሌለህን ነገር በእኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው፡፡ በቅርቢቱም ዓለም በመልካም ሥራ ተወዳጃቸው፡፡ ወደእኔም የተመለሰን ሰው መንገድ ተከተል፡፡ ከዚያም መመለሻችሁ ወደኔ ነው፡፡ ትሰሩት የነበራችሁትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ (አልነው)፡፡” (ሉቅማን፡15)*

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የተወለዱበትንና የሚወዷትን መካን ለቅቀው ለመሰደድ በተዘጋጁበት ሌሊት ዓሊን (ረ.ዐ.) ጠርተው ወደመዲና እንዲሰደዱ መለኮታዊ መመሪያ የወረደላቸው መሆኑን ገለጹላቸው፡፡ ከዚያም በመቀጠል እርሳቸው ወደ ኋላ እንዲቀሩና መካውያን ከእርሳቸው ዘንድ በአደራ ያስቀመጧቸውን ገንዘብና ንብረት ለየባለበቶቻቸው ከመለሱላቸው በኋላ እንዲከተሏቸው አሳሰቧቸው፡፡ ምክንያቱም መካ ውስጥ ውድና ዋጋ የሚያወጣ ኃብት ኖሮት ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘንድ ያላስቀመጠ ብዙ አይገኝም ነበርና፡፡ ጠላቶቻቸው እንደዚያ ግድያና ታላቅ አደጋ ሊያደርሱባቸው እየፈለጉ

ውድ ንብረቶቻቸውን ከእርሳቸው ዘንድ ማስቀመጣቸው እውነተኛና ታማኝ በመሆናቸው እንጂ በሌላ አልነበረም።

የከሃዲያኑን እቅድ አስመልክተው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዓሊን (ረ.ዐ.) ሲያስጠነቅቋቸው እንዲህ አሉ፡-

"ዓሊ ሆይ! ሌሊቱን በመኝታዬ ላይ ጋደም በል። በዚህ መጐናፀፊያዬም ራስህን ሸፍን። የማትወደው ነገር ይደርስብኛል ብለህ ምንም ፍርሃት እንዳይዝህ።"

ታላቅ በሆነ የእምነት ወኔ የደነደነው ዓሊ (ረ.ዐ.) በአካላቸው ላይ ሊሽቀሸቁ በተዘጋጁ ብዙ ጦሮችና ጐራዴዎች ጥላ ታጅበው እነሆ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መኝታ ላይ ተኝተዋል። አስፈሪ በሆነ ቁጣና እልህ እየተደናፉ የመጡት አጋሪዎች የአላህን መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገድለው ለመገላገል ወስነው ይጠባበቃሉ። ሌሊቱ ሊገባደድ አቅራቢያ በሩን በኃይል በርግደው ወደ ውስጥ ሲዘልቁ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) መጐናፀፊያ ለብሰው የተኙት ዓሊ (ረ.ዐ.) መሆናቸውን ተመለከቱ። የንዴት እሳት ለብሰውም እንዲህ በማለት ጮሁ፡-

"ዓሊ ሆይ! የአጎትህ ልጅ የት ነው ያለው?"

"እኔ አላውቅም። ይህን ጉዳይ በተመለከተም ምንም መረጃ የለኝም። እኔ እርሳቸውን ስከታተል አልቆየሁም። እንደሚመስለኝ ግን ከመካ ውጣልን ያላችኋቸው በመሆኑ መካን ሳይለቅቁ አይቀሩም።"

ይህን እንደሰሙ ዓሊን እየተራገሙና እያመናጨቁ ወስደው በመስጂደል ሃረም ውስጥ አሰሯቸው። ሆኖም ግን ብዙም ሳይቆዩ ፈቷቸው።

በአንድ አጋጣሚ የነጅድ ሕዝቦች ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከመጡ በኋላ ኢስላምን ለመማር እንደሚፈልጉ በመግለጽ የሚያስተምሯቸው ሰዎች እንዲመድቡላቸው ይጠይቋቸዋል። በዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ቁጥራቸው ሰባ የሚሆኑ ሶሐቦቻቸውን ላኩላቸው።

እነዚያ ሰባ የሚሆኑ ሰዎች ሁሉም ቁርአንን በቃላቸው ያጠኑ (ሃፊዞች) ከመሆናቸውም በላይ የኢስላምን ኃይማኖት ጠንቅቀው የተገነዘቡ ነበሩ።

ለረዥም ጊዜ ከተጓዙ በኋላ ቢእር ማዑና ከሚባል ቦታ ሲደርሱ አረፍ አሉ፡፡ በዚያን ጊዜ ከሃዲያኑ አድፍጠው በመክበብ ከሞላ ጐደል ሁሉንም ፈጇቸው፡፡ በዚያ ክስተት ውስጥ ከሸማቂዎቹ አንዱ የነበረው ጀባር ቢን ሰልማ ቀስቱን በማስወንጨፍ በአምር ኢብን ፉሃይራ ጀርባ ሰኩበት፡፡ ኢብን ፉሃይራ በዚያን ወቅት የአርባ ዓመት ጐልማሳ የነበረ ሲሆን እጅግ ታላቅ በሆነ ደስታ እንዲህ በማለት ጮኸ፡-

"በአላህ ይሁንብኝ ፍላጐቴን አገኘሁ!"

ኢብን ጡፈይል የተባለውና ይህን ተንኮል የተሞላበት ክህደት የፈጸሙት ሰዎች መሪ ከዚያ ፍጅት የተረፈ አንድ ሙስሊም አግኝቶ ይዞት ከመጣ በኋላ ከተሰውት ሰዎች አንዱን እያሳየው እንዲህ አለው፡-

"ይህ ሰው ማን ነው?"

"እርሱማ አምር ቢን ፉሃይራ ይባላል፡፡" አለ ሙስሊሙ፡፡

"የዚህ ሰው አካል ወደ ሰማይ ሲወሰድ አየሁ፡፡ እስካሁንም ድረስ በሰማይና በምድር መካከል እንደተንሳፈፈ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ተመልሶ በመውረድ መሬት ላይ አረፈ፡፡"

ይህን የመሰለ ተዓምር በዓይኑ የተመለከተውና በአረቢያ ምድር ዝነኛ ባለቅኔ የነበረው ኢብን ጡፈይል ግን ኢስላምን ሊቀበል አልቻለም፡፡ ይሁን እንጂ ጀባር የተባለውና ኢብን ፉሃይራን የገደለው ሰው በመጨረሻ ሙስሊም ሆኗል፡፡ ሰማእት እንዲሆን ያደረገው ሰው ድምጽ በጀባር ሕሊናው ይደውልበት ነበር፡፡

"በአላህ ይሁንብኝ! ፍላጐቴን አገኘሁ!" የሚሉት ቃላት

ለብዙ ጊዜያት እንቆቅልሹ ያልተፈታ ምስጢር ሆኖበት ነበር፡፡ "እኔ እየገደልኩት እንዴት ፍላጐቴን አገኘሁ" ሊል ቻለ? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?" እያለ በሃሳቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ነበር የቆየው፡፡ ጀባር ይህን እንቆቅልሽ የሚፈታለት ሰው ሲፈልግ ከእለታት አንድ ቀን ደሃቅ ኢብን ሱፍያን (ረ.ዐ.) የተባለውንና እንደ መቶ ሰዎች ይቆጠራል ተብሎ የሚታሰበውን ሰው አገኘ፡፡ ከዚያም "ያ የሙሐመድ ባልደረባ፡ "በአላህ

ይሁንብኝ ፍላጐቴን አገኘሁ!" ሲል ምን ማለቱ ነበር?" በማለት ጀባር ጠየቀው፡፡ እርሱም ፡- "ጀነት ገባሁ" ማለቱ እንደሆነ ሲገልጽለት ጀባር ከእንቅልፉ ባነነ፡፡ ከዚያም ኢስላምን ሳያወላውል ተቀበለ፡፡

የኡሁድ ጦርነት እንዳበቃ - ሰፍያ (ረ.ዐ.) በዚያ ውጊያ ሰማእት የሆኑትንና አካላቸውም እጅግ ዘግናኝ በሆነ አኳኋን የተቆራረጠውን የወንድሟን የሃምዛን አስከሬን ለማግኘት ጓጉታለች፡፡ ይህን እያሰበችም ሰማእታቱ የወደቁባቸውን ቦታዎች ለማሰስ ፊቷን መለሰች፡፡ በዚያው ሰዓት ልጇ ዙቤይር (ረ.ዐ.) አገኛትና እንዲህ አላት፡-

"የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ኋላ እንድትመለሺ አዘዋል፡፡"

"ለምን? እንደዚያ ከሆነ ወንድሜን ላየው አልችልም ማለት ነው?" አለች፡፡ ቀጠል አድርጋም፡- "እርግጥ ነው ሰውነቱ በምን ዓይነት አሰቃቂ ሁኔታ እንደሚቦጫጨቅ አውቃለሁ፡፡ ይህን የመሰለ መከራ የወደቀበትም ለአላህ ብሎ ነው፡፡ ይህን ከማሰብና ከመጽናናት ውጭ ሃዘናችንን ልንረሳበት የሚያስችለን ሌላ መንገድ የለም፡፡ አላህ ከሻ እኔም ሃዘኔን ዋጥ በማድረግ ምንዳየን ከእርሱው እጠብቃለሁ" አለች፡፡

ዙበይር (ረ.ዐ.) ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከተመለሰ በኋላ እናቱ ያለችበትን ሁኔታ፣ የተናገረቻቸውንም ነገሮች ዘርዝሮ አስረዳቸው፡፡ እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡-

"እንደዚያ ከሆነ ተዋት፤ ትሂድና የወንድሟን አስከሬን ትመልከት፡፡"

ሶፊያ ከዚያ በኋላ በጀግንነት ተሰውተው የወደቁትን ወንድሟን አካል እያየች የሰማእታት ሁሉ አለቃ በመሆናቸው እየተጽናናች ከልቧ ዱዓ አደረገችላቸው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለተለያዩ የዓለም መሪዎች የላኳቸውን ታሪካዊና ክቡር የሆኑ ደብዳቤዎች ይዘው የሄዱት ባልደረቦቻቸው እጅግ ደማቅ ታሪክን አስጽፈዋል፡፡ እነዚያ የተባረኩና ልበ ሙሉ ጀግና መልእክተኞች የክቡሩን መልእክተኛ ደብዳቤዎች በመያዝ ጋራና ሸንተረር፣ አቀበትና ቁልቁለት፣ የወንዝ ሙላትም ሆነ የበረሃ ጥማት

ሳይበግራቸው ነበር ጉዟቸውን ያከናወኑት፡፡ እዚያ እንደደረሱም ከአላህ በስተቀር ማንንም ምድራዊ አካል የማይፈሩ ሆነው በፈላጭ ቆራጭ አምባገነኖችና ጭራቅ በሆኑ ሰው በላ መሪዎች ፊት በጽናት ቆመዋል፡፡ ይህን ታላቅና እጅግ ከባድ ኃላፊነት የሚጠይቅ ተልእኮ ሲሸከሙም መከራና ሥቃይ እንደሚያገኛቸው ከዚያም ፈቀቅ ሲል ሕይወታቸውን ጭምር ሊያጡ እንደሚችሉ አጥተውት አልነበረም፡፡ ሆኖም ግን እነርሱ በጦርና በጐራዴዎች ጥላ ሥር ሆነው እንኳን ተልእኳቸውን በጀግንነት ከመፈፀም አላመነቱም፡፡

ከእነዚህ የኢስላም የቁርጥ ቀን ልጆች ዜና መዋእል የተገኙ ተምሳሌታዊ ገድሎቻቸውን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለተከዮቻቻው እንዲህ በማለት ጥያቄ አቀረቡ፡-

“ሰዎች ሆይ! አላህ የሚሰጠውን ምንዳ በማሰብ ለአሌክሳንደሪያው ንጉስ ሙቀውቂስ ይህን ደብዳቤ ከእናንተ ውስጥ የሚሰጥልኝ ማን ነው?”

ዓቲብ ኢብን አቢ በልታእ (ረ.ዐ.) በፍጥነት ተነስቶ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አጠገብ ከደረሰ በኋላ እንዲህ አለ፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ እወስድልዎታለሁ፡፡”

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) ዓቲብን ወደ ግብጽ ላኩት፡፡

ዓቲብ ኢብን አቢ በልታእ አሌክሳንደሪያ (ግብጽ) እንደደረሰ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ደብዳቤ ለንጉሱ አነበበለት፡፡ ሙቀውቂስ ዓቲብ ከጐኑ እንዲሆን ጋበዘው፡፡ የኃይማኖት አባቶች እንዲሰበሰቡም አደረገ፡፡ ከዚህ በኋላ ያለውን የታሪኩን ክፍል ከራሱ ከዓቲብ (ረ.ዐ.) ትረካ አብረን እንከታተል፡ -

“ሙቀውቂስ እንዲህ አለኝ ፡- “ግንዛቤ ላገኝበት ስለምፈልገው ጉዳይ ካንተ ጋር መወያየት እፈልጋለሁ፡፡”

“እካክህ መወያየት እንችላለን፡፡”

“አለቃህ ነቢይ ነውን?”

“አዎን፣ እርሳቸው የአላህ መልክተኛ ናቸው”

“እርሱ እውነተኛ ነቢይ ከሆነ ከምድሩ እንዲወጣና በስደት ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ እንዲኖር ያስገደዱትን የራሱን ሰዎች ያጠፋለት ዘንድ ለምን አላህን አይለምንም?” አለ፡፡

እኔም ለዚህ የሚከተለውን መልስ ሰጠሁት፡-

“የማሪያም ልጅ ኢየሱስ ትክክለኛ ነቢይ መሆኑን ትመሰክራለህን? እርሱ እውነተኛ ነቢይ ከሆነ ሕዝቦቹ ሲይዙት፣ ሊሰቅሉት ሲሞክሩና ሌላም ስቃይ ሲያደርሱበት ወደ ሰማይ ከመሄድ ይልቅ አላህ ያጠፋለት ዘንድ ለምን አልፀለየም?”

ሙቀውቂስ ይህን ንግግሬን ካዳመጠ በኋላ መልስ አልነበረውም፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ ያክል ዝም ብሎ ሲያስብ ቆይቶ ቃላቶቼን እንድደግምለት ጠየቀኝ፡፡ ቀደም ብዬ የነገርኩትን ነገር ደግሞ ካዳመጠ በኋላ አሁንም የተወሰነ ጊዜ ፀጥ ብሎ ሲያስብ ቆይቶ እንዲህ አለ፡-

“የተናገርከው ነገር መልካም ነው፡፡ ብልህ ሰው ነህ፡፡ የተናገርከው ትክክለኛ የሆኑ ቃላትን ነው፡፡ የላከህም ሰው እንዳንተው ብልህ መሆን አለበት፡፡”

ይህንን የሙቀውቂስን ንግግር ተከትሎ እንዲህ አልኩት፡-

“ከአንተ በፊት በዚህ በግብጽ ምድር አምላክ ነኝ የሚል አንድ ሰው ስልጣን ላይ ነበር፡፡ ይህ ሰው ፈርኦን የሚባል ሲሆን ትእቢቱንና ግድድሩን ያስተዋለው ኃያሉ አላህ በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም ቅጣቱን አከናንቦታል፡፡ ከዚህ ሰው ትምክህት ልትወስደው የሚገባህ ትምርት አለ፡፡”

ሙቀውቂስ እንዲህ አለ፡-

“እኛ የራሳችን የሆነ ኃይማኖት አለን፡፡ ከዚያ የተሻለ ነገር እስካላገኘን ድረስም የያዝነውን አንለቅም፡፡”

በዚህ ጊዜ እንዲህ አልኩት፡-

“ኢስላም እናንተ ከምትከተሉት ኃይማኖት በእርግጠኝነት በጣም የበለጠ ነው። ኃያሉ አላህ ለሕዝቦቹ የመረጠው ወደሆነው የኢስላም ኃይማኖት ትገባ ዘንድ ግብዣችንን እናቀርብልሃለን። ሙሐመድ ሙስጦፋ (ሰ.ዐ.ወ.) አንተን ብቻ ሳይሆን የሰውን ዘር በሙሉ ነው ወደ ኢስላም የጠሩት። ከሁሉም በላይ ጨካኝና መጥፎ የነበሩት የቁረይሽ ከሃዲያን ናቸው። ከሁሉም በላይ ለነቢዩም ሆነ ለሙስሊሞች  ጠላትነት ያላቸው ሕዝቦች አይሁዳውያን ናቸው። ከሁሉም የተሻለ የሚቀርቧቸው ደግሞ ክርስቲያኖች ናቸው። ሙሣ (ዐ.ሰ.) የእየሱስን መምጣት እንዳበሰሩት ሁሉ ኢየሱስ (ዐ.ሰ.) ደግሞ የሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) መምጣት እንዲሁ አብስረዋል። እኛ አሁን እናንተን ወደ ቁርአን የምንጠራችሁ ልክ እናንተ ክርስቲያኖች የተውራት ተከታዮች የሆኑትን አይሁዳውያን ወንጌልን እንዲቀበሉ እንደጋበዛችኋቸው ብጤ ነው። ሁሉም ቢሆን በዘመኑ የተላከለትን ነቢይ መከተል ነው ያለበት። እናንተን ወደ አኢስላም ስንጠራችሁ እናንተን ከእየሱስ ኃይማኖት መለየታችን አይደለም። እንዲያውም በተቃራኒው በሃይማኖታችሁ የታዘዛችሁትን መልእክት እንድታራምዱ ነው እድል የምንከፍትላችሁ።”

ሙቀውቂስ እንዲህ አለ፡-

“የዚህን ነቢይ ኃይማኖት መረመርኩት። እንደሚገባኝ ከሆነ ኃይማኖቱ ከዓለም እንድንገለል አያዝም። እንዲሁም የሚወደድና ተቀባይነት ያለውንም ነገር አይከለልም። እርሱ መንገዱን የሳተ አስማተኛ አይደለም። እንዲሁም የሩቁን ምስጢር አውቃለሁ ብሎ የሚዋሽም አይደለም። ከዚያ በተቃራኒ ነቢይ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች አልሉ። የሆነ ሆኖ እኔ ጉዳዩን በጽሞና መመርመር ይኖርብኛል።”

ሙቀውቂስ ይህን ካለ በኋላ ቆየት ብሎ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ደብዳቤ የጻፈላቸው ቢሆንም ከዚህ የተሻለ እርምጃ ለማድረግ ግን አልቻለም። ኢስላምንም አልተቀበለም። ለእኔ ግን የሚከተለውን ምክር ለገሰኝ፡-

“ተጠንቀቅ! ክርስቲያኖች ካንተ አንድም ቃል እንዲሰሙ አታድርግ፡፡ ሊጉዱህ ይችላሉና፡፡”

እነዚህ የሃቲብ ቃላት ምን ዓይነት ያማሩና ተምሳሌታዊ ናቸው! ምን አይነት የጀግንነትና አርቆ አስተዋይነት አብነት ነው! በአንድ ፈላጭ ቆራጭ ንጉሥ ፊት ቆሞ ያለምንም ፍርሃት አቋምን መግለጽ መቻልስ ምን ዓይነት ቆራጥነት ነው!

ኪስራ ፔርቬዝ ለተባለው የፋርስ (ኢራን) ንጉስ የተላከውን ደብዳቤ ይዞ የሄደው ደግሞ አብዱላህ ኢብን ሁዘይፋ (ረ.ዐ.) ነበር፡፡ ኪስራ ገና ደብዳቤው ሙሉ በሙሉ ተነቦ ሳያልቅ የያዘውን መልእክት እንኳን በቅጡ ሳይገነዘበው በንዴት ቱግ የሚያደርገው ነገር ተከሰተ፡፡ ይኸውም የነቢዩ ስም ከእርሱ ስም ቀድሞ መጻፉ ነበር፡፡ ከዚያም ያንን የተባረከ ደብዳቤ ከመልእክተኛው እጅ ተቀብሎ ቦጫጭቆ ጣለው፡፡ መልእክተኛውንም ፀያፍ በሆኑ ቃላት ወረፈው፡፡

ከእምነቱ በሚቀዳ ታላቅ የጀግንነትና የክብር መንፈስ አብደላህ (ረ.ዐ.) ለኪስራና ለተከታዮቹ የሚከተለውን ንግግር አደረገላቸው፡-

“እናንት የፋርስ ሕዝቦች! የዘመናቶቻችሁን ብዙውን ክፍል ያለነቢይና ያለ መጽሐፍ ኖራችኋል፡፡ እናንተ አሁን በእጃችሁ የሚገኘውን መጠነኛ ስፋት ያለው ግዛት ነው የምትቆጣጠሩት፡፡ ሕይወታችሁን ደግሞ ቅዠት በመሰለ ሁኔታ እየገፋችሁ ነው፡፡ ከምድር ውስጥ እናንተ የማትቆጣጠሩት ክፍል ደግሞ እጅግ ታላቅ ነው፡፡ ኪስራ ሆይ! የዚህኛውንም ሆነ የመጪውን ዓለም ምንዳ የሚሹ ብዙ መሪዎች ካንተ በፊት አልፈዋል፡፡ የመጪውን ዓለም ፀጋ የሚሹ የሆኑት የዚህንም ዓለም ምንዳ አግኝተዋል፡፡ ሆኖም ግን የዚህችን ዓለም ምንዳ ብቻ ይሹ የነበሩ የመጪውንም ዓለም ምንዳ አጥተዋል፡፡ እንድትቀበሉት ለእናንተ ያቀረብንላችሁን ይህን ኃይማኖት ዝቅ አድርጋችኋል፡፡ በአላህ ይሁንብኝ! የትም ብትሆን ይህ ዝቅ ያደረግኸው ነገር ያጋጥምሃል፡፡ ያኔ ፍርሃት የማይለቅህ ሲሆን ራስህን ለመከላከልም አትችልም፡፡”

“ለዚህ ንግግሬ ኪስራ የሰጠኝ መልስ ንግስናውና በእጁ ያለው ሃብት የራሱ የግሉ እንደሆነና እሸነፋለሁ ብሎ እንደማይፈራ እንዲሁም ሥልጣኑን የሚጋራው ማንም እንደሌለ ነው፡፡ ያንን ከተናገረ በኋላም ወደውጭ አውጥተው ይጥሉኝ ዘንድ ለአገልጋዮቹ ትእዛዝ ሰጣቸው፡፡”

አብደላህ የኪስራን ቤተመንግስት እንደለቀቀ ከፈረሱ ላይ ወጥቶ ወደ መዲና አመራ፡፡ በጉዞ ላይ እያለም የሚከተለው ሃሳብ በአእምሮው ላይ እየተመላለሰበት ነበር፡-

“በአላህ ይሁንብኝ! በእኔ ላይ ለሚደርሰው ነገር ምንም ግድ አልነበረኝም (ብገደልም ወይም በሕይወት ብቆይ)፡፡ እኔ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) መልእክት አድርሻለሁ፤ ይኸው ነው፡፡”

ይህ ነበር እንግዲህ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.0.ወ.) ደብዳቤ ለአምባገነኑ ኪስራ ፔርሼስ ያደረሰለት ልበ ሙሉ ጀግና ገድል፡፡ በእርግጥም እርሱ ሕይወቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ ቢሆንም ተልእኮውን በብቃት በመፈፀሙ ሰላማዊ ሕሊናን ይዞ ነበር ወደ ሃገሩ የተመለሰው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበውም ታሪክ የዚሁ ደንዳና ልብ ያለው ሙስሊም ጀግና የአብደላህ ኢብን ሁዘይፋ (ረ.ዐ.) ታሪክ ሲሆን አቻ ያልተገኘለት ወኔ ባለቤት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ትምህርታዊነቱ የላቀ ነው፡፡

በኡመር (ረ.ዐ.) የኸሊፋነት ዘመን ቄሳሪያ ወደምትባለው የደማስቆ አውራጃ የሙስሊም ሰራዊት ተልኮ ነበር፡፡ አብደላህ ኢብን ሁዘይፋም ከዚሁ ሰራዊት ውስጥ ይገኝ ነበር፡፡ በውጊያ ላይም በሮማውያን ተማረከ፡ ፡ ከንጉሳቸው ፊት ካቀረቡት በኋላም እንዲህ አሉ፡-

“ይህ የሙሃመድ ባልደረባ ነው፡፡”

ከአንድ ቤት ውስጥ ያለምንም ምግብና ውሃ ከተቆለፈበት በኋላ የተወሰነ የወይን ጠጅና የአሳማ ስጋ እንዲበላ ተላከለት፡፡ አብደላህ ለሶስት ቀናት ያህል በዚያ ወይን ጠጅና የአሳማ ስጋ ላይ እጁን አለማሳረፉን ተከታተሉት፡፡ ከዚያም ለንጉሣቸው እንዲህ አሉት፡-

“እስረኛው በጣም ተዳክሟል፡፡ እንዲወጣ የማታደርገው ከሆነ መሞቱ አይቀርም፡፡”

ንጉሱ ወደርሱ እንዲቀርብ ካደረገው በኋላ እንዲህ በማለት ጠየቀው፡-

“ይህን ምግብ እንዳትበላና መጠጡንም እንዳትጠጣ ያገደህ ምንድን ነው?” አብደላህ እንዲህ አለ፡-

“እርግጥ ነው አንድ ሙስሊም እነዚህን ነገሮች ወደ ሆዱ ማስገባት ያለበት በጣም አደገኛ ከሆነ ሁኔታ ውስጥ ከወደቀና ምርጫ ከሌለው ብቻ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ራሴንም ሆነ ኃይማኖቴን በእናንተ ፊት መቀለጃ አድርጌ ለማቅረብ አልፈለግኩም፡፡”

ለዚህ ክብር የተመላበት አስተያየት አፀፋ ንጉሱ የሚከተለውን ተናገረ፡-

“ክርስቲያን ብትሆንና ካለኝ ሃብት ውስጥ ግማሽ ያህሉን ብሰጥህ፣ እንዲሁም በግዛቴ ውስጥ ሁሉ ተጋሪ ባደርግህና ሴት ልጄንም በጋብቻ ብሰጠህ ምን ይመስልሃል?”

ለዚህ የንጉሱ ጥያቄ አብደላህ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መለሰ፡-

“ያለህን ሃብት ሁሉ እንዲሁም የመላው አረቢያን ሃብት ብትጨምርልኝ ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ኃይማኖት ለቅጽበት ያክል እንኳን አልዞርም፡፡”

“እንደዚያ ከሆነ እገድልሃለሁ፡፡” አለ ንጉሱ፡፡

“ያንን መወሰን ያንተ መብት ነው” አለ አብደላህ (ረ.ዐ.)፡፡

ከዚያ በኋላ አብደላህ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፡፡ የቀስት ፍላፃቸውን በማስወንጨፍና ጨረፍ እያደረገው እንዲያልፍ በማድረግ ሊያስፈራሩት ሞከሩ፡፡ ከዚያም ለመጨረሻ ጊዜ ክርስቲያን ይሆን ዘንድ እድል ተሰጠው፡፡ ያ የተባረከ ሶሃባ ትንሽ ዝንባሌ አንኳን ሳይታይበት ቀረ፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሱ “ወይ ክርስቲያን ትሆናለህ፤ ካልሆነ ግን በፈላ ዘይት ውስጥ እንከትሃለን” አለ፡፡

አብደላህ (ረ.ዐ.) አሁንም ከአቋሙ ፍንክች ባለማለቱ ከነሃስ በተሰራ ትልቅ ማሰሮ ውስጥ ከልክ በላይ የፈላ ዘይት ቀረበ። ከዚያም ንጉሱ ከሙስሊም ምርኮኞቹ አንዱ እንዲቀርብ አዘዘ። ከዚያም ክርስቲያን እንዲሆን ግብዣ ቀረበለት። ምርኮኛው ግብዣውን ውድቅ ሲያደርግ በዚያ የፈላ ማሰሮ ውስጥ እንዲገባ ተደረገ። አብደላህ (ረ.ዐ.) ይህን ጉድ ያስተውላል። የዚያ ሙስሊም ቆዳ በቅጽበት ተገሽልጦና ሥጋው ከአጥንቱ ተለይቶ መንሳፈፍ ጀመረ።

ንጉሱ አሁንም አብደላህ ክርስቲያን ይሆን ዘንድ ሃሳብ አቀረበለት። አሁንም ሃሳቡን ውድቅ ሲያደርግ እዚያ ማሰሮ ውስጥ እንዲያስገቡት ትእዛዝ ሰጠ። አብደላህ ወደ ማሰሮው ውስጥ ሊጣል ሲል ማልቀስ ጀመረ። ሃሳቡን ቀይሮ ይሆናል ብሎ ያሰበው ንጉሥ አብደላህ እንደገና ወደርሱ እንዲቀርብ በማድረግ ክርስቲያን እንዲሆን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጥያቄ አቀረበለት። እምቢተኛነቱን ሲገነዘብም ንጉሱ በንዴት፡-

“ታዲያ ለምን አለቀስክ?” በማለት ጠየቀው።

“ያለቀስኩት” አለ አብደላህ “ለራሴ ‘አሁን እዚህ ጋን ውስጥ ልትጣል ነው። ነፍስህም በቅጽበት ከአካልህ ትለያለች አልኩት’ እኔ ግን በእውነት በአካላቴ ላይ ባሉት ፀጉሮች ቁጥር ብዙ ነፍሶች ኖረውኝ ለአላህ ስል ሁሉም በዚህ ጋን ውስጥ ቢጣሉ ፍላጐቴ ነበር።” የአብደላህ አቋም ንጉሱን በጣም አስደነቀው። የእምነቱ ጽናት፣ ታማኝነቱ፣ ቆራጥነቱ፣ ለኢስላም የነበረው ጥልቅ ፍቅር ተጽእኖ አሳደረበት። እናም አብደላህን እንዲህ ሲል ጠየቀው፡-

“ነጻ እለቅህ ዘንድ ጭንቅላቴን አንድ ጊዜ ሳመኝ?”

“ሁሉንም ሙስሊም እስረኞች ጭምር የምትለቅ ከሆነ?” ሲል አብደላህ ጠየቀ።

አዔው ይህንን ለማድረግ ተስማማ። አብደላህ ደግሞ ለራሱ

“ከአላህ ጠላቶች መካከል አንዱ የሆነውን ሰው ስሜው እኔንና ሌሎቹን ሙስሊም እስረኞች በሙሉ ይለቅቀናል። ይህንን በማድረጌ ምንም ጥፋት

ሊኖርብኝ አይችልም፡፡” ሲል አሰበ፡፡ ከዚያ ቀጥ ብሎ ወደ አዜው ሄደና ገንባሩን ሳመው፡፡ ሁሉም ሙስሊም እስረኞች ተለቅቀው ለአብደላህ ተሰጡ፡፡

በመጨረሻ አብደላህ ኢብን ሁዘይፋህ (ረ.ዐ.) ወደ ኡመር ኢብን አል-ኸጧብ መጣና ስለሆነው ነገር ሁሉ አወራቸው፡፡ ኡመርም እጅግ በጣም ተደሰቱ፡፡ እስረኞቹን ሲመለከቱም “እያንዳንዱ ሙስሊም የአብደላ ኢብን ሁዘይፋህን ጭንቅላት የመሳም ግዴታ አለበት፡፡ እኔው እጀምራለሁ፡፡” በማለት ከተቀመጡበት ተነስተው የአብደላህ ኢብን ሁዘይፋህን (ረ.ዐ.) ጭንቅላት ሳሙ፡፡ በዚያን ጊዜ ሰማኒያ የሚሆኑ ሙስሊም እስረኞች ነበሩ ነጻ የተለቀቁት፡፡

ሙስሊሞች ነገሮችን የሚመዝኑተና የሚያስተውሉት በዚህች በቅርቢቱና ጠፊ በሆነችው ዓለም ሳይሆን በመጪው ዓለም መነጽር ነው፡፡ ይህን የሚያደርጉት ኃይማኖታቸው የምናብ አድማሳቸውን ስለሚያሰፉላቸው ነው፡፡

ሌላው ለእምነቱ ጥልቅ ፍቅር የነበረው ጀግና ወህብ ቢን ከብሻህ (ረ.ዐ.) ነው፡፡ የዚህ ክቡር ሶሃባ መቃብር  የሚገኘው በቻይና ነው፡፡ ነቢዩ ወህብን ወደቻይና ሄዶ ኢስላምን እንዲሰብክ ታላቅ የሆነ ተልእኮን አሸክመው ላኩት፡፡ ይሁን እንጂ በዚያ ዘመን አንድ ሰው ከመዲና ተነስቶ ቻይና ለመድረስ አንድ ዓመት ያክል ጊዜ ይፈጅበት ነበር፡፡ ወህብ ኢብን ከብሻህ (ረ.ዐ.) ቻይና ከደረሰ በኋላ ኢስላምን እያስፋፋ ለረዥም ዘመን ቆይቶ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ናፍቆት በጣም ስለበረታበት ዓይናቸውን ለማየት ወደ መዲና ተመለሰ፡፡ አንድ ዓመት ከፈጀ የመከራ ጉዞ በኋላም መዲና ደረሰ፡፡ ሆኖም ግን ምን ያደርጋል! ናፍቆት እንዳንገበገበውና ዓይናቸውን ለማየት እንደጓጓ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ሳያያቸው ሊቀር ግድ ሆነ፡፡ ሞተው ነበር የደረሰው፡፡

ምንም እንኳን ናፍቆቱና ሰቀቀኑ ቢበረታበትም እንደገና ወደ ቻይና መመለስ ነበረበትና ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ምክንያቱም ይህንን የተቀደሰ ዓላማ እንዲያራምድ ኃላፊነት የሰጡት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)

እንደመሆናቸው ትእዛዛቸው መከበር ነበረበት፡፡ ወህብ ኢብን ከብሻ (ረ.ዐ.) ቻይና ደርሶ እምነቱን እያስፋፋ እያለ እዚያው አረፈ፡፡ በዚህም ተግባሩ በቻይና የመጀመሪያው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አምባሳደር የመሆንን ደረጃ ተጎናፀፈ፡፡

ፈራሽ የሆነው አካሉ በቻይና ቢቀበርም የማትሞተው ነፍሱ ግን ከአላህ መልእክተኛ ጋር ልትገናኝ በብርሃን ወደምታበራው መዲና መምጣቷ አልቀረም፡፡

የኦቶማን ቱርክ መሪ በነበረው ሱልጣን ባያዚድ ሁለተኛና በወንድሙ ጀም ሱልጣን ተፈጥሮ የነበረው ሁኔታ በቀደምት ቱርካውያን አባቶች መካከል የነበረውን ኢስላማዊ ሥነ-ምግባርና የእምነታቸውን ጥልቀት የሚያሳይ ነው፡፡

እ.ኤ.አ. 1481 የኦቶማን ሱልጣን በመሆን መንበሩን የያዘው ባያዚድ ሁለተኛው (አላህን ከመፍራቱ የተነሳ ቅዱስ ባያዚድ በመባልም ይታወቃል) የመጀመሪያዎቹን 14 የሚሆኑ የሥልጣን ዓመታት ያሳለፈው ከወንድሙ ጀም ሱልጣን ጋር በመወዛገብ ነበር፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚቆጠረው ጀም ሱልጣን የኦቶማን ቱርክ ሱልጣንነት ለእኔ ይገባኛል ማለቱ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ባያዚድ ሁለተኛ ከክርስቲያኑ ዓለም ጋር የነበረውን ፍትጊያ ንቃት ባለው ሁኔታ እንዳይከታተለው አንቅፋት መፍጠሩ አልቀረም፡፡

ይህ በእንዲህ እያለም ጀም ሱልጣን የሚከተለውን ሃሳብ ለባያዚድ ሁለተኛ አቀረበለት፡-

"ሃገራችንን ለሁለት እኩል ቦታ ላይ እንክፈልና አንደኛውን ክፍል አንተ አስተዳድር ሌላኛውን ክፍል ደግሞ እኔ አስተዳድራለሁ፡፡"

ባያዚድ ይህንን የወንድሙን ሃሳብ ውድቅ በማድረግ እንዲህ አለው፡-

"ወንድሜ ሆይ! ይህ አገር የእኔና ያንተ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡም ነው፡፡ እኛ የምንከፋፍለው ከሆነ ኃይሉ ይዳከማል፡፡ ከዚያም እኛ ደካማ የሆኑ ሁለት ትንንሽ ሃገራት መሪዎች እንሆናለን፡፡ ይህ ደግሞ ታላቅ የሆነ

ውድቀትን ነው የሚያመጣብን፡፡ እኔን በተመለከተ አካሌን ለሁለት መቆራረጥ ወይም መክፈል እችል ይሆናል፡፡ ሃገሬና ሕዝቤ ግን በምንም መልኩ ለሁለት አይከፋፈሉም፡፡"

ወንድማማቾቹ ይህን ከተነጋገሩ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የሮድ መሳፍንቶች ሃገራቸውን እንዲጐበኝ ለጀም ሱልጣን ግብዣ አቀረቡለት፡፡ በንግግራቸው ትሕትና የተማረከው ጀም ብዙም ሳይጨናነቅ ግብዣቸውን ተቀብሎ ሄደ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚያ አጥባቂ ክርስቲያን የሆኑ መሳፍንት ቃል ኪዳናቸውን በማፍረስ ጀምን ልክ እንደ ባሪያ ለጳጳሱ ሸጡላቸው፡፡ ጳጳሱ ደግሞ ያንን የኦቶማን ቱርክ ልዑል የሚቀጥለውን የመስቀል ዘመቻ ሲከፍቱ በኦቶማኖች ላይ ሊጠቀሙበት እቅድ ነድፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አኳያ ሊሳካላቸው እንደማይቻል የተገነዘቡት ጳጳስ ጀም ሱልጣን ክርስቲያን እንዲሆን ሃሳብ አቀረቡለት፡፡ ይህ ድፍረታቸውም የጀም ሱልጣንን ስሜት በኃይል ጐዳው፡፡ በጣም በሃዘን እንደተነካም ጳጳሱን እንዲህ አላቸው፡-

"የኦቶማን ቱርክን ግዛት ቀርቶ መላው ዓለምን ቢሰጡኝ እንኳን ኃይማኖቴን በፍፁም አልቀይርም፡፡"

መስቀለኞች ኢስላምን ለመጉዳት ሊጠቀሙበት እንደሚፈልጉ የተገነዘበው ጀም ኃያሉ አላህን አምርሮ እንዲማፀንና ከዚህ ጉድ እንዲያወጣው ማድረግ መቻሉ የኃይማኖቱን ጽናትና ቀናኢ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲህ በማለት ነበር አላህን የተማፀነው፡-

"ጠባቂዬ ሆይ! የሙስሊሙን ዓለም ለመጉዳት ከሃዲያን እኔን መሣሪያ አድርገው ሊጠቀሙብኝ ፈልገው ከሆነ ከዚህ በላይ ባሪያህ በሕይወት እንዲቆይ አታድርግ፡፡ ነፍሴን ወደተከበረው ቦታህ በፍጥነት ውሰዳት፡፡ …"

ይህ ያደረገው ፀሎት ተቀባይነት ያገኘ ይመስላል፡፡ ጀም ገና የ36 ዓመት ጉልማሳ እያለ በኔፐልስ አረፈ፡፡ በመሞቻው የመጨረሻ ቀናቶች አጠገቡ ለነበሩት ሰዎች የሚከተለውን ኑዛዜ መተው ችሎም ነበር፡፡

“የመሞቴን ዜና በመላው ዓለም ያለ ሕዝብ ሁሉ ይስማ። ምክንያቱም ከሃዲያን በሙስሊሞች ላይ ሊያደርሱ ለሸረቡት ሴራ እንደመሣሪያ ሊጠቀሙብኝ እንደማይችሉ ግልጽ ይሆናልና። ከዚያ በኋላ ወደ ወንድሜ ሱልጣን ባያዚድ ሂዱ። ከዚያም ምንም ያክል አስቸጋሪ ቢሆን አስከሬኔን ወደሃገሬ በማስወሰድ እንዲቀብረኝ ንገሩት። በከሃዲያን ምድር ላይ መቀበር አልሻምና። እስካሁን ድረስ በእኔና በርሱ መካከል የሆነው ነገር ሁሉ አንዴ ሆኗል። ይህን ጥያቄየን እንደማይቃወም አረጋግጡ። በተጨማሪም ያሉብኝን እዳዎች ሁሉ እንዲከፍልልኝ ንገሩት። በፈጣሪዬ ፊት ባለእዳ ሆኜ መቅረብ አልሻምና። መላ ቤተሰቤን፣ ልጆቼንና ሲያገለግሉኝ የነበሩትን ሁሉ ይቅርታ ያድርግላቸው። ባሉበት ሁኔታም ይቆዩ ዘንድ ፈቃዱ ይሁን።”

ወንድምየው ሱልጣን ባያዚድ ሁለተኛ ይህ የጀም ኑዛዜ ተፈፃሚ እንዲሆን አድርጓል።

ይህ ነው እንግዲህ ኢስላምን የሚኖሩት ሰዎች የሚያሳዩት ትክክለኛ ባህሪና ሁኔታ የሚንፀባረቅበት መንገድ። እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች በመጨረሻ ላይ ያሳዩት መደጋገፍና ለሃገራቸው ብሎም ለመላው ሙስሊም ዓለም ያሳዩት ተቆርቋሪነት በአርአያነቱ የሚጠቀስ ነው። እንዲሁም ለሕዝባቸው ያላቸው አሳቢነት ሁልጊዜም አንድነቱና ሰላሙ የተጠበቀ ሆኖ እንዲኖር ያደረጉት መስዋእትነት ለአብነት የሚበቃ ተምሳሌታዊ ተግባር ነው።

በኦቶማን ቱርክ ባህር ኃይል ታሪክ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጠው ሥራ የሰሩ ኢሊያስ ኡሩክና ሂዚር የሚባሉ ወንድማማቾች ይገኛሉ። እነዚህ ወንድማማቾች የጂሃድ ሰንደቃቸውን በሜዲቴራኒያን ባሕር ላይ ከማውለብለባቸው በፊት የተዋጣላቸው የባህር ላይ ነጋዴዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ይህ የንግድ እንቅስቃሴያቸው በሜድቴራኒያን ባህር ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ አደጋ እየተደቀነበት ይሄድ ጀመር። ይህም የሆነው በባህር ላይ ነጣቂዎችና የመርከብ ጠላፊዎች ምክንያት ነበር። ኡሩክ በባህር ወንበዴዎች ተይዞ ለባርነት ከተዳረገ በኋላ ወንድምየው ሂዚር

ረኢስ ወንድሙን ለማስለቀቅ ቤዛ የሚሆን ገንዘብ ቢልክም ተንኮለኛ የሆኑት ወንበዴዎች ቃላቸውን ሊጠብቁ ባለመቻላቸው የወንድምየው የባርነት ዘመናት እየተራዘሙ ሄዱ። በዚህ ብቻ ያልረኩት ከሃዲያኑ ወንበዴዎች በባርነት ወዳገቱት ኡሩክ ክርስትናን ይቀበል ዘንድ በድፍረት የሚናገር ቄስ ላኩ። ይሁን እንጂ የኡሩክ ረኤስ መልስ በፊታቸው ላይ እንዳረፈ ጥፊ አስደንጋጭ ነበር፡-

“እናንተ ደንቆሮ መኃይማን ትክክለኛ የሆነውን ኃይማኖት ትቼ እንዴት የሃሰት ኃይማኖት አባል ልሆን እችላለሁ?” ነበር ያላቸው።

በዚህ ንግግር የተበሳጩት ጠላፊዎች እንዲህ አሉ፡-

“ጉዳዩ እንደዚያ ከሆነ ያንተ ሙሐመድ[1] ይምጣና ያድንህ!” በአነስተኛ ጀልባ ላይ ከጫኑት በኋላ ወደ አንድ ያልታወቀና ራቅ ያለ ህንጻ ውስጥ ወስደው በመደበቅ ባርነቱን እንዲቀጥል አደረጉት።

በዚያ ጊዜም ኡሩክ ለአላህ እንዲህ በማለት ልመናውን አቀረበ፡-

“መጠጊያዬ ሆይ! አንተ ባሪያህን እንዴት እንደምትረዳኝ አሳያቸው።”

አላህ ልመናውን ከንቱ አላስቀረውም። ብዙም ሳይቆይ ከእስር ነጻ የሚወጣበትን ሁኔታ አመቻቸ። ይህን ያገኘው በአላህ ላይ በነበረው የእምነት ጽናትና ባደረገውም ተማጽኖ መሆኑን ያወቀው ኡሩክ ኃይማኖቱን ይበልጥ አጥባቂ ሆነ። ከዚህ ክስተት በኋላ ኡሩክ ከወንድሙ ሂዚር ረኢስ ጋር በመሆን በሜዲቴራንያን የባህር ላይ ወንበዴዎች ላይ ምህረት የሌለው ጦርነት ከፈቱ።

የዶርዳናል ጦርነትም ሌላው አስደናቂ የሆነና የአማኝ ሰውን ውስጣዊ የእምነት ግለት ማሳያ ተምሳሌት ነው።

---

[1] ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) ማለታቸው ነው።

የዴርዳነልን ጦርነት በአዛዥነት የመራውና በኋላ በጡረታ የተገለለው ኮሎኔል በጦርነቱ ውስጥ ክፉኛ የቆሰለ ሲሆን በእለታዊ የማስታወሻ መዝገቡ የሚከተለውን አስፍሮ ተገኝቷል፡-

"የዴርዳነል ጦርነት ከተካሄደባቸው ቀናት ውስጥ በአንዱ እለት ነበር፡፡ በዚያ እለት የተደረገው ጦርነት እስከምሽት ድረስ የቀጠለ ሲሆን ምንም እንኳን በውጊያ መሣሪያ አንጻር የጠላት ጦር የበላይነት የነበረው ቢሆንም የማታ ማታ ድሉ የእኛ ነበር፡፡ ከመቆጣጠሪያ ማማዬ ላይ ሆኜ የጦርነቱን እያንዳንዷን ሁኔታ በጉጉት እከታተል ነበር፡፡ "አላህ! አላህ!" የሚለው የሙስሊም ተዋጊዎች ጩኸት አድማሱን ሁሉ የሞላው ሲሆን አስፈሪና ታላቅ ሽብር የሚለቀውን የመድፍ ድምጽ ሳይቀር ውጦት ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እያለም የሆነ ሰዓት ላይ ከአጠገቤ የሰው እርምጃ ኮቴ በመስማቴ ዘወር ስል ከሃምሳ አለቃ ዓሊ ፊት ጋር ተጋጨን፡፡ ምን ችግር እንደተፈጠረ የመጠየቅ እድል እንኳን ሳላገኝ ሁሉንም ነገር በግልጽ ያስረዳኝን ክንዱን አሳየኝ፡፡ ያየሁትን በማየቴ በፍርሃት ልቤ ራደ፡፡ የግራ ክንዱ አንጓ በመመታቱ እጁ ከነጣቶቹ ሊቆረጥ ደርሷል፡፡ ተቆርጦ ወለሉ ላይ ከመውደቅ የዳነውም ገና ያልተቆረጠ ስስ ቆዳ ይዞት ስለነበር ነው፡፡ ሃምሳ አለቃ ዓሊ ይህ ሁሉ ሲሆን ከስቃዩ ብዛት ጥርሱን እያፋጨ ስቃዩን ለመቋቋም ይሞክር ነበር፡፡ ከዚያም በቀኝ እጁ ከሰገባው ያልወጣ ጩቤ አቀበለኝና እንዲህ አለ፡-

"ኮማንደር! እባክህ ቆርጠህ ጣለው!"

እነዚህ ጥቂት ቃላት በውስጤ የፈጠሩብኝን መረበሽ ሁኔታዎች ብዙ እንዳገናዝብ ባያደርገኝም ለጊዜው ለሰውየው ላደርግለት የምችለው ነገር ይህ ብቻ ስለነበር እጁ ከክንዱ ጋር የተንጠለጠለበትን ቆዳ በሰጠኝ ጩቤ ቆርጬ ጣልኩት፡፡ ይህን ዘግናኝና የደም ዝውውርን የሚያቆም ሥራ ከፈፀምኩኝ በኋላ የሃምሳ አለቃ ዓሊን ሞራል ከፍ ለማድረግ ጥረቴን እንዲህ በማለት ቀጠልኩ፡-

"ብዙ አትዘን ሃምሳ አለቃ ዓሊ፡፡ አላህ ከቁስልህ ይፈውስህ፡፡" ሆኖም ግን ብዙም ሳይቆይ ሃምሳ አለቃ ዓሊ ለሕዝቦቹ እጁን ብቻ ሳይሆን መላ አካሉንም መስዋእት አደረገ፡፡ ሊሞት አቅራቢያ አይኖቹን ሲከድን በደም ኩሬ ውስጥ እንደተጋደመ የሚከተለውን ዓረፍተ ነገር ይደጋግም ነበር፡-

"ሙስሊሟ ሃገሬ ለዘላለም ትኑር! ከእምነት እንዳታፈነግጥ አላህ ይጠብቃት … ሕይወቴንም ለኃይማኖቴ ብዬ የምሰዋ ያድርገኝ!"

በዴርዳን ጦርነት ሮማውያን የቆፈሯቸውና ለመተኮሻነት ሙስሊም ቱርኮች የተጠቀሙባቸው ምሽጐች በጠላቶቻቸው እንግሊዞች እንዳልነበሩ ሆነው ተደምስሰዋል፡፡ በውስጣቸው የነበረ ብዙ መሣሪያም እየፈነዳ ወደ አየር የተበተነ ሲሆን ስልሳ የሚሆኑ መድፈኞችም ሰማእት (ሸሂድ) ሆነዋል፡፡ በዚያ ውጊያ ከአንድ ባታሊዮን ጦር የተረፉ ቢኖሩ አንድ ካፒቴንና ሁለት ወታደሮች እንዲሁም አንድ እንከናማ መድፍ ብቻ ነበሩ፡፡

ካፒቴኑ ያሉበትን ሁኔታ በአካባቢያቸው ለሚገኝ ጦር ሊያሳውቅ ወደዚያው ሄዷል፡፡ ከሁለቱ ወታደሮች አንዱ የሆነው ኮካ ሰይድ የእንግሊዞች መርከብ ጭሷን እያንቧለቀች ባህሩን ሰንጥቃ ስትሄድ ያስተውላል፡፡ ከዚያም በረዥሙ ከተነፈሰ በኋላ አይኖቹ በእንባ ተሞሉ፡፡ በሃዘን የቆሰለችው ልቡ በተስፋ መቁረጥና በጠላት ፊት ምንም ማድረግ ባለመቻል ትመታለች፡፡ ከዚያም እጆቹን ወደ ሰማይ አነሳና እንዲህ በማለት አላህን መለመን ጀመረ፡-

"ጠባቂዬ የሆንከው አላህ ሆይ! የኃይል ባለቤት የሆንከው አላህ ሆይ! ጥንካሬህን አላብሰኝ፡፡"

በቅጽበትም ኮካ ሰይድ ከዚህ ዓለም በሆነ መንፈሳዊ ኃይል የተሰወረ ያክል ሆነ፡፡ ከዚያም በጌታው ፊት ያለ መሰለ፡፡ እንባዎቹ ከአይኖቹ እየወረዱ ጉንጮቹን ይነኩትና ወደ መሬት ይፈሳሉ፡፡ ከዚያም ለአፍታ ያህል "ከአላህ በስተቀር ኃይልንም ሆነ ታላቅነትን የሚያጐናጽፍ ማንም የለም፡፡" በማለት ከተናገረ በኋላ በቅጽበት "አላህ!" በማለት ጩኸቱን ለቀቀው፡፡ በዚያው ቅጽበት ጓደኛው በግርምት ለጉድ እያስተዋለው

በግምት 276 ኪ.ግ. ወደ ሚመዝነው የመድፍ ጥይት አመራ፡፡ ከዚያም ተሸክሞት ወደ መድፉ ላይ ካወጣው በኋላ በአፉ ውስጥ አስገብቶ ለሶስት ጊዜያት ያክል  በብረት መጕርጕሪያ ሸቀሸቀው፡፡ ይህን ሁሉ ሲያደርግ የደረቱና የትከሻው ጡንቻ ሲንጫጫ ይሰማ ነበር፡፡ ላቡ እንደ ውሃ በመላ አካሉ  እየተንጠባጠበ በደረቁ ከናፍሮቹ አላህን እንዲህ በማለት ተማፀነ፡-

“አላህ ሆይ! ጥንካሬዬን አትውሰድብኝ!”

በመጨረሻም የጦርነቱ እጣ ፋንታ በዚያ መድፍ ውስጥ በጨመረው ሶስተኛ አረር ምክንያት ሙሉ በሙሉ ተለወጠ፡፡ ዘ-ኦሽን (ውቅያኖስ) ተብላ የምትጠራውና እስከ አፍንጫዋ በትጥቅ የሞላችው የእንግሊዞች መርከብ በዚያ የመድፍ ጥይት ተመትታ በእሳት በመያያዟ የእሳት ነበልባል ሲጕረድ ይታይ ነበር፡፡

ይህን ሁኔታ ያስተዋለው ከቫት ፓሻ እንዲህ አለ፡-

“የእኔ ልጅ! በጣም የተሳካ ሥራ ሰርተሃል፡፡ አሁን ደግሞ ምን ሽልማት ብሰጥህ እንደምትመርጥ ንገረኝ፡፡”

ይህ ሁሉንም ነገር በመርሳት በአላህ ላይ ብቻ የሚመካ ምስኪን የሚከተለውን ተናገረ፡-

“አለቃዬ! እኔ ምንም እንዲሰጡኝ አልሻም፡፡ ሆኖም ግን ልክ እንደ ነጻ ትግል ስፖርተኛ ሰውነቴ የፈረጠመ በመሆኑ በቀን አንድ ዳቦ ብቻ መመገቤ በቂ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ስለሆነም በየእለቱ ሁለት ዳቦዎች ይሰጡኝ ዘንድ የሚመለከታቸውን ያዙልኛልን? ያንን ካገኘሁ አሁንም በጠላቶቼ ላይ ጠንካራ እንደሆንኩ መዝለቅ እችላለሁ፡፡

ከቫት ፓሻ በዚህ በሰይድ ጥያቄ ፈገግ ካለ በኋላ የጠየቀው እንደሚሟላለት ቃል ገባለት፡፡ ከዚያም ምሽቱ ላይ ሁሉም ሰው ራሽኑን አንድ አንድ ዳቦ ብቻ ሲቀበል ኮካ ሰይድ ግን ሁለት ዳቦ ወሰደ፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ አማኝ የሆነ ጀግና ሰው ልብ ይህን ሊቀበል አልቻለም፡፡ የምግብ እጥረት በሰፈነበት በዚያ ጊዜ ከጓደኞቹ  ተለይቶ ሊጠቀም

አልፈለገም፡፡ የተሰጠውን ዳቦ ከመለሰ በኂላ ዳግመኛም ሁለት ዳቦ ላይቀበል ለራሱ ቃል ገባ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ኢኽላስ[1] (ፍጹምነት)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) "ሥራ የሚለካው በንያ (ቁርጠኛ ሃሳብ) ነው።" ብለዋል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ይህም በመሆኑ የሁሉም መልካም ሥራዎች ፍሬ ነገርና የአምልኮት ዓይነቶች ሁሉ ዋነኛ ዓላማ አላህን ማስደሰትና የእርሱን ውዴታ ማግኘት ነው። ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ኢኽላስ (ፍጹምነት) ሲኖር ነው። በሌላ አገላለጽ አንድን መልካም ሥራ ወደ አምልኮት (ኢባዳ) ደረጃ ከፍ ለማድረግና ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማስቻል ልብን ፍጹማዊ ማድረግ የግድ ነው ማለት ነው። አላህ የሰዎችን መልካም ሥራ የሚቀበልበት ዋነኛ ቅድመ ሁኔታ ወይም መሥፈርት ኢኽላስ የሆነውም ለዚሁ ነው።

ኢኽላስ ማለት አንድን መልካም ሥራ የአላህን ውዴታ ለማግኘት ብቸኛ ዓላማ መሥራትና ሥጋዊና ዓለማዊ ጥቅማጥቅሞችን በመቀላቀል አለመበረዝ ማለት ነው። ኢኽላስ የሌለው ሥራ ሰሪውን ከማድከምና በመጨረሻም ፍሬ የሌለው ከመሆን ያለፈ እጣ የለውም።

ኢኽላስ ወደ ኃያሉ አላህ ለመቃረብ በሚደረግ ጥረት ላይ ልብን የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን በማሰብ ከመበከል መጠንቀቅን የሚያመለክት ቃል ነው። እናም አንድ ሰው መልካም ሥራው ኢኽላስ አለው የሚባለው ለታይታ (ሪያእ) እና ለኩራት (ዑጅብ) እስካልሰራው ድረስ ብቻ ነው።

ስለሆነም የአላህን ውዴታ ከማግኘት በመለስ ማንኛውንም ምኞት ከልብ ማስወገድ በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ አስፈላጊና ግዴታ የሆነ ተግባር

---

[1] በአረብኛ ኢኽላስ የሚለው ቃል "ኸለሰ" ከሚለው ሥርወ-ቃል የተገኘ ሲሆን ይህም ማለት ማጥራት፣ አለመቀላቀልና ንጹህ ማድረግ የሚሉትን ትርጓሜዎች ይይዛል።

ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው ሁልጊዜም ማወቅና መጠንቀቅ ያለበት ኢኽላስ አላቸው የሚባሉ ሰዎች እንኳን ይህን ውብ የሆነ የልብ ጌጥ የማጣት ቋሚ አደጋ የተደቀነባቸው መሆኑን ነው፡፡

ይህም የሚሆነው ነፍስ በሰው ልጅ ላይ በመንገሷና በስጋዊ ስሜት ማየል ምክንያት ነው፡፡ እናም ሁልጊዜም ከነፍስ በላይ ሆኖ መኖር ከባድና አስቸጋሪ የመሆኑን ያክል ኢኽላስንም ጠብቆ መልካም ሥራዎችን መከወን የዚያኑ ያክል አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ዘኑን ሚስሪ የተናገረው ሁልጊዜም ተጠቃሽ ነው፡-

"ሁሉም ሰው በአደጋ ውስጥ ነው፤ የእውቀት ባለቤቶች ብቻ ሲቀሩ፡፡ ሁሉም የእውቀት ባለቤቶች በአደጋ ውስጥ ናቸው፤ ባወቁት ነገር የሚሰሩ ሲቀሩ፡፡ ሁሉም መልካም ሥራ የሚሰሩ ሰዎች በአደጋ ውስጥ ናቸው፤ ኢኽላስ ያላቸው ብቻ ሲቀሩ፡፡ እንዲሁም ሁሉም ኢኽላስ ያላቸው ሰዎች ቋሚ በሆነ አደጋ ውስጥ ናቸው…"

ይሁን እንጂ ያለውን አስቸጋሪ ነገር ሁሉ ተቋቁመው ኢኽላስ ያለው ሥራ መከወን የቻሉ ሰዎች ታላቅ የሆነን መለኮታዊ ፀጋ የታደሉ ናቸው፡፡

ለአንድ አማኝ ከኢኽላስ የበለጠ የአላህን ውዴታ የማግኛ ሌላ ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡ የአላህም ዓላማ ሰዎች በዚህች ምድር ላይ እያሉ የእርሱን ውዴታ በመሻት የሰሯቸውን መልካም ሥራዎች ይዘው እንዲገናኙት ነው፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلۡ إِنِّيٓ أُمِرۡتُ أَنۡ أَعۡبُدَ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ ١١ ﴾ الزمر: ١١

*"በል እኔ አላህን ኃይማኖትን ለእርሱ ያጠራሁ ሆኘ አንድገዛው ታዘዝኩ፡፡ " (አዝ-ዙመር፡ 11)*

﴿ إِنَّآ أَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ فَٱعۡبُدِ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ ٢ ﴾ الزمر: ٢

*“እኛ ወደ አንተ መጽሐፉን በእውነት (የተመላ) ሲሆን አወረድነው:: አላህንም ኃይማኖትን ለእርሱ ብቻ ያጠራህ ሆነህ ተገዛው::” (አዝ-ዙመር:2)*

**ኢኽላስና ሥራን ማጥራት አንድን አማኝ ከሰይጣን ጥቃት ያድነዋል:: ምክንያቱም ሰይጣን የሚለክፈውና የሚቆጣጠረው ኢኽላስ የሌለውን ሰው ነውና:: አላህ በብርሃን በተሞላው መጽሐፉ እንዲህ ይላል:-**

﴿ قَالَ رَبِّ بِمَآ أَغْوَيْتَنِي لَأُزَيِّنَنَّ لَهُمْ فِي ٱلْأَرْضِ وَلَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ ٣٩ إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ ٱلْمُخْلَصِينَ ٤٠ ﴾ الحجر: ٣٩ - ٤٠

*“(ኢብሊስ) አለ:- ጌታዬ ሆይ! እኔን በማጥመምህ ይሁንብኝ ለእነርሱ በምድር ላይ (ኃጢአትን) እሸልምላቸዋለሁ:: መላቸውንም አጠማቸውም አለሁ:: ከእነርሱ ፍጹሞቹ ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ::” (አል-ሒጅር: 39-40)*

**አላህ በሚቀጥለው የቁርአን አንቀጽ የሚከተለውን የምስራች የያዘ እውነት ሲናገር እንዲህ ይላል:-**

﴿ وَمَا تُجْزَوْنَ إِلَّا مَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ٣٩ إِلَّا عِبَادَ ٱللَّهِ ٱلْمُخْلَصِينَ ٤٠ ﴾ الصافات: ٣٩ - ٤٠

*“ትሰሩትም የነበራችሁትን እንጂ ሌላን አትመነዱም:: ግን ምርጥ የሆኑት የአላህ ባሮች (ቅጣትን አይቀምሱም)::” (አስ-ሷፍፋት:39-40)*

**መልካም ሥራ የቱንም ያህል ትንሽ ብትሆን በኢኽላስና በልባዊ እሳቤ ልትሰራ ይገባል:: ይህን ያደረገ ሰውም ያለ ኢኽላስ ብዙ መልካም ሥራ አግበስብሶ ከአላህ ፊት ከሚቀርብ ሰው ይልቅ በላጭና እድለኛ ነው:: የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ:-**

**“ሥራችሁን አጥሩ! ይህን ካደረጋችሁ ትንሽም ቢሆን ይበቃችኋል::”**

**ኢኽላስና ሥራን ማጥራት መለኮታዊ ቡራኬ አይለየውም:: የአላህ መልእክተኛ እንደሚከተለውም ማለታቸው ተጠቅሷል:-**

“አላህ ይህን ኡማ (ሕዝብ) የሚረዳው በዱዓው (ልመናው)፣ የግዴታ ሶላቶችን በመስገዱና ሥራውን በማጥራቱ ነው።” (ነሳኢ)

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ማብራሪያ መገንዘብ እንደሚቻለው ኢኽላስና ሥራን ማጥራት ለድል የሚያበቃ መሣሪያ መሆኑን ነው። ምክንያቱም በኢኽላስ የተሰሩ መልካም ሥራዎች ከብክለት የተጠበቁና ምንም ዓይነት አደጋ ስለማያጋጥማቸው ነው። በታሪክ ገፆች ውስጥ እዚህም እዚያም ማንበብ እንደሚቻለው አነስተኛ ሰራዊትን ይዘው በልባዊነት (ኢኽላስ) የታገሉና እጅግ ታላቅ የሚባል ሰራዊትን በአላህ ፈቃድ ያሸነፉ ብዙ ናቸው። ይህም የሚያሳየው በሁሉም የሕይወትና የአምልኮት ዘርፍ ኢኽላስ የድል መሠረት መሆኑን ነው።

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሕይወት የተሞላው በኢኽላስ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ክስተት የተፈጠረው በመጀመሪያዎቹ የተልእኳቸው ጊዜያት ሲሆን ለዚህ ጥሩ ማሳያ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፦

ከሃዲያኑ የቁረይሽ ሹማምንት በተለያዩ ጊዜያት አጎታቸውን አቡ ጧሊብን ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በመላክ ይህን ዳዕዋቸዉን እንዲተው ይነዘንዟቸው ነበር። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በአንድ ወቅት ይህን መልስ ነበር የሰጡት፦

“አጎቴ ሆይ! በአላህ ይሁንብኝ ፀሃይን በቀኝ እጄ፣ ጨረቃን ደግሞ በግራ እጄ ቢያስጨብጡኝ እንኳ ይህን ተልእኮዬን ፈጽሞ አልተውም። ወይ አላህ በዓለም ሁሉ ይዘረጋውና ተልእኮዬ ያበቃል። አለያም ደግሞ በዚሁ ላይ እያለሁ እሞታለሁ።”

አጋሪዎቹ የመካ ሰዎች በአቡ ጧሊብ በኩል ያደረጉት ሙከራ እንዳልሰመረላቸው ከተረዱ በኋላ ራሳቸው በቀጥታ ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በመሄድ ድፍረት በተሞላበት ሁኔታ የሚከተለውን አቀረቡላቸው፦

“የምትፈልገው ሃብት ከሆነ እንስጥህና ካንተ ጋር የሚወዳደር አንድም ሰው በመካከላችን እስከማይኖር ድረስ የናጠጥክ ሐብታም እናድርግህ፣ የምትሻው መሪ መሆንን ከሆነም እንሹምህና መሪያችን ሁን። እንዲሁም የመካ ገዥም እናድርግህ። የተከበረች ሴትን ማግባት ፈልገህ ከሆነ በቁረይሽ ውስጥ ካሉ ሴቶች ሁሉ ቆንጆና የተከበረች የሆነችውን መርጠን እንድርሃለን። ይኸን ነገር እስከተውክ ድረስ አንተ የምትፈልገውን ነገር ለማድረግ ዝግጁ ነን።”

ለዚህ የከሃዲያኑ ርካሽ አለማዊና ስጋዊ ፍላጐቶችን ብቻ የተንተራሰ ጥያቄ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን መልስ ሰጧቸው፡-

“እኔ እናንተ ምንም ነገር እንድትሰጡኝ አልሻም። እኔ ሃብት፣ ንብረት፣ ንግስና፣ መሪነትን ወይም ሴትን አልፈልግም። እኔ ከእናንተ የምፈልገው አንድ ነገር ብቻ ሲሆን እርሱም የሃሰት አማልክትን ትታችሁ አላህን ብቻውን እንድታመልኩት ነው።”

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሕይወታቸውን የገፉት የአላህን መልእክት በማስተማርና በማሰራጨት ሲሆን ለዚህ ድርጊታቸውም ከሰዎች አንድም ዓይነት አለማዊ ጥቅማጥቅም በመፈለግ ለስሜታቸው አላደሩም። እርሳቸውም ሆኑ ሌሎች ቀደምት የአላህ ነቢያት ክቡር የሆነውን የአላህ ኃይማኖት ወደሰዎች ሲያደርሱ ይህን የመሰለ አቋም የነበራቸው መሆኑን ቁርአን ሲገልጽልን እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٍۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَىٰ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٢٧ ﴾ الشعراء: ١٢٧

*“በእርሱም ላይ ምንም ዋጋ አልለምናችሁም። ዋጋዬ በዓለማት ጌታ ላይ እንጅ በሌላ ላይ አይደለም።” (አሽ-ሹዓራ፡127)*

የሚከተለውና በነቢዩ ሙሣ (ዐ.ሰ.) ሕይወት ላይ የደረሰ ክስተት የኢኽላስን ደረጃ በጉልህ ያንፀባርቃል፡-

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَمَّا وَرَدَ مَآءَ مَدۡيَنَ وَجَدَ عَلَيۡهِ أُمَّةٗ مِّنَ ٱلنَّاسِ يَسۡقُونَ وَوَجَدَ مِن دُونِهِمُ
ٱمۡرَأَتَيۡنِ تَذُودَانِۖ قَالَ مَا خَطۡبُكُمَاۖ قَالَتَا لَا نَسۡقِي حَتَّىٰ يُصۡدِرَ ٱلرِّعَآءُۖ وَأَبُونَا شَيۡخٞ كَبِيرٞ
﴿٢٣﴾ ﴾ القصص: ٢٣

*“ወደ መድየንም ውሃ በመጣ ጊዜ በርሱ ላይ ከሰዎች ጭፍሮችን (መንጋዎቻቸውን) የሚያጠጡ ሆነው አገኘ፡፡ ከእነርሱ በታችም (ከውሃው መንጐቻቸውን) የሚከለክሉን ሁለት ሴቶች አገኘ፡፡ ነገራችሁም ምንድን ነው? አላቸው፡፡ እረኞቹ ሁሉ (መንጋዎቻቸውን) እስከሚመልሱ አናጠጣም፡፡ አባታችንም ትልቅ ሽማግሌ ነው አሉት፡፡” (ቀሶስ፡23)*

እነዚህ ሁለት ልጃገረዶች ሳፉራና ሱፈይራ የሚባሉ የነቢዩ ሹዓይብ ልጆች ነበሩ፡፡ ነቢዩ ሙሣ (ዐ.ሰ.) ከሃገረ ግብጽ ተነስተው የሲናይን የሚያነድ ምድረ በዳ በማቋረጥ በረሃብና በጥም ለስምንት ቀናት ተጉዘዋል፡፡ ከዚያ በኋላ አረፍ ባሉበት ቦታ ነው ይህ ክስተት የተፈጠረው፡፡ በመሆኑም ድካማቸውና ርሃባቸው እንዳለ ሆኖ ውስጣቸው በነበረው ተፈጥሮአዊ ደግነት ያንን ተቋቁመው ለልጆቹ ከብቶቻቸውን አጠጡላቸው፡፡ እነርሱም አመስግነዋቸው ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡

ኋላ ላይ ነቢዩ ሹዐይብ (ዐ.ሰ.) ሙሣን (ዐ.ሰ.) ምግብ ይቀማምሱ ዘንድ ወደቤት እንዲመጡ ጋብዘዋቸው ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ሙሣ (ዐ.ሰ.) ለቀናት ረሃብ የጠናባቸው ቢሆንም የተደረገላቸውን ግብዣ ለመቀበል ሲያመነቱ ተስተዋሉ፡፡ ሹዐይብ (ዐ.ሰ.) ይህ ለምን እንደሆነ ሙሣን (ዐ.ሰ.) ሲጠይቋቸው የሚከተለውን መልስ ሰጡ፡-

“እኛ የዚህን ዓለም ፀጋ ሁሉ ብንሰጥ እንኳን ለመጪው ዓለም ያስቀደምነውን አንድ መልካም ሥራ ለመለወጥ የማንፈቅድ ቤተሰብ ነን፡ ፡ እኔ ልጆቹን የረዳኋቸው ምግብ እንዲሰጡኝ ፈልጌ ሳይሆን የአላህን ውዴታ በመሻት ስለነበረ ነው፡፡”

ሹዐይብ በዚህ ንግግር በጣም በመደሰታቸው እንዲህ አሉ፡-

“ይህን ምግብ እንድትበላ የጋበዝንህ ላደረግክልን መልካም ተግባር አፀፋ ይሆን ዘንድ አስበን ሳይሆን አንተ አንግዳችን በመሆንህ ነው፡፡ እካክህ ወዲህ ቀረብ በልና እንብላ!”

በዚህ ጊዜ በረሃብና በድካም የጠወለጉት ሙሣ (ዐ.ሰ.) ግብዣውን በደስታ ተቀበሉ፡፡

ይህ ምሳሌ የሚያሳየን መልካም ሥራን በኢኽላስ የመሥራትንና ከማንኛውም ዓለማዊ ጥቅማጥቅም ንያን (እሳቤን) የማጽዳትን ተገቢነት ነው፡፡

ወሲላ ኢብን አስቃ (ረ.ዐ.) በተቡክ ዘመቻ የተመለከተውን ኢኽላስ እንደሚከተለው ይተርካል፡-

“ሙስሊሙ ሰራዊት ወደ ተቡክ ዘመቻ ለመሄድ በሚንቀሳቀስበት ሰዓት እኔ ምንም ዓይነት ገንዘብም ሆነ የምጓጓዝበት እንስሳ አልነበረኝም፡፡ ይህን የመሰለ የተባረከ ዘመቻ እንዳያመልጠኝ ስላልፈለግኩ መዲና ውስጥ ሆኜ እንዲህ በማለት እጮህ ጀመር፡፡

“በጦርነቱ ውስጥ ከማገኘው ምርኮ የሚጋራውና ወደ ዘመቻው ስሄድ ከመጓጓዣው ላይ የሚያወጣኝ ማን ነው?” አንድ አንሷር የሆነ ሽማግሌ ከመጓጓዣው ላይ እንደሚያወጣኝና ወደ ጦር ግንባርም ይዞኝ እንደሚሄድ ነገረኝ፡፡ እኔም ወዲያው “ውል ይኖረናል ማለት ነው” በማለት ተናገርኩ፡፡ እርሱም፡-

“እንደዚያ ከሆነ በአላህ ፀጋ ከእኔ ጋር ጉዞ እንጀምር” አለኝ፡፡

በዚህ አኳኋን ጥሩ ባልደረባ በማግኘቴ ጉዞ ጀመርን፡፡ በዚያ ጉዞ እንደአጋጣሚ ሆኖ እኔ ምርኮ አገኘሁ፡፡ የተወሰኑ ግመሎች በእጄ ገቡ፡፡ ወደዚያ የአንሷር ሽማግሌ ይዣቸው ስሄድ እንዲህ አለኝ፡-

“ግመሎችህን ለራስህ አድርግ!”

“ጉዞ ከመጀመራችን በፊት በነበረን ውል መሠረት እነዚህ ግመሎች ያንተ ናቸው፡፡ መውሰድ አለብህ፡፡” አልኩት፡፡ ግና ምን ያደረጋል፡፡ ብዙ

ጊዜ ይህን አረፍተ ነገር ብደጋግምም ሰውየው እንዲህ በማለት እንደማይቀበል ገለፀልኝ፡-

“ወንድሜ ሆይ! የምርኮ ገንዘብህን ያዝ፡፡ የእኔ ፍላጎት አንተ እንደምትለው አይደለም፡፡ የእኔ ፍላጎት አንተ ዘምተህ ከምታገኘው አጅር (ምንዳ) ተካፋይ መሆንና ከአላህ ደመወዜን መቀበል ነው፡፡” (አቡዳውድ)

እነዚያ የተባረኩ የሶሃባ ትውልድ አባላት ያላቸውን ነገር ሁሉ በአላህ መንገድ ላይ ወጪ ካደረጉ በኋላ አላህን አስደስተው ምንዳቸውን ከእርሱ መጠበቅ ነው ሁሌም የሚመኙት፡፡ በዚያ ሁኔታ ወደ ዘመቻ ሲሄዱም ሆነ አማኝ ወንድማቸውን በአንዳች ነገር ሲደግፉ ሁልጊዜም የአላህን ውዴታ በልባቸው በማሰብ መሆኑ ያስደንቃል፡፡

ዓኢሻ (ረ.ዐ.) ድሆችን በረዳችና ምጽዋት በሰጠች ቁጥር ለሚያደርጉላት ዱዓ ያንኑ የመሰለ ዱአ ለእነርሱ በማድረግ አፀፋውን የመመለስ ልማድ ነበራት፡፡ ይህን የምታደርገው ለምን እንደሆነ ተጠይቃ ስትመልስ እንዲህ አለች፡-

“አንድ በጐ ነገር ባደረግሁላቸው ቁጥር የሚያደርጉልኝ ዱዓ ላደረግኩት መልካም ነገር ምንዳዬ ሆኖ እንዳይቀርብኝ ስለምፈራ ተመሳሳይ የሆነ ዱዓ እኔም አደርግላቸውና ምንዳዬን ከአላህ እጠባበቃለሁ፡፡”

ይህ ምን አይነት ኢኽላስ (ስራን ማጥራት) ነው? የነቢዩ ባልደረቦች ሥራቸውን ለአላህ ብቻ በማጥራት የሚስተካከላቸው አልነበረም፡፡

የሚከተለውን ገጠመኝ ስናነብ የዓሊ (ረ.ዐ.) ኢኽላስ ምን ያክል ጥልቀት እንዳለው በአላህ ፈቃድ እንገነዘባለን፡፡

በአንድ ውጊያ ላይ ዓሊ (ረ.ዐ.) አንድ የጠላት ተዋጊን መሬት ላይ ጥለው ሊገድሉት በተዘጋጁበት ሰዓት በአንፀባራቂው ፊታቸው ላይ ምራቁን ተፋባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አንዳች ዓይነት የብቀላና ግላዊ ስሜትን የተንተራሰ ንዴት በውስጣቸው ተቀጣጠለ፡፡

የአላህ አንበሳ በመባል ለሚታወቁት ዓሊ (ረ.ዐ.) ይህን ሰው በሰይፍ ቆራርጦ መጣል እንደ ህፃን ጨዋታ ቀላል ነበር፡፡ ሆኖም ግን ዓሊ (ረ.ዐ.) ያን በማድረግ ፈንታ በወደቀበት ትተውት በመነሳት ዘወር አሉ፡፡ ከዚያም ዙልፊቃር በመባል የሚታወቀውን ልዩ ሰይፋቸውን ወደ ሰገባው መለሱ፡፡

በድንጋጤ ሞቱን ይጠባበቅ የነበረውና በውርደት መሬት ላይ በጀርባው የተንጋለለው ሰው በዚህ ሁኔታ በጣም ተደነቀ፡፡ እርሱ ይጠብቅ የነበረው ዓሊ (ረ.ዐ.) መጀመሪያም መሬት ላይ የጣሉት በመሆኑ ምራቁን ሲተፋባቸው የዚያ ንዴትና ለምን ተደፈርኩ ባይነት ተጨምሮ በቅጽበት እንደሚከታትፉት ነበር፡፡ ሆኖም ግን እርሱ እንዳሰበው ሳይሆን ቀረ፡፡ ያ ሰው ያንን የኢስላም ጀግና እንዲሁም በያንዳንዱ ሙስሊም ልብ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው ሰው በጉጉት ጠየቀ፡-

“አሊ ሆይ! ልትገድለኝ እየቻልክ ለምን ይሆን የተውከኝ? ሃሳብህን እንድትቀይር ያደረገህ ነገር ምንድን ነው? ያን ከመሰለ አስፈሪ ሁኔታ በአንድ ጊዜ የቀዘቀዝከው ምን ሆነህ ይሆን?…”

ዓሊ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መልስ ሰጡት፡-

“ይህን የነቢዩን ሰይፍ የምጠቀምበት በአላህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ የነፍሴን ዝንባሌ ጣልቃ ላስገባ አልፈልግም፡፡ አንተ ምራቅህን ስትተፋብኝ ልታናድደኝና ልትሰድበኝ ፈልገህ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ በዚያ ሁኔታ ላይ እያለሁ ብገድልህ ለአላህ ብዬ ሳይሆን ለነፍሴ በማድላት ይሆንብኛል ብዬ ፈራሁ፡፡ ልጋደልህ የፈለግኩት ለአላህ ብዬ ሲሆን የራሴን ክብር በመከላከል እንዳልገድልህ በመስጋቴ ነበር የተውኩህ፡፡”

በዚህ ጊዜ በኢስላም ኃይማኖት ረቂቅ እሳቦትና ሕይወት ባላቸው አስተምህሮቶቹ ልቡ የተነካው ያ ሰው ኢስላምን ተቀበለ፡፡

በአንድ ወቅት በባግዳድ ገበያ ላይ ታላቅ የሚባል እሳት ተነሣ፡፡ ከሚቃጠሉት የገበያ መደቦች መካከል በአንዱ ውስጥ ሁለት ህፃናት ይገኙ ነበር፡፡ ልጆቹ የድረሱልን ጩኸታቸውን እያቀለጡት ቢሆንም

የእሳቱ ነበልባል እጅግ ኃያል ከመሆኑ የተነሣ ማንም ሰው ይህንን ተግባር ደፍሮ ሊፈጽም አልቻለም፡፡

ይህ በእንዲህ እያለም እናታቸው በተስፋ መቁረጥ ውጭ ቆማ እያለቀሰች እንዲህ ትል ነበር፡-

“ልጆቼን ከዚህ ነበልባል ላዳነልኝ ሰው 1000 ወቄት ወርቅ እሰጠዋለሁ፡፡”

በዚህ ጊዜ አቡል-ሁሴይን ኑሪ በዚያ በኩል ሲያልፉ ነበርና ዘለው እሳቱ ውስጥ በመግባት ወደ ልጆቹ አመሩ፡፡ እሳቱ በዚያ ጊዜ ለእርሳቸው ልክ አበባ እንደሞላበት መናፈሻ ነበር የሆነላቸው፡፡ በአላህ እርዳታ ይህ ብሩክ ሰው ሁሉም ሰው እየተመለከተ እነዚያን ልጆች ከእሳቱ ውስጥ ይዘዋቸው ወጡ፡፡

በዚህ ጊዜ እናታቸው ያንን ቃል የገባችውን ወርቅ በስጦታ መልክ ደስ እያላት አቀረበች፡፡ በዚህ ጊዜ አቡል ሁሰይን ፊታቸውን ኮስተር አድርገው እንዲህ አሉ፡-

“ወርቅሽን ያዥና ታላቅ የሆነውን አላህ አመስግኚ፡፡ ያደረግኩትን ነገር ለአላህ ብዬ ሳይሆን አንዳች ቁሳዊ ነገርን ለማግኘት አድርጌው ቢሆን ኖሮ ልጆቹን ከእሳቱ ላንቃ ላወጣቸው ባልቻልኩ ነበር፡፡”

ከዚህ ክስተት የምናገኘው ትምህርት ብዙ የአላህ ባሮች በነዲድ እሳት ውስጥ እየገቡ አንዳች ጉዳት ሳይደርስባቸው አምልጠዋል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በልባቸው ውስጥ በነበረው የኢኽላስ ደረጃ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ለምሳሌ የነቢዩ ኢብራሂምን (ዐ.ሰ.)ሁኔታ ብናይ እርሳቸው ምርጥ የአላህ ወዳጅ ነበሩ፡፡ ከእርሱ ጋርም በነበራቸው የሚያምር ግንኙነት እሳት ውስጥ ተጥለው እያሉ እሳት እንዳታቃጥላቸው አላህ ልዩ ትእዛዝ ሊሰጣት ችሏል፡፡ እናም ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) በሰላም ከዚያ ጉድ ማምለጥ ቻሉ፡፡

ኢኽላስ (ራስን ለአላህ ብቻ ማጥራት) በሁሉም ድርጊቶች ውስጥ ተጽእኖ ሲኖረው ልናይ እንችላለን፡፡ አንድ ሰው በልቡ ውስጥ ባለው ኢኽላስ ልክ ከፈጣሪው ምንዳውን ማግኘቱ የማይቀር ሲሆን የምንዳው ትልቅ

መሆንና ማነስም የሚወሰነው በሰውየው ኢኽላስ ማነስና ትልቅ መሆን ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው ገንዘቡን በሰደቃ መልክ ሲሰጥ ያንን ገንዘብ በስህተት ለማይገባው ሰው ቢሰጥ እንኳን ከምንዳው አንዲት ነገር አይጐድልበትም፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን እውነታ በሚከተለው ሐዲስ ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ ጊዜ የሆነ ሰው እንዲህ አለ፡- “እኔ ሰደቃ ልሰጥ ነው፡፡”

በዚያው ምሽት የሰደቃውን ገንዘብ ይዞ ከቤቱ ከወጣ በኋላ በአንድ የታወቀ ሌባ እጅ ላይ አስቀምጦለት ወደቤቱ ይመለሳል፡፡ በቀጣዩ ቀን የከተማዋ ሰዎች እንዲህ እያሉ ያወሩ ጀመር፡-

“የሚገርም ነገር ነው፡፡ ባለፈው ምሽት የሆነ ሰው ለአንድ ሌባ የምጽዋት ገንዘብ ሰጠው!”

ሰውየው እንዲህ አለ፡-

“አላህ ሆይ! ልቅና የሚገባው ላንተ ነው፡፡ ዛሬ ምሽትም እንዲሁ ምጽዋት እሰጣለሁ፡፡”

እንደገናም ገንዘቡን ይዞ ከቤት ወጣ፡፡ ለአንዲት ሴተኛ አዳሪ ሰጥቷት ተመለሰ፡፡ በቀጣዩ ቀን የከተማዋ ሰዎች አሁንም እንዲህ አሉ፡- “ይህ ፈጽሞ ሊታመን አይችልም! ባለፈው ምሽት የሆነ ሰው ለአንድ ሴተኛ አዳሪ ምጽዋት ሰጠ፡፡››

ሰውየው አሁንም እንዲህ አለ፡-

“አላህ ሆይ! ልቅና የሚገባው ላንተ ብቻ ነው፡፡ ምንም እንኳን ምጽዋቴን ለሴተኛ አዳሪ ሰጥቼ ወደ ቤቴ ብገባም እንደገና ዛሬም እሰጣለሁ፡፡”

በዚያው ምሽት ያ ሰው ገንዘብ ይዞ ከቤቱ ወጣ፡፡ በአንድ ሃብታም ሰው እጅ ላይም አስቀምጦት ተመለሰ፡፡

አሁንም የከተማዋ ሰዎች በመደነቅ እንዲህ ተባባሉ፡-

“ይኽ ሰው ምንድን ነው የሚሰራው! ባለፈው ምሽት ደግሞ ምጽዋቱን ለአንድ ሃብታም ሰጠ!”

ሰውየው እንዲህ አለ፡-

“አላህ ሆይ! አኔ ምጽዋት እንድሰጥ ስላደረግኸኝ አመሰጋኝ ነኝ፡፡ ምንም እንኳን ምጽዋቴን ለሌባ፣ ለሴተኛ አዳሪና ለሃብታም ብሰጥም ቅሉ፡፡”

ይህ ሰው በነበረው ኢኽላስ ምክንያት አንድ ሰው በህልሙ እንዲህ አለው፡-

“ለሌባው በሰጠኸው ምጽዋት ምክንያት ሃፍረት ሊይዘውና ዳግመኛ እንዳይሰርቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ እንዲሁም ሴተኛ አዳሪዋም ብትሆን በምትሰራው ፀያፍ ድርጊቷ ተፀፅታ ወደፈጣሪዋ በመመለስ ንጽህት ሴት ልትሆን ትችላለች፡፡ ሃብታሙ ሰው ደግሞ አላህ ከሰጠው ገንዘብ ለድሆች አውጥቶ መስጠት እንዳለበት ትምህርት ሊወስድ ይችላል፡፡” (ቡኻሪ፡ ኪታቡ ዘካት፡ 14)

ከዚህ ሃዲስ የምንቀስመው ትምህርት በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ኢኽላስና ቁርጠኛ ሃሳብ (ንያ) እስካለ ድረስ ያደረገው መልካም ነገር ሁሉ በመጨረሻ ፍሬ ማፍራቱና ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ የማይቀር መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ከአንድ መልካም ሥራ ይልቅ ጥሩ ንያ ወሳኝ መሆኑን ጭምር ነው፡፡ ሆኖም ግን ምንጊዜም ማስተዋል ያለብን ጉዳይ ምጽዋታችንን ስንሰጥ በግዴለሽነት መሆን እንደሌለበት ነው፡፡ ስለሆነም ምጽዋታችንን ስንሰጥ ለእነዚያ በትክክል ለሚያስፈልጋቸውና ለተቸገሩ ሰዎች መሆኑን በትክክል ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡

የሚከተለው አጋጣሚ ከላይ ለቀረበው ሐዲስ እንደማረጋገጫ መሆኑ ለእኛ ተግሳጽ ይሆናል፡-

በአንድ ወቅት አንድ ቱርካዊ ሸይኽ ወደ አናቶሊያ ግዛት እየተጓዙ ሳለ አንድ ሰው በድንገት መንገዳቸው ላይ ገብቶ መኪናቸውን አስቆማቸው፡፡ ሲጋራ የሚገዛበት ገንዘብ እንዲሰጡትም ጠየቃቸው፡- አብረዋቸው ከሚጓዙት ሰዎች መካከል የተወሰኑት በቃል ባይገልጹትም በልባቸው

እንደሚቃወሟቸው እያወቁ የልግስና ውቂያኖስ የሆኑት ሸይኽ እንዲህ አሉ፡-

“እስከጠየቀን ድረስ እኛ ያለብን መስጠት ነው፡፡”

ይህን ካሉ በኋላ አብረዋቸው ያሉት እየተገረሙ ምንም ሳያቅማሙ አውጥተው ሰጡት፡፡ በዚህ ሁኔታ የተደሰተው ያ ድሃ ሃሳቡን ቀይሮ፡-

“አሁን እንግዲህ ልሂድና በዚህ ገንዘብ ዳቦ ልግዛበት፡፡” በማለት ጉዞውን ቀጠለ፡፡

ይህ አጋጣሚ በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ያለ ደግነት ያነሳሳው መልካም ሥራ መጨረሻ ወደሚያምር ሁኔታ እንደሚቀየር የሚያረጋግጥልን ማሳያ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በኢስላም የመጀመሪያዎቹ ብሩክ ዓመታት በብዙ የመዲና ድሃ ሰዎች በር ላይ ለቀለብ የሚሆኑ የተለያዩ እህሎችን የያዙ ጆንያዎች ይገኙ ነበር፡፡ ይህም ለብዙ ጊዜ የቀጠለ ሲሆን አንድ እለት ማለዳ ላይ ግን ድሆቹ ሰዎች በራቸውን ሲከፍቱ የሚፈልጉት ነገር አልተቀመጠላቸውም ነበር፡፡ የዚህ ሁኔታ መከሰት ግራ ያጋባቸው ሰዎች ምክንያቱን ሲያጠያይቁ የዓሊ (ረ.ዐ.) የልጅ ልጅ የነበሩትን ዘይነል አቢዲንን አሳዛኝ ዜና እረፍት ሰሙ፡፡ የመዲና ከተማ በዚህ ዜና ከዳር ዳር የተናጠች ሲሆን ሕዝቦቿም በሃዘን ተመቱ፡፡

ለካ ያንን ሁሉ ድሃ ቀጥ አድርገው በመያዝ ለረዥም ዘመናት ሲቀልቡ የኖሩት እርሳቸው ነበሩ፡፡ አስከሬናቸው ሲታጠብ በዚህ ትሁት የአላህ ባሪያ ጀርባ ላይ እባጭ የሚመስል ያጉበረ ነገር ታየ፡፡ የሚያጥበው ሰው በዚህ በጣም ተደንቆ ምንነቱን ሲያጠያይቅ ከአህለል በይት[1] አባላት አንዱ ምስጢሩን እንዲህ በማለት አጫወተው፡-

“በእያንዳንዱ ሌሊት ዘይነል አቢዲን ለቀለብ የሚውሉ የምግብ እህሎችን የያዙ ጆንያዎችን በትከሻቸው ተሸክመው በመውሰድ በእያንዳንዱ ድሃ ቤት በር ላይ አስቀምጠው ይመለሳሉ፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ማንም ሰው

[1] የነቢዩ ቤተሰቦች ማለት ነው፡፡

አይቷቸው አያውቅም፡፡ ከጀርባቸው ላይ ያለው እባጭ ጀንያ ሲሸከሙበት የኖሩት ቆዳቸው መጅ (ምልክት) አውጥቶ ነው፡፡" (ኢብን ከሲር፡ አል-ቢዳያ፤ አቡ ኑዓይም)

ይህ ነው አንግዲህ ልቡ በኃይማኖቱ ግለት የተቃጠለ አማኝ ሰው የሚያሳየው ቅዱስ የሆነ ተግባር፡፡ ይህ ነው የተስተካከለና ከአላህ ውዴታ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር ያልተከጀለበት የሆነ የኢኽላስ መገለጫ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ትረካ ሱልጣን አልፓርስላን የተባለ የኦቶማን ቱርክ መሪ ያንፀባረቀው የኢኽላስ ሁኔታ ምን ውጤት እንዳስገኘለት የሚያሳይ ማለፊያ ምሳሌ ነው፡፡

በ1071 (እ.ኤ.አ.) ወደ ተካሄደውና በቱርኮችና በሮማውያን መካከል ወደተደረገው የማላዝጊርት ጦርነት ከማምራቱ በፊት ሱልጣን አልፓረስላን ነጭ የሆነ ንጹህ ጨርቅ በእጁ ይዞ እንዲህ አለ፡- "ይህ ከፈኔ ነው፡፡" በሌላ አባባል እየተዘጋጀ ያለው ሹሃዳ (ሰማእት) የመሆን ልባዊ ምኞቱን ለማሳካት ነው፡፡ ወደ ጦርነቱ ከመሄዱ በፊትም ለሰራዊቱ የሚከተለውን አጭር ንግግር አድርጎ ነበር፡-

"ከሁለት መልካም እድሎች አንዱን አላጣም፡፡ ወይ አሸንፍና በድል እመለሳለሁ፡፡ ካልሆነም ደግሞ ሰማእት ሆኜ ጀነት እገባለሁ፡፡ ከእኔ ጋር መሆን የምትፈልጉም ይህንን ሃሳብ በልባችሁ አስቀምጡ፡፡ በዚህ ጦርነት መካፈል የማትፈልጉ ደግሞ መሄድ ትችላላችሁ፡፡ ዛሬ ምንም አይነት ትእዛዝ የሚሰጣችሁ ሱልጣን እዚህ አይገኝም፡፡ እንዲሁም ለመታዘዝ የሚፈልግ ወታደርም መኖር የለበትም፡፡ ዛሬ እኔ ከእናንተ መካከል እንደ አንዱ ነኝ፡፡ ዛሬ እኔ ከእናንተ ጋር የምዘምት ወታደር ነኝ፡፡ ከእኔ ጋር በመሄድ ስትዋጉ የተገደላችሁ ነፍሳችሁን ለአላህ ሰጥታችኋልና ሰማእታት ትሆናላችሁ፡፡

ሆኖም ግን ሞት ሳያገኛችሁ ድል በማድረግ የተመለሳችሁ ጀግኖች ናችሁ፡፡ እኛን ትታችሁ ወደ ቤታችሁ የምትገቡ ግን መመለሳችሁ ውርደትና የጀሃነም እሳት መሆኑን እወቁ፡፡"

ይህን የመሰለ ኢኽላስ የነበረው ሱልጣን አልፐርስላን ከእርሱ አምስት እጅ የሚበልጥ ሰራዊት ይዞ ይጠብቀው የነበረውን ሮማዊ ጀኔራል ድል አደረገው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀውም እውነተኛውን መድህን የሚያገኙት ንያቸውን ከልባቸው አስተካክለው የተነሱና ኢኽላሳቸውን ያሳመሩ ብቻ ናቸው። ይሁን እንጂ ኢኽላስ ያላቸው ሰዎች ምንግዜም ቢሆን ለአደጋ የተጋለጡ ናቸውና፣ ታላቁ የኢስላም አዛዥ ሱልጣን አልፐርስላንም ይህ ዓይነት አደጋ አልቀረለትም ነበር።

በ1072 (እ.ኤ.አ.) የማላዝጊርትን ድል ካጣጣመ በኋላ ፊቱን ያዞረው ወደ ማሻሩኒቨር ዘመቻ ነበር። ከእርሱ ጋር አብረው የተሰለፉ ብዙ ጀግኖች ነበሩ። አንድ ምሽግ ከበበ። ግና ዘመቻውን እዳር ማድረስ ሳይችል በአንድ ሙናፊቅ ሽፍጥ ተጠቃ። በጩቤ ተወጋ። ጉዳዩን የርሱ ወታደሮች ወዲያው ሲገድሉት አልፐርስላን ግን ክፉኛ እንደቆሰለ ለጊዜው ቢተርፍም በ1072 ጥቅምት 25 ቀን በዚሁ አደጋ ሳቢያ ከጌታው ጋር ተገናኘ። ከመሞቱ በፊት የሚከተሉትን ቃላት ተናግሮ ነበር፡-

“ከጠላት ጋር በምጋጠምበት ጊዜ ልቅና ባለው ጌታዬ አላህ የምጠጋ ስሆን እርዳታውን ይሰጠኝ ዘንድም እለምነዋለሁ። ትናንት ግን አንድ ተራራ ስወጣ ከሰራዊቴ ብዛት የተነሣ ተራራው ከሥሬ ያለ እስኪመስለኝ ድረስ ክፉኛ ኩራት ተሰማኝ። በልቤም ውስጥ እንዲህ የሚል ሃሳብ መጣብኝ፡- “እኔ የዚህ ዓለም መሪ ነኝ፣ ከእንግዲህ ማን ነው የሚያሸንፈኝ?” በዚህ ሁኔታዬ ምክንያት ኃያሉ አላህ ከባሪያዎቹ መካከል መጥፎ በሆነው ሰው አማካይነት እነሆ! ቅጣቴን ሰጠኝ። ይህን የመሰለ ሃሣብ በልቤ በማሳደሬ ይምረኝ ዘንድ አላህን እለምነዋለሁ። እንዲሁም ባለፉት ጊዜያት የሰራኋቸውን ስህተቶቼንና ሃጢአቴን ይቅር እንዲለኝ እማፀነዋለሁ። ከአላህ በስተቀር የሚያመልኩት ጌታ የለም። ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው…”

አንድ የአላህ ወዳጅ በሕይወታቸው ሁሉ ሲደንቃቸው የሚኖርና ኢኽላስን የሚመለከት ክስተት ይኖር እንደሆነ ተጠይቀው የሚከተለውን ተናገሩ፡-

“አንድ ጊዜ መካ ውስጥ ገንዘብ የያዘ ቦርሳዬን በመጣሌ ያጣሁ የነጣሁ ድሃ ሆንኩ። ከበስራ የሚላክልኝን ገንዘብ እየተጠባበቅኩ ነበር። ሆኖም ግን በቀላሉ ሊደርሰኝ አልቻለም። ፀጉሬ በጣም ስላደገብኝ ወደ አንድ ፀጉር አስተካካይ ሄድኩና እንዲህ በማለት ጠየቅኩት።

“ምንም ገንዘብ የለኝም። ለአላህ ብለህ ፀጉሬን አታስተካክለኝምን?”

በዚህ ጊዜ ያ ፀጉር አስተካካይ ሌላ ሰው እያስተካከለ ነበር። “እዚያ ላይ ተቀመጥ” አለኝ። የጀመረውን ሰው ትቶ እኔን ማስተካከል ቀጠለ። ሰውዬው ድርጊቱን ተቃወመ። አስተካካዩ ወደ ሰውየው ዘወር ብሎ እንዲህ አለው፡-

“አዝናለሁ ክቡር ሆይ! እርስዎን የማስተካክለው ለገንዘብ ብዬ ቢሆንም ይህ ሰው ደግሞ ለአላህ ብዬ እንዳስተካክለው ጠየቀኝ። ለአላህ ተብለው የሚሰሩ ሥራዎች ሁልጊዜም ቅድሚያ ሊያገኙ የሚገባቸው ሲሆን የሚያስገኙትን ምንዳ ያለ አላህ በቀር ማንም አያውቀውም።”

ይህን ብሎ ካስተካከለኝ በኋላ ጥቂት የወርቅ ሳንቲሞችን በኪሴ እያደረገልኝ እንዲህ አለ፡-

“እነዚህ ሳንቲሞች ለጊዜያዊ ችግሮችህ ይሆኑሃል። አዝናለሁ። ያሉኝ እነዚህ ብቻ ናቸው።”

ጥቂት ቀናት አለፉ። ከበስራ እጠብቀው የነበረው ገንዘብ ደረሰኝ። ለዚያ ፀጉር አስተካካይ አነስተኛ በሆነች ከረጢት የወርቅ ሳቲሞች ይዠለት ብሄድም ሊቀበለኝ ባለመፈለግ እንዲህ አለ፡-

“በፍጹም አልወስድም! ማንም የአላህ ባሪያ ለአላህ ተብሎ የተሰራን መልካም ሥራ ዋጋውን ሊከፍል አይቻለውም። እባክህ ወደ መንገድህ ሂድ! የአላህ ሰላም ካንተ ጋር ይሁን።”

እኔም ከዚያ በኋላ ተለይቼው ሄድኩ። ከሌሊቱ አጋማሽ ላይ እየተነሳሁ ለዚያ ሰው ዱዓ ሳደርግ እነሆ አርባ አመታት አለፉ።”

ኃያሉ አላህ መልካም ሥራዎችን በመልካም ምንዳ ማካካሱና የበጎ ሥራን ዋጋ እጥፍ ድርብ አድርጐ መክፈሉ አይቀርም። እርሱ የሰሪዎችን ሥራ ዋጋ አያጠፋምና።

በጥንቱ የኦቶማን ቱርክ ማኀበረሰብ ውስጥ ሃብታምና ባለፀጋ የሆኑ ሰዎች በረመዳን ወር ቀን ላይ አልባሌ ልብስ ለብሰው በድሆች መኖሪያ አካባቢ ይዘዋወሩ ነበር። በዚያ ሁኔታም ወደ ገበያ፣ ግሮሰሪና ሱቆች በመሄድ የደንበኞቻቸውን የዱቤ ሽያጭ መዝገብ እንዲያሳዩዋቸው ባለሱቆቹን ይጠይቋቸዋል። ከዚያም ከመዝገቡ ላይ አንዳገኙ ከመጀመሪያ፣ ከመሃልና ከመጨረሻው ገጽ ላይ ያለውን የገንዘብ መጠን አስደምረው ሂሳቡን በመክፈል ራሳቸውን ሳያሳውቁ ይሄዳሉ። ባለቤቱን ግን እንዲህ ይሉታል፦

“ይህን እዳ ሰርዘው! አላህ ይህን በጐ ሥራችንን ይቀበለን።”

በዚህ ዓይነት ሁኔታ እዳው የተከፈለለት ሰው ማን እንደከፈለለት ሳያውቅ ባለቤቱም ማን እንደከፈለው ሳያውቅ እዳውን ይሰርዛል። እነዚያ ሰዎች ግዴታ ያልሆኑ ምጽዋቶችን በግልጽ ከመስጠት ይልቅ በድብቅ መስጠቱ የሚመረጥ መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ስለሆነም ይህን በመሰለ ዘዴ የቻሉትን ያክል የሚሰጡትን ምጽዋት ምስጢራዊ ለማድረግ ይጥራሉ። እነዚህ አባቶቻችን የቀኝ እጃቸው የሰጠውን የግራ እጃቸው እስከማያውቅ ድረስ መልካም ሥራቸውን ይህን ያክል ይደብቁ ነበር።

ሰዎች ሁለት ነገሮችን እንዲረሱ የአላህ ምርጥ ባሮች ይመክሩ ነበር።

1. የሰራኸውን መልካም ሥራ አታስታውሰው። እንደዚያ ካደረግህ በሰራኸው ሥራ ከመኮፈስና ልብህን ከማሳበጥ ትድናለህ።

2. ባንተ ላይ የተሰራብህን መጥፎ ነገር እርሳ። እንደዚያ ካደረግህ በልብህ ላይ የጥላቻና የብቀላ ዘር ሥሩን እንዳይሰድና እንዳይበቅል ታደርገዋለህ።

ባጭሩ ኢኽላስ እንደ ፈርጥ የሚቆጠር ሃብት ሲሆን ማግኘቱና ደብቆ ማስቀመጡ ቀላል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ልቦች ከአላህ ጋር በጥሩ ሁኔታ የሚገናኙት በርሱ በኩል ነውና፡፡ ኢኽላስ ክቡር የሆነ ባህሪ ሲሆን የአንድን ባሪያ ደረጃ ከፍ በማድረግ በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም ከአላህ ጋር ያቀራርባል፡፡ ልቅና የተገባው ጌታ ኢኽላስ የሚጐድላቸውን መልካም ምግባራት ፈጽሞ አይቀበልም፡፡ በፍርዱ ቀን ለእርካታ ወይም ለታይታ የተሰሩ መልካም ሥራዎች የልብን በሽታ የሚያጋልጡ ሆነው የሚቀርቡ ሲሆን በሰሪው ፊት ላይ እንዲለጠፉም ይደረጋል፡፡ ኢኽላስ ግን የልእልና ባለቤት በሆነው አላህ ዘንድ ክቡርና የባሮቹን ደረጃ ከፍ ማድረጊያ ሆኖ የሚቀርብ ሲሆን በቅርቢቱም ዓለም ለእድሜ መርዘምና ለሲሳይ መስፋት ሰበብ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# ተቅዋ

ተቅዋ[1] ማለት ከአላህ ጋር የሚያራርቅን ማንኛውም ነገር ከልብ ማራቅ ወይም ከአላህ ሌላ የሆነን ነገር በልብ ውስጥ አለማተለቅ ማለት ነው፡፡ ተቅዋ ማለት አንድ አማኝ አላህን ብቻ ጠባቂው፣ ተንከባካቢው፣ ሲሳይን ሰጪውና ሁሉን ነገር አድራጊው አድርጐ መያዝ ማለት ሲሆን ከእርሱ ጋር ከሚያራርቀው ነገር መቆጠብን ያመለክታል፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አቡ ዘርን (ረ.ዐ.) በገሰጹበት ንግግራቸው ተቅዋ ማለት በአላህ ዓይን ሰዎች የሚመዘኑበትና ደረጃ የሚያገኙበት መስፈርት ነው፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት፡-

"አንተ ከቀዩም ሆነ ከጥቁሩ ሰው የበላይ አለመሆንህን እወቅ፡፡ አንተን ከፍ የሚያደርግህ ነገር ተቅዋህ ብቻ ነው፡፡" (አህመድ)

የተባረኩት ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"እኔ ከሁላችሁም አላህን በመፍራት በላጫችሁ ነኝ፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ተቅዋን በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ሲያስገቡት ይታዩ ነበር፡፡ ለዚህም ነው የእርሳቸውን ሱና መተግበር አላህን ፈሪ (ተቅዋ ያለው ሰው) ለመሆን አስፈላጊ ነው የሚባለው፡፡

ነቢዩ ዒሣ (ዐ.ሰ.) ተቅዋን በሚከተለው አኳኋን ባማረ ሁኔታ ገልፀውታል፡-

---

[1] ተቅዋ የሚለው ቃል የመጣው ወቃ ከሚለው ስርው-ቃል ሲሆን ይህ ማለት መጠበቅ፣ መከላከል ማለት ነው፣፣ እንዲሁም ከማንኛውም ጣኦታዊነት መራቅ፣ ለአላህ ታማኝ መሆንና ቅድስና እንደማለት ነው፡፡

አንድ ሰው ወደርሳቸው መጣና እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“አንተ የደግነትና የጽድቅ መምህር ሆይ! አንድ ሰው በልዑል አምላክ ፊት እርሱን የሚፈራ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?”

ዒሣ (ዐ.ሰ.) እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ፡-

“ይህን ማድረግ ቀላል ነው፡፡ አምላክን ሊወደድ የሚገባውን ያክል በሙሉ ልብህና ነፍስህ ውደደው፡፡ እርሱን ለማስደሰት ከችሎታህ የመጨረሻው ጥግ ድረስ መልካም ሥራን ሥራ፡፡ ለሰዎች ታዛዥና ሩህሩህ ሁን - ለራስህ የምትሆነውን ያክል፡፡”

ከዚያም በመቀጠል እንዲህ አሉ፡-

“ባንተ ላይ ሊደረግብህ የማትፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አታድርግ! ያኔ ለፈጣሪህ ትክክለኛ የሆነ ፍራቻ (ተቅዋ) ያለህ ሰው ትሆናለህ፡፡” (አህመድ፡ አዝ-ዙህድ ገጽ፡59)

አንድ እለት ኡመር (ረ.ዐ.) ኡበይ ኢብን ካእብን (ረ.ዐ.) ተቅዋ ምን እንደሆነ ይነግራቸው ዘንድ ጠየቁት፡-

“ኡመር ሆይ! እሾህ በበዛበት መንገድ ሄደህ አታውቅምን?” በማለት ጥያቄያቸውን በጥያቄ መለሰላቸው፡፡ ኡመርም (ረ.ዐ.) ‹‹አዎን! ሄጃለሁ እንጂ” ባሉ ጊዜ “ታዲያ ምን አደረግክ?” በማለት ኡበይ (ረ.ዐ.) ጠየቃቸው፡፡

“መጐናፀፊያዬን ወደ ላይ ሰበሰብኩ፣ እሾሁ እንዳይጐዳኝም በጥንቃቄና በትኩረት ተጓዝኩ፡፡” አሉ ኡመር (ረ.ዐ.)

በዚህን ጊዜ ኡበይ ኢብን ካዕብ (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡-

“ተቅዋ ማለት ያ ነው፡፡” (ኢብን ከሲር ተፍሲሩል ቁርአን አልአዚም)

የተቅዋ ፍሬ ነገር አንድ ሰው ከእሳት ቃጠሎ ለማምለጥ እንደሚሸሸው ሁሉ ከክህደትና በአላህ ላይ አንዳችን ነገር ከማጋራት መሸሽ ማለት

ነው፡፡ የዚህም ምልክቱ ግዴታ የተደረጉ የአምልኮ ዓይነቶችን በአግባቡ መፈፀምና ከማንኛውም ኃጢአት መታቀብ ነው፡፡

የተባረኩት ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“የትም ብትሆን አላህን ፍራ፡፡ መጥፎ ሥራህን በመልካም ሥራ አስከትል -መጥፎውን ታሰርዝልሃለችና፡፡ ከሰዎች ጋር በመልካም ፀባይ ተኗኗር፡፡” (ቲርሚዚ)

የተቅዋ ከፍተኛው ደረጃ አንድ ባሪያ ልቡን አላህን ከመፍራት ከሚያዘናጉ ነገሮች መጠበቅና ወደእርሱ በሙሉ ትኩረቱ መመለስ ሲሆን የዚህም ባህሪ መጨረሻው አይታወቅም፡፡ ይህ ከፍተኛ የሆነ የተቅዋ ደረጃ በሚከተለው የቁርአን አንቀጽ የታዘዘው ነው፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٢ ﴾ آل

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት፡፡ እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጅ አትሙቱ፡፡” (አሊ-ኢምራን፡102)*

ከተቅዋ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ የፈለገ ሰው በሚችለው አቅሙ ያክል አጠራጣሪ ከሆኑ ነገሮች ራሱን ማራቅ አለበት፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“የአላህ ባሪያ አጠራጣሪ ነገሮችን እስካልተወና እነዚያን ነገሮች ቢሰራ ወደተከለከሉ ነገሮች ያቀርቡኛል ብሎ እስካልፈራ ድረስ እውነተኛ ተቅዋ አይኖረውም ፡፡” (ቲርሚዚ፡ ቂያማህ፣ ኢብን ማጃህ፡ ዙህድ)

አብደላህ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) እንደሚከተለው በማለት ያስጠነቅቁናል፡-

“አንድ ሰው ልቡን የሚያዋልለውን ነገር መሥራት እስካላቆመ ድረስ እውነተኛ ተቅዋ አይኖረውም ፡፡” (ቡኻሪ፡ ኢማን)

እንግዲህ ከተለያዩ ሰነዶች በቀላሉ እንደምንገነዘበው አንድ ባሪያ ተቅዋ እንዲኖረው ከፈለገ ነፍሱን ሁልጊዜም በቋሚነት ሊቆጣጠራት ግድ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ለአላህ ያለውን ፍራቻ ለማጠናከር በመጥፎ

ነገሮች የምታዘውን ነፍሱን ጉትጉታ መቋቋም መቻል አለበት፡፡ እርሷ ለልብ ታላቅ የሆነች ጠላት እንደመሆኗ ከመታለል የመጠበቂያዋ መንገድም ነፍስን ባለቤቷ ቀጥቶና አርርቆ ሲይዛት ብቻ በመሆኑ ነው፡፡

በጣም አዳጋችና ታላቅ ከሆነ ስሜትን የሚማርክ ኃጢአት ለማምለጥ ነቢዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ.) እንዳሳዩት ሁሉ ብቸኛው መንገድ የአላህን ፍራቻ (ተቅዋ) በልብ በማስፈን የእርሱን እገዛ መሻት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው መለኮታዊ እገዛን ለመሻት ተቅዋ ግዴታና ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ኃያሉ አላህ ተቅዋን ያላብሳቸው ዘንድ እንደሚከተለው በማለት ይጠይቁት ነበር፡-

“አላህ ሆይ! ነፍሴን ተቅዋ (አንተን መፍራትን) አላብሳት፡፡ ከመጥፎ ሁኔታም አንጻት፡፡ አንተ ብቻ ነህና ልታነጻት የምትችለው፡፡ የእርሷ ጠባቂና ጌታዋም አንተ ብቻ ነህና፡፡” (ሙስሊም)

“አላህ ሆይ! የቀልብ መመራትን፣ ፍርሃትን፣ ንጽህናንና ፀጋን ትሰጠኝ ዘንድ እጠይቅሃለሁ፡፡” (ሙስሊም)

በአላህ ሚዛን ከሰዎች ሁሉ በላጩ አላህን በመፍራት (ተቅዋ) በላጭ የሆነው ነው፡፡[1] የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ እርሱን የሚፈሩትን ባሮች የሚወዳቸው ሲሆን ሁልጊዜም ከእነርሱ ጋር ነው፡፡[2] ለእነዚህ ባሮቹም ስፋቷ የሰማያትና የምድርን[3] ያክል የሆነችን ጀነት ሊሰጣቸው ቃል ገብቷል፡፡ ኃያሉ አላህ እርሱን ለሚፈሩት ባሮቹ መልካምና እኩይ የሆኑ ነገሮችን የሚለዩበት ችሎታ የሚሰጣቸው ሲሆን ኃጢአታቸውን ይምራቸዋል፡፡[4] በጭንቅ ጊዜም የሚወጡበትን መንገድ ያደርግላቸዋል፡፡ እንዲሁም ከማያስቡት በኩልም ሲሳያቸውን ይሰጣቸዋል፡፡ ነገራቸውን

---

[1] አሊ-ኢምራን ቁ 76 ን ተመልከት
[2] አን-ናሕል ቁ. 128 ን ተመልከት
[3] አሊ-ኢምራን ቁ.133 ን ተመልከት
[4] አል-አንፋል ቁ. 29 ን ተመልከት

ሁሉ ቀላልና ገር በማድረግ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በማበስ ታላቅ ምንዳንም ያጐናጽፋቸዋል፡፡[1]

አቡ ዘር (ረ.ዐ.) ባስተላለፉት መሠረት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"ሰዎች አጥብቀው ቢይዙት በቂያቸው የሆነን አንቀጽ አውቃለሁ፡፡"

ተከታዮቻቸው በዚህ ጊዜ እንዲህ በማለት ጠየቋቸው፡-

"ይህ አንቀጽ ምንድን ነው የአላህ መልእክተኛ?"

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን አንቀጽ ከቁርአን አነበቡ፡-

﴿ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ٢ ﴾ الطلاق: ٢

*"…አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል፡፡" (አጥ-ጦላቅ: 2)*

ተቅዋ ያላቸው ሰዎች ከነቢያት ጋር በመንፈስ የተገናኙ ናቸው፡፡ ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል (ረ.ዐ.) የሚከተለውን ተናግሯል፡-

"የመንን እንዳስተዳድር የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሾመው ሲልኩኝ ከመዲና ዳርቻ ድረስ አብረውኝ በመጓዝ ነበር የተሰናበቱኝ፡፡ እርሳቸው በእግራቸው እየተራመዱ እያሉ እኔ ግን ከግመሌ ላይ ወጥቼ ነበር፡፡ የተወሰነ ምክር ከለገሱኝ በኋላ እንዲህ አሉ፡-

"ሙዓዝ ሆይ! ከዚህ ዓመት በኋላ በአካል ላታገኘኝ ትችላለህ፡፡ ምናልባትም ይህንን መስጊዴን ልትጐበኝ በሚቀጥለው ጊዜ ስትመጣ በእኔ ፈንታ መቃበሬን ይሆናል የምታገኘው፡፡"

"ይህንን እንደሰማሁ ባደረብኝ ከፍተኛ ሃዘን ማልቀስ ጀመርኩ፡፡ ከሚወዱትና እጅግ ከሚሳሱለት፣ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከመሰለ

[1] አጥ-ጦላቅ ቁ.2-5 ን ተመልከት

ሰው መለየት ባመጣብኝ ሃዘን ክፉኛ ተመታሁ፡፡ በዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ሙዓዝ ሆይ! እታልቅስ!” ይህን ካሉ በኋላ ፊታቸውን ወደ መዲና አቅጣጫ አዙረው እንዲህ አሉ፡-

“ለእኔ የሚቀርቡኝ ሰዎች የትም ቦታ ቢሆኑ አላህን የሚፈሩት ናቸው፡፡” (አህመድ፣ ሃይሰሚ፣ መጅሙዓዘዋኢድ)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አንደሚከተለውም ብለዋል፡-

“ያለጥርጥር የእኔ ወዳጆች ተቅዋ ያላቸው ናቸው፡፡” (አቡ-ዳውድ)

ተቅዋ ያደረባት ልብ በመለኮታዊ እይታ ስር ያለች መሆኗን የምታውቅና ይህ መለኮታዊ ጥበብና ምስጢርም የሚገለጽበት ሥፍራ ናት፡፡

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

እንደ አቡ ሃኒፋ፣ ኢማም ሻፊኢ፣ አህመድ ኢብን ሃንበልና ኢማም ማሊክ እውነተኛዎቹ ምሁራንና የአላህ ወዳጆች ያሉ ሕይወታቸውን የመሩት ተቅዋን ተላብሰው ነው፡፡ በአንድ ወቅት ኢማም አቡ ሃኒፋ ከመጐናፀፊያቸው ላይ አነስተኛ ጉድፍን ለማጽዳት ሲሞክሩ እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡-

“ኢማም ሆይ! በሰጡት ፈትዋ[1] ላይ አነስተኛ ጉድፍ (ቆሻሻ) ሶላትን እንደማያበላሽ ተናግረዋል፡፡ አሁን የምናይዎት ደግሞ ቆሻሻዋን ለማስወገድ ሲታገሉ ነው!” አቡ ሐኒፋ እንዲህ አሉ፡-

“ያኛው ፈትዋ ነበር፡፡ ይኸኛው ደግሞ ተቅዋ ነው፡፡”

---

[1] ፈትዋ ማለት በኢስላም ሕግጋትና አፈጻፀም ዙሪያ ለሚነሱ የተለያዩ ጉዳዮች የእውቀት ባለቤቶች ምሁራዊ ጥረት (ኢጅቲሃድ) በማድረግ የሚወስዷቸውን አቋሞችና የሚሰጧቸውን ብይኖች የሚያጠቃልል ቃል ነው፡፡

ከዚህ ሁኔታ  እንደምንገነዘበው ተቅዋ ማለት ታላቅ የሆነ ጥንቁቅነት የሚገለጽበትና በአላህ ፊት የታዘዙትንና የተከለከሉ ነገሮችን በተመለከተ ግለሰቡ የሚወስደውን አቋም ያሳያል፡፡

የሚከተለው ታሪክ አንዲት ሴት ያላትን ተቅዋ የሚያሳይ ሲሆን ስትናገር ንግግሯ ሁሉ ከቁርአን አንቀጽ የፈለቀ ሲሆን ይህንንም የምታደርገው ኃጢአት ላይ እንዳትወድቅ በመፍራት ነው፡፡

አብዱላህ ቢን ሙባረክ ሁኔታውን እንደሚከተለው ይተርኩታል፡-

“በአንድ ወቅት የሃጅን ፀሎት ለማድረስ የተቀደሰው ቤት ወደሚገኝበት መካ ሄድኩ፡፡ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) መቃብርም ዘየርኩ፡፡ ከዚያም በመንገዱ መካከል ላይ አንድ ጥቁር ነገር ተመለከትኩ፡፡ በደንብ ሳስተውልም ከሱፍ በተሰራ ካባ ጀርባዋን የተሸፈነችና ጭንቅላቷንና ፊቷን ደግሞ በዓይነርግብ የሸፈነች ሴት ሆና አገኘኋት፡፡... እንዲህ በማለት ሰላምታ አቀረብኩላት፡-

“አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱህ!”

እርሷም ከሱራ ያሲን ቁጥር 58 ላይ ጠቅሳ እንዲህ በማለት ለሰላምታዬ መልስ ሰጠችኝ፡-

“(ለእነርሱም) አዛኝ ከሆነው ጌታ በቃል ሰላምታ አልላቸው፡፡”

“አላህ መልካም ነገርን ያቅርብልሽ! ለመሆኑ እዚህ ምን እያደረግሽ ነው?” አልኳት፡፡

እርሷም በሱራ አዕራፍ ቁጥር 186 ላይ ያለውን በመጥቀስ መለሰችልኝ፡-

“አላህ የሚያጠመው ሰው ለእርሱ ምንም አቅኚ የለውም...”

መንገድ እንደጠፋባት ከዚህ ንግግሯ ተገነዘብኩ፡፡ ስለዚህ እንዲህ በማለት ጠየቅኳት፡-

“ወዴት ለመሄድ ነው የምትፈልጊው?”

ለጥያቄዬ መልስ ያደረገችው የሱራ አል-ኢስራእን የመጀመሪያ አንቀጽ የተወሰነ ክፍል ነበር፡-

"ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ ያስኬደው ጌታ ጥራት ይገባው…"

ከዚህ ንግግሯም የተገነዘብኩት ሐጅ አድርጋ ወደ እየሩሳሌም ለመመለስ መፈለጓን ነው። እናም ጠየቅኳት፡-

"እዚህ ከመጣሽ ስንት ጊዜ ሆነሽ?"

ለዚህ ጥያቄዬ ከሱራ መርየም አስረኛ አንቀጽ ላይ ያለውን ጠቀሰች፡-

"ሦስት ሌሊትን (ከነቀናቸው) ሰዎችን ለማነጋገር አለመቻልህ ነው አለው።"

"የምትመገቢው ነገር አለሽን?" በማለት ጠየቅኳት።

ለዚህ ጥያቄዬ መልስ ይሆን ዘንድ በሱራ ሹዓራ ቁጥር 79 ላይ ያለውን ጠቀሰች፡-

"ያም እርሱ የሚያበላኝና የሚያጠጣኝ ነው።"

"ለመሆኑ በዚህ ምድረ በዳ ውዱእ የምታደርጊው እንዴት ነው?"

ለዚህ ጥያቄዬ ደግሞ በሱራ ኒሳእ ቁጥር 43 ያለውን መለሰች፡-

"ውሃን ባታገኙ ንጹሕ የሆነን የምድር ገጽ አስቡ። ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በርሱ) አብሱ።…"

"የሚበላ ነገር ቢኖረኝ መመገብ ትፈልጊያለሽ?" ስል ለጠየቅኳት ከሱራ አል-በቀራህ አንቀጽ 187 በመጥቀስ መለሰችልኝ።

"…ከዚያም ፆምን እስከ ሌሊቱ ድረስ ሙሉ…"

"ግንኮ ይህ የረመዳን ወር አይደለም" አልኳት። እርሷም ከሱራ አል-በቀራህ አንቀጽ 158 በመጥቀስ መለሰችልኝ፡-

“መልካምንም ሥራ በፈቃደኝነት የሰራ ሰው (አላህ ይመነዳዋል)፡፡ አላህ አመስጋኝ ዓዋቂ ነውና፡፡”

“በጉዞ ላይ ያለ ሰው ፆሙን ቢፈታ ይፈቀድለታል” አልኳት፡፡ ለዚህ አባባሌ አሁንም በሱራ አል-በቀራህ ቁጥር 184 ላይ ያለውን በመጥቀስ እንዲህ አለች፡-

“ፆማችሁም ለእናንተ የበለጠ ነው፡፡ የምታውቁ ብትሆኑ፡፡”

“እኔ እንደማነጋግርሽ ለምን አንቺም በተመሳሳይ ሁኔታ አታነጋግሪኝም?” በማለት ጠየቅኳት፡፡ እርሷም ከሱራ ቃፍ 187 ላይ ያለውን ጠቅሳ እንዲህ በማለት መለሰችልኝ፡-

“ከቃል ምንም አይናገርም፣ በአጠገቡ ተጠባባቂና ዝግጁ የሆኑ (መላእክት) ያሉበት ቢሆን እንጅ፡፡”

“ከግመሌ ላይ ውጪና የጉዣዎችሽ ቅፍለት ወደሚገኝበት ቦታ ላድርስሽ?” በማለት ሃሳብ አቀረብኩላት፡፡ እርሷም ከሱራ አል-በቀራህ ቁጥር 197 ላይ ያለውን ሐሳብ በከፊል ጠቅሳ እንዲህ በማለት መለሰች፡-

“…ከበጎም ሥራ የምትሰሩትን ሁሉ አላህ ያውቀዋል…”

በዚህ ጊዜ ግመሌን አስተካክዬ እንድትወጣበት አቀረብኩላት፡፡ እርሷም ከሱራ ኑር አንቀጽ 30 ላይ እንዲህ በማለት ጠቀሰች፡፡

“ለምእመናን ንገራቸው ዓይኖቻቸውን (ያልተፈቀደን ከማየት) ይከልከሉ…”

ከግመሏ ላይ በመውጣት ላይ እያለችም ከሱራ አዝ-ዙኽሩፍ 13ኛና 14ኛ ቁጥር ከፊሉን አነበበች፡-

“…ያ ይህንን የማንችለው ስንሆን ለእኛ ያገራልን ጌታ ጥራት ይገባው፡፡ እኛም በእርግጥ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን…”

መጓዝ እንደጀመርንም ከሱራ ሙዘሚል 20ኛውን አንቀጽ የተወሰነ አነበበች፡-

“…ስለዚህ ከቁርአን የቻላችሁትን አንብቡ…”

በሱራ አል በቀራ 269 አንቀጽ ላይ ባለው የቁርአን አገላለጽ ተገፋፍቼ አነበብኩላት፡-

“ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል፡፡ ጥበብንም የሚሰሰጥ ሰው ብዙን መልካም ነገር በእርግጥ ተሰጠ፡፡”

ከዚያም እንዲህ አልኳት፡-

“አንቺ ብዙ መልካም ነገሮችን ተሰጥተሻል፡፡” እርሷ ግን አንቀጹን እንዲህ በማለት ጨረሰችልኝ፡-

“…የአእምሮ ባለቤቶች እንጂ (ሌላው) አይገሰጽም፡፡”

በመጨረሻም የሃገሯ ሰዎች ወደሚገኙበት ቅፍለት ደረስን፡፡ እንዲህ አልኳት “እነሆ ያንቺ ሃገር ሰዎች ቅፍለት፡፡ እዚያ ውስጥ ምን አለሽ?” እርሷም ከሱራ ካህፍ 46ኛውን አንቀጽ አነበበችልኝ፡-

“ገንዘብና ወንዶች ልጆች የቅርቢቱ ሕይወት ጌጦች ናቸው፡፡”

ከዚህ ነግግሯ በዚያ ቅፍለት ውስጥ ወንዶች ልጆች እንዳሏት ተገነዘብኩ፡
፡

እኔም “በቡድኑ ውስጥ ልጆችሽ ያላቸው ሚና ምንድን ነው?” ስል ጠየቅኳት፡-

እርሷም የሱራ አን-ነሕል 16ኛውን አንቀጽ አነበበችልኝ፡፡

“ምልክቶችንም (አደረገ)፡፡ በከዋክብትም እነርሱ ይምመራሉ፡፡”

ከዚህ አነጋገሯ ልጆቿ የቡድኑ መሪዎች እንደሆኑ ለማወቅ አልተቸገርኩም፡፡ ከዚያም ወደ ድንኳኖቹ እያመለከትኳት እንዲህ በማለት ጠየቅኳት፡-

“ልጆችሽ ከዚያ ውስጥ የትኞቹ ናቸው፣ እጠራልሽ ዘንድ?” እርሷም እንዲህ አለች፡-

“አላህም ኢብራሂምን ወዳጅ አድርጎ ያዘው። እንዲሁም አላህ ከሙሳ ጋር በቀጥታ ተነጋገረ። ያህያ ሆይ! መጽሐፉን በብርታት ያዝ አልነው።”

እኔም ወደ ቅፍለቱ ጠጋ ብዬ እንዲህ እያልኩ ጮህኩ፡-

“ኢብራሂም ሆይ! ሙሣ ሆይ! ያህያ ሆይ!” በዚህ ጊዜ ፊቶቻቸው እንደጨረቃ የሚያበሩ ሶስት ወጣቶች ከድንኳናቸው ወጡ። ከአጠገባችን መጥተው ቁጭ እንዳሉ እናታቸው ከሱራ ካህፍ 9ኛውን አንቀጽ እንዲህ በማለት አነበበች፡-

“…ከዚህችም ብራችሁ ጋር አንዳችሁን ወደ ከተማይቱ ላኩ። ከምግቦቿ የትኛዋ ንጹሕ መሆንዋንም ይመልከት። ከርሱም (ከንጹሑ) ምግብን ያምጣላችሁ።….”

ከሶስቱ ወጣቶች አንዱ ወደ ከተማ ሄዶ ምግብ ገዝቶ ካመጣ በኋላ ፊት ለፊታቸው ላይ አደረገ። ሱራ ሃቃህ አንቀጽ 24 ላይ ያለውን እናታቸው አነበበች፡-

“ባለፉት ቀናት ውስጥ (በምድረ ዓለም) ባስቀደማችሁት ምክንያት ብሉ ጠጡም (ይባላሉ)።”

በዚህ ጊዜ እኔ ልጆቹን “የእናታችሁን ሁኔታ እስካልገለጻችሁልኝ ድረስ የእናንተን ምግብ መመገቡ ለእኔ ላይፈቀድልኝ ይችላል።” አልኳቸው።

በዚህ ጊዜ ወጣቶቹ እንዲህ አሉ፡-

“ይህች አሮጊት እናታችን ከአዛኙ አላህ ፊት በንግግሯ ከስህተት ላይ እንዳትወድቅ በመፍራት ከቁርአን ላይ እየጠቀሰች ካልሆነ አትናገርም።”

እኔም በሱራ አልጁምዓ አንቀጽ 4 ያለውን አነበብኩላቸው

“ይህ የአላህ ችሮታ ነው። ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል። አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው።”

አንድ ሰው አጠራጣሪ የሆኑ ነገሮችን ሌላው ቀርቶ የተፈቀዱ ቢሆኑም እንኳን ወዳልተፈቀዱ ሁኔታዎች ያደርሱኛል ብሎ ከፈራ

እንዳይቀርባቸው የተቅዋ ባህሪ ያስገድዳል፡፡ ለዚህ እንደምሳሌ ሆኖ የሚያገለግለን የሚከተለው ታሪክ ነው፡-

“የኦቶማን ቱርክ ሱልጣን አብዱልአዚዝ ኻን የሃገሩን ጦር ሰራዊትና ባህር ኃይሉን በአስደናቂ ሁኔታ ደረጃው የላቀ እንዲሆን በማድረጉ እንዲሁም የሃገር ውስጥ የፖለቲካ ውዝግቦችን ግሩም በሆነ የፖለቲካ ጥበብ በማስከኑና የመንግስቱን ደረጃም በቀድሞ ጊዜ ወደነበረው ክብሩ መመለስ በመቻሉ የመላውን ዓለም ትኩረት ስቦ ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ ሱልጣኑ ፈረንሳይንና እንግሊዝን እንዲጐበኝ ተጋበዙ፡፡

ከኦቶማን ሱልጣኖች ሁሉ እጅግ አጥባቂ ኃይማኖተኛ የነበረው አብዱል አዚዝ ኻን ወደ አውሮፓ ለጉብኝት ሲሄድ ቦሉ ከተባለ አካባቢ የታወቀ የምግብ ዝግጅት ባለሙያ ይዞ ነበር የተጓዘው፡፡ ምክንያቱም የአውሮፓውያንን ምግብ በሸሪዓ መስፈርት አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል ብሎ በመፍራቱ ነበር፡፡

አብዱል አዚዝ ደግና ለኃይማኖቱ በጣም የሚጠነቀቅ ከመሆኑ የተነሣ ሌላው ቀርቶ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይጠጣ የነበረው የዘምዘምን ውሃ ብቻ ሲሆን ከሌላ ቦታ የተገኘን ውሃ አይቀምስም ነበር፡፡ ሶላቱን እጅግ በጥንቃቄና አላህን በመፍራት የሚሰግድና ቁርአንንም በብዛት ያነብ የነበረ ሰው ነው፡፡ በአሳዛኝና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በተገደለ ጊዜ ይቀራው የነበረው ቁርአን ሱራ ዩሱፍ በአነስተኛ ጠረጴዛ ላይ እንደተገለጠ ተቀምጦ ተገኝቷል፡፡ እርሱ በተሰዋ ጊዜ ደሙ ከቁርአኑ ላይ ተረጭቶ ስለነበር ያ ቁርአን እስካሁንም ድረስ በቶፐካፒ ቤተመንግስት በቅርስነት ተቀምጦ ይገኛል፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ..) በሐዲሳቸው እንዲህ ብለዋል፡-

“እንዳኗኗራችሁ ትሞታላችሁ፡፡ እንዳሟሟታችሁም ትቀሰቀሳላችሁ፡፡” (ሙስሊም)

ሌላው ታላቅ የተባለ የተቅዋ ደረጃ የነበረው የኦቶማን ቱርክ መሪ ሱልጣን አብዱል ሃሚድ ሁለተኛ ነው፡፡ ይህ ሰው ለማንኛውም

አስቸኳይ ጉዳይ በማንኛውም የሌሊቱ ክፍለ ጊዜም ቢሆን ከመኝታው እንዲቀሰቅሱት ለአገልጋዮቹ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በላይ ማንኛውንም ሥራ ለነገ ማሳደር አይወድም ነበር፡፡ አሰድ ቤይ የተባለው ፀሐፊው በማስታወሻው ላይ እንዲህ የሚል ነገር ጽፎ ተገኝቷል፡-

አንድ እለት እኩለ ሌሊት ላይ የሱልጣኑን በር አንኳኳሁ፡፡ ያንንም ያደረግሁበት አስቸኳይ ጀሆኑ ዶክሜንቶች ላይ ፊርማውን እንዲያኖርልኝ በማሰብ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በሩን ሳይከፍትልኝ ዘገየ፡፡ ከዚያም የተወሰነ ጊዜ ሳላንኳኳ ከቆየሁ በኋላ ደግሜ አንኳኳሁ፡፡ አሁንም መልስ አልሰጠኝም፡፡ በዚህ ጊዜ ድንጋጤ ያዘኝ፡፡ ድንገት የአላህ ቀጠሮ ደርሶ ሱልጣኑ ሞቶ ይሆን እንዴ? ስልም ራሴን ጠየቅኩ፡፡ ከዚያም ትንሽ ቆየት ብዬ ሳንኳኳ ሱልጣኑ በእጁ ፎጣ እንደያዘ በሩን ከፈተልኝ፡፡ ፊቱን በዚያ ፎጣ እያደራረቀ ነበር፡፡ ፈገግ አለና እንዲህ አለኝ፡-

“ልጄ ሆይ! በዚህ ሰዓት የመጣኸው በጣም ጠቃሚ ለሆነ ጉዳይ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ የነቃሁት መጀመሪያ ስታንኳኳ ነው፡፡ ሆኖም ግን ውዱእ እስካደርግ ድረስ ነበር ሳልከፍትልህ የቆየሁት፡፡ ምክንያቱም ውዱእ ሳላደርግ ሕዝቤን ጀሚመለከት ጉዳይ ላይ ፊርማዬን አስቀምጨ አላውቅም፡፡ አሁን አምጣውና ልፈርምልህ…”

ይህን ካለ በኋላ ‹‹ቢስሚላህ›› ብሎ ከሰነዱ ላይ ፈረመልኝ፡፡

የአብዱልሃሚድ ሁለተኛ ባለቤት በጣም ጠንቃቃ ስለመሆኑ ስትናገር እንዲህ ብላለች፡-

“አብዱልሃሚድ ኻን ሁልጊዜም ከአልጋው እግር ስር አንድ ንጹህ የሆነ የሸክላ ጡብ ያስቀምጣል፡፡ ከአልጋው እንደወረደ በዚያ ሸክላ ተየሙም ካደረገ በኋላ ነው ወደ መታጠቢያ ቤት ገብቶ የተሟላ ውዱእ የሚያደርገው፡፡ ይህንንም ያደርግ የነበረው መታጠቢያ ቤት እስኪደርስ ድረስ መሬቱን ያለ ውዱእ እንዳይረግጥ በማሰብ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ይህን የሚያደርገው ለምን እንደሆነ ስጠይቀው እንዲህ በማለት መለሰልኝ፡-

“የብዙ ሙስሊሞች ኸሊፋ እንደመሆኔ እኔ በሱና ጉዳዮች ላይ ጠንካራ ካልሆንኩ በዚህ ምክንያት የሙሐመድ ኡመት ጉዳት ያገኘዋል ብዬ ስለምፈራ ነው፡፡”

አብዱል ሃሚድ ሁለተኛ ይህን የመሰለ ተቅዋ ስለነበረው በፖለቲካው መስክ ብርቱ እንዲሆን አስችሎታል፡፡ በዓለም ታሪክ ውስጥ ሃገረ ቱርክ እጅግ አደገኛና አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በነበረችበት ጊዜ የወሰዳቸው አርቆ ማስተዋል የተሞላባቸው እርምጃዎቹ ተመዝግበውለታል፡፡

እንግዲህ በአጭሩ ተቅዋ ማለት ከሁሉም መልካም ሥራዎች ሁሉ በቁንጮ ላይ የሚቀመጥና አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆን የሚያገለግል የመንፈሳዊ ሕይወት ውበት ነው፡፡ አንድ ሰው በቀጣዩ ዓለም ለስኬት የሚበቃ ሕይወት ይኖረው ዘንድ በዚህችኛዋ ዓለም የሚያስቀምጠው ካፒታሉ ተቅዋ ነው፡፡ ተቅዋ የሌለው ሕይወት አደጋው የበዛ ነው፡፡ ተቅዋን ተላብሰው ያልኖሩት ሕይወት በመጨረሻው እስትንፋስ ወቅት ለዘላለማዊ ፀፀት የሚያበቃን ፍጻሜ መላበሱ አይቀሬ ነው፡፡ አላህ ከዚህ ይጠብቀን፡፡ በዚህች በቅርቢቱ ዓለም ደራሽ ከሆኑ ስጋዊ ፍላጐቶችና አምሮቶች ራሳችንን ጠብቀን ለዘላለማዊው ሃገር በጥንቃቄ በመኖር መዘጋጀት ታላቁ አላማችን መሆን አለበት፡፡

ጦርነት የተወሰነ ጊዜ አለው፡፡ አንዴ ከፈነዳ በኋላ ይጧጧፍና በመጨረሻ አሸናፊና ተሸናፊው ተለይቶ ይደመደማል፡፡ ከነፍስያ ጋር የሚደረገው ግብግብ ግን ዘልዓለማዊ ነው፡፡ እስከሞት ድረስ ይቀጥላል፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَٱعۡبُدۡ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأۡتِيَكَ ٱلۡيَقِينُ ﴿٩٩﴾ ﴾ الحجر: ٩٩

*“እውነቱም (ሞት) እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ፡፡” (አል-ሒጅር፡ 99)*

# ምዕራፍ አራት
# ተውባና እስቲግፋር

የሰው ልጅ ሲባል በነፍሱ ዝንባሌ ቁጥጥር ስር ሲውልና የእምነትንና የመንፈሳዊነትን ብርሃን እያጣ ሲሄድ ኃጢአት የመፈፀም ጠባይ ይስተዋልበታል፡፡ በኅሊናው በኩልም የሞራል ድጋፉ ሲቀዘቅዝና እየቀነሰ ሲመጣ መንፈሳዊ ጥልቀት እየጠፋ ዝቅጠት እየነገሰ ይሄዳል፡፡ ስለሆነም ሰውዬው ሃቀኛ ለመሆን በሚጓዝበት መንገድ ላይ ብዙ ጋሬጣዎች ይደረደሩበታል፡፡ ኃጢአቶች ልክ እንደ ጣፋጭ ሙዚቃ ለነፍስ የተወደዱ ይሆናሉ፡፡ ነፍስም የሚያስከትሉትን አስከፊ ውጤት ሳታመዛዝን ዝም ብላ ትዘፈቅባቸዋለች፡፡

ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ወደዚህች ዓለም ሲመጣ ምንም ዓይነት እንከን የሌለበትና በሚገባ እንደተወለወለ መስታዎት የዋህና ንጹህ ሆኖ ነው፡፡ ኃይማኖት ለሰው ልጅ የተሰጠው ይህንን ንጽህናውን ጠብቆ እንዲያቆይ ለማድረግ ሲሆን ይህም የፈጣሪው እዝነትና ችሮታ መገለጫ ነው፡፡ በውጤቱም አንድ ባሪያ በተፈጥሮ ያገኘውን ንጹህነት ጠብቆ ለማቆየት ኃይማኖቱንና መንፈሳዊነቱን ከተጠቀመ የግዴለሽነትን መጋረጃ ቀዳዶ በመጣል ያሳለፋቸውን የኃጢአት ጊዜያት ያሳየዋል፡፡ ይህም የኃጢአቱን ታላቅነት አግንኖ በማሳየት ሕሊናው ኃጢአቱን እንዲፀየፍ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም በውስጡ የተቀመጡ የሕሊናው አንቀሳቃሽ ኃይላት በኃጢአት የቆሰሉ በመሆናቸው ውስጡ በፀፀት መታመስና መቃጠል ይጀምራል፡፡ ከዚያም በእንባ የተሞሉ ዓይኖቹን ወደ ፈጣሪው መልሶ ምህረት ለማግኘት እጆቹን ይዘረጋል፡፡ ይህ በፀፀት የታጀበ የሚያቃጥል ስሜት ነው እንግዲህ "ተውባ" ተብሎ የሚጠራው፡፡ ምህረት ለማግኘት የሚደረገው ለቅሶና ከልብ የመነጨ ልመና ደግሞ "ኢስቲግፋር" ይባላል፡፡

ሰውየው ወደ ጀነት እንዳይገባ ሃጢአቶች መሰናክል ይፈጥራሉ፡፡ በተቃራኒው በመልካም ሥራዎች የተጠናከረና የታጀበ ተውባና ንስሃ ከእሳት ለመራቅ ሰበቦች ናቸው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ የአላህ ባሪያ ኃጢአት ሲፈጽም በልቡ ላይ ጥቁር ነጥብ (ኑቅጣ) ይጣልበታል። ኃጢአቱን በመተው ተውበት ካደረገና ወደ አላህ ከተመለሰ ያ ጥቁር ነጥብ ከልቡ ላይ ይፀዳለታል። ያንን ማድረግ ሳይችል ከቀረና በኃጢአቱ ላይ ከዘወተረ ያ ጥቁር ነጥብ እየሰፋ ሄዶ በመጨረሻ ሁሉንም ልቡን ይሸፍነዋል። ይህም አላህ በቁርአን እንደሚከተለው ያወሳውን ሁኔታ ያስከትላል፡-

﴿ كَلَّا بَلْ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُوا يَكْسِبُونَ ﴿١٤﴾ ﴾ المطففين: ١٤

*“ይከልከሉ፡ ይልቁንም በልቦቻቸው ላይ ይሰሩት የነበሩት (ሃጢአት) ደገደገባቸው።” (አል-ሙጠፊፊን፡14)*

(ቲርሚዚ ዘግበውታል)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ እንዲህ የሚል ተጠቅሶ እናገኛለን፡-

“የሰውን ልጅ ሊያስጨንቀው የሚገባው ትልቁ ነገር ኃጢአት ሲሆን መድኃኒቱ ደግሞ በሌሊት ጨለማዎች ውስጥ የሚደረግ ኢስቲግፋር ነው።” (ዳይለሚ)

አንድ ሰው በሰብአዊነቱ ምክንያት ባሉበት ድክመቶች የተነሳ (ይህ በሁሉም የሰው ዘር ዘንድ የተለመደ ነው) ኃጢአት ቢፈጽም ወዲያውኑ ፊቱን ወደ አላህ መልሶ መፀፀትና ይቅርታ መጠየቅ ይኖርበታል። በስህተት ላይ በወደቁ ጊዜ ፈጥነው ወደርሱ የሚመለሱትን ሙተቂን (ፈራህያን) ባሪያዎቹን አላህ እንደሚደሰትባቸው በሚከተለው አኳኋን ገልጿል፡-

﴿ وَالَّذِينَ إِذَا فَعَلُوا فَاحِشَةً أَوْ ظَلَمُوا أَنفُسَهُمْ ذَكَرُوا اللَّهَ فَاسْتَغْفَرُوا لِذُنُوبِهِمْ وَمَن يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا اللَّهُ وَلَمْ يُصِرُّوا عَلَىٰ مَا فَعَلُوا وَهُمْ يَعْلَمُونَ ﴿١٣٥﴾ ﴾ آل عمران: ١٣٥

*“ለእነዚያም መጥፎ ሥራን በሰሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሱና ለኃጢአቶቻቸው ምህረትን የሚለምኑ ለሆኑት*

*ከአላህም ሌላ ሃጢአቶችን የሚምር አንድም የለ (በስሕተት) በሰሩትም ላይ እነርሱ የሚያውቁ ሲሆኑ የማይዘወትሩ ለሆኑት (ተደግሳለች)። (አሊ-ዒምራን:135)*

﴿ كَانُوا۟ قَلِيلًا مِّنَ ٱلَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ ﴿١٧﴾ وَبِٱلْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ ﴿١٨﴾ ﴾ الذاريات: ١٧ - ١٨

*"ከሌሊቱ ጥቂትን ብቻ ይተኙ ነበሩ። በሌሊቱ መጨረሻዎችም እነርሱ ምህረትን ይለምናሉ።"*

ኃያሉ አላህ በብዙ የቁርአን አንቀጾች የሚነግረን ከልባቸው ተፀፅተው ወደርሱ የሚመለሱ ባሮቹን ይቅር እንደሚላቸው ነው። እርግጥ ይሰሯቸው የነበሩ ኃጢአቶችን እርግፍ አድርገው በመተው ከልባቸው ወደእርሱ የሚመለሱትን ባሮቹን ኃጢአቶች ወደ መልካም ሥራ (ሃሰናት) እንደሚቀይርላቸው ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَٰلِحًا فَأُو۟لَٰٓئِكَ يُبَدِّلُ ٱللَّهُ سَيِّـَٔاتِهِمْ حَسَنَٰتٍ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿٧٠﴾ ﴾ الفرقان: ٧٠

*"ተፀፅቶ የተመለሰና ያመነ መልካምንም ሥራ የሰራ ሰው ብቻ ሲቀር እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል። አላህም እጅግ መሃሪ አዛኝ ነው።" (አል-ፉርቃን:70)*

ብሩክ የሆኑት ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ማለታቸውን አቡ ሙሣ አል አሽዓሪ (ረ.ዐ.) አስተላልፈዋል፡-

"ሃያሉ አላህ ቀን ሃጢአትን የሰሩ ባሮቹን ይቅርታ ለመቀበል ሌሊት እጆቹን ይዘረጋል። በሌሊት ሃጢአት የሰሩ ባሮቹን ይቅርታ ለመቀበልም በቀን እጆቹን ይዘረጋል። ይህም ፀሐይ በምእራብ በኩል እስከምትወጣበት ጊዜ (እስከ ትንሳኤ መቃረቢያ ቀን) ድረስ ይቀጥላል።" (ሙስሊም)

ለተውበት ተቀባይነት ዋነኞቹ ቅድመ ሁኔታዎች ከልብ መፀፀትና ሃቀኝነት ናቸው። እነዚያ በየጊዜው ተውበታቸውን እያበላሹ ወደ መጥፎ

ሥራቸው የሚመለሱት በግልጽ እንደሚታወቀው የሰይጣን ምርኮኞች ናቸው። ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقّٞۖ فَلَا تَغُرَّنَّكُمُ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَا وَلَا يَغُرَّنَّكُم بِٱللَّهِ ٱلۡغَرُورُ ٣٣﴾ لقمان: ٣٣

*"...የአላህም ቀጠሮ እውነት ነውና። ቅርቢቱም ሕይወት አትሸንግላችሁ። በአላህም (መታገስ) አታላዩ (ሰይጣን) አያታላችሁ።" (ሉቅማን፡33)*

በሌላ በኩል ደግሞ ተውባና እስቲግፋር አንድ ሰው በዚህችም ሆነ በመጪው ዓለም ለሚደርስበት ቅጣት የማምለጫ ሰበቦች ናቸው። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ ለሕዝቤ ሁለት ዋስትናዎችን እንደሰጣቸው በመግለጽ የሚከተሉትን ሁለት የቁርአን አንቀፆች አውርዶልኛል፡-

1. አንተ በውስጣቸው እያለህ አላህ የሚቀጣቸው አይደለም።
2. አላህም እነርሱ ምህረትን የሚለምኑ ሲሆኑ የሚቀጣቸው አይደለም። (አንፋል፡33)

"እኔ ከሕዝቤ ስለይ ሁለተኛውን የመዳን ዋስትና እተውላቸዋለሁ። እርሱም እስቲግፋር ሲሆን ከአላህ ቅጣት ያድናቸዋል። እስከ ፍርዱ ቀን ድረስም ይጠብቃቸዋል።" (ቲርሚዚ)

ተውባና እስቲግፋር ወደ አላህ መቃረቢያ የሆኑ ሁለት ስኬታማ መንገዶች ናቸው። ምክንያቱም እውነተኛ የሆነው ባህሪያቸው እንደሚያሳየው ሁለቱም የሃቀኛ መፀፀትና የአላህን እርዳታ የመሻት ውጤቶች ናቸውና። እስቲግፋርን ለብቻው ከወሰድነው ወደ አላህ በመመለስ ሂደት ላይ ጉልህና የማይተካ ሚና የሚጫወት ሲሆን ባሪያው ከአላህ ጋር ግንኙነቱ እንዲታወክ የሚያደርጉትን መንፈሳዊ ጉድፎች መጥረጊያ (ማጽጃ) መሣሪያ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ተቀባይነት ያለው

ተውባ በባሪያውና በጌታው መካከል የተደነቀረውን መሰናክል በማስወገድና መንፈሳዊውን ግርዶ በመግፈፍ ግንኙነታቸውን የማስተካከል ሂደት ነው። ይህም ለስኬት በሚበቃ ጊዜ ባሪያው ከአላህ ዘንድ ውዴታን እንዲያተርፍ ምክንያት ይሆንለታል። ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلتَّوَّٰبِينَ وَيُحِبُّ ٱلۡمُتَطَهِّرِينَ ﴿٢٢٢﴾ ﴾ البقرة: ٢٢٢

*“አላህ (ከሃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል። ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው።” (አል-በቀራህ :222)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በንጹህ ተውበት ወደርሱ የሚቃረቡትን ባሪዎቹን ምን ያህል እንደሚደሰትባቸው ለማሳየት የሚከተለውን ሐዲስ ተናገሩ፡-

አነስ ኢብኑ ማሊክ (ረዐ.) እንዳወሩት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በምሳሌ ሲያስረዱ እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ ሰው ስንቅ የተጫነች ግመሉ ጠፋችበት። እስኪደክመው ድረስ ፈለጋት። እንደማያገኛት ተስፋ ቆርጦ ከአንዲት ዛፍ ስር ቆም አለ። በዚያው እንቅልፍ አሻለበው። ሲነቃ ግመሉን ከአጠገቡ አያትና ከደስታ ብዛት የሚሆነውን አጣ። በሐሴት ከመስከሩ የተነሳ፡- ‹‹አላህ ሆይ አንተ ባሪያዬ እኔ ደግሞ ጌታህ ነኝ፡›› በማለት ተሳሳተ። አላህ ባሪያው ሲቶብት ከዚህ ሰው የበለጠ ይደሰታል።” (ሙስሊም፣ ቲርሚዚ)

በሌላ ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የኢስቲግፋርን ጥቅም ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

“ሰውዬው አላህን ምህረት መጠየቅ እስካላቆመ ድረስ የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ ከጭንቅ የሚወጣበትን መንገድ ያሳየዋል፣ ከሃዘኑ ያላቅቀዋል፤ እንዲሁም ከማያስበው በኩል ሲሳዩን ይሰጠዋል።” (አቡ-ዳውድ)

ስለሆነም ለአንድ የአላህ ባሪያ ትልቁና ጠቃሚው ጉዳይ ነፍሱንና ልቡን (ቀልቡን) ማጽዳት ነው፡፡ እንግዲህ ስለተውባና እስቲግፋር ስናነሳ እነዚህን ሁለት ጠቃሚ ነገሮች አንድ ሰው የራሱ ካደረገ ወደ አላህ በሚወስደው ቀና ጐዳና (ሲራጠል ሙስተቂም) እንደ በር አድርጐ ሊቆጥራቸው ይችላል፡፡ ከዚያ በኋላ መልካም ሥራዎችን በጥራትና በብዛት ማስከተሉ የግድ ነው፡፡ አንድ ሰው የግዴታ የአምልኮ ተግባራትን ከፈፀመ በኋላ አስፈላጊና ሱና የሆኑ መልካም ሥራዎችን ያስከትል፡፡ ከዚያ በኋላ የተለያዩና ውብ የሆኑ ምግባራትን ለምሳሌ የሌሎችን ሰዎች መብቶች መጠበቅ፣ የወላጆችን ሃቅ መወጣት፣ የተቸገሩትን ለአላህ ብሎ መርዳት፣ እንዲሁም ሁሉንም ፍጡራን በሃዘኔታ፣ በርህራሄና በይቅር ባይነት መመልከት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ በጎ ምግባራት ናቸው፡፡

# የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"እናንተ ሰዎች ሆይ! ወደ አላህ ተመለሱ፡፡ ምህረቱንም ለምኑት፡፡ እኔ በቀን መቶ ጊዜ ምህረቱን በመለመን እመለሳለሁና፡፡" (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ላለፈውና መጪው ኃጢአታቸው ምህረት ተደርጐላቸው ሳለ ይህን ያክል በየእለቱ ምህረትን የሚጠይቁ ከሆነ ይህ ለእኛ ምን ትምህርት ነው የሚሰጠን? እርግጥ ነው የእርሳቸው ድርጊት አንድም ፈጣሪያቸው ለዋለላቸው ፀጋ አመስጋኝ መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ተከታዮቻቸው በየእለቱ በብዙ ኃጢአቶች ውስጥ ስንነከር ስለምንውል የአላህን ምህረት በብዛት መለመን የሚያስፈልገን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የተባረኩት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አበክረው የሚያሳስቡት የአንድ የአላህ ባሪያ ዋነኛው ተግባሩና በዚህች ዓለም የመገኘቱ ዓይነተኛ ግብ አላህን ማስታወስና በእያንዳንዷ የጊዜ ክፍልፋይ እርሱን መገዛት መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ባገኘው አጋጣሚ ለጥፋቱ ተውባ ማድረግ እንዲሁም እስቲግፋር ማብዛት እንዳለበት ይመክራሉ፡፡ የሰው ልጅ አቅሙና

ሁኔታው በፈቀደለት ያክል የአምልኮ ደረጃውን በየጊዜው እያሻሻለና ወደጌታው እየቀረበ መሄድ እንዳለበትም ያስገነዝባሉ፡፡

ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን ዱዓ በተቀመጡበት ለ100 ጊዜያት ያክል ሲደጋግሙት እንሰማ ነበር፡፡"

**اللهم اغفر لى وتب على إنك أنت التواب الرحيم**

"አላህ ሆይ! ማረኝ ተውበቴንም ተቀበለኝ፡፡ አንተ መሃሪና እጅግ አዛኝ ነህና፡፡" (አቡ ዳውድ፣ ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በየጊዜው የሚያደርጉት ተውባና አስቲግፋር ኃጢአት ስለሚፈጽሙ ወይም ስህተትን ስለሚሰሩ አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ የልቅና ባለቤት ከሆነው አላህ ጋር ይበልጥ ለመቀራረብና የእርሱን ውዴታ ለማግኘት ነው፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በየጊዜው በመንፈሳዊ እድገት ላይ ስለነበሩና ያለፉትን ደረጃዎቻቸውን ማለትም አዲስ መንፈሳዊ እድገት ከመገኘቱ በፊት የነበሩበትን ሁኔታ እንደሃጢአት ይቆጥሩት ስለነበር ነው፡፡ (አላህ የበለጠ ያውቃል)፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በመጨረሻዎቹ የመሞቻ ቀናቶቻቸው በተደጋጋሚ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

**سبحانك اللهم وبحمدك أستغفرك وأتوب إليك**

"አላህ ሆይ! ጥራት ይገባህ፡፡ ምስጋናም ይድረስህ፡፡ አላህ ሆይ! ማረኝ"

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባለቤት የነበረችው ዓኢሻ (ረ.ዐ.) አንድ ጊዜ እንዲህ በማለት ጠየቀቻቸው፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እነዚህን ቃላት በተደጋጋሚ ሲሉ ሰማሁዎት፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው?"

እርሳቸው እንዲህ በማለት መልስ ሰጧት፡-

“ጌታዬ በሕዝቤ ውስጥ ምልክትን እንደማይ ጌታዬ ነገረኝ፡፡ ይህንን ምልክት ማየት ከጀመርኩኝ በኋላ ይህንን ውዳሴ ማድረግ ጀመርኩኝ፡፡ ያ ያየሁት ምልክት በሱራ አን-ነስር የተጠቀሰው ሲሆን እርሱም የመካ መከፈት ነው፡፡

﴿ إِذَا جَآءَ نَصۡرُ ٱللَّهِ وَٱلۡفَتۡحُ ١ وَرَأَيۡتَ ٱلنَّاسَ يَدۡخُلُونَ فِي دِينِ ٱللَّهِ أَفۡوَاجٗا ٢ فَسَبِّحۡ بِحَمۡدِ رَبِّكَ وَٱسۡتَغۡفِرۡهُۚ إِنَّهُۥ كَانَ تَوَّابَۢا ٣ ﴾ النصر: ١ - ٣

*“የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤ ሰዎችንም ጭፍሮች እየሆኑ በአላህ ኃይማኖት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ጊዜ፤ ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው፡፡ ምኅረትንም ለምነው፡፡ እርሱ ፀፀትን በጣም ተቀባይ ነውና፡፡” (አን-ነስር፡1-3)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለሕዝባቸው የተለያዩ የእስቲግፋር አባባል መንገዶችን አስተምረዋል፡፡ ከእነዚህ መንገዶች መካከል ዋናው ሰይዱል ኢስቲግፋር የሚባለው ሲሆን ከዚህ በታች በቀረበው ሐዲስ ተጠቅሷል፡-

“ለአንድ የአላህ ባሪያ ከፍ ያለው የእስቲግፋር ዓይነት የሚከተለው ነው፡፡

**اللهم أنت ربى لاإله إلا أنت خلقتنى وأنا عبدك وأنا على عهدك ووعدك ماستطعت أعوذ بك من شر ما صنعت أبوء لك بنعمتك على وأبوء بذنبى فاغفرلى فأنه لايغفر الذنوب إلا أنت**

*‹‹አላህ ሆይ፣ ፈጣሪ አንተ ነህ፡፡ ካንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ፈጥረህኛል፡፡ እኔ ደግሞ ባሪያህ ነኝ፡፡ እኔ የአንተን ቃል ኪዳን ትእዛዝ መሙላት አልቻልኩም፡፡ ከሰራሁት ተንኮል ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡ በዋልክልኝ ጸጋ እውቅናን እሰጣለሁ፡፡ ወንጀሌንም ወዳንተ እናዘዛለሁ፡፡ ማረኝ፡፡ ያላንተ በቀር ሐጢአትን የሚምር የለም፡፡››*

ተውባንና ኢስቲግፋርን ሁልጊዜም ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ከዚያ በኋላ መልካም ሥራን በማስከተል ማጠንከር ተገቢ ነው፡፡ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ ሰው ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-‘እኔ ታላቅ የሆነ ኃጢአት ፈጽሜያለሁ፡፡ ተውበት የማድረግ እድል ይኖረኛልን?’

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ጠየቁት፡- ‘እናትህ በሕይወት ይገኛሉን?’

‘አትገኝም’ አለ ሰውዬው፡፡

‘አክስትስ የለህችህምን?’ በማለት ጠየቁት፡፡

ሰውዩውም ‘አለችኝ’ አለ፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን የሰውዩውን መልስ እንደሰሙ እንዲህ አሉ፡-

“እንደዚያ ከሆነ እርሷን ተንከባከባት፡፡ የእናትህ እህት ልክ እንደ እናት ማለት ናትና፡፡” (ቲርሚዚ፣ አህመድ)

እዚህ ላይ የምናስተውለው ቁም ነገር ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ታላቅ ኃጢአት ፈጽሞ በፀፀት እየተቃጠለና እስቲግፋር እያደረገ ያለውን ባልደረባቸውን ይህን ተውበቱን የሚያጠናክርለትን መልካም ሥራ እንዲሰራ የመከሩት መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም መልካም ሥራ መጥፎ ሥራን ታብሳለችና፡፡

አንድ ሌሊት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ቢላልን (ረ.ዐ.) በሕልማቸው አዩት፡፡ በቀጣዩ ጠርተው እንዲህ አሉት፡-

“ቢላል ሆይ! ባለፈው ሌሊት በጀነት ውስጥ የእግርህ ዱካዎች ከፊትለፊቴ አየሁ፡፡ ምን ዓይነት መልካም ሥራ እንደምትሰራ ንገረኝ፡፡”

ቢላል (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አንዳች አነስተኛ ሃጢአት በፈፀምኩ ቁጥር ወዲያውኑ ሁለት ረከዓ ሶላት እሰግዳለሁ፡፡ እንዲሁም ውዱ በፈታሁ ጊዜ ወዲያውኑ ውዱእ አደርጋለሁ፡፡”

በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ይህ ነው ምክንያቱ፡፡”

ስለሆነም ማንኛውንም መጥፎ የሚባል ነገር ስንፈጽም ወዲያው ጊዜ ሳናጠፋ ተውበት ማድረግ ያለብን ሲሆን መልካም ሥራም ልናስከትልበት ይገባናል፡፡

ካዕብ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ.) ባሳየው ቸልተኝነት በተቡክ ዘመቻ ለመሳተፍ ከተጓዘው ሰራዊት ጋር አብሮ መጓዝ አልቻለም ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ወዲያው ነበር በፀፀት መቃጠልና ተውባ ማድረግ የጀመረው፡፡ በፈጸመው ከባድ ጥፋት የተነሣ የአላህን ቅጣት በመፍራት እስቲግፋር እያደረገ ቢቆይም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከዘመቻ ከተመለሱ በኋላም ቢሆን አጠቃላይ የንግግርና የሰላምታ ማእቀብ ተጥሎበት ስለነበር ምድር ከሥፋቷ ጋር ጠባብ ሆናበት ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ሃምሳ ለሚሆኑ ቀናት ያክል ከቆየ በኋላ አላህ ተውበቱን እንደተቀበለውና ከእርሱ ጋር ሁለት ሰዎች አብረው በቁርአን መጠቀሳቸውን ሲሰማ በደስታ ሱጁድ አድርጓል፡፡ (ኢብን ማጀህ)

ከዚያ በኋላ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጥቶ ሁሉንም ሃብቱን በሰደቃ መልክ ለማከፋፈል እንደሚፈልግና ይህንንም የሚያደርገው አላህ ለዋለለት ፀጋ ምስጋና (ሹክር) ለማድረግ መሆኑን ገለጸ፡፡ ይሁን እንጂ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ግማሹን ሃብቱን ለቤተሰቡ እንዲያስቀርና ግማሹን እንዲመፀውት መከሩት፡፡ (ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)፣ ለድሆች እንዲያከፋፍሉላቸው ሰዎች ምጽዋት ሲሰጧቸው የቀልባቸውን (ልባቸውን) ሁኔታ አይተው ነበር የሚቀበሏቸው፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ያላቸውን ሁሉ ከመፀወቱ በኋላ ችግር በሚያጋጥማቸው ጊዜ በመፀፀት ሥራቸውን እንደሚያበላሹ ስለሚያውቁ ነበር፡፡

ኃያሉ አላህ ለእነዚያ በተውባና በእስቲግፋር ወደርሱ ለሚጠጉ ባሮቹ ከማንኛውም አይነት ጭንቀት በማላቀቅ ብዙ ፀጋዎችን ያላብሳቸዋል፡፡ በአንድ ወቅት አራት የሚሆኑ ሰዎች ቅሬታዎቻቸውን ይዘው ወደ ሃሰን አል-በስሪ መጡ፡፡ አንዱ ድርቅ፣ ሌላው ድህነት፣ ሌላው የመሬት ምርታማ አለመሆን፣ የመጨረሻው ደግሞ ልጅ ማጣቱን እየገለጹ

የእርሳቸውን እርዳታ እንደሚሹ ነገሯቸው፡፡ ያ ታላቅ የሆኑ የአላህ አገልጋይ እነዚያ ሰዎች እያንዳንዳቸው እስቲግፋር እንዲሉ ምክር በመስጠት ሸኟቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አብረዋቸው የነበሩ ሰዎች እንዲህ አሉ፡-

“የእነዚህ ሰዎች ችግሮችና ጭንቀታቸው የተለያየ ሆኖ ሳለ እርስዎ ግን ለሁሉም አንድ ዓይነት ምክር ነው የሰጧቸው፡፡” ሃሰን አል-በስሪ ለእነዚህ ሰዎች አስተያየት መልስ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አነበቡላቸው፡-

﴿ فَقُلْتُ ٱسْتَغْفِرُوا۟ رَبَّكُمْ إِنَّهُۥ كَانَ غَفَّارًا ﴿١٠﴾ يُرْسِلِ ٱلسَّمَآءَ عَلَيْكُم مِّدْرَارًا ﴿١١﴾
وَيُمْدِدْكُم بِأَمْوَٰلٍ وَبَنِينَ وَيَجْعَل لَّكُمْ جَنَّٰتٍ وَيَجْعَل لَّكُمْ أَنْهَٰرًا ﴿١٢﴾ ﴾ نوح: ١٠ - ١٢

*“አልኳቸውም፡- ጌታችሁም ምሕረትን ለምኑት እርሱ በጣም መሐሪ ነውና፡፡ በእናንተ ላይ ዝናምን ተከታይ አድርጎ ይልካል፡፡ በገንዘቦችና በልጆችም ይለግሳችኋል፡፡ ለእናንተም አትክልቶችን ያደርግላችኋል፡፡ ለእናንተም ወንዞችን ያደርግላችኋል፡፡” (ኑሕ፡10-12)*

ተውባን በማዘግየትና የሰይጣንን ጉትጎታ በማስተናገድ በወንጀል ላይ መቆየት ሕይወት በመጥፎ ሁኔታ እንድታልፍ ማድረግ መሆኑን ልብ ማለት ያሻል፡፡ ብልህ የሆነ አማኝ ለኃጢአቶቹ ምህረትን በመጠየቅ እስከ መጨረሻው እስትንፋሱ ድረስ ራሱን አዘጋጅቶ ይጠባበቃል፡፡

በአንዳንድ ዘገባዎች ተጠቅሶ እንደሚገኘው አንድ ልብስ ሰፊ አንድን ሷሊህ ሰው እንዲህ በማለት ይጠይቃቸዋል፡-

“የክብርና የልእልና ባለቤት የሆነው አላህ የባሪያውን ተውበት ነፍሱ ልትወጣ ከጉሮሮው እስካልደረሰች ድረስ ይቀበለዋል፣ በሚለው ሐዲስ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?

ሷሊሁ ሰው ልብስ ሰፊውን እንዲህ በማለት ጠየቁት

“ይህ እውነት ነው፡፡ ሆኖም ግን አንተ ስራህ ምን እንደሆነ ንገረኝ?”

“እኔማ ልብስ ሰፊ ነኝ” አለ፡፡

"በልብስ መስፋት ሂደት ውስጥ ቀላሉ ሥራ ምንድን ነው?"

"መቀሴን ይዤ ልብስ መቅደድ" አላቸው፡፡

"ለመሆኑ ይህን ሥራ ስትሰራ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ?"

"ለ30 ዓመታት ሰፍቻለሁ"

"ነፍስህ ልትወጣ አንገትህ ላይ ስትደርስ መቀስህን ይዘህ ልብስ መቁረጥ የምትችል ይመስልሃል?"

‹‹አይ እንደዛ ማድረግ አልችልም፡፡"

በዚህ ጊዜ ሷሊሁ ሰው እንዲህ አሉት፡-

"አንተ ልብስ ሰፊ ሆይ፡ ላለፉት 30 ዓመታት ስታከናውነው የኖርከውን ነገር ነፍስህ ልትወጣ ስትል በቀላሉ ልትሰራው ካልቻልክ ከዚህ በፊት አድርገሽው የማታውቀውን ተውባ ነፍስህ ልትወጣ ስትቃረብ ማድርግ ይሳካልኛል ብለህ እንዴት ታስባለህ? አሁን ጥንካሬና ጉብዝና እያለህ ተውበት አድርግ፡፡ ያ ካልሆነ በመጨረሻው ሰዓትህ ምህረትና መልካም ፍጻሜን አታገኝም፡፡ …ለመሆኑ ሞት ከመምጣቱ በፊት ተውባ እንድታደርግ ከዚህ በፊት የነገረህ ሰው የለምን?"

በዚህ ጊዜ ልብስ ሰፊው በፍጥነት ተውበት አድርጐ ከልቡ ወደ ፈጣሪው መመለስ በመቻሉ ራሱም ሷሊህ ለመሆን በቃ፡፡

የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ፡- "ሰዎች እንዳኗኗራቸው ይሞታሉ፡፡ እንዳሟሟታቸውም ይቀሰቀሳሉ፡፡" ብለዋል፡፡ (ሙስሊም)

አንድ ዶክተር መድሃኒት እየቀመመ ሳለ ሱልጣን ባያዚድ ባጠገቡ ሲያልፍ እንዲህ በማለት ጠየቀው፡-

"ዶክተር ሆይ፡ ለእኔ በሽታ የሚሆን መድሃኒት ይኖርሃል?"

"የእርስዎ በሽታ ምንድን ነው?"

"የሃጢአት በሽታ" በማለት መለሰ ባያዚድ፡፡

ዶክተሩ በዚህ ጊዜ እጆቹን ወደ ላይ አድርጎ እንዲህ አለ፡-

“እኔ ኃጢአትን የሚያድን (የሚፈውስ) መድሃኒት አላውቅም፡፡”

በዚያው ቅጽበት ንክ የሚመስል አንድ ወጣት በዚያ ቦታ ላይ ነበርና እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ፡-

“እኔ ለአንተ በሽታ የሚሆን መድሃኒት አውቃለሁ፡፡” ባያዚድም በደስታ

“እባክህ ንገረኝ አንተ ወጣት!” አለው፡፡

ወጣቱ ኃጢአትን ለማከም የሚያስችለውን ዘዴ እንዲህ በማለት አብራራ፡ -

“አሥር የሚሆኑ የተውባ ዛፍ ስሮችን እንዲሁም አሥር የሚሆኑ የእስቲግፋር ቅጠሎችን ያዝ፡፡ ከዚያም በልብህ ወፍጮ ውስጥ አስቀምጣቸው፡፡ ከዚያም በተውሂድ ዘነዘና ውቀጣቸው፡፡ ከዚያም በደግነት ወንፊት ንፋቸው፡፡ በእንባህም ለውሳቸው፡፡ ከዚያም በፍቅርና በፀፀት ምድጃ ላይ አብስላቸው፡፡ ከዚያም ይህን መድሐኒት በየቀኑ አምስት ማንኪያ ውሰድ፡፡ በውስጥህ አንድም በሽታ አይቀርም፡፡”

ባያዚድ ቢስቲማኢ ትረካውን በጉጉት ሲከታተል ከቆየ በኋላ በረዥሙ ተንፍሶ እንዲህ አለ፡-

“እነዚያ ራሳቸውን ጥበበኞችና ጉበዞች አድርገው የሚቆጥሩና አንተን ደግሞ እብድ ነው የሚሉ ወዮላቸው!”

በአጭር አነጋገር የሰው ልጅ ሲባል ስህተት ከመስራት የማይወገድ እንደመሆኑ ከከናፍሮቹ ላይ ተውባና እስቲግፋር ሊለየው አይገባም፡፡ እንዲሁም መልካም ሥራዎችን ለመሥራትም መነየት አለበት፡፡ እስቲግፋር (አላህን ምህረት መጠየቅ) እና መልካም ሥራ የአላህ ባሪያ ሆኖ ለመቀጠል ወሳኝ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ አላህ በቁርአን እንደሚከተለው ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقّٞۖ فَلَا تَغُرَّنَّكُمُ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَاۖ وَلَا يَغُرَّنَّكُم بِٱللَّهِ ٱلۡغَرُورُ ٥ ﴾

*“እናንተ ሰዎች ሆይ! የአላህ ቀጠሮ እውነት ነው። የቅርቢቱም ሕይወት አታታላችሁ። አታላዩም (ሰይጣን) በአላህ መታገሥ አያታላችሁ።” (ፋጢር፡ 5)*

አንድ ሰው ሃጢአት መስራቱን በማቆም ተውበት አድርጎ የሚመለስበትን ጊዜ በነፍሱ ዝንባሌና በሰይጣን ጉትጎታ ተዘናግቶ ወደ እድሜ ዘመኑ መገባደጃ ማራዘሙ ታላቅ የሆነ መታለል ሲሆን ማሳረጊያውም ኪሳራ ነው።

# ምእራፍ አምስት

## አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) መታዘዝ

የአንድ አማኝ ከአላህ ዘንድ የሚኖረው ደረጃ የእርሱንና የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ትእዛዛት ለመፈፀም ካለው ጽናትና ቁርጠኝነት ጋር የተሳሰረ ነው። የአንድ ሰው እምነት እየጠራ የሚሄደውም የሚያደርገው ጥንቃቄ (ተቅዋ)፣ መንፈሳዊ ግለት፣ ለኃይማኖቱ ያለው ፍቅርና ቀናኢነት እየጨመረ የሚሄድ ከሆነ ነው። አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) በመውደድና ለእነርሱ ትእዛዛት እጅ በመስጠት ሂደት ላይ ከፍ ከፍ እያሉ የሚሄዱ ሰዎች በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም ለታላቅ እጣ የታጬ ናቸው። በቁርአን እንዲህ የሚል ተጽፎ እናገኛለን፡-

﴿ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ فَأُوْلَٰٓئِكَ مَعَ ٱلَّذِينَ أَنْعَمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِم مِّنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلصِّدِّيقِينَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَٱلصَّٰلِحِينَۚ وَحَسُنَ أُوْلَٰٓئِكَ رَفِيقًا ٦٩ ﴾ النساء: ٦٩

*"አላህንና መልእክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚህ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሰላቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማእታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይሆናሉ። የእነዚያም ጓደኝነት አማረ!" (አን-ኒሳእ:69)*

የአላህ መልእተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይሉናል፡-

"የክብርና ልእልና ባለቤት የሆነው ጌታችሁ እንዲህ ይላል፡- "ባሮቼ እኔ እንደምፈልገው ከታዘዙኝ በሌሊት ዝናምን እያዘነምኩ በቀን ደግሞ ፀሐይ በእነርሱ ላይ እንድትወጣ አደርጋለሁ። ሌላው ቀርቶ የነጐድጓድን ድምጽ እንኳን እንዲሰሙ አላደርግም።" (አህመድና ሐኪም)

አላህን በሙሉ ልባቸው በማፍቀር ትእዛዙን የሚፈጽሙና በተሰጡት ነገር የሚረኩ ሰዎች ልቦናዎች ጥበብ፣ መልካምነትና ብልጽግና የሚበሩባቸው መቅረዞች ናቸው። ከዚህ በተቃራኒ ካልተፈቀዱና አጠራጣሪ ከሆኑ ነገሮች የማይርቁ ልቦችና አካሎች የሰይጣን መከተሚያዎችና የሞራል አልባነት ጉጆዎች ናቸው።

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

በበድር ዘመቻ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከሃዲያንን ከመግጠማቸው በፊት የባልደረቦቻቸውን አቋም ለማወቅ ፈለጉ። ሚቅዳድ ቢን አስወድ (ረ.ዐ.) ተነሳና የሚከተለውን ተናገረ፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እንዲፈጽሙ የታዘዙትን ነገር ሁሉ ያድርጉ። እኛ ከእርስዎ ጋር ነን። በአላህ እምላለሁ! የእስራኤል ልጆች ለነቢያቸው ለሙሣ (ዐ.ሰ.) የተናገሩትን አምሳያ አንናገርም። እንዲህ ነበር ያሉት፡-

﴿ فَٱذۡهَبۡ أَنتَ وَرَبُّكَ فَقَٰتِلَآ إِنَّا هَٰهُنَا قَٰعِدُونَ ﴿٢٤﴾ ﴾ المائدة: ٢٤

*"...ስለዚህ ሂድ አንተና ጌታህ ተጋደሉም። እኛ እዚህ ተቀማጮች ነን። ...." (አልማኢዳህ:24)*

"እርስዎን እውነተኛ ነቢይ አድርጐ በላከዎት አላህ እምላለሁ! በርከልጊማድ[1] ድረስ እንድንሄድ ቢፈልጉ ከእርስዎ ጋር እስከሆንን ድረስ ከዚህም በላይ አስቸጋሪ ነገር መጋፈጥ እንችላለን። እኛ ሁልጊዜም ጠላትን እስከመጨረሻው ከቀኝዎ፣ ከግራዎ፣ ከፊት ለፊትና ከኋላዎ ለመግጠም ዝግጁዎች ነን።"[2] (ቡኻሪ)

ሚቅዳድ (ረ.ዐ.) ከተናገረ በኋላ ሰዕድ ቢን ሙዓዝ (ረ.ዐ.) ተነስቶ እንዲህ አለ፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛ በእርስዎ ነቢይነት እናምናለን፤ እናረጋግጣለንም። ለእርስዎ የወረደው ቁርአንንና ሱናዎ ሃቅ መሆኑን እንመሰክራለን። በእርግጠኝነት ቃል የምንገባልዎ እያንዳንዷን የእርስዎን ቃል በማዳመጥ የምንታዘዝዎ መሆኑን ነው። የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እርስዎ የፈለጉትን ያድርጉ! የሃቅ ነቢይ አድርጐ በላከዎት አላህ

---

[1] በርከል ጊማድ ከመከተል ሙከረማ የአምስት ቀን መንገድ ወደ ቀይ ባህር በኩል ይርቃል። የመን ውስጥ የሚገኝ አንድ ከተማ ነውም ተብሏል።
[2] ኢብን መስዑድ እንዲህ ብለዋል፡- "ሚቅዳድ ያንን ንግግር ሲያደርግ እዚያው የነበርኩ ሲሆን የእርሱን የሚመስሉ ጠቃሚ ንግግሮችን ያዳመጥኩ ቢሆንም እንደርሱ ንግግር ግን ያስደሰተኝ አልነበረም።" (ቡኻሪ)

እምላለሁ ባህር ቢያሳዩንና እንድንገባበት ቢያዝዙን ከእርስዎ ጋር ከመግባት ከእኛ ማንም ወደኋላ የሚቀር የለም፡፡ በነገው እለት እኛን ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ቢያጋጥሙን ምንም ዓይነት የመከፋት ስሜት አያድርብንም፡፡ በጦርነት ላይ ትእግስት ማድረግና ጽናት እንዲሁም በፍልሚያ ታማኝ መሆን መለያ ባሕሪያችን ነው፡፡ አላህ ከእኛ ውስጥ ለአይንዎ ደስ የሚያሰኝዎትንና የሚረጉበት ነገር ያሳይዎት ይሆናል፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ወደ አላህ ችሮታ ይዘውን ይሂዱ፡፡"

ይህንን የታማኝነትና የማያለወላውል አቋም ከሰሙ በኋላ የአላህ መልክተኛ በተባረከው ፊታቸው ላይ የፈገግታ ፀዳል እየታየ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ፡-

"እንደዚያ ከሆነ ኑ ከእኔ ጋር ወደ አላህ ቸርነት እንጓዝ፡፡ ይህም ለእናንተ የምስራች ነው፡፡ ከሁለቱ ነገሮች አንዱን ትሩፋት እንደሚሰጠኝ ቃል ገብቶልኛል፡፡[1] በአላህ ይሁንብኝ! ቁረይሾች በዚህ ጦርነት እንደሚሸነፉና በውጊያው ግንባር ሰዎቹ ተገድለው የሚወድቁባቸውን ቦታዎች እያየሁ ነው፡፡" አሉ፡፡ (ሙስሊም)

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ለአላህና ለመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) የነበራቸውን ፍቅርና ታዛዥነት እንዴት ባማሩ ቃላት ነበር የሚያቀርቧቸው?

አነስ (ረ.ዐ.) ያስተላለፉት የሚከተለው ሐዲስ የተባረኩ የሆኑትን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ተከታዮች ኢኽላስ፣ ሐቀኝነት፣ ታዛዥነት፣ ትእዛዝን በንቃት የመቀበልና የመፈፀም ብቃት በጉልህ ያሳያል፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

"በአቡ ጦልሃ[2] ቤት ውስጥ መጠጥ አሳላፊ ነበርኩ፡፡ በመሆኑም የእንግዶችን ዋንጫ በወይን በመሙላት አገለግል ነበር፡፡ በዚያው ወቅት

---

[1] ቅፍለቱን ወይም ጦርነቱን ማሸነፍን

[2] አቡ ጦልሃ (ረ.ዐ.) የአነስን እናት ኡሙ ሱለይምን (ረ.ዐ.) በማግባታቸው የአነስ እንጀራ አባት መሆናቸውን ያጤኗል፡፡

በድንገት አስካሪ መጠጥን (ኸምር) መጠጣት ተከለከለ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለመዲና ነዋሪዎች ይህንኑ እየተዘዋወረ የሚያውጅ ሰው መድበው እየጮኸ ይለፍፍ ጀመር፡፡ እኛም እቤት ውስጥ እንዳለን ይህን ዜና ሰማን፡፡ አቡ ጦልሃ በዚህ ጊዜ እንዲህ አሉኝ፡-

"ወደውጭ ውጣና ይህ እየጮኸ የሚለፍፈው ሰው ስለምን እንደሚናገር አጣራ፡፡" እኔም ወደውጭ ከወጣሁ በኋላ ተመልሼ በመግባት እንዲህ አልኳቸው፡-

"አዋጅ ነጋሪው ነው የሚጮኸው 'ተጠንቀቁ! ተጠንቀቁ! የአልኮል መጠጥ ሃራም ተደርጓል' እያለ ነው የሚናገረው፡፡" በዚህ ጊዜ አቡ ጦልሃ ወደ እኔ ዞር አሉና "እንደዛ ከሆነ ይህን ውሰድና በውስጡ ያለውን ሁሉ ድፋው፡፡"

ከዚያች ቅጽበት በኋላ የመዲና ከተማ ጐዳናዎች በተደፋ የአስካሪ መጠጥ (ኸምር) ተጥለቀለቁ፡፡ (ቡኻሪ)

እነዚያ ብሩክ የሆኑ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች የአልኮል መጠጥን እንዲያቆሙ መለኮታዊ መመሪያ መውረዱን እንደተገነዘቡ ያለምንም ማቅማማት ነበር እርምጃ የወሰዱት፡፡ የተለያዩ ምክንያቶችን ወይም ሰበቦችን በመደርደር ይቅርታን ለማግኘት ወይም በእጁ ያለችውን እንኳን ልጨርሳት የማለት አዝማሚያ እስከወዲያኛው አላሳዩም፡፡ አዋጁን ሰሙ፡ ፡ በቅጽበት እርምጃ በመውሰድ ከአስካሪ መጠጥ ጋር የሚያገናኛቸውን ሰንሰለት ቆራርጠው ጣሉ፡፡

ከአስለም ጐሣ የሆነ አንድ ወጣት ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና እንዲህ አላቸው፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከሰራዊቱ ጋር አብሬ መዝመት እፈልጋለሁ፡፡ ሆኖም ግን ለዘመቻ የሚሆን ስንቅና ትጥቅ የለኝም፡፡"

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወጣቱን እንዲህ አሉት፡-

“እንዲህ እንዲህ ዓይነት ሰው ወደ ዘመቻ ለመሄድ ሁሉንም ነገር አዘጋጅቶ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በሕመም ምክንያት አልሄደም፡፡”

ወጣቱ ወደዚያ ሰው በቀጥታ ከሄደ በኋላ እንዲህ አለው፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሰላምታ አቅርበውልሃል፡፡ ከዚያም ለዘመቻ ያዘጋጀኸውን ነገር ሁሉ ለእኔ እንድትሰጠኝ አዝዘውሃል፡፡” ይህን እንደሰማ ሰውዬው ወደ ሚስቱ ዞረና እንዲህ አላት፡-

“የምወድሽ ሆይ! ለዘመቻ የተዘጋጀልኝን ማንኛውም ነገር ለዚህ ወጣት ስጭው፡፡ አንድም ነገር ወደኋላ እንዳታስቀሪ፡፡ ይህ የአላህ ሃቅ ነውና፡፡ ምናልባትም በዚህ ሰበብ በረከት እናገኝ ይሆናል፡፡” (ሙስሊም)

ይህ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባ የእርሳቸውን ትእዛዝ በሙሉ ልብና በታላቅ ስሜት በመታዘዝ ባለቤቱ ለእርሱ ያዘጋጀችለትን ስንቅ በሙሉ ምንም ነገር ሳታስቀር እንድትሰጠው አዘዛት፡፡ በዚህ ድርጊቱ ያንፀባቀረው ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ያለውን ፍቅር፣ ሙሉ ታዛዥነትና ታማኝነት ሲሆን መልካም ሥራ የመስራት ተነሳሽነቱንም አሳይቷል፡፡

ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“መካ በተከፈተበት ቀን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ካእባ ካመሩ በኋላ ከጠባቂዎቹ አንዱ የሆነውን ኡስማን ቢን ጦልሃን (ረ.ዐ.) ቁልፉን እንዲያመጣ ጠየቁት፡፡

ኡስማን (ረ.ዐ.) ቁልፉን ወደያዘችው እናቱ በመሄድ እንድትሰጠው ጠየቃት፡፡ ይሁን እንጂ ጣኦት አምላኪ የነበረችው አናቱ ቁልፉን ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነችም፡፡ በዚህ ጊዜ ኡስማን (ረ.ዐ.) እንዲህ አላት፡-

“ወላሂ! ወይ ትሰጭኛለሽ ካልሆነ ደግሞ ይህንን ሰይፌን ከሰገባው እመዝዘዋለሁ፡፡”

ሴትዮዋ ቁልፉን ከእጁ ላይ አስቀመጠችለት፡፡ ወስዶ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አስረከበ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የካዕባን በር ከፍተው ወደ ውስጥ

ገቡ። ኡሳማ፣ ቢላልና ኡስማን (አላህ የሁሉንም ሥራ ይውደድላቸውና) አብረዋቸው ገቡ። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ካዕባ ውስጥ ገብተው ሳይወጡ ለረዥም ጊዜ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ወጡ። የእርሳቸውን መውጣት ተከትለውም ብዙ ሰዎች ወደ ውስጥ ለመግባት ተራኮቱ።"

ወደ ውስጥ ከገቡት ሰዎች መካከል የመጀመሪያው ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) ነበር። ልክ እንደገባም ቢላልን (ረ.ዐ.) ከበሩ አጠገብ ቆሞ አገኘው። ከዚያም "የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የት ጋ ሆነው ሰገዱ?" በማለት ጠየቀው ቢላል የሰገዱበትን ቦታ አመለከተው። አብዱላህ (ረ.ዐ.) በኋላ ሁኔታውን ሲተርክ ስንት ረከዓ እንደሰገዱ መጠየቁን ረሳሁ።" ብሏል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከዚህ ምሳሌ የምንወስደው ግንዛቤ የኡስማንን (ረ.ዐ.) ቆራጥነትና የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መታዘዝ፣ እንዲሁም የኢብን ኡመርን (ረ.ዐ.) የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ፈለግ የመከተል ጥንቃቄ የተሞላበት ጥረት ነው።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"አንዳችሁ የሆነ ሰው ከተቀመጠበት እንዲነሳለት በማድረግ በእርሱ ቦታ አይቀመጥ። ስትቀመጡ ሰፊ ክብ ስሩ። ሰዎችም ከአጠገባችሁ እንዲቀመጡ ቦታ አስፉላቸው። አላህ ያሰፋላችኋልና።››

አብደላህ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) ይህንን ትእዛዝ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አፍ ካዳመጠ በኋላ እድሜልኩን ሲተገብረው ቆይቷል። ወደ አንድ ቦታ ሄዶ የሆነ ሰው ተነስቶ በእርሱ ቦታ እንዲቀመጥ ሲጠይቀው በዚያ ቦታ ላይ ፈጽሞ አይቀመጥም ነበር። (ቡኻሪና ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"አንዳችሁ ወደ ሆነ ቦታ ግብዣ ከተጠራ ግብዣውን ይቀበል።" ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) ይህን እንደሰማ በሰርግ ወይም በሌላ ምክንያት የሚደረግለትን ማንኛውንም ግብዣ ተቀብሎ ፆመኛ ቢሆንም እንኳን ይሄድ ነበር። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ፆሙ የግዴታ ያልሆነ ከሆነ ፆሙን በማቋረጥ በሌላ ጊዜ ያካክስ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ፆሙ የግዴታ ከሆነ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ትእዛዝ ለማክበር ሲል ብቻ በግብዣው ላይ ይገኝ የነበረ ቢሆንም ፆሙን ግን አይገድፍም ነበር፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ እለት ከመስጊዱ በሮች አንዱን ሴቶች ብቻ እንዲገቡበት መድበው ነበር፡፡ ይህን የሰማው ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) እስኪሞት ድረስ በዚያ በር ገብቶ አያውቅም፡፡ (አቡዳውድ)

የኡበይ ኢብን ከዓብ (ረ.ዐ.) ልጅ የሆነው ጡፈይል ታቢዒን እንደሆነ ነው የሚቆጠረው፡፡ እርሱም በሕይወት ይገኙ የነበሩ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች እየፈለገ ከእነርሱ ብዙ እውቀትን መሰብሰብ ችሏል፡፡ አብደላህ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) ጋር ግንኙቱን በማጠናከር አብሮት ገበያ መሄድ ያዘወትር ነበር፡፡

አብደላህ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ፈለገ ሕይወት (ሱና) ለመከተል የሚያደገውን ጥንቃቄ ጡፈይል ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

“ወደ ገበያ በሄድን ቁጥር ኢብን ኡመር ላገኘው ሰው ሁሉ ሰላምታ ያቀርብ ነበር፡፡ አገልግሎት ላይ የዋሉ ሸቀጦችንም ሆነ ሌሎች ጠቃሚ ነገሮችን የሚሸጥ ሰው፣ ድሃም ቢሆን ያልታወቀ ለሁሉም ሰላምታውን ያቀርባል፡፡ አንድ እለት እንደልማዴ ልጠይቀው ወደ ቤቱ ሄድኩ፡፡ እርሱም ወደ ገበያ አብረን እንድንሄድ ሃሳብ አቀረበ፡፡ እኔም “እዚያ ገበያ ምን የምታደርገው ነገር አለ?” በማለት ጠየቅኩት፡፡ ቀጠል አድርጌም፡- አንተ ስለመግዛትና መሸጥ ምንም የምታውቀው ነገር የለህም፡፡ የምትገዛውን ነገር ኖሮህ ዋጋ አትጠይቅም፡፡ እረ እንዲያውም ምንም ነገር አትገዛም፡፡ ሰዎች ተቀምጠው በሚያወሩበት ቦታ ላይ እንኳን ተቀምጠህ አታወራም፡፡ ወደ ገበያ ከምንሄድ ይልቅ እዚሁ ቁጭ ብለን ብናወራ ይሻላል፡፡” አለኩት፡፡

ይህንን ንግግሬን ከሰማ በኋላ አብደላህ (ረ.ዐ.) እንዲህ አለኝ፡-

“የእኔ ወንድም! ወደ ገበያ የምንሄደው ላገኘነው ሰው ሁሉ የአላህን ሰላምታ ለመስጠት ነው። ከዚህ የተለየ ዓላማ የለንም።” (ሙወጣእ፣ ቡኻሪ ፡ አዳቡል ሙፍረድ)

ሁሉም የተባረኩ የሶሃባ ትውልድ አባላት የአላህንና የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ትእዛዝ ለመፈፀም ከፍ ያለ ጥረት ያደርጉ ነበር። የአላህን ሰላም በማስፋፋትና የሰዎችን ፍቅር በመግዛት የሙስሊም ወንድማማችነት የሚጠናከርበትን ጽኑ መሠረት በምእመናን ልብ ውስጥ ያስቀምጡ ነበር። ከዚህ አንጻር የአብደላህ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) ተምሳሌትነት ምንኛ የሰዎችን ቀልብ የሚነካና ያማረ ተግባር ነው!

አንድ እለት የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ወረደ

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَرۡفَعُوٓاْ أَصۡوَٰتَكُمۡ فَوۡقَ صَوۡتِ ٱلنَّبِيِّ ﴾ الحجرات: ٢

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ድምፆቻችሁን ከነቢዩ ድምጽ በላይ ከፍ አታድርጉ…” (አል-ሑጁራት፡2)*

ሳቢት ኢብን ቀይስ (ረ.ዐ.) ይህን እንደሰማ እቤቱ ገብቶ ቁጭ በማለት ማልቀስ ጀመረ።

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሳቢትን ሲያጡት የት እንዳለ ጠየቁ። አንድ ሰው እንዲህ አላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ ያለበትን አውቃለሁ።” ከዚያም በቀጥታ ወደ ቤቱ ሲሄድ ጭንቅላቱን አቀርቅሮ ሲያለቅስ አገኘው። ከዚያም “ምን ችግር ተፈጠረ? ለምንድን ነው የምታለቅሰው?” በማለት ጠየቀው።

“እባክህ ተወኝ! እኔ በጣም ብዙ መጥሮ ነገሮችን ፈጽሜያለሁ። ድምጼን ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ድምጽ በላይ ከፍ ሳደርግ ነበር። ሁሉም መልካም ሥራዬ ዋጋ ቢስ ነው። እኔ ለእሳት የተዘጋጀሁ ነኝ።” በማለት መለሰለት።

ያ ሰው ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ተመልሶ ከኄደ በኋላ ሳቢት (ረ.ዐ.) የተናገረውን ነገር ሁሉ አጫወታቸው። በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"ሂድና እርሱ ለእሳት ሳይሆን ለጀነት እንደሆነ ንገረው።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

ሳቢት (ረ.ዐ.) በተፈጥሮው ድምጹ አስገምጋሚ ስለነበር የአላህን ትእዛዝ እንደጣሰ በመቁጠር ነበር በሃዘን የተቆራመደው። የሁን እንጂ ድምጹ እንደዚያ መሆኑ የተፈጥሮው ክፍል በመሆኑና እርሱም እውነተኛ ልብ (ቀልብ) የነበረው ሰው በመሆኑ የእርሱ ጉዳይ በልዩ ሁኔታ የሚታይ ሆነ። ከዚያ በኋላ ያ ባልደረባው ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሰማውን ታላቅ የምስራች ይዞለት በመሄድ በጀነት አበሰረው።

ይህ ባልደረባው ራሱ በጣም መልካም የሆነና አርአያነት ያለው ተግባር የፈፀመ ሲሆን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አንዳች ነገር ሽተው ወይም ጠይቀው ያንን ነገር ወዲያውኑ እንዲያገኙ ለማድረግ መረባረብ የሁሉም ባልደረቦቻቸው ተግባር ነበር ማለት ይቻላል።

የአብደላ ኢብን ረዋሃ (ረ.ዐ.) ባለቤት እንዲህ ትላለች ፡-

"የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ኹጥባ (ዲስኩር) ሊያደርጉ ሚንበር ላይ ወጥተዋል። በተመሳሳይ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሚንበር ላይ ወጥተው የሚቀመጡበትን የሶላት ጥሪ አብደላህ (ረ.ዐ.) ከሩቅ ቦታ ሲሰማ እየፈጠነ መጣ። ምንም እንኳን መስጊድ ባይደርስም ባለበት ቦታ ቁጭ አለ። ይህ የአብደላህ (ረ.ዐ.) ሁኔታ ሲነገራቸው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉት፡-

"ልቅና የተገባው አላህ እርሱንና መልእክተኛውን የመታዘዝ ጉጉትህን ይጨምርልህ!"

አብደላህ ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

"ኡየይና ቢን ሂስን የወንድሙን ልጅ ሁር ቢን ቀይስን (ረ.ዐ.) ሊጠይቀው መዲና መጣ። ሁር ከኡመር (ረ.ዐ.) የመማከርት ቡድን

አባላት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ቡድን ወይም ኮሚቴ ውስጥ ምሁር እስከሆነ ድረስ ወጣትም ይሁን ሽማግሌ ይካተት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ኡየይና የወንድሙን ልጅ ሁርን እንዲህ አለው፡-

“የወንድሜ ልጅ! እንደማየው በመንግስቱ አስተዳዳሪ ዘንድ ያለህ ተሰሚነት ከፍ ያለ ነው፡፡ ስለዚህ ኸሊፋውን አገኘው ዘንድ የሆነ ነገር አድርግ፡፡”

ሁር (ረ.ዐ.) የኡመርን (ረ.ዐ.) ፈቃድ ከጠየቀለት በኋላ ኡየይና ኡመር ከመማክርቶቻቸው ጋር በተቀመጡበት ቦታ ገባና እንዲህ አለ፡-

“የኸጧብ ልጅ ሆይ! ወላሂ አንተ ለእኛ ብዙ ነገር አትሰጠንም፡፡ በፍትህም እያስተዳደርከን አይደለም፡፡”

ኡመር (ረ.ዐ.) በዚህ ሰው ሸካራ የሆነ ንግግር በጣም ስለተቆጡ ሊቀጡት ፈለጉ፡፡ ይህን ያስተዋለው ሁር ጣልቃ ገብቶ እንዲህ አለ፡-

“የምእመናን አዛዥ ሆይ! አላህ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያላቸውን አስታውስ፡-

‘ገርን ጠባይ ያዝ፡፡ በመልካምም እዘዝ ፣ ባለጌዎቹንም ተዋቸው፡፡’ (አል-አዕራፍ፡199) የእኔ አጐት ከእነዚያ ሰዎች አንዱ ነው፡፡”

ወላሂ! ወዲያው በመቀየር ኡየይናን ላለመቅጣት ወሰኑ፡፡ ኡመር (ረ.ዐ.) እንደሚታወቀው ቁርአንን ሙሉ በሙሉ የሚተገብሩ ሰው ነበሩና፡፡” (ቡኻሪ)

የአላህ ትእዛዝ ምን እንደሆነ ኡመር (ረ.ዐ.) ሲነገራቸው ንዴታቸውን በፍጥነት በማግታት ለቁርአን ሕግ ተንበረከኩ፡፡ ክብራቸው በመደፈሩ ሊወስዱት ያሰቡትን እርምጃ በመተው የቁርአንን ግሳፄ አክብረው ቀጥ አሉ፡፡ ኡመር የአላህንና የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ትእዛዛት በማክበርና በመተግበር ምልዓትን የተላበሱ መሆናቸውን ይህ ድርጊታቸው ያሳያል፡፡

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች አንዱ የሆነው ሂሻም ቢን ሃኪም (ረ.ዐ.) በአንድ ወቅት ፍልስጤም ውስጥ ነበር፡፡ በዚያ ሳለም ሙስሊም ያልሆነ የገበሬዎች ስብስብ ግብር ባለመክፈላቸው ምክንያት ታግተው በአንድ

አካባቢ እንዲቆዩ ከተደረገ በኋላ በላያቸው ላይ የወይራ ፍሬ ከዛፍ ላይ እንዲረግፍባቸውና ፀሐይም እንዲመታቸው በማድረግ ሲቀጡ አስተዋለ፡፡ ከዚያም በቀጥታ ወደ አስተዳዳሪው ዘንድ በመሄድ ይህን ዓይነት ግፍ በሰዎቹ ላይ መፈፀም እንደማይኖርበት ነገረው፡፡ ከዚያም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከራሳቸው የሰማውን የሚከተለውን ሐዲስ ጠቀሰለት፡-

"ሌሎችን ያለአግባብ የሚያሰቃዩ ሰዎችን አላህ የሰቃያቸዋል፡፡" ይህን የሰማው አገረ ገዥ እነዚያን ገበሬዎች በነጻ አሰናበታቸው፡፡ (ሙስሊም፣ አቡ ዳውድና አህመድ)

መለኮታዊ ብርሃን በአድማሱ ሙሉ ባረፈበት ብርቅዬ ዘመን የኖሩ የሶሃባ ትውልድ አባላት አንዳች ግሣፄ በተሰጣቸው ጊዜ ወዲያው ቀና ምላሽ መስጠታቸው እዚህም እዚያም ይታይ የነበረ ሃቅ ነው፡፡

አንድ እለት ምሽት ላይ የዒሻ ሶላትን ለመስገድ ለተሰበሰቡ ባልደረባዎቻቸው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ተናገሩ፡-

"በነገው የሶላት ወቅት ሁላችሁም ተሰባስባችሁ እንድትመጡ፡፡ አንድ ልነግራችሁ የምፈልገው ጉይዳ አለ፡፡" ይህንን ከሰሙትና ከእርሳቸው ተከታዮች አንዱ እንዲህ አለ፡-

"እገሌና እገሌ ሆይ! የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መጀመሪያ ላይ የሚናገሩትን ነገር በደንብ አዳምጡና ያዙ፡፡ እገሌና እገሌ የሚቀጥለውን የንግግራቸውን ክፍል በሚገባ ያዙ፡፡ እገሌና እገሌ ደግሞ ቀጣዩን ንግግራቸውን በአእምሯችሁ መዝግቡ፡፡ ይህን ካደረግን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከሚያደርጉት ንግግር ውስጥ አንዲትም ቃል አታመልጠንም፡፡" (ሃይሰሚ)

ከዚህስ ምንድን ነው ልንማር የምንችለው? የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ተከታዮች የሆኑት እነዚያ ብሩክ ፍጥረታት የእርሳቸውን ከመለኮታዊ የእውቀት አምባ እየተቀዳ የሚመጣ ንግግር አንዷም ቃል እንኳን እንድታመልጣቸው የማይፈልጉ ጉጉዎች መሆናቸውን ነው፡፡ አዎን! የትውልዱ አባላት ሁሉ እውቀትና ተግባር አንድ ላይ የተዋሃደላቸው

የተግባር ሰዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ (አላህ የሁሉንም ሥራ ይውደድላቸው)፡፡

አቡ ደርዳእ እንዲህ አሉ፡-

“በአንድ ወቅት አቡ ሙሣ አል-አሽዓሪ (ረ.ዐ.) በጣም ታመሙና ራሳቸውን ስተው ጭንቅላታቸውን በባለቤታቸው ጭን ላይ አድርገው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ባለቤታቸው መጮህና ማልቀስ ጀመረች፡፡ በዚያ ሁኔታ ላይ የነበሩት አቡ ሙሣ (ረ.ዐ.) ለጊዜው የባለቤታቸውን ድርጊት ማስቆም አልቻሉም ነበር፡፡ ከሕመማቸው እንዳገገሙ ባለቤታቸውን እንዲህ በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጧት፡፡

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ያልተደሰቱበትና ከራሳቸው ያራቁት ማንኛውም ነገር እኔንም ስለማያስደስተኝ ራሴን አርቃለሁ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሙሾ ከሚያወርዱ፣ ፀጉራቸውን ከሚነጩና ልብሳቸውንም ከሚቀድዱ ሴቶች ራሳቸውን አርቀዋል፡፡” (ቡኻሪ፣ ሙስሊም፣ ነሳኢ)

በሞት ጣእር ላይ የሆኑት ታላቁ ሶሃባ አቡ ሙሳ አል-አሽዓሪ (ረ.ዐ.) በዚያ የመጨረሻቸው በሚመስል ሰዓት እንኳን የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ትእዛዝ ለመጠበቅ ያን ያክል ይጥሩ የነበሩ መሆኑ ያስደንቃል፡፡”

የተወሰኑ ሰዎች ሱናን ሲፃረሩ ዶሃያ ቢን ከሊፋ (ረ.ዐ.) ተመልክተው እንዲህ አሉ፡-

“በአላህ ይሁንብኝ! አሁን እስከዛሬ ድረስ ይሆናል ብዬ በአእምሮዬ አስቤው የማላውቀውን ነገር ፊት ለፊት እያየሁት ነው፡፡ የተወሰኑ ሰዎች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እና ከተከታዮቻቸው ሱና አፈንግጠዋል፡፡ አላህ ሆይ! ከእንግዲህ በኋላ መቆየት ስለማልሻ ነፍሴን ውሰዳትና ወዳንተው አስጠጋኝ፡፡” (አቡዳውድ)

አብዱል ኻሊቅ ጉዱቫኒ የተባሉ የአላህ አገልጋይ እውነተኛ ባርነት ምን እንደሆነ የገለጹበት መንገድ ምንኛ ማራኪና ውብ ነው!

አንድ እለት እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡-

“ነፍሳችን የምትጠይቀንን እንፈጽም ወይስ የእርሷን ፍላጐት መቃረን ነው ያለብን?”

ይህን ጊዜ እኒህ የአላህ ባሪያ እንዲህ አሉ፡-

“በአሁኑ ጊዜ እነዚህን ሁለት ነገሮች መለየት በጣም ከባድ ነው፡፡ ነፍስ በአጠቃላይ እነዚህ ፍላጐቶች ከአላህ የመጡ ወይም ከሰይጣን የመነጩ መሆናቸውን በማምታታት ሰዎችን እያጠመመቻቸው ትገኛለች፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ምኑም ባልተጨበጠበት በዚህ ዘመን የታዘዘውን በመፈፀም የተከለከለውን ሁሉ በመታቀብ ቢወሰን በቂው ነው፡፡ ይህ ነው እውነተኛ የአላህ ባሪያነት መገለጫው፡፡

በእውነት መንገድ የሚጓዙ ሁሉ ሁልጊዜም የማይሻር የሆነውን የአላህን ሕግጋት መጠበቅ፣ ኃይማኖታቸውንና የእምነት አጋሮቻቸውን ማገልገል እንዲሁም በኢስላም ወንድሞቻቸው የሆኑ ሰዎችን መምከር ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ነገሮች ዘላለማዊ የመደሰቻ ሃገር በሆነችው ጀነት ለመስፈር ምክንያት የሚሆኑ ሲሆን ይህም የሚረጋገጠው የአላህን ውዴታ ለማግኘት ተብለው ከተሰሩ ብቻ ነው፡፡

አንድ እለት ዳውድ ጣኢ ከተባሉ ሰው ሃለቃ (የኢልም መስጫ ሥፍራ) የሚቀማመጥ አንድ ሰው ማእሩፍ ኪርሂ ለተባለ ሰው እንዲህ አለው፡-

“መልካም ሥራዎችን መሥራት አለማቋረጥህን አረጋግጥ፡፡ ምክንያቱም መልካም ሥራ የአላህን ውዴታ ያስገኝልሃል፡፡” ማእሩፍ እንዲህ በማለት ጠየቀ፡-

“ምን አይነት መልካም ሥራን ነው መሥራት ያለብኝ?” ሰውየው እንዲህ አለ፡-

“ሁልጊዜም ቢሆን ፈጣሪህን ታዘዝ፤ ሙስሊሞችን አገልግል፤ ምክርህንም ለግሳቸው፡፡”

ባጭሩ - መታዘዝ ታላቅ የሆነ የፍቅር ማሳያ ምልክት ነው። እንዲህ የሚል አባባል አለ፡- “ያፈቀረ ታዛዥ ነው።” ስለዚህ ጌታቸውን የሚወዱ አማኞች ሁልጊዜም እርሱን በሚታዘዙበት ሁኔታ ላይ መገኘት አለባቸው። እርሱን በሙሉ ልብና በታዛዥነት በመገዛት የተፈፀመች ኢምነት ነገር የእርሱን ትእዛዝ ባለማክበር ከሚፈፀም ተራራ የሚያክል በጐ ምግባር ትበልጣለች። ምክንያቱም ባርነት የሚጀምረው እርሱን በመታዘዝና ለእርሱ በማደር ነውና። ሰይጣን ከፈጣሪው ጋር የተጣላውና ከባለሟልነት የተባረረው ፈጣሪውን በሚገባ ባለማምለኩ አልነበረም። ከዚያ ይልቅ የአላህን ትእዛዝ ባለማክበሩና በመኩራቱ ነው።

# ምዕራፍ ስድስት

# በአምልኮ ጥንቁቅ መሆን

ይህ አጽናፈ ዓለም የመለኮታዊው ክብር ባለቤት የሆነው ብቸኛ አምላክ የእጅ ሥራና የእርሱም ታላቅነት የተገለፀበት ክንውን ነው፡፡ በዚህ አጽናፈ ዓለም ውስጥ ካሉ ፍጡራን ሁሉ ማእከላዊ ሥፍራ የተሰጠውና ታላቅ ጥበብ የተንፀባረቀበት ፍጡር ደግሞ የሰው ልጅ ነው፡፡ ሰው የተፈጠረው ለታላቅ ዓላማ ሲሆን ይኸውም ፈጣሪውን ማምለክ ነው፡፡

በብዙ የቁርአን አንቀፆች ኃያሉ አላህ የሰው ልጅ ዘላለማዊ የሆነ አካላዊና መንፈሳዊ ፍዳ ሲከፍል እንዳይኖር፣ ሰላማዊ ቀልብ ይዞ ወደርሱ እንዲሄድ ያስገነዝባል፡፡ አምልኮት ማለት አንድ ባሪያ የመጪው ዓለም ወይም የፍርዱ ቀን ከመከሰቱ በፊት ለጌታው ያለውን ታማኝነት የሚያረጋግጥበት የቃል ኪዳኑ ምልክት ነው፡፡ የአምልኮት ጊዜያት የሰው ልጅ ወደፈጣሪው ይበልጥ የሚቀርብባቸው ቅጽበቶችና የጊዜ ክፍልፋዮች ናቸው፡፡ ነገሩን ከሌላ አቅጣጫ ስንመለከተው ደግሞ አላህን በብቸኝነት ማምለክ በዚህ ዓለም ላይ የሰላምና የምቾት ምንጭ ሲሆን የሰውን ልጅ በመጪው ዓለም ይደርስብኛል ብሎ ከሚያስበው የቅጣት ፍርሃትም ነጻ ያደርገዋል፡፡ አምልኮት ለአንድ የአላህ ባሪያ የመረጋጋቱ ምንጭ፣ የልቡ እረፍት፣ የመንፈሱ ስክነት፣ በአጠቃላይ ሰብአዊ ክብሩ ከፍ የሚልበት መለኮታዊ በረከት ነው፡፡

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ መንደርደሪያ ሃሳብ የምንወስደው ቁም ነገር የአምልኮታችንን ጉዳይ እንዲህ በቀላሉ እንዳናየውና ትኩረት ሰጥተን ራሳችንን እንድናስተካክል ሲሆን በመጪው ዓለም የሚኖረን ስኬትና ውድቀትም በአምልኮታችንና ከአላህ ጋር ባለን ቀረቤታ ላይ የተመካ መሆኑን ነው፡፡

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

ሁላችንም ብንሆን በቀጥታ ከፈጣሪያችን ጋር ወደምንገናኝበት የሶላት አምልኮ ከመሄዳችን በፊት የተሟላ ውዱእ ማድረግ ግዴታችን ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ቸል ማለት ወይም እንደነገሩ መያዝ በዋነኛው የአምልኮ ተግባር (በሶላታችን) ላይ አፍራሽ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡

አንድ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሱብህን ሶላት እያሰገዱ ነበር፡፡ የሩምን ምዕራፍ እያነበቡ ሳሉ የተወሰነ ቦታ ላይ ተሳሳቱ፡፡ ሶላቱ እንደተጠናቀቀም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ሰጋጆቹ ፊታቸውን አዙረው እንዲህ አሉ፡-

“አንዳንድ ሰዎች ውዱእ ሳይኖራቸው ወደ መስጊድ ይመጣሉ፡፡ ይህም ሰይጣን በምናነብበው የቁርአን አንቀጽ ላይ ተጽእኖ እንዲያደርግ በር ይከፍታል፡፡ ወደ መስጊድ ስትመጡ የቻላችሁትን ያክል ተጠንቅቃችሁ ውዱእ አድርጉ፡፡”

ስለዚህም አካልን መታጠብና የተሟላ ውዱእ ማድረግ ሶላታችን ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ መውሰድ የሚገባን ወሳኝ እርምጃ ነው ፡፡

በተጨማሪም አንድ ሰው የቻለውን ያክል ውዱእ ያለው ቢሆን ይህ ታላቅ የሆነ ፀጋ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሁሉንም ሥራቸውን ውዱእ ያላቸው ሆነው መፈፀም ይመርጡና ይወዱም ነበር፡፡

አቡ ጁሃይም (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ጊዜ ከጀመል ግምብ በኩል ሲመጡ አንድ ሰው አገኛቸውና ሰላምታ አቀረበላቸው፡፡ እርሳቸው ግን ለሰላምታው አፀፋ አልመለሱለትም ነበር፡፡ ሰውየው ወዲያው ወደ ግምቡ በመሄድ በመዳፎቹ ግድግዳውን ከመታ በኋላ እጆቹንና ፊቱን በማበስ (ተየሙም በማድረግ) ተመልሶ መጣና ሰላምታ አቀረበላቸው፡፡ እርሳቸውም ለሰላምታው አፀፋውን መለሱ፡፡ (ቡኻሪ)

በዚህ ድርጊታቸው የአላህ ነቢይ ያስተላለፉት መልእክት አንድ ሰው ምንጊዜም ቢሆን ውዱእ ያለው ሆኖ መንቀሳቀስ እንዳለበት ነው፡፡ ይህም

አንድ ሰው የሚሰራውን ሥራ (ያ ሥራ የግዴታ ባይሆን እንኳን) ውዱእ ካደረገ በኋላ ቢጀምረው ትሩፋቱ የበለጠ እንደሚሆን ነው።

በአንዳንድ ዘገባዎች መሠረት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ትጥበት በወጀበባቸው ጊዜ በግድግዳ ላይ መዳፎቻቸውን በማኖር ተየሙም ያደርጋሉ። ይህንም ያደርጉ የነበረው ዋናውን ትጥበት ከመፈፀማቸው በፊት ያለ ውዱእ እንዳይሆኑ በመፍራት ነው። (ሃይሰሚ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን በመሰለ ሁኔታ ነበር ሕዝባቸው አካላዊና መንፈሳዊ ንጽናህውን እንዲጠብቅ ያስተምሩት የነበረው።

አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ወደ አንድ የመቃብር ሥፍራ ሄዱ። ከዚያም እንዲህ በማለት ለሙታኑ ዱዓ አደረጉ፡-

"እናንተ በዚህ ቦታ የሰፈራችሁ ምእመናን ሆይ! የአላህ ሰላምታ በእናንተ ላይ ይሁን። በአላህ ፈቃድ እኛም አንድ ቀን እንቀላቀላችኋለን። ወንድሞቼን ለማየት እንዴት ፈልጌያለሁ! እንዴት ነው የናፈቁኝ!"

"እኛ የእርስዎ ወንድሞች አይደለንምን?" በማለት ባልደረቦቻቸው ጠየቋቸው እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡-

"እናንተ ባልደረባዎቼ ናችሁ። ወንድሞቼ እነዚያ ገና ወደዚህች ዓለም ያልመጡት ናቸው።"

ባልደረቦቻቸው አሁንም ጠየቁ፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ገና ወደዚህ ዓለም ያልመጡ የሆኑትን ሰዎች ከሕዝቦችዎ ውስጥ እንዴት ለይተው ያውቋቸዋል?"

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲመልሱ እንዲህ አሉ፡-

"ግምባሩና እግሩ ንጹህ ነጭ የሆነ ፈረስ ያለውን ሰው አስቡ። ይህ ሰው ይህን ፈረሱን ከመንጋ ሙሉ ጥቁር ፈረሶች መካከል ሊለየው አይችልምን?"

“በሚገባ ይለየዋል እንጂ የአላህ መልእክተኛ!” በማለት ተከታዮቻቸው መለሱ፡፡ የአላህ ነቢይና የተባረኩት መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“እነዚያ ወንድሞቼ ፊታቸው፣ እጆቻቸውና እግሮቻቸው በሚያደርጉት ውዱእ ምክንያት እያበሩ ወደእኔ ይመጣሉ፡፡ እኔ ደግሞ በሃውዴ ላይ ሆኜ የሚፈልጉትን ነገር ልሰጣቸው እጠብቃቸዋለሁ፡፡ ሆኖም ግን ተጠንቀቁ! ከመንጋ ውስጥ በጥባጭ የሆነ ግመል እየተደበደበ ራቅ ተደርጐ እንደሚባረረው ሁሉ የተወሰኑ ሰዎች ከሃውዴ ይባረራሉ፡፡ እኔም እንዲህ እያልኩ እጠራቸዋለሁ፡- “ኑ ወደዚህ!” በዚህ ጊዜ እንዲህ እባላለሁ፡-

“ከአንተ በኋላ ብዙ ነገሮችን ቀይረዋል፡፡ (ያንተን ሱና ትተው የጥመትን መንገድ ተከትለዋል)” እኔ (ይህን እንደሰማሁ) እላለሁ፡-

“ከእኔ አርቁልኝ! ከእኔ አርቁልኝ!” (ሙስሊም)

ከዚህ በመጠኑ ዘለግ ያለ ሐዲስ ምን ተማርን? አዎን! እነዚያ ውዱአቸውን አሳምረው የሚያደርጉ የአላህንና መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ውዴታ የሚያገኙ ሲሆን እርሳቸውም “ወንድሞቼ” በሚል የቀረቤታ አጠራር ጠርተዋቸዋል፡፡ በሌላ በኩል በየጊዜው የሚያደርጉት ውዱእ የተነሣ ፊቶቻቸው እጆቻቸውና እግሮቻቸው የሚያበሩ፣ ዳሩ ግን ከእርሳቸው ሱና በማፈንገጥ የተለያዩ የፈጠራ (ቢድአ) ድርጊቶችን ሲሰሩ የኖሩና በፍርዱ ቀን ወደዚያ ሃውድ የሚመጡ ልክ እንደ አመፀኛ ግመል ፊቶቻቸውንና ሌላውን አካላቸውን በመላእክት እየተደበደቡ ከዚያ ቦታ በአሣፋሪ ሁኔታ ይመለሳሉ፡፡

ከእርሳቸው ሃውድ መራቅና መባረር ምንኛ እድለቢስነት ነው! ምንኛ አዋራጅ ሁኔታ ነው! እርሳቸውም “ከእኔ አርቁልኝ” ብለው የመሰከሩበት ሰው ከዚያ በኋላ ምን እጣ ነው የሚገጥመው? አላህ ይህን ከመሰለ ጥፋትና አደጋ ይሰውረን፡፡

አንድ ጊዜ አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ውዱእ ሲያደርጉ እጆቻቸውን እስከ ብብታቸው ድረስ ሲያጥቡ ከታቢዒን አባላት መካከል የነበሩት አቡ

ሃዚም አስተዋሉ። ከዚያም እንዲህ በማለት አቡ ሁረይራን (ረ.ዐ.) ጠየቋቸው፡-

“አቡ ሁረይራ ሆይ! ይህ ምን ዓይነት ውዱእ ነው?” አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መለሱ፡-

“አንተ የበኑ ፈርሩህ ሰው ሆይ! እዚህ መሆንህን አላወቅኩም ነበር። እዚህ መሆንህን ባውቅ ኖሮ በዚህ ሁኔታ ውዱእ አላደርግም ነበር።”

ከዚያም ገለጻቸውን ቀጠሉና እንዲህ አሉ፡-

“ጓደኛዬ የሆኑት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ሰማኋቸው፡- ‘በፍርዱ ቀን የአማኞች ብርሃን በውዱእ ውሃ ያዳርሱት እስከነበረው የሰውነታቸው ክፍል ድረስ ሁሉ ላይ ይሆናል።’” (ሙስሉም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አላህን መገዛት ያፈቅሩ እንደነበር ዓሊ (ረ.ዐ.) በሚከተለው የሚያምር ሁኔታ ገልፀውታል፡-

“በበድር ቀን ከሚቅዳድ በስተቀር አንድም ፈረሰኛ አልቀረም። አስታውሳለሁ በዚያ ሌሊት በአንድ ዛፍ ስር ሆነው እስከንጋቱ ድረስ ሲሰግዱ ከቆዩት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በስተቀር ሁሉም ተኝቷል፡ :”

ይህ ነው እንግዲህ በሰላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ አላህን የመገዛትና ወደርሱ የመቃረብ የማይናወጽ አቋም። ኃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَٱعۡبُدۡ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأۡتِيَكَ ٱلۡيَقِينُ ٩٩ ﴾ الحجر: ٩٩

*“እውነቱም (ሞት) እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ።” (አል-ሒጅር:99)*

﴿ كَلَّا لَا تُطِعۡهُ وَٱسۡجُدۡ وَٱقۡتَرِب ١٩ ﴾ العلق: ١٩

*“...ስገድም (ወደ አላህ) ተቃረብም።” (አል-ዐለቅ:19)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በሶላቱ ላይ በጣም ጠንቃቃ የነበረውን አብደላህ ኢብን ረዋሃን (ረ.ዐ.) ያወደሱት ሲሆን ‘ወንድሜ’ በማለትም አሞካሽተውታል፡-

“የሶላት ወቅት በገባ ቁጥር ወዲያውኑ ተነስቶ የሚሰግደውን ወንድሜን አብደላህ ኢብን ረዋሃን አላህ ይዘንለት፡፡” (ሃይሰሚ)

ጀርህ ቢን አብዱላህ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

“አንድ ምሽት ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ጋር ተቀምጠን ሳለ ሙሉ የሆነችውን ጨረቃ ተመልክተው እንዲህ አሉ፡-

“ይህችን ጨረቃ እርስበርሳችሁ ሳትጋፉና ሳትጉሻሸሙ በቀላሉ እንደምታዩዋት ሁሉ ጌታችሁንም እንዲሁ በግልጽ ታዩታላችሁ፡፡ ፀሐይ ከመግባቷ በፊትና ከመውጣቷም በፊት ያሉትን ሶላቶቻችሁን በጊዜያቸው ለመስገድ ሁልጊዜም ተበራቱ፡፡” ከዚያ በኋላ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አነበቡ፡-

“….ጌታህንም ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ከመግባቷም በፊት የምታመሰግን ሆነህ አጥራው (ስገድ)፡፡ ከሌሊት ሰዓቶችም፣ በቀን ጫፎችም አጥራው፡፡ (በሚሰጥህ ምንዳ) ልትወድ ይከጀላልና፡፡” (ጣሃ፡ 130) (ቡኻሪና ሙስሊም)

ስለዚህም በመጪው ዓለም ፈጣሪያችንን ያለምንም ግርዶሽ በግልጽ ልናየው የምንናፍቅና የምንከጅልም ከሆነ በሶላቶቻችን ላይ መጽናት ይኖርብናል፡፡

ማንኛውንም የምንፈጽመውን የኢባዳ (አምልኮት) ዓይነት ልክ ወደ ጀነት እንደሚያስገባን የይለፍ ወረቀት በመቁጠር በከፍተኛ ጥንቃቄና ሞቅ ባለ መንፈስ ነው መፈፀም የሚኖርብን፡፡

መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“አንድ ሰው ሩኩኡንና ሱጁዱን አሳምሮ ሶላቱን የሚሰግድ ከሆነ ሶላቱ ሰውየውን እንዲህ ይለዋል፡-

“(አስተካክለህ) እንደሰገድከኝ አላህ አንተንም ያሳምርህ! ካለ በኋላ ወደ ሰማይ ይወጣል፡፡

ሰውየው ሶላቱን ሳያስተካክልና ሩኩእና ሱጁዱንም በግብር ይውጣ ከሰገደ ሶላቱ እንዲህ ይለዋል፡-

“እንዳበላሸኸኝ አንተንም አላህ ያበላሽህ፡፡” ከዚያም እንደ አሮጌ ቁራጭ ጨርቅ ወርዶ ከፊቱ ላይ ይለጠፋል፡፡”[1]

በቁርአን እንዲህ የሚል አንቀጽ ተጽፎ እናገኛለን፡-

﴿ فَوَيۡلٞ لِّلۡمُصَلِّينَ ۝٤ ٱلَّذِينَ هُمۡ عَن صَلَاتِهِمۡ سَاهُونَ ۝٥ ﴾ الماعون: ٤ - ٥

*“ወዮላቸው ለሰጋጆች ፤ ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለሆኑት (ሰጋጆች)” (አል-ማዑን:4-5)*

የሶላትን ወቅት እስከመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ድረስ ማዘግየት በጣም አደገኛ ባሕሪ ነው፡፡ ከዚያም በመታከትና ፍላጎት ባነሰው ሁኔታ ተነስቶ ግዴታ የሆነን የኢባዳ (የአምልኮት) ተግባር መፈጸም አላህ ወደሚጠላው የመናፍቅነት ሁኔታ ያስገባል፡፡

አላ ቢን አብዱር ራሕማን (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ አነስ ኢብኑ ማሊክን (ረ.ዐ) ልንጠይቃቸው ሄድን፡፡ እዚያ ዳንደደረስን አነስ ብድግ አሉና የአሥርን ሶላት ሰገዱ፡፡ ሶላቱን እንዳጠናቀቁም ከወቅቱ መጀመሪያ ላይ የሰገዱ መሆናቸውን ነገርናቸው፡፡ እርሳቸውም ለምን ቀደም ብለው እንደሰገዱ እንደሚከተለው በማለት ገለጹልን፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- ‘ይህች የመናፍቃን ሶላት ናት! ይህች የመናፍቃን ሶላት ናት! የህች የመናፍቃን

[1] ሱዩጢ አል-ጃሚኡ ሰጊር

ሶላት ናት፡፡[1] ከእነርሱ አንዱ ዝም ብሎ ይቀመጥ፣ ይቀመጥና ፀሐይ ልትጠልቅ ከአድማስ ላይ ብርቱካናማ መልክ ሲኖራትና በሁለቱ የሰይጣን ቀንዶች መካከል ስትሆን ተነስቶ ጥሬ እንደምትለቅም ዶሮ ትክ ትክ በማድረግ ይሰግዳል፡፡ በሶላቱ ውስጥ አላህን አያወሳም፣ በትንሹ ቢሆን እንጂ፡፡' (ሙወጣእ፣ ቁአርን አልከሪም፣ ሙስሊም)

ኡመር (ረ.ዐ.) በየሥፍራው ላሉ አገረ ገዥዎች የሚከተለውን ምክር አስተላለፉላቸው፡-

"ለእኔ የእናንተ ዋነኛው ጠቃሚ ተግባራችሁ ሶላት ነው፡፡ ሶላትን ጠብቆ የያዘና በጊዜያቷ ላይ የተጠነቀቀ በእርግጥ ሃይማኖቱንም ጠበቀ፡፡ አርሷን ጠብቆ ያልያዘና ጊዜዋን ያባከነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኃይማኖቱንም ይተዋል፡፡" (ሙወጣእ ፡ ወቅቱ ሶላት)

ሚስወር ቢን መሕረማ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

"ኡመር ቢን አል ኸጧብ (ረ.ዐ.) በጩቤ በተወጉ ጊዜ ሕሊናቸውን ስተው መሬት ላይ ተዘረሩ፡፡ ልጠየቃቸው ከተኙበት ክፍል ገባሁ፡፡ ሰውነታቸውን ሸፍነዋቸው እንደተንጋለሉ ነበር፡፡ ዙሪያቸውን ያሉትን ሰዎች ጠየቅኩ፡-

"አሁን እንዴት ናቸው?"

"እንደምታየው ሕሊናቸውን ስተዋል" በማለት መለሱልኝ፡፡

"ለሶላት ጥሪ አደረጋችሁላቸውን? በሕይወት ካሉ ከሶላት በስተቀር ሊያነቃቸው የሚችል አንድም ነገር የለም፡፡" በዚህ ጊዜ ሰዎቹ እንዲህ አሉ፡-

'የምእመናን አዛዥ ሆይ! ሶላት፣ ሶላት እየተሰገደ ነው፡፡' ይህን የሰሙት ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ፡-

---

[1] በዚህ ሐዲስ የተጠቀሰው መናፍቅነት የእምነት ሳይሆን የድርጊት መናፍቅነት ነው፡፡

“እንደዚያ ነው? ወላሂ ሶላትን የተዎ፣ ከኢስላም አንዳች ነገር የለውም።” ይህን ካሉ በኋላ ከሰውነታቸው ደም እየፈሰሰ ተነስተው ሶላታቸውን ሰገዱ።” (ሃይሰሚ፣ ኢብን ሰዓድ፡ ሙወጣእ)

ኩፋ መስጊድ ውስጥ ዓሊ (ረ.ዐ.) ኹጥባ ሲያደርጉ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሰሙትን እንደሚከተለው በማለት ደገሙት፡-

“ጁምዓ (ዓርብ) እለት ሰይጣን በጧት ወደ ሱቆችና ገበያ በመሄድና ሰዎች ወደ መስጊድ እንዳይመጡ አንድ ሺህ አንድ የሚሆኑ መሰናክሎችን ይደረድራል። ያንን ማድረግ ባልተሳካለት ጊዜም ቢያንስ ዘግይተው ወደ መስጊድ እንዲሄዱ ለማድረግ ይጥራል። በሌላ በኩል መላእክት በጧት ወደ መስጊድ ሄደው ከበሩ ላይ በመሆን ይጠባበቃሉ። እዚያ ሆነውም መስጊድ የሚመጡትን ሰዎች በሚከተለው አኳኋን ይመዘግባሉ፡- በመጀመሪያው ሰዓት የመጡ፣ በሁለተኛው ሰዓት የመጡ ወዘተ… ይህም ሁኔታ ኢማሙ ሚንበር ላይ እስኪወጡ ድረስ ይቀጥላል። አንድ ሰው ኢማሙን ለማየትና ድምጻቸውን ለመስማት ከሚያስችለው ቦታ ላይ ተቀምጦ በሙሉ ልቡ ኹጥባውን ካዳመጠና ምንም ዓይነት ነገር ሳይናገር ፀጥ ብሎ ከተቀመጠ ሙሉ ምንዳ (አጅር) ይጻፍለታል። አንድ ሰው ኢማሙን ሊያያቸው በሚያስችለው ቦታ ላይ ተቀምጦ እያለ ድምጹን ከፍ አድርጐ የሚናገር ከሆነና ፀጥ ብሎ ካልተቀመጠ ሁለት እጥፍ ኃጢአት ይፃፍበታል።” (አቡዳውድ)

የእለተ ጁምዓን ሶላት ምንዳ ለማግኘት ከልባቸው አስበው ወደ መስጊድ በመሄድ የኢማሙን ንግግር በሚገባ ሊያዳምጡ በሚያስችላቸው ቦታ ላይ የተቀመጡና በንግግሩም የተገሰጹ እንዲሁም ክብር የሰጡ ይህን ካላደረጉ ሰዎች ይልቅ እጅግ ትርፋማ ሆነው ከመስጊድ ይወጣሉ።

ቁርአንን አስተካክሎ በመቅራትና በትንታኔውም ከታወቁት የታቢዒን ምሁራን አንዱ የነበረው ሙጃሂድ እንዲህ ዳላል፡-

“አብደላህ ኢብን ዙቤይር (ረ.ዐ.) አላህን በመገዛት ማንም ካልደረሰበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። በአንድ ወቅት የካዕባ ዙሪያና ሰዎች ጠዋፍ የሚያደርጉበት ሥፍራ ሁሉ በጐርፍ በተጥለቀለቀበት ጊዜ ሰዎች

ለሳምንት ያክል በካዕባ ዙሪያ ጠዋፍ ለማድረግ አልቻሉም ነበር። ይሁን እንጂ አብደላህ ኢብን ዙበይር (ረ.ዐ.) ግን በዚያ ሳምንት እየዋኘ ካዕባን ይጠውፍ ነበር።›› (አሊ፡ አል-ሙተቂ፣ ዘሃቢ)

አንድ ሰው በሚናገረውና በልቡ በሚያስበው ነገር መልካም ሥራው እንዴት ሊበላሽበት እንደሚችል "ጉሊስታን" በተባለው ኪታባቸው ሸይኽ ሰዕድ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

"ገና ልጅ እያለሁ የሌሊት ሶላት በመስገድ ይህን ዓለም ትቶ በተመስጦ መብረር በጣም ያጓጓኝ ነበር። አንድ ምሽት ላይ ከአባቴ ጉን ተቀምጬ እያለሁ ሌሊቱን በሙሉ እንቅልፍ በአይኔ ሳይዞርና ቁርአኑንም ሳላስቀምጠው ነበር ያደርኩት። በዙሪያዬ የነበሩ ብዙ ሰዎች ግን ተኝተው ነበር። በዚህ ጊዜ አባቴን እንዲህ አልኩት፡-

"እዚህ ካሉት ሁለት ረከዓ ሶላት ለመስገድ ጭንቅላቱን ቀና ያደረገ አንድም ሰው የለም። ልክ እንደሞቱ ሁሉ ድብን ብለው ተኝተዋል።"

ንግግሬን ያዳመጠው አባቴ ግንባሩን አኮማተረና እንዲህ አለኝ፡-

"ልጄ ሰዓድ! ሰዎችን ከምታማ ይልቅ ሄደህ ብትተኛ ይሻልሃል። ምክንያቱም አሁን ቁልቁል የምታያቸው ሰዎች ሁሉ ምናልባት ባለመስገዳቸው የአላህን ምሕረት አያገኙ ይሆናል። ይሁን እንጂ ሌላው ቢቀር መላእክት ግን ስለእነርሱ አንዳች መጥፎ ነገርን አይመዘግቡባቸውም። ሆኖም ግን ባንተ የሥራ መዝገብ ላይ ምን እየተጻፈብህ ነው? የእምነት ወንድሞችህን አሳንሰህ እያየሃቸው ሲሆን የሃሜትን ኃጢአትም እየፈፀምክ ነው።"

ሙስሊሞች ሌላው ቀርቶ በጦርነት ጊዜ እንኳን በአምልኮታቸው ላይ ጠንቃቃ መሆናቸውን አሳይተዋል። በዚህም የተነሣ የአላህን እርዳታ (ድል ማድረግን) ተችረዋል። የቬኒሱ ትራቪጃኒ፣ የየልድሪን ባያዚድን አይበገሬና ድል አድራጊ ሰራዊት ከተመለከተ በኋላ እንዲህ ብሏል፡-

"በእኛ ሰራዊት በሽበሽ የሆኑት ወይን፣ ቁማርም ሆነ ሴቶች በኦቶማን ሰራዊት ውስጥ የሉም። ከዚህም በተጨማሪ በጦር ልምምድ ጊዜ ፈጽሞ

የማይደነቃቀፉ ሲሆን ሁልጊዜም ታላቅ የሆነውን የአላህን ስም በማውሳት ቀንና ሌሊት በዚሁ የተጠመዱ ናቸው፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የእነርሱ ድል አድራጊነትና የሁልጊዜም አሸናፊነት ምስጢር፡፡

የባያዚድ መስጊድ ግንባታው አልቆ ለአገልግሎት የተከፈተው ጁምዓ እለት ነበር፡፡ እናም ኢማም ሆኖ ያሰገደው ባያዚድ ሁለተኛ ራሱ ነበር፡፡ ኢልቫ ቸለቢ ክስተቱን እንደሚከተለው በማለት ይተርካል፡-

“የመስጊዱ ግንባታ እንደተጠናቀቀ በይፋ ለአገልግሎት የተከፈተው ሞቅ ባለ ድግስና በጁምዓ እለት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ሱልጣን ባያዚድ ሁለተኛ እዚያ ለተገኘው ምእመን እንዲህ በማለት ሃሳብ አቀረበ፡-

‘የአስርንና የኢሻን የመጀመሪያ (ቀብልያ) ሱናዎች ሁልጊዜም የሚሰግድና እነዚህ ሱናዎች አምልጠውት የማያውቅ ሰው በዚህ በተባረከ እለት ወደፊት ይምጣና ኢማም ሆኖ ያሰግደን፡፡’ በዚያ ሁሉ የሕዝብ ውቂያኖስ ውስጥ ማንም ወደፊት ሊመጣ ስላልቻለ ራሱ ባያዚድ ተነስቶ እንዲህ አለ፡-

‘አልሃምዱሊላህ! እነዚህን ሱናዎች በጦርነትም ሆነ በሰላም ጊዜ ፈጽሞ ትተናቸው አናውቅም፡፡ …’ ይህን ካለ በኋላ ኢማም ሆኖ ማሰገድ ቀጠለ፡ ፡”

ሱልጣን ሙሐመድ ረሺድ በኦቶማን ቤተመንግስት ውስጥ የሚገኙ ልጆችን በዲን እየኮተኮተች እንድታሳድግ ሰፊዬ ሃኒም (ወይም የሶላት መምህር በመባልም ትታወቃለች) ኃላፊነት ሰጣት፡፡

ሱልጣኑ ከሰጣት መመሪያዎች የመጀመሪያው እንዲህ ይል ነበር፡-

“ሶላት ለማይሰግዱና ለማይፆሙ ልጆች ዳቦና ጨው እንዲሰጣቸው አልፈቅድም፡፡ ይህ ፍላጐቴ ለሁሉም ፓሻዎችና[1] ለእንስት ሱልጣኖች ሁሉ በአንቺ በኩል ይድረስ፡፡”

[1] ፓሻ የሚለው ስያሜ በኦቶማን ቱርኮች ዘንድ ለከፍተኛ ባለስልጣን የሚሰጥ የማዕረግ ስያሜ ሲሆን በእኛ ሃገር የነገስታት ልጆች ልዑል እየተባሉ ይጠሩ እንደነበረው ማለት ነው፡፡ (ተርጓሚው)

የኦቶማን ሱልጣኖችን አለማዊ ፀጋ አላህን እንዳያመልኩና በእርሱም ትእዛዝ ሥር ቀጥ እንዳይሉ እንዳላገዳቸው ከዚህ ሁኔታ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሶላትንና ፆምን የመሳሰሉ የአምልኮ ተግባራትን ትኩረት ቸረው ለመጪው ዓለም ስንቅ ሲዘጋጁባቸውና አዲሶቹንም ትውልዶች በዚያው መስመር ለመቅረጽ ሲተጉ ይታዩ ነበር፡፡

እጅግ በጣም ጠንካራና በአምልኮ ላይ ጽኑ በመሆኑ ታላቅ ምሳሌ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለው የካውካሱ ሙጃሂድ ሸይኽ ሻሚል ሲሆን በብዙ ቦታዎች ላይ በሳንጃ፣ በሰይፍና በጥይት ተመትቶ ቆስሏል፡፡ በ1829 (እ.ኤ.አ.) በተደረገው የጊርሚ መከላከል ጦርነት በሰይፍ በመወጋቱ ከደረቱ በኩል የገባው ሰይፍ ሳንባውን፣ የጉድን አጥንቱንና ከአንገቱ አካባቢ ክፉኛ ጉድቶት ነበር፡፡ ለስድስት ወራት ያክል ከታከመ በኋላ ነበር ለማገገም የበቃው፡፡ ይህ ወጣት ሙጃሂድ ከቆሰለ በኋላ ለ25 ቀናት ያክል ሕሊናውን ስቶ ነበር የቆየው፡፡ በ25ኛው ቀን መጨረሻ ላይ አይኑን ሲገልጥ ከአጠገቡ እናቱን እንዳያት ከአንደበቱ መጀመሪያ ያወጣቸው ቃላት እንዲህ የሚሉ ነበሩ፡-

“የምወድሽ እናቴ! የሶላት ወቅት አልፎኝ ይሆን?”

የዳርዳኔል ጦርነት በተፋፋመበት ጊዜ የኢድ ዋዜማ ቀርቦ ነበር፡፡ የቱርኮች ፊት አውራሪ ጦር አዛዥ የሆነው ፓሻ የ9ኛውን ባታሊዮን ኢማሙን ጠርቶ ሃዘን እየተሰማውና እያመነታ እንዲህ አላቸው፡-

“የተከበሩ ሃፊዝ ሆይ! ነገ የረመዳን ኢድ ነው፡፡ ስለሆነም የሰራዊቱ አባላት የኢድን ሶላት በጀመዓ መስገድ ይፈለጋሉ፡፡ የቻልኩትን ያክል ጥረት ባደርግም ሃሳባቸውን ላስቀይራቸው አልቻልኩም፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አጋጣሚ ለእኛ እጅግ አደገኛ ነው፡፡

ምክንያቱም ጠላቶቻችን ይህንን እድል ተጠቅመው ሙሉ በሙሉ ይደመስሱናል፡፡ እባክዎ! ይህንን ሁኔታ ለጦሩ አባላት በልስላሴ ሊነግሯቸው ይሞክሩ፡፡”

ኢማሙ ፓሻውን ተለይተው እንደሄዱ ፊታቸው የሚያበራ አንድ ሰው ከጦሩ መሃል ብቅ ብለው እንዲህ አሉ፡-

"የእኔ ልጅ! ለወታደሮቹ አሁን ምንም አትበላቸው፡፡ ቀኑ ይዞልን የሚያመጣውን ነገር እስቲ እንጠብቅ! አላህ ያለው ሁሉ ከመሆን አይዘልም፡፡"

በቀጣዩ ማለዳ ሁሉንም ያስደነገጠ መለኮታዊ ተዓምር ተከሰተ፡፡ ሙስሊሞቹ የኢድን ሶላት እየሰገዱ እያሉ ግዙፍ ዳመና ከሰማይ በአላህ ፍቅር የተሞሉትን ወታደሮች አጠለላቸው፡፡ በጦር ሜዳ መነጽር የሙስሊሞቹን ሁኔታ ሲከታተሉ የነበሩት ጠላቶቻቸው ነጭ ከሆነ ዳመና በስተቀር በአካባቢው ምንም ነገር ሊመለከቱ አልቻሉም፡፡ በዚያ ማለዳ አድማሱን ሙሉ ሲያስተጋባ የነበረው 'አላሁ አክበር' የሚለው የተክቢራ ድምጽ ብቻ ነበር፡፡

እኒያ ፊታቸው የሚያበራ ሽማግሌ ሰው ከቁርአን ውስጥ የድልን ብስራት የሚነግሩ አንቀጾችን እያነበቡ የምእመናኑን ልብ በብርሃን ሲሞሉት ድምጻቸው ከጠላቶቻቸው ሰፈር ድረስ ዘልቆ ይሰማ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር በእንግሊዛውያኑ ሰራዊት ውስጥ አመጽና ብጥብጥ የተነሳው፡፡ እንግሊዛውያኑ ከተለያዩ ቅኝ ግዛቶቻቸው ብዙ ሙስሊሞችን እያታለሉ አምጥተው ከቱርኮች ጋር እንዲዋጉ አሰልፈዋቸዋል፡፡ እነዚያ ሙስሊሞች ከቱርኮቹ ሰፈር የሚሰማውን የተክቢር ድምጽና ላኢላሃኢለሏህ የሚለውን ከሊማ ሲሰሙ ከሙስሊሞች ወንድሞቻቸው ጋር ሊዋጉ ፊት ለፊት መጋፈጣቸውን በማወቃቸው አመጽ አስነሱ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ባለማወቅ ግራ የተጋቡት የእንግሊዝ ጦር አዛዦች ከሙስሊሞቹ አማጽያን የተወሰኑት ለመቀጣጫ እንዲሰየፉ ካደረጉ በኋላ የቀሩትን ወደኋላ ሆነው በደጀንነት እንዲቆሙ አደረጉ፡፡

የሙስሊሞች ጽኑ እምነት የጠላት ጦር ሊያጠቃቸው ባሰፈሰፈበት ሁኔታ የኢድን ሶላት በጀመዓ እንዲሰግዱ አስቻላቸው፡፡ በዚያ ሁኔታቸው የተደሰተው አላህ መለኮታዊ እርዳታውንና ሰላሙን ከሰማይ በማንቧቧት ከጠላቶቻቸው ጥቃት ሸፈናቸው፡፡ ጫማቸውንም አደላደለ፡፡

በጠላቶቻቸው ሰፈርም ያልታሰበ ሁከት እንዲነሳና ትኩረታቸው እንዲዞር በማድረግ ከተንኮላቸው ጠበቃቸው፡፡

አንድ ሰው የሲራጥ ድልድይን ለማለፍ የሚኖረው ፍጥነት የሚወሰነው አላህን በመገዛት ላይ ይሰጠው በነበረው ትኩረት ልክ መሆኑን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

“ሰዎች ወደ ጀሃነም ይመጡና በላዩዋ ላይ እንደየሥራቸው ሁኔታ ያልፋሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ስብስቦች ልክ እንደመብረቅ ፍጥነት በቅጽበት ያልፋሉ፡፡ ሁለተኛዎቹ ደግሞ እንደንፋስ ፍጥነት ይፈተለካሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ እንደ ፈጣን ፈረሰኛ፣ አሁንም ሌሎቹ እንደ ግመል ጋላቢ፣ ሌሎቹ ደግሞ በሩጫ፣ ከዚያ በኋላ ያሉት እየተራመዱ (ሲራጥን) ያልፋሉ፡፡” (ቲርሚዚ)

ጠቅለል ባለ አነጋገር አላህን የመገዛትና የእርሱ ሃቀኛ ባሪያ የመሆን ዋነኛ ዓላማ ልብን ከአላህ ፈቃድ ጋር ማስማማት ነው፡፡ ይህም ማለት ስለ ዓለማቱ ጌታ አላህ ባህሪያት (ሲፋት) እና ስሞች ጠንቅቆ ማወቅና እርሱን ማፍቀር ማለት ነው፡፡ አምልኮትን ለአላህ ብቻ ማድረግ ለአንድ ሰው ለዛና ውበት የሚያላብስ ሲሆን ይህም በግልጽ ይንፀባረቃል፡፡ በፍላጐትና በሙሉ ትኩረት የሚደረግ አምልኮ ለነፍስ ጥልቀትን በመስጠት ወደ አላህ ያቃርባል፡፡ መብቃቃትንና ለሰዎች ቸር መሆንን፣ እንዲሁም አዛኝነትን ያላብሳል፡፡ ኃያሉ አላህ ለእንዲህ ዓይነት ባሪያዎቹ የሚያዩበት ዓይንና የሚሰሙበት ጆሮ ይሆናቸዋል፡፡ ይህም ማለት እይታቸው፣ የሚሰሙትና የሚያስቡት ነገር ሁሉ መለኮታዊ ይሁንታና ቡራኬ ያለውን ነገር ብቻ ይሆናል፡፡ አላህ ከእንዲህ ዓይነት ሰዎች ያድርገን ፡፡ አሚን!

## ሀ- ነዋፊል (ሱና) የአምልኮ ተግባራት

ሱና ሶላቶች ግዴታ (ፈርድ) የሆኑ ሶላቶችን የሚደግፉና ወደ አላህ ለመቃረብ ምክንያት የሚሆኑ ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ሆኖ ግዴታ ሶላቶችን በተሟላና አላህ በሚፈልገው መልኩ መስገድ አይቻልም፡፡

የቱንም ያክል ጥረትና ጥንቃቄ ቢደረግ እንኳን ስህተቶች መፈጠራቸው የግድ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ ሱና ሶላቶችን ከመስገድ ውጭ ይህንን ክፍተት ወይም ጉድለት የመጠገኛ ሌላ መንገድ የለም፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"በፍርዱ ቀን አንድ ባሪያ መጀመሪያ የሚጠየቀው ሶላቱን የተመለከተ ጥያቄ ነው፡፡ ግዴታ የተደረጉበት ሶላቶች የተስተካከሉ ከሆነ የእርሱ ጉዳይ ቀላል ስለሚሆን ሌላ ችግር ሳይገጥመው ፈተናውን ያልፋል፡፡ ሶላቱ ያልተስተካከለ ከሆነ ፈተናውን ስለሚወድቅ ከባድ ችግር ይገጥመዋል፡፡ የሰውዬው ግዴታ (ፈርድ) ሶላቶች ችግር ካለባቸው እጅግ ኃያሉና የላቀ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡-

"ባሪያዬ አንዳች ዓይነት የሱና ሶላት እንዳለው ፈልጉለት፡፡" ሱና ሶላቶች በፈርድ ሶላት ላይ የተከሰተውን ጉድለት ያካክሳሉ፡፡ በዚህ ዓይነት በሌሎች ጉዳዮቹም ምርመራው ይቀጥላል፡፡ (ቲርሚዚ)

እዚህ ላይ ግዴታ (ፈርድ) የተደረጉ ሶላቶችንም ሆነ ሌሎች የአምልኮ አይነቶችን ችላ ብለን ሱና በሆኑት ላይ ትኩረት እናድርግ የሚል የተሳሳተ ግምት ሊኖረን አይገባም፡፡ ግዴታ የሆኑትን ብቻ እየሰሩ ሱናዎቹን ችላ ማለቱም ትክክል አይደለም፡፡ ትክክለኛው አቋም የግዴታ ሶላቶችን በአግባቡ መስገድና ሱና የሆኑትን ደግሞ አቅም በፈቀደና የቻሉትን ያክል ለመስራት ጥረት ማድረግ ነው፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እና የተከታዮቻቸው አቋምም ይኸው ነው፡፡

በሌላ በኩል በተለያዩ ሸሪዓዊ ምክንያቶች ግዴታ (ፈርድ) ሶላቶቻቸውን ሳይሰግዱ ያሳለፉ ሰዎች ቀዷ (ማካካሻ) ሶላታቸውን በመስገድ ያካክሱ፡፡ ሱና ሶላትን  ጨርሶ መተው ግን ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ያልሰገዳቸውን የግዴታ ሶላቶች በተለይ መስገድ ከሚጠላባቸው ወቅቶች (ፀሐይ ስትወጣና ስትገባ አካባቢ) በስተቀር በማንኛውም ጊዜ መስገድ ስለሚቻል ነው፡፡ ሆኖም ግን ሱና ሶላቶች (ለምሳሌ ኢሽራቅ፣ ተሃጁድ ወዘተ…) ወቅታቸው ካለፈ ቢሰገዱም ተቀባይነት ስለሌላቸው ወቅታቸውን ጠብቆ መስገድ ይመረጣል፡፡

አንድ ባሪያ ፈርድ የሆኑ ነገሮችን ከመፈፀም ውጪ ወደ አላህ የሚቀርብበት መንገድ የለም፡፡ ከዚያ በኋላ ሱና የሆኑ ተግባራትን በመፈፀም ወደ አላህ ይበልጥ እየቀረበና እየተጠጋ ይመጣል፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደተናገሩት አላህ የሚከተለውን በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

"የእኔን ወዳጅ የሚተናኮል እፋለመዋለሁ፡፡ ባሪያዬ ከእኔ ጋር ሊቃረብ የሚችለው ግዴታ ያደረግኩበትን ነገር ሲፈጽም ነው፡፡ ባሪያዬ ነዋፊል (ትርፍ) በሆኑ ነገሮች ወደእኔ በሚቃረብበት ወቅት እወደዋለሁ፡፡ ከወደድኩት ደግሞ የሚሰማበት ጆሮ፣ የሚያይበት ዓይን፣ የሚዳስስበት እጅ፣ የሚሄድበት እግር እሆነዋለሁ፡፡ ቢጠይቀኝ እሰጠዋለሁ፡፡ ጠብቀኝ ካለኝም እጠብቀዋለሁ፡፡" (ቡኻሪ)

ሱና (ነዋፊል) የሆኑ የአምልኮት ዓይነቶች የአንድን አማኝ ሰው መንፈስ በማንቃትና ልቡ ሕያው ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ በኩል ያላቸው ተጽእኖ ታላቅ ነው፡፡ ነፍስን በማጽዳት የአማኙን ሰው ፊት በብርሃን ፀዳል ያደምቁታል፡፡ እነዚህ አማኝ የሆነ ሰው በቅርቢቱ ዓለም ከሚያገኛቸው ሽልማቶች የተወሰኑት ሲሆኑ በመጪው ዓለም ደግሞ ታላቅ የሆነ ፀጋ ይሸለማል፡፡

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ቀናትና ሌሊቶች በሱና ዒባዳዎች የፈኩ ነበሩ፡፡ ከተለያዩ ፈርድ ሶላቶች በፊትና በኋላ ይሰግዷቸው የነበሩ የሱና ሶላቶች፣ የኢሽራቅ (ዱሃ) ሰላት፣ ከሌሊቱ ግማሹን ወይም አብዛኛውን ክፍል የሚሸፍነውና ከወረደላቸው ቁርአን ብዙ ሱራዎችን የሚቀሩበት የተሃጁድ ሶላት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሱና ጾሞች፣ ለድሆች በየጊዜው የሚሰጧቸው ችሮታዎች (ሰደቃ)፤ በአላህ መንገድ ላይ የሚያደርጉት ያላሰለሰ ትግል፣ እንዲሁም ሁልጊዜም ከሚያምረው ፊታቸው ላይ እንደውብ ጽጌረዳ ፈክቶ የሚያታየው ፈገግታቸው ሁሉ ከበጐ ምግባሮቻቸው የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

አንድ የሚያስደስት ነገር በገጠማቸው ወይም አስደሳች ዜና በሰሙ ጊዜ ሱጁድ ያደርጋሉ። ይህንም የሚያደርጉት አላህ ለዋለላቸው ፀጋ ምስጋናቸውን ለመግለጽ ነው። የተለያዩ ተፈጥሯዊና ያልተለመዱ የሆኑ ነገሮች ለምሳሌ የፀሐይ ግርዶሽ፣ ኃያል አውሎ ነፋስ ወዘተ... ሲፈጠር ተናንሰውና ተዋርደው ከዚያ መዓትና ከቁጣው ይሰውራቸው ዘንድ ጌታቸውን ይማፀኑታል። ዝናብን ሲሹ፣ በሽታና ድርቅን ለማስወገድ፣ ወዘተ... እንዲሁ ወደ ፈጣሪያቸው ያጕነብሱና ሱጁድም ያደርጉ ነበር። በወርሃ ረመዳን ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከአዘቦቱ የኢባዳ ተግባራቸው እጅግ በተሻለና በጋለ ስሜት ነበር ፈጣሪያቸውን የሚያመልኩት። የተራዊህ ሶላቶችን ከቤተሰባቸው ጋር ይሰግዳሉ። የመጨረሻዎቹን አስር ቀናት ደግሞ መላ ቤተሰባቸውን ጭምር ለኢባዳ ያተጉ ነበር። እንዲሁም በመስጊድ ኢእቲካፍ  በማድረግ ወደፈጣሪያቸው ይበልጥ ይቃረባሉ። ከረመዳን በኋላም የተለያዩ የሱና አጽዋማትን ለምሳሌ ሰኞና ሐሙስን አዘውትረው ይፆሙ ነበር። ለዚህ ድርጊታቸው የሚከተለውን ምክንያት ይሰጣሉ፡-

"የሰው ልጆች ሥራ ሁሉ ሰኞና ሐሙስ ቀናት ወደ ኃያሉ አላህ ይቀርባሉ። እኔም ፆመኛ ሆኜ ሥራዎቼ እንዲቀርቡልኝ እሻለሁ።" (ቲርሚዚ)

እንደ ሒጅራ አቆጣጠር 13ኛው፣ 14ኛውና 15ኛውን የወሩን ቀናትም መፆም ያዘወትሩ ነበር። በእነዚያ ቀናት ተከታዮቻቸውም እንዲፆሙ ይመክሯቸው ነበር። ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይላሉ፡-

"የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በጦርነት ጊዜ ይሁን በሰላም ጨረቃ ሙሉ የምትሆንባቸውን ቀናት የሚፆሙ ሲሆን ይህንንም ሁልጊዜም አቋርጠው አያውቁም።" (ነሳኢ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከሸዋል ወርም ስድስት ቀናትን፣ የአሹራን 9ኛና 10ኛና 11ኛ ቀናት በፆም ያሳልፉ ነበር። (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሐጅንና ኡምራን ፈዳኢል (ምንዳ) ሁልጊዜም ይገልጹና በእነዚያም ቀናት አላህን ከማመስገን፣ ከማወደሰና

የእርሱን ምሕረት ከመከጀል አይወገዱም፡፡ በእነዚያ ጊዜያት በራሳቸውና አቅም በሌላቸው  ተከታዮቻቸው ስም የመስዋእት እንስሳ ያርዳሉ፡፡

ራቢዕ ቢን ካዕብ እንዲህ ይላል፡-

“እኔ ሁልጊዜ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ውዱእ የሚያደርጉበት ውሃና ሌላም የሚፈልጓቸውን ነገሮች ማታ ማታ አቀርብላቸው ነበር፡፡ በዚያ ጊዜም እንዲህ ሲሉ እሰማቸዋለሁ ‘ሰሚአላሁ ሊመን ሃሚዳህ’ ከዚያም ደግሞ እንዲህ ይላሉ ‘አልሃምዱሊላሂ ረቢል አለሚን’፡፡”  (ኢብን ሰዕድ)፡፡

አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉኝ፡-

“የምትፈልገውን ነገር ጠይቀኝ!” እኔም እንዲህ አልኳቸው፡-

“እኔ ከእርስዎ ጋር በጀነት አብሬ መሆን ነው የምፈልገው፡፡” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን እንደሰሙ እንዲህ አሉ፡-

“ሌላስ የምትጠይቀኝ ነገር የለህም?” እኔም “ይህን ብቻ ነው የምፈልገው” አልኳቸው፡፡ ይህን እንደሰሙ እንዲህ አሉኝ፡-

“እንደዚያ ከሆነ ሱጁድ በማብዛት እርዳኝ፡፡” (ሙስሊም)

ይህ “ሱጁድ” ተብሎ በታላቁ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) አፍ የተጠቀሰው ሌላ ሳይሆን መደበኛ የሆነውና ነዋፊል የሆኑት ሶላቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ሁሉ ብዙ ሱጁዶች ይኖራሉ፡፡ ስለሆነም ጀነት መግባትና በዚያም ውስጥ የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) ጐረቤት ለመሆን የሚሻ ብዙ መስገድና ሱጁዱንም በማብዛት ወደ አላህ እንዲቃረብ ያሻል ማለት ነው፡፡

የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) መኖሪያ የሆነችው ጀነት ከሌሎች ነቢያት መኖሪያ ትበልጣለች፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው በጀነት ውስጥ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ለመጠጋት ከፈለገ በሱናቸው ላይ ቀጥ ማለትና ግዴታ የተደረጉበትንና ነዋፊል ሶላቶችንም በጥልቅ ተመስጦና በብዛት መስገድ ይጠበቅበታል፡፡

ኡሙ ሃቢባ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብላለች፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ሰማኋቸው፡- ‘ከግዴታ ሶላቶች በተጨማሪ በየእለቱ 12 የሚሆኑ ሱና ሶላቶችን (ሙአከድ የሚባሉትን ቀብሊያና ባዕዲያ) የሰገደ አላህ በእርግጠኝነት በጀነት ቤት ይገነባለታል፡፡’ ይህን መልካም ዜና ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከሰማሁ በኋላ ከእነዚህ ነፍል ሶላቶች አንዱንም አልተውኩም፡፡

ኸይበር በተከፈተበት እለት አንድ ሰው ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና እንዲህ አላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ዛሬ በዚህ ሸለቆ ውስጥ ያለ ማንም ሰው ያላየውን ትርፍ ነው ያገኘሁት፡፡”

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ.)፡- ‹‹ምንድን ነው ያገኘኸው?” አሉት፡፡

“አንድም ጊዜ ሳላቋርጥ ስገዛና ስሸጥ በመዋሌ 300 ኡቂያ[1] አተረፍኩ፡፡”

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን የሰውዬውን ንግግር እንደሰሙ እንዲህ አሉ፡-

“ከሁሉም ነገር የበለጠውን ትርፍ ላመላክትህን?”

“እርሱ ምንድን ነው የአላህ መልእክተኛ?”

“ከፈርድ ሶላት በኋላ ሁለት ረክዓ ሱና ሶላቶችን መስገድ ነው፡፡” (አቡዳውድ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በአንድ ወቅት ወደ አንድ አካባቢ ለወታደራዊ ዘመቻ ተዋጊዎቻቸውን ልከው ነበር፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰራዊቱ ታላቅ የሆነ ምርኮን በመያዝ ተመለሰ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ሰው እንዲህ አለ፡-

“የአላህ መልእክተኛ! እንዲህ ፈጣን በሆነ ጊዜ ብዙ ምርኮን ሰብስቦ የተመለሰ ሰራዊት አይተን አናውቅም፡፡”

---

[1] ኡቂያ የእህልን ክብደት ለመለካት የሚያገለግል ጥንታዊ መስፈሪያ ሲሆን አንድ ኡቂያ 1283 ግራም እህል ይይዛል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ከዚህ የበለጠ ፈጣን የሆነ ምንዳና የተሻለ ምርኮ ላመላክታችሁን?” ካሉ በኋላ ቀጥለው እንዲህ አሉ፡-

“አንድ ሰው በትክክል ውዱእ ካደረገ በኋላ ወደ መስጊድ በመሄድ የፈጅር ሶላቱን ከሰገደና (ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ ጠብቆ) የዱሃ ሶላቱን ካከለ የሚያገኘው ምንዳ ብዙ ምርኮ ከመሰብሰብ ይበልጥለታል፡፡›› (ኢብን ሂብባን)

ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

አቡ ዘርን (ረ.ዐ.) እንዲህ አልኳቸው፡-

“ውድ አጐቴ! የተወሰነ ምክር ሊሰጡኝ ይችላሉ?” እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡-

“አንተ የጠየቅኸኝን ጥያቄ እኔም ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ጠይቄያቸው እንዲህ አሉኝ፡- ‘ረፋድ ላይ ሁለት ረከዓ ሶላቶችን ከሰገድክ መሃይማን ከሚሰኙ ሰዎች ውስጥ ስምህ አይሰፍርም፡፡ አራት ረከዓ ከሰገድክ ደግሞ አቢዶች (አላህን ተገዢዎች) ከሚባሉት ውስጥ ትመዘገባለህ፡፡ ስድስት ረክዓ ሶላቶችን ከሰገድክ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ ታገኛለህ፡፡ ስምንት ረክዓ ከሰገድክ ደግሞ “ቃኒቲን” ከሚባሉት (አላህን በብዛት ከሚገዙት) ሰዎች ውስጥ ትመዘገባለህ፡፡ አስር ረከዓዎችን ከሰገድክ ግን በጀነት ቤት ይገነባልሃል’፡፡”

ሰዎችበመልካም ሥራዎች ላይ እስከተጉ ድረስ አላህ የሥራዎቻቸውን ምንዳዎችና የሚፈልጉትን ነገር ያለ ጥርጥር ይሰጣቸዋል፡፡ የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ እርሱን ከማስታወስ የበለጠ ጸጋ ለባሮቹ አልሰጠም፡፡” (ሃይሰሚ፣ አሊ፣ አል-ሙተቂ)

የተባረኩት ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“በጀነት ውስጥ የሚገኝና “የዱሃ በር” የሚባል በር አለ፡-

“በፍርዱ ቀን ተጣሪ እንዲህ እያለ ይጣራል፡- ‘በዱሃ ሶላታቸው ላይ ዘውታሪ የነበሩት የታሉ? እነሆ! መግቢያ በራችሁ። ስለሆነም በአላህ እዝነት በእርሱ ውስጥ ወደ ጀነት ግቡ።››(ሱዩጢ)

ከእያንዳንዱ ውዱእና ትጥበት በኋላ ቢያንስ ሁለት ረከዓ ሶላት መስገድና ኢስላምን ስለሰጠን ኃያሉ አላህን ማመስገን፣ እንዲሁም ውዱዕን ሳይፈቱ ማቆየት (ከፈቱም ማደስ) ምርጥ የሆነ ፀጋ ነዉ።

ኡስማን (ረ.ዐ.) አንድ ጊዜ የውዱእ አደራረግን ለሰዎች ካስተማሩ በኋላ እንዲህ አሉ፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን በመሰለ ሁኔታ ውዱእ አድርገው እንደጨረሱ እንዲህ አሉ፡-

“ልክ እኔ ባደረኩት አይነት ውዱዕ ያደረገና ሁለት ረክዓ ሶላትን የሰገደ በሶላቱም ላይ ከነፍሱ ጉትጉታ ራሱን ያራቀ ያለፈው ኃጢአቱ ይታበስለታል።” (ቡኻሪ)

አንድ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ቢላልን (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉት፡-

“ቢላል ሆይ! ሙስሊም ከሆንክ በኋላ ከሁሉም መልካም ሥራህ ይበልጥ ምንዳ ሳላገኝበት አልቀርም ብለህ የምትገምተው ሥራህ ምንድን ነው? ምክንያቱም በጀነት ውስጥ የጫማህን ኮቴ ከፊት ለፊቴ ሰማሁ።” ቢላል (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መልስ ሰጠ፡-

“ውዱእ ካደረግኩ በኋላ የቻልኩትን ያክል በቀንም ሆነ በማታ እሰግዳለሁ። ምናልባት የተሻለ ምንዳ ያስገኝልኛል ብዬ የማስበው መልካም ሥራዬ ይህ ነው።” (ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በህልማቸው ቢላል (ረ.ዐ.) በጀነት ውስጥ ከፊት ለፊታቸው ሲራመድ የጫማውን ኮቴ አዳመጡ። ኃያሉ አላህ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን ያሳያቸው ሱና የሆኑ መልካም ምግባራትን በመስራት ላይ እንድንበረታና ዘውታሪም እንድንሆን በመሻቱ ነው።

አንድ እለት አቡ ቀታዳ (ረ.ዐ.) ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መስጊድ ገባ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በባልደረቦቻቸው መካከል መቀመጣቸውን ባየ ጊዜ ሄደና ከጐናቸው ተቀመጠ፡፡ ይህን ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ አቡ ቀታዳ (ረ.ዐ.) ዞሩና እንዲህ አሉት፡-

“ከመቀመጥህ በፊት እንዳትሰግድ ያገደህ ነገር ምንድን ነው?”

አቡ ቀታዳ እንዲህ አለ፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እርስዎና ባልደረቦችዎ አንድ ላይ ተቀምጣችሁ ስመለከት አልሰገድኩም፡፡” ከዚያም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“አንዳችሁ ወደ መስጊድ በገባ ጊዜ ከመቀመጡ በፊት ሁለት ረከዓ ይስገድ፡፡” (ሙስሊም)

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች የሆኑት ሶሃባዎች (አላህ የሁሉንም ሥራ ይውደድላቸውና) አንዳች ችግር ወይም ጭንቀት በገጠማቸው ጊዜ ሶላት ይሰግዱና ዱዓ አድርገው ከአላህ እርዳታን ይሻሉ፡፡ በአንድ የበጋ ቀን የአነስ (ረ.ዐ.) አትክልተኛ ወደርሳቸው መጣና ዝናብ ስለጠፋ አትክልታቸው እየጠወለገ መሆኑን ነገራቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አነስ ውሃ እንዲሰጣቸው አዘዙትና ውዱእ አድርገው የተወሰኑ ረከዓዎችን ሰገዱ፡፡ ከዚያም አትክልተኛቸውን እንዲህ በማለት ጠየቁት፡-

“በሰማዩ ላይ ምንም የምታየው ምልክት የለም?” እርሱም

“ምንም የማየው ነገር የለም፡፡” አላቸው፡፡

አነስ (ረ.ዐ.) እንደገና ወደ ቤት ገቡና መስገድ ጀመሩ፡፡ ከዚያም ወጡና ለሶስተኛ ወይም ለአራተኛ ጊዜ ጠየቁት፡-

“በሰማዩ ላይ አንዳች ነገር ታያለህን?” አትክልተኛው እንዲህ አለ፡-

“የወፎችን ክንፍ የሚያክል አነስተኛ ዳመና ይታየኛል፡፡” በዚህ ጊዜ መስገዳቸውንና ዱዓ ማድረጋቸውን ቀጠሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከቆዩ በኋላ ከአጠገባቸው የነበረው አትክልተኛቸው እንዲህ አለ፡-

“ሰማዩ በዳመና ተሞልቷል፡፡ ዝናብም እየጀመረ ነው፡፡”

አነስ (ረ.ዐ.)እንዲህ አሉ፡-

“በሺር ቢን ሸጋፍ ከላከው ከዚህ ፈረስ ላይ ውጣና ዝናቡ ምን ያህል መሬት እንደሸፈነ ተመልከት፡፡”

አትክልተኛው በታዘዘው መሰረት ከፈረሱ ላይ ወጥቶ ዙሪያውን ከቃኘ በኋላ ከአነስ (ረ.ዐ.) ማሳ ውጪ ከየትኛውም የሌላ ሰው ማሳ ላይ እንዳልዘነበ አረጋገጠ፡፡ (ኢብን ሰዓድ)

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ሱና በሆኑ የአምልኮት (የኢባዳ ተግባራት) ብርቱዎች ከመሆናቸውም በላይ ለልጆቻቸውም ይህንኑ በረከት ያስተላልፉ ነበር፡፡ ከሴት ሶሃቢያት መካከል አንዷ የነበረችው ሩባዒ ቢንት ሙአዊዝ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብላለች፡-

“…የአሹራን ቀን ሁልጊዜም እንፆም ነበር፡፡ እንዲሁም ትናንሽ ልጆችንም ሳይቀሩ እንዲፆሙ እናደርግ ነበር፡፡ ልጆቻችንን ይዘን ወደ መስጊድ እንሄድና የሚጫወቱበት አሻንጉሊት እንሰራላቸዋለን፡፡ ከእነርሱ አንዱ ምግብ በመፈለግ ካለቀሰ ያንን አሻንጉሊት ስናስይዘው ፀጥ ይላል፡፡ የምናፈጥርበት ሰዓት እስኪደርስ በዚህ ዓይነት እየሸነገልን እናቆያቸዋለን፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም)

ባጭሩ አምልኮት (ኢባዳ) በሁለት የሚከፈል ሲሆን ግዴታ የሆነ (ፈርድ) እና ሱና ተብሎ ይጠራል፡፡ አንድ ሰው ግዴታ የተደረጉበትን የኢባዳ ዓይነቶች ካልፈፀመ ለታላቅ ቅጣት የሚዳረግ መሆኑ እውነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከግዴታዎቹ የአምልኮ (ኢባዳ) ተግባራት ጐን ለጐን ልንሰራቸውና አቅማችን በፈቀደልን ያክል ልንፈጽማቸው የሚገቡን የአምልኮት (ኢባዳ) ተግባራት አሉ፡፡ በእነዚህ ነፍል (ሱና) ተብለው በሚታወቁ የኢባዳ ዓይነቶች የበረታና አቅሙ እስከቻለ ድረስ በሙሉ ስሜትና ፍቅር የፈፀመ ሰው ወደ አላህ መቃረቡ የማይቀር ነው፡፡ ወደ አላህ ሲቀርብ ደግሞ አላህ ይወደዋል፡፡ እርሱ ከወደደ ደግሞ ሱብሃነሏህ! የጠየቀውን ነገር ሁሉ መርሃባ ይለዋል፡፡ የሁለቱንም ዓለም ኑሮውን

ያሳምርለታል፡፡ አንድ አማኝ በኢባዳ ሲበረታ ወደ ልዩ መንፈሳዊ ድባብ ውስጥ ይገባል፡፡ የተለያዩ የእምነት እርከኖችን አልፎ ‹‹ኢህሳን›› ከተሰኘው ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡

## ለ- ሶላትን በጀማዓ (በኅብረት) መስገድ

ማኅበራዊ መስተጋብርን ማጠናከር ከኢስላም መርሆዎች ውስጥ እጅግ ጠቃሚው ነው፡፡ ከእነዚህ የማኅበራዊ መስተጋብር ማጠናከሪያ ስልቶች አንዱ ደግሞ ሶላትን አምልኮትን በአንድ ልብ ለፈጣሪ ማቅረብን የመሰለ አንድነትንና ወንድማማችነትን የሚያመጣ ነገር አይገኝም፡፡ በኅብረት ሶላት የሚሰገድበት ቦታ የኢስላም ማኅበራዊ መዋቅር መንፈሳዊ መሠረት የሚጣልበት የመጀመሪያ ሥፍራ ነው፡፡

ኢስላም አማኞች እርስበርሳቸው እየተረዳዱና እየተደጋገፉ በሁሉም ጉዳያቸው ሳይነጣጠሉ በአላህ መንገድ አንድ እንዲሆኑ ያዝዛል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلَّذِينَ يُقَٰتِلُونَ فِي سَبِيلِهِۦ صَفًّا كَأَنَّهُم بُنْيَٰنٌ مَّرْصُوصٌ ۝٤ ﴾

*"አላህ እነዚያን እነርሱ ልክ እንደተናሰ ግንብ የተሰለፉ ሆነው በመንገዱ (በኃይማኖቱ) የሚጋደሉትን ይወዳል፡፡" (አስ-ሶፍ:4)*

የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"…እኔ የምፈልገው እናንተ ሁላችሁ አንድ እንድትሆኑና መለያየትና መከፋፈልን በኃይል እንድታስወግዱ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን ሁልጊዜም ብቻቸውን (ተነጥለው) ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ነውና፡፡ ቁጥራቸው አንሶ ሁለት ብቻ እንኳን ቢሆኑ አብረው እስከሆኑ ድረስ ሰይጣን አይጠጋቸውም፡፡ በጀነት ማእከላዊ ሥፍራ ለመስፈር የሚፈልግ ሰው ከጀመዓ ሶላት ላይ መበርታት አለበት፡፡…" (ቲርሚዚ)

በእያንዳንዱ የሶላት ረከዓ የሚከተለውን አንቀጽ እየደጋገምን እናነባለን፡-

“አንተን ብቻ እንግገዛለን፣ አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን፡፡” (አል-ፋቲሃ፡4)

ይህን አንቀጽ እያንዳንዱ ሰው ቢያንስ በቀን ለ17 ጊዜ ያክል እየደጋገመ ያነብባል፡፡ እኛም እንደሙስሊምነታችን የምንገኘው በዚሁ ማኅበረሰብ ውስጥ ነው፡፡

የእኛ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) ለመጀመሪያ ጊዜ ቁባ ወደምትባለው መንደርና ወደ መዲና ከተማቸው ሲገቡ አስቀድመው የቀለሱት የራሳቸውን ጐጆ ሳይሆን አላህ የሚመለክባቸውን መስጊዶች ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ስደተኞቹና ነዋሪዎቿ (አንሷሮች) የመኖሪያ ጐጆዎችን በመስጊዶቹ ዙሪያ መቀለስ ያዙ፡፡

መስጊዱ በሚገነባበት ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ራሳቸው በጉልበት የረዱ ሲሆን ከመስጊዱ መሠረት ጋርም የእምነት፣ የወንድማማችነትና የፍቅር መሠረት አብሮ እየተጣለና እያደገ ነበር፡፡

ሶላትን በጀማአ (በኅብረት) መስገድ የኢስላም ዋነኛው የትኩረት ማእከል ሲሆን አላህም በቀጥታ ያዘዘው ጉዳይ ነው፡፡

የእውነት ነቢይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ከቤተሰብ አባላት መካከል ውጭ የቆዩት ሲመለሱ የቀሩት ዘመዶቻቸው የሚደሰቱትን ያህል አላህ እርሱን ለማስታወስ ወደ መስጊድ በሚመላለሱት ይደሰታል፡፡” (ኢብኑ ማጃህ)

“የመስጊድ ወዳጅ የሆነ ሰው አላህም ለእርሱ ወዳጅ ይሆናል፡፡” (ሱዩጢ)

ከአቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) በተላለፈው መሠረት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አላህ ኃጢአቶችን የሚያብስባትንና ደረጃዎችን ከፍ የሚያደርግባትን ነገር ልጠቁማችሁ ወይ?” `የአላህ ለምእክተኛ ሆይ! አዎ ይጠቁሙን` ተባሉ፡፡ “አስቸጋሪም ቢሆን የተሟላ ውዱእ ማድረግ፣ ወደ መስጊዶች ብዙ መራመድ፣ ከአንዱ ሶላት (መጠናቀቅ) በኋላ ተከታዩን ሶላት

መጠባበቅ (ሃሳብን በሶላት ላይ ማንጠልጠል)፤ በአላህ መንገድ ላይ መታገል (ጅሃድ) ማለት ይኸ ነው።” (ሙስሊም)

ዓኢሻ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብላለች

“የሶላት ጥሪ (አዛን) እየሰማ ወደ መስጊድ የማይሄድ ሰው መልካም ነገርን ለማግኘት አልሻም። መልካም ነገር እንዲያገኝም አልተሻለትም።” (በይሃቂ አስ-ሱነን አል-ኩብራ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የጀማዓ ሶላትን ለሚተው ሰው ይቅርታ አላደረጉም። አንድ እለት እንዲህ አሉ፡-

“የሶላትን ጥሪ እየሰማ ምንም ዓይነት በቂ ምክንያት ሳይኖረው ወደ መስጊድ የማይሄድ ለብቻው የሚሰግደው ሶላት ተቀባይነት የለውም።›› ይህን የሰሙት ባልደረቦቻቸው እንዲህ በማለት ጥያቄ አቀረቡላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ይህ በቂ የተባለው ምክንያት ምንድን ነው?”

“አንዳች አደጋ ይደርስብኛል ብሎ መፍራትና ሕመም” በማለት መልስ ሰጧቸው።

በጀማዓ የሚሰገድን ሶላት ያለ በቂ ምክንያት መተው የሙስሊሙን ኡማ መፈረካከስ ያስከትላል። የሙስሊሙን ኡማ (ማኅበረሰብ) የሚከፋፍለውን አላህ እንዲህ በማለት ያወግዛል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ فَرَّقُواْ دِينَهُمۡ وَكَانُواْ شِيَعٗا لَّسۡتَ مِنۡهُمۡ فِي شَيۡءٍۚ إِنَّمَآ أَمۡرُهُمۡ إِلَى ٱللَّهِ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم
بِمَا كَانُواْ يَفۡعَلُونَ ١٥٩ ﴾ الأنعام: ١٥٩

*“እነዚያ ኃይማኖታቸውን የለያዩ አሕዛብም የሆኑ በምንም ከእነርሱ አይደለህም። ነገራቸው ወደ አላህ ብቻ ነው። ከዚያም ይሰሩት የነበሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል።” (አል-አንዓም፡159)*

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“በአንድ ዘመቻ ላይ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በዴካንና በኡስፋን መካከል በሚገኝ ቦታ ላይ ቆይታ አድርገው ነበር፡፡ አጋሪዎቹ እንዲህ አሉ፡-

“ሙስሊሞቹ ከአባቶቻቸውና ከወንዶች ልጆቻቸው ይልቅ አብልጠው የሚወዱት ሶላት አላቸው፡፡ ይህም የአስር ስግደት ነው፡፡ ለዚያ ሰዓት ሁላችሁም ተዘጋጁና አንድ ላይ ሆነን እየሰገዱ እያሉ እናጠቃቸዋለን፡፡”

በዚህ ጊዜ መልአኩ ጂብሪል ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በመውረድ በአን-ኒሳእ ምእራፍ 102ኛው አንቀጽ ላይ በጦርነት ጊዜ እንዴት የጀመዓ (የሕብረት) ስግደትን እንደሚፈጽሙ በማብራራት ገለፀላቸው፡፡” (ቲርሚዚ)

ሙስሊሞች በተጋጋለ ጦርነት ላይ ቢሆኑ እንኳን ሶላታቸውን በጀመዓ የመስገድ ግዴታ እንዳለባቸው ይህ ክስተት ያሳየናል፡፡

ጃእፈር ቢን አምር ከአባቱ የሰማውን ገጠመኝ እንዲህ በማለት ይተርካል፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የበግ ጠቦት እግር ቆርጠው መብላት ሲጀምሩ ተመለከትኩ፡፡ በዚያው ቅጽበት ለሶላት ጥሪ (አዛን) በመደረጉ በእጃቸው ይዘውት የነበረውን ቢላ አስቀምጠው ውዱእ እንደ አዲስ ሳያደርጉ ወደ መስጊድ ሄደው ለሶላት ቆሙ፡፡” (ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሶላትን በጀመዓ ለመስገድ እጅግ ጉጉ ስለነበሩ የመጀመሪያው ጥሪ መሰማት ሲጀምር ነው ምግባቸውን ጥለው ወደ መስጊድ ያመሩት፡፡ እርሳቸው የመጀመሪያውን ጥሪ ሲሰሙ መጓዝ ይጀምሩ እንጂ ሶላቱ እስኪጀመር ድረስ የቀረበላቸውን ምግብ በልተው ሊጨርሱ ይችሉ ነበር፡፡

የአላህ መልእክተኛ (.ዐ.ወ.) ይህችን ዓለም ተሰናብተው ለመሄድ ያበቃቸው በሽታ ይዟቸው እንኳን እጅግ አድርጐ ያስጨንቃቸው የነበረው የጀመዓ ሶላት ጉዳይ ነበር፡፡ አነስ (ረ.ዐ.) እንዳወሩት የአላህ

መልእክተኛ (ሰ.0.ወ.) ሶላታቸውን በጀመዓ መስገድ ያልቻሉት ለመጨረሻዎቹ ሶስት ቀናት ብቻ ነበር፡፡ (ቡኻሪ)

ዓኢሻ (ረ.0.) እንዲህ ትላለች፡-

“ባልደረቦቼ ሶላታቸውን ሰገዱን?”

“አልሰገዱም የአላህ መልእክተኛ! እርስዎን እየጠበቁ ነው፡፡” አልኳቸው፡፡

“እንደዚያ ከሆነማ ትንሽ ውሃ አዘጋጅልኝ፡፡” አሉኝ ፡፡ እኔም ውሃ ሰጠኋቸውና ራሳቸው ታጠቡ፡፡ ከዚያ በኋላ ለመነሳት ሲሞክሩ ባለመቻላቸው ራሳቸውን ሳቱ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ራሳቸውን ሲያውቁ እንደገና እንዲህ በማለት ጠየቁኝ፡-

“ባልደረቦቼ ሰግደዋልን?”

“አልሰገዱም የአላህ መልእክተኛ! እርስዎን እየጠበቁ ነው፡፡” አልናቸው፡፡ “እንደዚያ ከሆነ ጥቂት ውሃ ይዘጋጅልኝ፡፡” አሉ፡፡ አሁንም የተወሰነ ውሃ አመጣሁላቸውና ታጠቡበት፡፡ እንደገና ለመነሳት ሲሞክሩም ራሳቸውን ሳቱ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ህሊናቸውን ገዙ፡፡

ይህ ሁኔታ ለጥቂት ደቂቃ ያክል ቀጠለ፡፡ በዚህ መካከል መስጊድ ውስጥ ቁጭ ብለው የኢሻን ሶላት ከነቢዩ (ሰ.0.ወ.) ጋር ለመስገድ ይጠባበቃሉ፡፡ ከዚያም አቡበክር (ረ.0.) ሶላቱን እንዲያሰግዱ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ.) ነገሯቸው፡፡ አቡበክር (ረ.0.) በጣም ልበ-ሩህሩህና ለዛባ ሰው ስለነበሩ ኡመርን (ረ.0.) እንዲህ አሏቸው፡-

“ኡመር ሆይ! ሶላቱን አንተ አታሰግድምን?” ኡመር (ረ.0.) ይህን የእርሳቸውን ግብዣ ባለመቀበል እንዲህ አሉ፡-

“ለዚህ ኃላፊነት ከእኔ ይልቅ አንተ የተገባህ ነህ፡፡” በዚህ ጊዜ አቡበክር (ረ.0.) ሶላቱን አሰገዱ፡፡ በማግስቱ በዙህር ሶላት ወቅት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ.) በመጠኑ የተሻላቸው መሰሉ፡፡ በመሆኑም የዙህርን ሶላት ለማሰገድ ከግራና ከቀኝ ክንዶቻቸውን በሁለት ሰዎች ትከሻ ላይ

አድርገው ወደ መስጊድ ሄዱ፡፡ (እስካሁን ድረስ እግራቸውን መሬት ላይ ማቆም አቅቷቸው እንዴት ይጐትቱት እንደነበር ይታወሰኛል፡፡)” (ቡኻሪ)

በዚያ ጊዜ አቡበክር (ረ.ዐ.) ሶላቱን እያሰገዱ ሳሉ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በመምጣታቸው ወደኋላቸው ለማፈግፈግ ፈለጉ፡፡ ይሁን እንጂ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባሉበት እንዲቆዩ በምልክት ነገሯቸው፡፡ ከዚያም ከአቡበከር (ረ.ዐ.) አጠገብ ቆሙ፡፡ ከዚያም አቡበከር (ረ.ዐ.) ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ሲከተሉ ሕዝቡ ደግሞ አቡበከርን ተከትሎ በመስገድ ሶላቱ ተጠናቀቀ፡፡ (ቡኻሪ)

አነስ (ረ.ዐ.) የሚከተለውን አውርተዋል፡-

“አንድ ጊዜ አቡበከር ሶላት እያሰገዱ ነበር፡፡ እለቱ ሰኞ የነበረ ሲሆን ሁላችንም መስመራችንን (ሶፍ) አስተካክለን ቆመናል፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የክፍላቸውን መጋረጃ አንስተው ቆመው ይመለከቱን ጀመር፡፡ ፊታቸው እያበራ በፈገግታ ደምቀው ጥርሶቻቸውም ይታዩ ነበር፡፡ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚያ ሁኔታ ስናያቸው በጣም ከመደሰታችን የተነሣ ሶላታችንን ለማቋረጥ ደርሰን ነበር፡፡ አቡበከር (ረ.ዐ.) ምናልባት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከኋላ እየመጡ እንደሆነ በማሰብ የሚያሰግዱበትን ቦታ ለቅቀው ወደ ኋላ በመመለስ ከመጀመሪያው ሶፍ ለመቀላቀል አቅማምተው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሶላታቸውን እንዲጨርሱ ምልክት ከሰጧቸው በኋላ መጋረጃቸውን ዘግተው ወደ ክፍላቸው ገቡ፡፡ ይህ ነበር ለመጨረሻ ጊዜ ያየናቸውና ወደዚያኛው ዓለምም የሄዱበት እለት፡፡ (ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ቀደም ሲል በተጠቀሰው ሁኔታ የተደሰቱትና ፈገግታ የታየባቸው ባልደረቦቻቸው በልበ ሙሉነት የጀማዓ ሶላታቸውን በመስገዳቸው ነበር፡፡ ያ በዳመና እንደተሸፈነች ጀንበር ብልጭ ብሎ የጠፋው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ፈገግታ በዚያ ቦታ ይሰግዱ ለነበሩ ባልደረቦቻቸው የሕይወት ሙሉ የደስታና የተስፋ ምንጭ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ መጋረጃቸውን መልሰው ወደ ክፍላቸው

ገብተው ብዙም ሳይቆዩ ይህችን ዓለም ተሰናብተው ለመሄድ ከጣእራቸው ጋር መታገል ጀመሩ፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሊሞቱ አቅራቢያ ለመጨረሻ ጊዜ የተናገሯቸው ቃላት እንዲህ የሚሉ ነበሩ፡-

“ሶላታችሁን! ሶላታችሁን! የሶላታችሁን ነገር በተለይ ተጠንቀቁ! እንዲሁም በስሮቻችሁ ያሉትን (አገልጋዮች) በተመለከተ አላህን ፍሩ፡፡” (አቡ ዳውድ፣ ኢብን ማጃህ)

ጃቢር ኢብን አብዱላህ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይላል፡-

“የእኔ ጐሣ አባላት የሆኑት በኒ ሰሊም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መስጊድ ራቅ ያለ ቦታ ነበር ያሉት፡፡ በመስጊዱ አካባቢ ለመስፈሪያ የሚሆን ክፍት ቦታ ስለነበር ቤቶቻችንን ሸጠን ወደ መስጊዱ ጠጋ ብለን ለመስፈር ፈለግን፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሃሳባችንን እንደሰሙ እንዲህ አሉን፡-

“ወደ መስጊዴ ቀረብ ብላችሁ ለመስፈር ፈልጋችኋል ሲባል ሰማሁ፡፡ ይህ እውነት ነው?”

“አዎን የአላህ መልእክተኛ! በእውነት እንደዚያ ለማድረግ ፈልገናል፡፡” አልናቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ

“በኒ ሰሊም ሆይ! እዚያው ባላችሁበት ቦታ ቆዩ፡፡ ወደ መስጊድ ስትመላለሱም በእያንዳንዱ እርምጃችሁ ምንዳችሁን አግኙ፡፡ አዎን! እዚያ ባላችሁበት ሆናችሁ ወደ መስጊድ በምትመጡበት በእያንዳንዷ እርምጃ ምንዳ ይጻፍላችኋል፡፡” (ሙስሊም፣ ቲርሙዚ)

አብደላ ኢብን ኡሚ መኽቱም (ረ.ዐ.) አንድ ጊዜ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! መዲና በመርዘኛ ነፍሳትና በጐጂ አውሬዎች የተሞላች ናት፡፡ እነዚህ ነፍሳትና የሚናከሱ አውሬዎች ይጐዱኛል ብዬ እፈራለሁ፡፡ ወደ መስጊድ ከመምጣት ይልቅ እቤቴ ሆኜ መስገድ እንድችል አይፈቅዱልኝምን?”

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ሃያ አለ ሶላህ (ወደ ሶላት ኑ)፣ ሃያ አለል ፈላህ (ወደ ተሳካ ሕይወት ኑ)የሚለውን የሶላት ጥሪ ትሰማለህ? እንደዚያ ከሆነ ወደ መስጊድ መምጣት አለብህ፡፡” (አቡ-ዳውድ)

ስለዚህም ምንም ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥመን የሶላት ጥሪ (አዛን) ከሰማን መልስ የመስጠት ግዴታ እንዳለብን ነው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በአጽንኦት ያስገነዘቡን፡፡

ሰዎች ወደ መስጊድ ይመጡ ዘንድ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ማስጠንቀቂያ ይሰጡ ነበር፡፡ ኡበይ ኢብን ከዓብ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይላል፡-

“አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የፈጅርን ሶላት ከሰገዱ በኋላ እንዲህ አሉ፡-

“እገሌና እገሌ ለሶላት መጥተዋልን?”

“አልመጡም” የሚል መልስ ተሰጣቸው፡፡

“እገሌና እገሌስ አልመጡምን?” አሉ፡፡

“አልመጡም” የሚል መልስ ሰጧቸው፡፡ በዚህ ጊዜ እንዲህ አሉ፡- “እነዚህ ሁለት ሶላቶች (የፈጅርና የኢሻ ሶላት) ናቸው በመናፍቃን ላይ ከባድ የሚሆኑት፡፡ እነዚህ ሶላቶች የያዙትን ትርፍና ትሩፋት ብታውቁ ኖሮ በእንብርክካችሁ እየዳሃችሁ መጥታችሁ በጀመአ ትሰግዱ ነበር፡፡ የመጀመሪያው (አወል) ሶፍ ልክ እንደመላእክት ሶፍ ነው የሚቆጠረው፡፡ በእርሱ ውስጥ ያለውን ትሩፋት ብታውቁ ኖሮ ቦታውን ለመያዝ ትሽቀዳደሙ ነበር፡፡ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር በመሆን የሚሰግደው ሶላት ብቻውን ከሚሰግደው ሶላት ይልቅ ብዙ ትሩፋትና ብዙ ምንዳን ያስገኝለታል፡፡ ከሁለት ሰዎች ጋር በመሆን የሚሰገድ ሶላት ከአንድ ሰው ጋር ሆኖ ከሚሰገድ ሶላት ይልቅ በላጭና ብዙ ትርፋማ ነው፡፡ የሰጋጆች ቁጥር በበዛ ቁጥር የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ ይደሰታል፡፡ (አቡዳውድ፣ ነሳኢ)

አብደላህ ኢብን መስኡድ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“በአላህ እምላለሁ፣ መናፍቅ ከሆነና መናፍቅነቱም በሁሉም ሰው ዘንድ የታወቀ ከሆነ ሰው በስተቀር ሶላቱን የሚተው ሰው አላየሁም፡፡ በአላህ እምላለሁ አንድ የታመመ ሰው በሁለት ሰዎች ተደግፎና እግሮቹን መሬት ላይ እየጐተተ መጥቶ በሁለቱ ሰዎች መካከል በሶላት ሶፍ ላይ ቆሞ ሲሰግድ አይቻለሁ፡፡” (ሙስሊም)

አንድ እለት አብደላህ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) በገበያ ውስጥ ይዘዋወሩ በነበረበት ጊዜ የሶላት ጊዜ ደረሰ፡፡ ከዚያም ልክ የሶላት ጥሪ (አዛን) ሲሰሙ ሙስሊሞች ሱቆቻቸውንና መደብሮቻቸውን እየዘጉ ወደ መስጊድ ሲያመሩ ተመለከቱ፡፡ ይህን እንዳስተዋሉም እንዲህ አሉ፡-

“እነዚህ ሰዎች የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ እንደሚከተለው በማለት በቁርአን ካወደሳቸው ሰዎች ውስጥ ናቸው፡-

﴿ رِجَالٌ لَّا تُلْهِيهِمْ تِجَٰرَةٌ وَلَا بَيْعٌ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ وَإِقَامِ ٱلصَّلَوٰةِ وَإِيتَآءِ ٱلزَّكَوٰةِ ۙ يَخَافُونَ يَوْمًا تَتَقَلَّبُ فِيهِ ٱلْقُلُوبُ وَٱلْأَبْصَٰرُ ﴿٣٧﴾ ﴾ النور: ٣٧

*“አላህን ከማውሳትና ሶላትን ከመስገድ ዘካንም ከመስጠት ንግድም ሽያጭም የማያታልላቸው ልቦችና ዓይኖች በእርሱ የሚገለባበጡበትን ቀን የሚፈሩ የሆኑ ሰዎች (ያጠሩታል)፡፡” (አል-ኑር፡37)*

(ኢብን ከሲር ፣ ሃይሰሚ)

ሺፋ ቢንት አብዲላህ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብላለች፡-

“አንድ እለት ኡመር ኢብን ኸጧብ (ረ.ዐ.) ሊጠይቁን ወደኛ መጡ፡፡ ሁለት የቤተሰባችን አባላት ተኝተው ሲመለከቱ እንዲህ በማለት ጠየቁ፡-

“እነዚህ ሰዎች ምን ችግር ኖሮባቸው ነው በፈጅር ሶላት ላይ ከእኔ ጋር በጀማአ ያልሰገዱት?” እኔም፡-

“የምእመናን አዛዥ ሆይ! እነርሱ የተራዊህን ሶላት (ወቅቱ ረመዳን ነበርና) አብረው ሲሰግዱ ካነጉ በኋላ የፈጅርን ሶላትም አንድ ላይ ሰግደው ነው ወደመኝታቸው የሄዱት” አልኳቸው።

ኡመር ግን እንዲህ በማለት ተናገሩ፡-

“እስከ ንጋቱ ድረስ ከመስገድ ይልቅ መስጊድ መጥተው የፈጅርን (ሱብሂ) ሶላት ከእኔ ጋር መስገዳቸው ይበልጥ ያስደስተኛል።” ኡስማን ኢብን አፋን (ረ.ዐ.) አንድ እለት የዒሻን ሶላት ለመስገድ ወደ መስጊድ ሄዱ። ሆኖም ግን የሰጋጁን ሁኔታ ሲመለከቱ ቁጥሩ አነስተኛ በመሆኑ ከመስጊዱ የኋለኛ ክፍል ሄደው ጋደም በማለት ሰዎች እስኪመጡ ድረስ መጠባበቅ ያዙ።

በዚሁ ጊዜ ኢብን አቢ አምር (ረ.ዐ.) መጣና ከጐናቸው ቁጭ አለ። ኡስማን (ረ.ዐ.) ማን እንደሆነ ጠየቁት። እርሱም ማን እንደሆነ ራሱን አስተዋወቀ።[1] ከዚያም “ከቁርአን ምን ያህል አጥንተሃል?” በማለት ጠየቁት። ለጥያቄያቸው መልስ ከሰጣቸው በኋላ እንዲህ አሉ፡-

“አንተ የወንድሜ ልጅ! የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡-

“የኢሻን ሶላት በጀመዓ የሰገደ ግማሽ ሌሊት እንደሰገደ ይቆጠርለታል። የሱብህን ሶላት በጀመዓ የሰገደ ሌሊቱን በሙሉ እንደሰገደ ይቆጠርለታል፡ ፡ (ሙወጣእ ሶላቱል ጀማአ፡ አብዱር-ረዛቅ አል ሙሰነፍ፣ ሙስሊም)

ሳቢት ቢን ሐጃጅ ሶላተል ጀማአ የማይሰግዱ ሰዎችን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

[1] በዘመኑ እንደ አሁኑ ጊዜ መብራት እንደልብ ስለማይገኝ የሱብህና የኢሻ ሶላት ላይ ሰው ከሰው መተያየት አይችልም ነበር። ይህም በመሆኑ ነበር መናፍቃን በሱብህና በኢሻ ሶላት ላይ ተገኝተው የማይሰግዱት። ምክንያቱም በዚያ ሰዓት ማንነታቸው ስለማይታወቅ ሰግደዋል ተብሎ እንደሚገመት ስለሚያውቁ ነው፡ (ተርጓሚው)

“አንድ ጊዜ ኡመር ኢብን አል-ኸጧብ (ረ.ዐ.) ሶላት ሊሰገዱ ወደ መስጊድ መጡ፡፡ ከዚያም ሰዎችን ዘወር ብለው ከተመለከቱ በኋላ ሙአዚኑ ኢቃም እንዲል አዘዙና ቆመው የሚከተለውን ተናገሩ፡-

“ማንንም ከዚህ በኋላ አንጠብቅም!” ሶላቱን አሰግደው እንደጨረሱም ወደ ሰጋጆቹ ዞረው እንዲህ አሉ፡-

“አንዳንድ ሰዎች ከጀመዓ ሶላት የሚቀሩትና ሌሎችም እንዲያፈገፍጉ የሚያደርጉት ለምንድን ነው? በአላህ እምላለሁ! እነዚህን ሰዎች እየያዙ የሚያመጡልኝ ሰዎች መድቤ ካመጡልኝ በኋላ የጀማአ ሶላትን ዳግመኛ እንዳይተው ለማስጠንቀቅ አስቤያለሁ፡፡››

ኡሙ ደርዳእ (ረ.ዐ.) እንደሚከተለው ብላለች፡-

“አቡ ደርዳዕ (ረ.ዐ.) ወደእኔ ሲመጣ ተናድዶ ነበር፡፡ እኔም ምንድን ነው እንዲህ ያናደደህ ነገር? በማለት ስጠይቀው የሚከተለውን መልስ ሰጠኝ፡-

“እኔ የሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) ኡማ (ሕዝብ) የማውቀው ሶላትን በጀማዓ በመስገዱ ነው፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ጀማዓ ያመለጠው እንደሆን የሚቀጥለው የሶላት ወቅት እስኪመጣ ድረስ በተከታታይ ሲሰግድ ይቆያል፡፡ የኢሻን ሶላት በጀማዓ ካልሰገደ ራሱን በይበልጥ ይቀጣል፡፡ እስኪነጋ ድረስም ምንም ሳያቋርጥ ሲሰግድ ያድራል፡፡” (ኢብን ሐጀር)

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የተባረኩ ባልደረባዎች አንዱ የነበረው ሐሪስ ቢን ሃሰን (ረ.ዐ.) ጋብቻ መሠረተ፡፡ በዚያ ጊዜ አንድ ያገባ ሰው ለብዙ ቀናት ከቤቱ አይወጣም ነበር፡፡ ስለሆነም በተለይ በሱብህ ሶላት ወቅት ወደ መስጊድ አይሄድም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሐሪስ (ረ.ዐ.) በጫጉላው ሌሊት የፈጅርን ሶላት ሊሰግድ ወደ መስጊድ ሄደ፡፡ ሰዎችም እንዲህ በማለት ጠየቁት፡-

“ባለፈው ምሽት ማግባትህን እናውቃለን፡፡ ታዲያ ቤትህን ለቅቀህ ልትመጣ የቻልከው እንዴት ነው?” እርሱም ለሰዎች የሚከተለውን መልስ ሰጣቸው፡-

“በአላህ እምላለሁ! የሱብሂን ሶላት በጀመዓ እንዳልሰግድ የምታግደኝ ሴት ምን የተረገመች ብትሆን ነው!” (ሃይሰሚ)

ከታቢዒን አባላት መካከል የታወቁትን አጧእን እንዲህ በማለት ኢብን ጁረይጅ ጠየቃቸው፡-

“አንድ ሰው የግዴታ ሶላቱን እቤቱ እየሰገደ እያለ ከሁለቱ አዛኖች (ከአዛንና ከኢቃማ) አንዱን ቢሰማ ሶላቱን አቋርጦ ወደ አስጊድ መሄድ ይኖርበታልን?” አጣዕ እንዲህ በማለት መለሱ፡-

“አዎን! ከሚሰገደው ሶላት የተወሰነ ክፍል አገኛለሁ ብሎ ተስፋ ካደረገ መሄድ አለበት፡፡”

“ሁለተኛውን ጥሪ (ኢቃምን) ከሰማሁ ልክ እንደ መጀመሪያ ጥሪ ወደ መስጊድ በመሄድ መልስ መስጠት ይኖርብኛልን?”

አጣዕ ለዚህም “አዎን” የሚል መልስ ሰጡ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) ከግዴታ ሶላቱ ውስጥ ሁለት ረከዓ የሚሆነውን እቤቱ ከሰገደ በኋላ የቀረውን ሁለት ሳይጨርስ ኢቃም ሲባል ስለሰማ ወዲያውኑ ሶላቱን አቋርጦ ወደ መስጊድ ገስግሷል፡፡

አምር ቢን አብዱላህ ሊሞት እያጣጣረ ነበር፡፡ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ማለቱን ያስተዋሉት ዙሪያውን ያሉት ዘመዶቹ ማልቀስ ጀመሩ፡፡ በዚህ መካከል የመግሪብ ሶላት መድረሱን የሚያበስረው አዛን ሲሰማ አምር በዙሪያው ያሉትን ሰዎች እንዲህ አላቸው፡-

“አንሱኝና ልሂድ!”

“ለምንድን ነው የምንትነሳው? የት ለመሄድ ነው?” አሉት፡፡

“ወደ መስጂድ” አላቸው፡፡ እነርሱ በአግራሞት እያስተዋሉት

“በዚህ ሁኔታ ላይ እያለህ?” አሉት፡፡

አምር ታላቅ ጽናት በሚታይበት መንፈስ እንዲህ አለ፡-

“ሱብሃነኋህ! ለሶላት ጥሪ ሲደረግ እየሰማችሁ አይደለምን? ከዚያ በኋላ መቅረት ይቻላልን? አንሱኝና ልሂድ እባካችሁ!”

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወደ መስጊድ ተወስዶ አንድ ረከዓ ሶላት ከሰገደ በኋላ በሱጁድ ላይ እያለ ነፍሱ ወጣች፡፡

ምን ያማረ መጨረሻ ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) "እንዳኗኗራችሁ ትሞታላችሁ" ያሉትን ሐዲስ በትክክል ተግባራዊ ያደረገ ክስተት ነበር ይህ የአምር አሟሟት፡፡ በኃያሉ አላህ እዝነት በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ለጀማዓ ሶላት ታላቅ ትኩረት ይሰጥ የነበረው ይህ ሰው በሚወደው ሶላት ላይ እያለ ነፍሱ ወጥታለች፡፡

አጣ ኢብኑ ሳቢት (አላህ ይዘንላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡-

"ከአላህ ወዳጆች አንዱ የሆኑት አብዱላህ ሰለሚ መታመማቸውን ሰማን፡ ፡ እናም ሄደን ልንጠይቃቸው እንደሚገባን አሰብን፡፡ መታመማቸውን የነገሩን ሰዎች አብዱላህ የሚገኙት መስጊድ መሆኑን ገለጹልን፡፡ በጠና መታመማቸው እየተነገረ መስጊድ የመሄዳቸው ነገር ግራ አጋባን፡፡ ወደ መስጊድ ስንሄድ እየሰገዱ አገኘናቸው፡፡ በጣም ተዳክመውና ትንፋሻቸውንም በመከራ ሲያወጡ በማየታችን ስለፈራን እንዲህ አልናቸው፡-

"ሸይኻችን ሆይ! እቤትዎ ሄደው ቢተኙ ለእርስዎ የተሻለ አይሆንምን?"

እርሳቸው ግን እንዲህ አሉ፡-

"በደረሰኝ ሐዲስ መሠረት የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሶላትን በጀመዓ መስገድ በላጭ መሆኑን ነግረውናል፡፡ እኔም ከመስጊድ ውስጥ ሆኜ እየሰገድኩ ነፍሴ እንድትወጣ ፈለግኩ፡፡"

ሙሐመድ ቢን ሰማድ አላህን በጣም የሚገዛ ሰው ነበር፡፡ በተለይም ደግሞ የጀመዓ ሶላትን በተመለከተ እጅግ በጣም ጠንቃቃ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

"ሶላቴን ሁልጊዜም የምሰግደው በጀማዓ ነው፡፡ ለአርባ ዓመታት ያክል የመጀመሪያው የሶላት ተክቢር (ተክቢረተል ኢሕራም) አምልጦኝ አያውቅም፡፡ እስከማስታውሰው አንድ ጊዜ ብቻ እናቴን ሳስቀብር የመጀመሪያው ረከዓ አምልጦኛል፡፡ ያችን ያመለጠችን ረከዓ ለመተካትና

የሙሉ ጀመዓ ሶላትን ምንዳ ለማግኘት አስቤ ያንን ሶላት ሃያ አምስት ጊዜ ያክል ሰገድኩት። በዚያው ሌሊት በሕልሜ እንዲህ ተባልኩ፡-

"ሙሐመድ ሆይ! ሶላትህን ለሃያ አምስት ጊዜ ያክል ሰገድክ። ይሁን እንጂ መላእክቶች በጀመዓ ሶላት ጊዜ "አሚን" የሚሉትን በምን ታካክሰዋለህ?" (ከንደቡል- ፈዷኢለል አእማል ገጽ፡275)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"ኢማሙ የፋቲሃን ምእራፍ አንብቦ ሲጨርስ ተከታዮቹ "አሚን" ይበሉ። ምክንያቱም የጀመዓው ቃል በሰማይ ካሉት (መላእክት) ቃል ጋር አንድ አይነት ከሆነ የእያንዳንዱ ሰው ያለፉት ጥቃቅን ኃጢአቶች ሁሉ ይማራሉና።" (ቡኻሪ)

ዘገባዎች እንደሚያሳዩት የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ በፍርዱ ቀን እንሚከተለው በማለት ይጠይል፡-

"ጐረቤቶቼ የታሉ?"

መላእክት ይጠይቃሉ፡-

"ጌታችን ሆይ! ላንተ ጐረቤት የሆነው ማን ነው?"

የላቀው ጌታ እንዲህ ይላል፡-

"እነዚያ መሳጂዶቼን የጀመዓ ሶላት በመስገድ ሲያሸበርቁ የኖሩት።"

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"መስጊድ የእነዚያ የሙተቆች (አላህን ፈሪዎች) ቤት ነው። እነዚያ መሳጂዶችን ቤቶቻቸው ያደረጉ አማኞች ምቾትን፣ እዝነትንና በሲራጥ ድልድይ ላይ ያለጭንቀት ማለፍን፣ እንዲሁም ጀነት ገብተው የእርሱን ውዴታ ማግኘትን እንደሚታደሉ አላህ ቃል ገብቶላቸዋል።" (ጦበራኒ)

ከኦቶማን ቱርክ የታሪክ ፀሐፍት አንዱ የሆነው አሲቅ ፓሻዜድ አንድ ጊዜ እንዲህ አለ፡-

“እነዚህ የኦቶማን መሪዎች ከተከበረ የዘር ሃረግ የተገኙ ናቸው፡፡ አንዳቸውም ሕገወጥ ነገር ሲሰራ አይታይም፡፡ የኢስላም ምሁራን ኃጢአትነቱን ያፀደቁት አንዳች ነገር ካለ በቻሉት አቅማቸውና ጥረታቸው ያንን ነገር ሳያስወግዱት አይቀሩም፡፡”

ይህ ከፍ ሲል የተጠቀሰው ባሕሪያቸው ምክንያት ሆኖ ሊሆን ይችላል ሸይኹል ኢስላም ሞላ ፈነሪ የተባሉ ምሁር የሱልጣን የልድሪን ባያዚድን በችሎት ላይ ምስክርነት መስጠት በግልጽ እንዲቃወሙ ያስቻላቸው፡፡ ይህንንም ያደረጉት ሱልጣኑ ሶላቱን በጀማዓ ስለማይሰግድ ነበር፡፡ ሱልጣኑ ያንን አቋም ለምን በግልጽ እንደወሰዱ ላቀረበላቸው ጥያቄ ሸይኹ ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል፡-

“ክቡር ሱልጣን! እኔ በጀማዓ ሶላት ላይ ስትሰግድ አላይህም፡፡ አንተ የዚህ ታላቅ ሃገር መሪ እንደመሆንህ በመጀመሪያው ሶፍ ላይ መገኘት ይገባህ ነበር፡፡ በሌላ አባባል የመልካም ሥራ አርአያ ሆነህ መታየት ነበረብህ፡፡… ሶላተልጀማዓን የማትቀላቀል ከሆነ ለሕዝቦችህ መጥፎ አርአያነትን ስለሚያስከትል ለምስክርነትም ብቃት እንዳይኖርህ ያደርጋል…”

ከዚህ ክስተት በኋላ ሱልጣን የልድሪን ባያዚድ ዝነኛውንና ቡርሳ ውስጥ የሚገኘውን መስጊድ አስገንብቶ በየእለቱ አምስት ወቅት ሶላቱን እዚያ ይሰግድ ነበር፡፡

ለማጠቃለል ሶላትን በጀማዓ መስገድ የአንድን ሰው የእምነት ጽናት የሚያረጋግጥ መገለጫ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“አንድ ሰው አዘውትሮ ወደ መስጊድ ሲመላለስ ካያችሁት ኢማን (እምነት) አለው ብላችሁ መስክሩለት፡” ይህን ካሉ በኋላ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አነበቡ፡-

﴿ إِنَّمَا يَعۡمُرُ مَسَٰجِدَ ٱللَّهِ مَنۡ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَأَقَامَ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَى ٱلزَّكَوٰةَ وَلَمۡ يَخۡشَ إِلَّا ٱللَّهَۖ فَعَسَىٰٓ أُوْلَٰٓئِكَ أَن يَكُونُواْ مِنَ ٱلۡمُهۡتَدِينَ ١٨ ﴾

*"የአላህን መስጊዶች የሚሰራው በአላህም በመጨረሻው ቀን ያመነ ሶላትንም በደንቡ የሰገደ ግዴታ ምጽዋትንም የሰጠ ከአላህም ሌላ (ማንንም) ያልፈራ ሰው ብቻ ነው፡፡ እነዚያም ከተመሩት ጭምር መሆቸው ተረጋገጠ፡፡" (አት-ተውባህ፡18)*

ሶላትን በመስጊድ በቀን አምስት ጊዜ መስገድ የሚከተሉትን ጥቅሞች እንደሚያስገኝ የአላህ ወዳጆች ይናገራሉ፡-

- አላህ በመሳጂዶች ውስጥ ከሚፈስሰው ፀጋና ችሮታ ለመጠቀምና በምእመናን ልቦች መካከል ጠንካራ ትስስር ለማግኘት ያስችላል፡፡
- ሶላትን በመጀመሪያዎቹና ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው ሰዓቶች ለመስገድ ያስችላል፡፡
- ዱዓ ለማድረግ፣ አላህን ምህረት ለመለመንና የመላእክትንም ምስክርነት ለማግኘት ይረዳል፡፡
- ከሰይጣን ጉትጉታ የመራቂያው ብቸኛ ቦታ በመሆኑ፡፡
- የመጀመሪያውን ተክቢራ (ተክቢረተል ኢሕራምን) ከኢማሙ ቀጥሎ ማለት ከአላህ ዘንድ የሚያስሰጠውን ታላቅ ምንዳ ለማግኘት ያስችላል፡፡
- በጎ ሥራን ከይዩልኝና ከይስሙልኝ ነጻ ለማድረግ ያግዛል፡፡
- አላህን በሕብረት በማውሳት የሚያስገኘውን ታላቅ ጥቅም ያስገኛል፡፡
- በሙስሊሞች (ምእመናን) መካከል የሚኖረው ትስስር ቀጣይነት እንዲያገኝ ያግዛል፡፡
- አላህን በመፍራትና እርሱን በመታዘዝ እርስ በርስ ለመረዳዳት ያበቃል፡፡

- የቁርአንን ሕግጋት ለማጥናትና ድምጽን ከፍ አድርጐ በመቅራት ለመለማመድ ያግዛል፡፡

- ሶላትን በጥራትና ሰላማዊ በሆነ ድባብ ለመስገድ ያስችላል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ብዙ ጥቅሞች የሚገኙት ሶላትን በጀማዓና መስጊድ ውስጥ በመስገድ ነው፡፡ ለዚህም ነው የላቀው አላህና የእርሱም ተወዳጅ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.)፣ ምእመናን ሶላቶቻቸውን መስጊድ ውስጥ በጀመዓ እንዲሰግዱ አበክረው የሚያሳስቡት፡፡

## ሐ- የሌሊት ሶላት (ተሃጁድ)

ፀጥ ባለውና ፍጥረታት ሁሉ በእንቅልፍ በተረቱበት ሌሊት የታላቅ ግርማና የመፈራት ባለቤት ከሆነው አላህ ጋር መገናኘት የሚያስገኘውን ሃሴት ከቶም በቃላት መግለጽ አይሞከርም፡፡ የሌሊት ሶላት ጽንፍ አልባ የሆነውን የአላህ እዝነት፣ ይቅርታውን እና ውዴታውንም ለማግኘት በፍቱንነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ፀጋ ነው፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ تَتَجَافَىٰ جُنُوبُهُمْ عَنِ ٱلْمَضَاجِعِ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ خَوْفًا وَطَمَعًا وَمِمَّا رَزَقْنَٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿١٦﴾ ﴾ السجدة: ١٦

*“ጌታቸውን በመፍራትና በመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጐኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃሉ፡፡ ከሰጠናቸውም (ፀጋ) ይለግሳሉ፡፡” (አስ-ሰጅዳህ፡16)*

በሌሊት (ተሃጁድ) ሶላት ውስጥ አላህ ያስቀመጠውን ጥበብና ፀጋ የሚያውቀው የሞከረውና ያጣጣመው ብቻ ነው፡፡ ይህ ከአላህ ጋር የሚኖር ግንኙነት ይበልጥ የሚሰምረው ወይም የሚደበዝዘው በባሪያው ልብ ውስጥ ባለው ፍራቻና ክጀላ ልክ ነው፡፡ በጥልቁ ጨለማ በታጀበው ግርማዊ ሌሊት ወደፈጣሪዋ የምትቃትት ነፍስ፣ ምህረቱን የምትከጅልና አንዳች ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ትሩፋት የምትሻ ሩህ ያለምንም ግርዶ ሁሉንም ጉዳይዋን ገላልጣ ለፈጣሪዋ የምትገልጽበት ማለፊያ ሰዓት ነው፡፡

በሐዲስ እንዲህ የሚል ነገር ተጠቅሶ ይገኛል፡-

“ሙስሊሞች የዚህችኛዋንም ሆነ የመጪውን ዓለም ጉዳያቸውን ለአላህ ቢያቀርቡ ተቀባይነት የሚያገኙበት ጊዜ በሌሊቱ የተወሰነ ክፍል ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህም ጊዜ በእያንዳንዱ ሌሊት አለ፡፡” (ሙስሊም)

ሐጅ አሊ ራሚተኒ (አላህ ይዘንለትና) እንዲህ ይላል፡-

“ሶስት ልቦች ከተገጣጠሙ የአንድ አማኝ ጉዳይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ እነርሱም ፍፁማዊ የሆነው የባሪያው ልብ፣ የቁርአን ልብ (ይኸውም ሱራ ያሲን) እና የሌሊቱ ልብ (ይህም ከንጋት በፊት ያለው ሰዓት) ናቸው፡፡ ይህንን ምርጥ ሁኔታ በሚገባ የተገነዘበ ማንም የአላህ ባሪያ ወደ ፈጣሪው በመመለስ፣ ምህረቱን በመለመንና የሚፈልገውን ነገር እንዲሰጠው በመማፀን ወደርሱ ተናንሶ ከቀረበ የሻውን ነገር ሁሉ ማግኘቱ አይቀሬ ነው፡፡ ኃያሉ አላህ ይህንን ሁኔታ ወደው በየጊዜው የሚጠቀሙበትን ባሪያዎቹን ሲያወድስ እንዲህ ይላል፡-

﴿ كَانُوا۟ قَلِيلًا مِّنَ ٱلَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ ﴿١٧﴾ وَبِٱلْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ ﴿١٨﴾ ﴾ الذاريات: ١٧ - ١٨

*“ከሌሊቱ ጥቂትን ብቻ ይተኙ ነበሩ፡፡ በሌሊቱ መጨረሻዎችም እነርሱ ምሕረትን ይለምናሉ፡፡” (አዝ-ዛሪያት፡ 17-18)*

እንግዲህ ላወቀበትና የመጪውን ዓለም ታላቅ አደጋ ከራሱ ላይ ለመገፍተር ለወደደ ሰው ጣፋጩን እንቅልፍ መተውና ጐንን ከመጋደሚያዎች ማራራቅ በትልቁ እንደሚክስ ይገነዘባል፡፡ ይህ ጊዜ በእርግጥም በአላህ ፍቅርና የእርሱንም ታላቅነት በማወቅ ወደ አጽናፈ ዓለሙ ጌታና አስተናባሪ ምስጢራት ልብን የሚመራ መሆኑ እውነት ነው፡፡ ይህን ጣፋጭ የሆነ ጉዳይ የሚያውቁ ከቶም ከማንኛውም ምድራዊ ቁስና አጓጊ ነገር ሁሉ አብልጠው በመምረጥ ከእንቅልፋቸው መራራቃቸው የተለመደ ነው፡፡ ፍጥረት በሙሉ ነፍሱን ስቶ በወደቀበት ፀጥተኛ ሌሊት የፈጣሪን ውዴታ ከመፈለግና ወደርሱ ውዴታ የሚያደርሰውን መንገድ ከመምረጥ የተሻለ ምን ፀጋ ይኖራል? ኃያሉና

ጥበበኛው አላህ አሁንም በሌላ የቁርአን አንቀጽ እነዚህን ባሮቹን እንዲህ እያለ ያሞካሻቸዋል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ يَبِيتُونَ لِرَبِّهِمْ سُجَّدًا وَقِيَٰمًا ﴿٦٤﴾ وَٱلَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا ٱصْرِفْ عَنَّا عَذَابَ جَهَنَّمَ إِنَّ عَذَابَهَا كَانَ غَرَامًا ﴿٦٥﴾ ﴾ الفرقان: ٦٤ - ٦٥

*"የአር-ራሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚሄዱ፣ ባለጌዎች (በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው። እነዚያም ለጌታቸው በግንባራቸው ተደፊዎችና ቋሚዎች ሆነው የሚያድሩት ናቸው።" (አል-ፉርቃን:64:65)*

የሌሊትን ሶላት ለመስገድ መጣደፍ የመንፈስንና የልብን ግለት በመጨመር፣ ደስታንም በማጐናፀፍ ይክሳል። አንዳንድ የአላህ ባሪያዎች በሌሊት ሶላት የሚገኘውን የእምነት ለዛና ፍስሃ በሚገባ ካጣጣሙ በኋላ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፡-

"በእኔና በሌሊት ሶላቴ መካከል የሚገባብኝ ባይሆን ኖሮ ሞትን አልፈራም ነበር።"

ሰዎች ‹‹ጌታዬን ከልብ እወዳለሁ›› እያሉ በግዴለሽነት መጐናፀፊያ ተጀቡነው እስከንጋቱ ድረስ በእንቅልፍ ማሳለፋቸው ምፀት አይሆንምን? በእውነቱ ከአላህ ጋር ሳይገናኙ በግዴለሽነት የሚያልፍ ሌሊት የባከነና በምንም መልኩ ሊተካ የማይችል ክስረት ሲሆን የሚነፃፀረውም በምድረ በዳ ከዘነበ ዝናብ ጋር ነው።

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አብደላህ ኢብን አምር ቢን አል-አስን (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መክረዋቸዋል፡-

"አብደላህ ሆይ! እንደ እገሌ አትሁን። እርሱ የሌሊት ሶላት ሲሰግድ ከቆየ በኋላ አሁን ግን አቋርጧል።" (ቡኻሪ)

ይህ የሚያሳየው የሌሊት ሶላት ሲሰግዱ ከቆዩ በኋላ ችላ በማለት መተው ከአላህ ዘንድ የተጠላ ተግባር መሆኑን ነው።

እንግዲህ አንድ ሰው ከሌሊቱ የተወሰነውን ክፍል ከጌታው ጋር ለመገናኘት ከመደበ መጀመር ያለበት ምህረት እንዲያደርግለት በመለመን (በእስቲግፋር) ነው፡፡ ከዚያም ቀስ እያለ በቁርአን አንቀፆች እየተዋዛ በተባረከው ሌሊት ወደመንፈሳዊው ዓለም መቅዘፍ ነው፡፡ ከዚያም አላህ በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም መልካም ነገሮችን እንዲሰጠው ይለምናል፣ ከጀሃነም ቅጣት ይጠብቀው ዘንድ ይማፀናል፣ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ የአክብሮትና የእዝነት ሰላምታ ያወርዳል ወዘተ…

በተለይም ደግሞ በሌሊቱ መገባደጃና በቁርአን እንደተጠቀሰው በከዋክብት መጥለቂያ ሰዓት ላይ የሌሊት ሶላት መስገድ በጣም የተወደደና ምርጥ ተግባር ነው፡፡ ይህን እድል ማንም ሰው ቢሆን እንደቀላል ነገር በመቁጠር ማሳለፍ የለበትም፡፡ ሰውነታችን በአግባቡ ይንቀሳቀስና እኛም በሕልውና እንቀጥል ዘንድ ምግብ እንደሚያስፈልገን ሁሉ ነፍሳችንም መንፈሳዊ የሆነ ቀለብ እንደሚያስፈልጋት ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ለዚህም ነው ኃያሉ አላህ ከሌሊቱ ክፍል ሁሉ ይበልጥ በመጨረሻውና ወደ ንጋት ቀረብ ባለው ክፍል እንድናስታውሰው የሚፈልገውና የበለጠ ግምት የሚሰጠው፡፡ በቁርአን እንዲህ የሚል ተጽፏል፡-

﴿ كَانُوا۟ قَلِيلًا مِّنَ ٱلَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ ﴿١٧﴾ وَبِٱلْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ ﴿١٨﴾ ﴾ الذاريات: ١٧ - ١٨

*“ከሌሊቱ ጥቂትን ብቻ ይተኙ ነበር፡፡ በሌሊቱ መጨረሻዎችም እነርሱ ምሕረትን ይለምናሉ፡፡” (አዝ-ዛሪያት፡17-18)*

አላህ እንዲህም ይላል፡-

﴿ وَمِنَ ٱلَّيْلِ فَٱسْجُدْ لَهُۥ وَسَبِّحْهُ لَيْلًا طَوِيلًا ﴿٢٦﴾ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ يُحِبُّونَ ٱلْعَاجِلَةَ وَيَذَرُونَ وَرَآءَهُمْ يَوْمًا ثَقِيلًا ﴿٢٧﴾ ﴾ الإنسان: ٢٦ - ٢٧

*“ከሌሊቱም ለርሱ ስገድ በረዥምም ሌሊትም አወድሰው፡፡ እነዚህ ፈጣኒቱን ዓለም ይወዳሉ፡፡ ከባድን ቀንም በስተፊታቸው ሆኖ ይተዋሉ፡፡” (አድ-ዳህር፡26-27)*

አምር ቢን አበሳ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

“የአላህን መልትክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ጠየቅኳቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ወደ አላህ ለመቃረብ የሚያበቃ ከጊዜያቶች ሁሉ የበለጠ (የተለየ) ጊዜ ይኖራልን?” እርሳቸውም እንዲህ በማለት መለሱልኝ፡-

“እንዴታ! አለ እንጂ፡፡ አንድ ባሪያ ወደ አላህ የበለጠ የሚቀርብበት ሰዓት የመጨረሻው የሌሊቱ ክፍል አማካኝ ጊዜ ነው፡፡ በዚያ ሰዓት ጌታቸውን ከሚያስታውሱ ሰዎች መሆን ከቻላችሁ አድርጉት፡፡ ምክንያቱም በዚያ ሰዓት የሚሰገድን ሶላት መላእክት ይጣዱታልና፡፡ (በዚያ ሰዓት መላእክት የሰጋጁን ሰው በአንክሮ ይከታተላሉ ማለት ነው፡፡)” (ነሳኢ)

በአጭሩ አንድ አማኝ ሰው አላህና መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ባመላከቱትና በመከሩት መሠረት ትርጉም ባለው አኳኋን ሌሊቱን ከተጠቀመ ከቀኑ የበለጠ ብርሃናማ ይሆንለታል፡፡

በያዚድ ቢስቲማኢ የተባለው የኦቶማን ቱርክ ሱልጣን እንዲህ ብሎ ነበር፡-

“ሌሊቴ ከቀኔ ጋር እስኪመሳሰል (ብርሃናማ እስኪሆን ድረስ) ምንም ዓይነት (የአምልኮት) ምስጢር አልተገለፀልኝም ነበር፡፡”

እነዚያ የሌሊቱን ትክክለኛ ዋጋ በሚገባ የተገነዘቡና በውስጡ የያዘውን ታላቅ በረከት የተረዱ በሕይወታቸው ላይ ታላቅ ለውጥ ለማምጣትና በመንፈሳዊው ዓለም የመጠቀ ስብዕናን ለመላበስ ተጠቅመውበታል፡፡ እናም የሌሊቱን የተወሰነ ክፍል (በተለይም የሌሊቱን የመጨረሻ ሲሶ) ለመማረክና የአላህን ሞገስ ለማግኘት የሚሻ ሰው ቀኑን በአግባቡና ከኃጢአት ርቆ ማሳለፍ ይጠበቅበታል፡፡

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

በሌሊቱ ሰማይ ላይ ያጠለለውን ተዝቆ የማያልቅ ፀጋ ምዕመናን እንቅልፋቸውን ተወት አድርገው ይዘርፉ ዘንድ የምንጊዜም አርአያቸው የሆኑትን ተወዳጅ ነቢይ አላህ እንዲህ በማለት አዝዟቸዋል፡፡

﴿ وَمِنَ ٱلَّيۡلِ فَتَهَجَّدۡ بِهِۦ نَافِلَةٗ لَّكَ عَسَىٰٓ أَن يَبۡعَثَكَ رَبُّكَ مَقَامٗا مَّحۡمُودٗا ٧٩ ﴾

*“ከሌሊትም ላንተ ተጨማሪ የሆነችን ሶላት በርሱ (በቁርአን) ስገድ፤ ጌታህ ምስጉን በሆነ ሥፍራ በእርግጥ ያቆምሃል፡፡” (አል-ኢስራእ፡79)*

ይህ መለኮታዊ ትዕዛዝ ከወረደ በኋላ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በተባረከውና የብዙ ትሩፋት ባለቤት በሆነው ሌሊት እየተነሱ አላህን ምህረት ከመለመን፣ ቁርአንን ከማንበብና ዱዓም ከማድረግ ቦዝነው አያውቁም፡፡ ይህንንም በሕመም ላይ እያሉና በሁለት እግራቸው ተስተካክለው መቆም በማይችሉበት ጊዜ ሁሉ ይፈጽሙት ነበር፡፡ ሁኔታዎች አስቸጋሪ ከሆኑባቸው ደግሞ ቁጭ ብለውም ቢሆን ይሰግዳሉ እንጂ ፈጽሞ ትተውት አያውቁም፡፡

የተባረኩ የሆኑት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የተሃጁድ ሶላትን በሕይወት ዘመናቸው በሙሉ ሲሰግዱ ኖረዋል፡፡ ይህም አጠቃላይ አሥራ ሶስት የሚሆኑ ረከዓዎችን ከዊትር ሶላት ጋር ይይዛል፡፡ በኋለኞቹ የሕይወት ዘመኖቻቸው ወደ አሥራ አንድ ረከዓ ዝቅ አድርገውት ነበር፡፡ ሊሞቱ አቅራቢያ ደግሞ ዘጠኝ ረከዓዎችን ይሰግዱ ነበር፡፡ (አቡዳውድ)

የነቢዩ (.ዐ.ወ.) ተወዳጅ ባለቤት የነበረችው ዓኢሻ (ረ.ዐ.) እንዲህ ትላለች፡ -

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በረመዳንም ሆነ በሌላ ጊዜ የተሃጁድ ሶላትን ከአሥራ አንድ ረከዓ አስበልጠው ሰግደው አያውቁም፡፡ በመጀመሪያ በውበታቸው የሚለዩና በርዝመታቸውም የሚታወቁ የሆኑ አራት ረከዓዎችን ይሰግዳሉ፡፡ ከዚያም ሌሎች አራት ረከዓዎችን

ይጨምራሉ። እነዚህንም ቢሆን ስለውበታቸውና እርዝመታቸው አትጠይቁኝ፡ (በቀላሉ በቃላት ለመግለጽ አይቻልምና)። ከዚያ በኋላ ሶስት ረከዓዎችን ይጨምራሉ። አንድ ጊዜ እንዲህ በማለት ጠየቅኳቸው፡- “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የዊትርን ሶላት ሳይሰግዱ ሊተኙ ነውን?”

“ዓኢሻ ሆይ! አይኖቼ ቢያሸልቡም ልቤ ግን አይተኛም” በማለት መለሱልኝ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ይህ ሐዲስ የሚያሳየን የአላህ መልእክተኛ ልብ ሲሰግዱ ብቻ ሳይሆን ምንጊዜም ከአላህ ጋር መሆኑን ነው።

የአላህ መልእክተኛ በሶላት ላይ ሲሆኑ የሚታይባቸውን ሁኔታ ሁዘይፋ (ረ.ዐ.) አብሯቸው የሱና ሶላት ሲሰግድ አስተውሏል። እንዲህ በማለት ይተርካል-

“አንድ ምሽት ላይ ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ጋር መስገድ ጀመርኩ። ከበቀራ ምዕራፍ ማንበብ ጀመሩ። እኔም ‘ምናልባት መቶኛው አንቀጽ ላይ ሲደርሱ ሩኩዕ ያደርጋሉ’ ብዬ አሰብኩ። ሆኖም ግን መቶኛው አንቀጽ ላይ ሲደርሱ ማንበባቸውን ቀጠሉ። ‘ምናልባት በዚህ ምዕራፍ ሁለት ረከዓ ሊሰግዱ ፈልገው ይሆናል’ ስል አሰብኩ። እርሳቸው ግን ማንበባቸውን ቀጠሉ። ‘ይህ ምዕራፍ ሲያልቅ ሩኩዕ ይወርዱ ይሆናል’ አልኩ። ይሁን እንጂ ማንበባቸውን ቀጥለው ሱረቱል ኒሳእን ጀመሩ። ያንን ሲጨርሱ ወደ አሊ-ዒምራን ተሸጋገሩ። ሲያነብቡ ተረጋግተውና ቀስ እያሉ ነበር። አላህን ማወደስ የሚገባቸው ቦታ ላይ ሲደርሱ ‘ሱብሃነኋህ’ (ለአላህ ጥራት ይገባው) ይላሉ።

ዱዓ ማድረግ ካለባቸው አንቀጽ ላይ ሲደርሱ ዱዓ ያደርጋሉ። በአላህ መጠበቅ ካለባቸው አንቀጽ ላይ ሲደርሱ በአላህ ይጠበቃሉ።

ከዚያ በኋላ ሩኩእ አደረጉና ‘ሱብሃነ ረቢየል አዚም’ (ታላቅ የሆነው ጌታዬ ጥራት ተገባው) እያሉ ከቆሙበት ጊዜ ጋር በሚስተካከል አኳኋን ለረዥም ጊዜ አጐነበሱ።

ከዚያም "ሰሚአላሁ ሊመን ሃሚዳ፤ ረበና ለከል ሃምድ (አላህ ያመሰገነውን ይሰማል፤ ጌታችን ሆይ! ምስጋና ሁሉ ላንተ ይገባል) ብለው ከሩኩእ ተነሱ። አሁንም ዘለግ ላለ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ሱጁድ ወረዱ፡ ፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡- "ሱብሃነረቢየል አእላ" (የልቅና ባለቤት የሆነው ጌታዬ ጥራት ተገባው) ሱጁዳቸው የወሰደው ጊዜ ልክ የቆሙበትን ያክል ይሆናል።" (ሙስሊም)

ዓኢሻ (ረ.ዐ.) እንዲህ ትላለች፡-

"አንድ ሌሊት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከጐኔ እንደሌሉ አረጋገጥኩ። ምናልባትም ወደ አንዷ ሚስታቸው ሄደው ይሆናል ብዬም አሰብኩ። እፈልጋቸውም ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስመለስ ሩኩእ አድርገው ወይም ሱጁድ ላይ ሆነው እንዲህ ይሉ ነበር፡- "ሱብሃነከ ወቢሃምዲከ ላ ኢላሃ ኢላ አንተ"

(አላህ ሆይ! አንተ ከማንኛውም ጉድለት የጠራህ ነህ። ከአንተ በቀርም የሚያመልኩት ጌታ የለም።) በዚህ ጊዜ (ትንሽ ሃፍረት ብጤ እየተሰማኝ) እንዲህ አልኩ፡-

"እናትና አባቴ መስዋእት ይሁኑልዎ! የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ የጠረጠርኩዎት በሌላ! እርስዎ የሚገኙበት ሁኔታ ሌላ!..." (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለመንፈሳዊ ምጥቀት ፍቱን መድሃኒት የሆነውን የተሃጁድ (ለይል) ሶላት ሕዝባቸው በሙሉ እንዲለምደውና እንዲተገብረው ይፈልጉ ነበር። በዚህም መሠረት ይህን ታላቅ ፀጋ በመጀመሪያ ለእርሳቸው ቀረብ የሚሏቸው ሰዎች እንዲጀምሩት አደረጉ። ለምሳሌ አንድ ሌሊት የልጃቸው ባል የሆኑትን የዓሊን (ረ.ዐ.) እና የፋጢማን (ረ.ዐ.) ቤት አንኳኩተው እንዲህ አሉ፡- "ተነስታችሁ የለይል ሶላት አትሰግዱምን?" ይህን የሚያደርጉትና በዚህ ምክራቸው ይፀኑ የነበረው ከሌሊት ሶላት የሚገኘውን መንፈሳዊ ፀጋ እንዲጐናፀፉ በመጓጓት ነበር።

ሌሎች ባልደረቦቻቸውን ደግሞ እንዲህ ሲሉ መክረዋቸዋል፡-

“ሌሊት ተነስታችሁ ለመስገድ ጥረት አድርጉ። ይህ ከእናንተ በፊት የነበሩ ሰዎች ይሰሩት የነበረና ከአላህ ጋር ለመቃረብም ሰበብ ይሆናችኋል። (የሌሊት ሶላት) ሃጢአትን ከመፈፀም እንድትቆጠቡ፣ ለሰራችሁትም ሃጢአት ሥርየት እንድታገኙ ያደርጋል። ጭንቀትንም ያስወግዳል።” (ቲርሚዚ)

የነቢዩላህ ሱለይማን (ዐ.ሰ.) እናት ልጃቸውን እንዲህ ይሏቸው ነበር…

“የምወድህ ልጄ! የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በሌሊት ብዙ አትተኛ። ሌሊት ብዙ መተኛት በፍርዱ ቀን አንድን ሰው (የመልካም ሥራ) ድሃ ያደርገዋልና።” (ኢብኑ ማጀህ)

የሚቀጥለውን ክስተት የተረከው ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) ሲሆን በተጨባጭ የተሃጁድ ሶላት የሰውን ልጅ ከጀሃነም ቅጣት እንደሚያርቀው ያሳያል፡-

“በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሕይወት ዘመናት አንድ ሰው ህልም ካየ ለእርሳቸው ይነግራቸው ነበር። እኔም ሕልም ባይና ለእርሳቸው ብነግራቸው በጣም እመኝ ነበር። በዚያን ጊዜ ገና ወጣትና (ያላገባሁ) ስሆን የምተኛውም መስጊድ ውስጥ ነበር። አንድ ጊዜ በሕልሜ ሁለት መላእክት ወደእኔ መጥተው ወደ ጀሃነም ይዘውኝ ይሄዳሉ። እዚያም ሁለት የውሃ ጉድጓድ ግድግዳዎች የመሰሉ የግንብ አምዶችን አየሁ። የማውቃቸውንም ጥቂት ሰዎች እዚያ በማየቴ በጣም ተደነቅሁ። ከዚያም እንዲህ እያልኩ መጮህ ጀመርኩ፡-

“ከጀሃነም እሳት በአላህ እጠበቃለሁ! ከጀሃነም እሳት በአላህ እጠበቃለሁ!” በዚያ ጊዜ አንድ ሌላ መልአክ ይመጣና እንዲህ ይለኛል፡-

“አይዞህ አትፍራ። ምንም ነገር አይደርስብህም።”

ከዚያም ይህን ሕልሜን የነበዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባለቤት ለነበረችው ታላቅ እህቴ ለሃፍሳ (ረ.ዐ.) ስነግራት እርሷ ደግሞ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ተረከችላቸው። ሕልሜን ከሰሙ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ማለታቸውን ሰማሁ፡-

“አብደላህ ምን የተባረከ ሰው ነው! የሌሊት ሶላት ቢሰግድ ደግሞ ከዚህ በበለጠ ይባረካል፡፡”

ከዚያች እለት በኋላ አብደላህ (ረ.ዐ.) የሌሊቱን አብዛኛውን ክፍል ሲሰግድ በማደር ጥቂት ብቻ ያሸልብ ነበር፡፡” (ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ቀጥሎ በሚቀርበው ሐዲስ አል-ቁድስ ምጽዋቶቻቸውን በድብቅ የሚሰጡ፣ በሌሊት ተነስተው የሚሰግዱና በአላህ መንገድ በጽናት የሚጋደሉ ሰዎችን እንዲህ በማለት አወድሰዋቸዋል፡-

“ሶስት ዓይነት ሰዎችን አላህ ይወዳቸዋል፡፡ እንዲሁም ሶስት ዓይነት ሰዎችን ደግሞ ይጠላቸዋል፡፡ አላህ የሚወዳቸው ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡- የመጀመሪያው፡

አንድ ሰው ብዙ ሰዎች ወደ ተሰበሰቡበት ይመጣና ስለሚያውቃቸው ሳይሆን እንዲሁ ለአላህ ብለው ብቻ አንዳች ነገር እንዲሰጡት ይጠይቃቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ሰዎች የሚፈልገውን ነገር ሳይሰጡት ይቀራሉ፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከመካከላቸው ቀስ ብሎ ወደ ኋላ በመውጣት ማንም ሳያውቅበት ይህ ሰው የፈለገውን ነገር ይሰጠዋል፡፡ ይህን ያደረገው በምስጢር ከመሆኑ የተነሣ አላህና ሰውየው ብቻ ናቸው ስለጉዳዩ የሚያውቁት፡፡

ሁለተኛውን ሰው በተመለከተ ሰዎች በቡድን ሆነው ሲጓዙ በማደራቸው በጣም ተዳክመዋል፡፡ ለእነርሱ እንቅልፍን ከማግኘት የበለጠ ተወዳጅ ነገር አንድም አልነበረም፡፡ እናም የሆነ ቦታ ሲደርሱ አረፍ አሉ፡፡ የቀረውን ሌሊት በእንቅልፍ ለማሳለፍ ወስነው ሁሉም ተኙ፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ብቻ ተነስቶ እየሰገደ የእኔን አንቀፆች ያነብባል፡፡

ሶስተኛው ደግሞ በአላህ መንገድ የሚዋጋ ሙጃሂድ ነው፡፡ ከሌሎች ተዋጊዎች ጋር ሆኖ ጠላትን ይገጥማሉ፡፡ ሆኖም ግን ታላቅ የሆነ ሽንፈት ያጋጥማቸዋል፡፡ ሌሎቹ በሙሉ ሲሸሹ ይህ ሰው ብቻ ለመዋጋት

ወስኖ ብቻውን ጠላትን እስኪገደል ወይም ድል እስኪያገኝ ድረስ ይገጥማል፡፡

ከአላህ ዘንድ የተጠሉት ሶስት ሰዎች የሽማግሌ ዝሙተኛ፣ የድሃ ኩራተኛ፣ የሃብታም ግፈኛ (ጨካኝ) ናቸው፡፡›› (ቲርሚዚ፣ ነሳኢ)

አሊ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉት መሠረት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“በጀነት ውስጥ አንድ ቤተመንግስት አለ፡፡ የውጪውን ከውስጥ ሆኖ የሚያሳይና ውስጡን ደግሞ ከውጪ ሆኖ የሚያሳይ ነው፡፡”

ይህን የሰማ አንድ ገጠሬ አእራብ (በድዊን) እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“ይህ ቤተመንግስት ለማን ነው የአላህ መልእክተኛ?” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ፡-

“…ንግግሩን በጥሩና ጣፋጭ በሆነ ሁኔታ ለሚናገር አንደበተ ለስላሳ፣ ሰዎችን መመገብ ለሚወድ፣ አዘውትሮ ለሚፆምና ሰዎች ሁሉ በእንቅልፍ በተያዙበት ጊዜ ለአላህ ብሎ ተነስቶ ለሚሰግድ ሰው፡፡” (ቲርሚዚ)

በጣም የተከበረው የእኛ መምህር ማስተር ሙሣ (አላህ ይዘንለትና) ስለ ታላቁ መሪያችን ሙሐመድ ሳሚ ራማዛኖግሉ ባሕሪ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

“ምንም እንኳን የሙሐመድ ሳሚ ራማዛኖግሉ ፊት ሁልጊዜም በፈገግታ የደመቀ ቢሆንም ልቡ ግን ወደ ውስጡ እንዳነባች ነው፡፡ የሙስሊሙ ኡማ (ሕዝብ) ከጨቋኞች መዳፍ ነጻ እንዲወጣ እንደፀለየና ሁልጊዜም እንዳለቀሰ ነው የኖረው፡፡ ሃጢአተኞችንና መንገድ የሳቱትንም በዱዓው በማሰብ እንባው ሳይፈስላቸው የቀረበት ጊዜ የለም፡፡ ቁርአን ሲነበብ ካዳመጠ በታላቅ አክብሮታዊ ጉጉት የሚከታተል ሲሆን አንዳንድ ጊዜ እንባው እየፈሰሰ በጺሙ ውስጥ ሲሰርግ ይታያል፡፡ ለሐጅ በመካና መዲና መካከል ሲመላለስም የእንባው ነጠብጣቦች እንደሉል እንክብሎች ከዓይኑ እየወደቁ መሬት ሲያርፉ ይታይ ነበር፡፡ ባልደረቦቹ በሙሉ

በእንቅልፍ ዓለም ውስጥ ተውጠው ባሉበት ሰዓት እርሱ ግን ንቃትን ተላብሶ በጠፍ ጨረቃ ፈጣሪውን ሲያስታውስ ላየው የውበቱን መግነጢስ በቃላት ለመግለጽ ከባድ ነበር፡፡”

ሙሳ ቶፐባስ ለሌሊት ሶላት የነበረውን የጋለ ስሜት ያየና የታዘበ ሰው ከጌታው ጋር ለመገናኘት ከፍተኛ ጥማትና ፍቅር ያለው ሰው ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ይህ ፍላጐቱ በህመም ላይ ሆኖና አካሉ በደዌ ተተብትቦ እንኳን የማይበርድ መሆኑ ያስደንቃል፡፡ አንድ ጊዜ የዓይን ቀዶ ጥገና ተደርጐለት ገና የማደንዘዣው ስሜት በቅጡ ሳይጠፋ ከአጠገቡ የነበሩትን ሰዎች እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“አሁን ስንት ሰዓት ነው?” ማስተር ሆይ! ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል፡፡” የሚል መልስ እንዳገኘ እንዲህ አለ፡-

“የሌሊት ሶላትን መስገድ ወሳኝ የሆነበት ሰዓት ነው፡፡” ከዚያም አጠገቡ ባሉት ሰዎች እየተረዳ ተየሙም አድርጐ ልቡን ወደ ፈጣሪው በመመለስ ሁለት ረከዓ ሶላት ሰገደ፡፡ ይህን ያደረገው በታላቅ ጉጉትና በጋለ ፍላጐት ከመሆኑም በላይ ወዲያው ደግሞ አላህን ማስታወስ (ዚክር) ቀጠለ፡፡ ሁኔታውን ያጤነው ሰው የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ እንዲያስታውስ ያደርገዋል፡-

﴿ تَتَجَافَىٰ جُنُوبُهُمْ عَنِ ٱلْمَضَاجِعِ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ خَوْفًا وَطَمَعًا وَمِمَّا رَزَقْنَـٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿١٦﴾ ﴾ السجدة: ١٦

*“ጌታቸውን ለመፍራትና ለመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጐኖቻቸው ከመጋደሚያ ሥፍራዎች ይራራቃሉ፡፡ ከሰጠናቸውም (ፀጋ) ይለግሳሉ፡፡” (አል-ሰጅዳህ፡16)*

አንድ ጊዜ ኢብራሂም ኢብን አድሃም እንዲህ ተባሉ፡-

“በሌሊት ሰዓቶች ተነስቼ ለመስገድ አልቻልኩም፡፡ እባክዎ ምን ባደርግ ይሻለኛል?”

እርሳቸውም እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ፡-

“በቀን ሰዓቶች አላህን አታምጽ፡፡ በሌሊት ሰዓቶች እፊቱ ቆመህ ማርታውን ታገኝ ዘንድ ሁኔታዎችን ያመቻችልሃል፡፡ ከእርሱ ፊት በሌሊት ሰዓታት መቆም መቻል እጅግ የተላቀ የሆነ ክብር ነው፡፡ ኃጢአተኞች ደግሞ ለዚህ ክብር አይበቁም!”

በሌሊት የሚሰገድ ሶላት በጣም ጠቃሚ ነው ሲባል መንፈሳዊውንም ሆነ አካላዊውን ጤንነት ስለሚያጐናጽፍ ነው፡፡ የሌሊት ሶላት በሽታን በማራቅ ከአካላዊና መንፈሳዊ በሽታዎችን ይፈውሳል፡፡ እንዲሁም ብልህነትንና ግርማን ያላብሳል፡፡ የሚከተለው ክስተት ምን ያህል አስጠንቃቂ ነው!

በየርሙክ ጦርነት ሁለቱ ሰራዊቶች እርስበርስ በተፋጠጡ ጊዜ የሮማውያን የጦር አዛዥ የሙስሊሞቹን ሁኔታ በመሰለል አንዳንድ መረጃዎችን ያቀብለው ዘንድ አንድ የአረብ ሰላይ ወደ ሙስሊሞቹ ሰፈር አሰማራ፡፡ ያ ሰላይ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ከሰበሰበ በኋላ ወደሮማውያኑ ሰፈር ሲመለስ የሚከተለው ጥያቄ ቀረበለት፡-

“ሙስሊሞቹ ያሉበት ሁኔታ ምንድን ነው? አሁን ምን በመፈፀም ላይ ይገኛሉ? ያ ሰላይ በዓይኑ በብረቱ ያየውን እንዲህ ሲል ተናዘዘ፡-

بالليل رهبان وبالنهار فرسان

“በሌሊት ሰዓቶች መናኞች በቀን ደግሞ ፈረሰኛ ተዋጊዎች ናቸው፡፡”

ይህን የሰማው የጦር አዛዥ የሚከተለውን ተናገረ፡-

“አሁን አንተ ያልከው እውነት ከሆነ በምድር ገጽ ላይ ሆነን ከእነርሱ ጋር ከምንዋጋ ይልቅ (ሞተን ብናርፈውና) ከምድር ሥር ብንቀበር ይሻል ነበር፡፡”

ቀጥሎ የሚቀርበውም ተመሳሳይ የሆነ ክስተት ነው፡-

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች በጦርነት ጊዜ ማንም አያሸንፏቸውም ነበር፡፡ የሮማውያን ንጉሥ የነበረው ሂረቅል ሠራዊቱ

ከፉኛ ከተደቆሰና ሽንፈትንም ከቀመሰ በኋላ በንዴት እንዲህ በማለት ተዋጊዎቹን ጠየቃቸው፡-

"ለእናንተ አፈርኩ! ከእናንተ ጋር የተዋጉት ሙስሊሞች እንደእናንተው ሰዎች አይደሉምን?"

"እርግጥ ነው ሰዎች ናቸው" አለ።

"መልካም! በቁጥር የምትበልጧቸው እናንተ ናችሁ ወይስ እነርሱ?"

" ከቁጥር አንፃር ከእነርሱ ይልቅ እኛ በብዙ እጅ የበለጥን ነን።" አሉ።

"ታዲያ ሁልጊዜም ከእነርሱ ጋር ስትጋጠሙ በየጊዜው አስደንጋጭ ሽንፈት የሚገጥማችሁ ለምንድን ነው?" በዚህ ጊዜ ከሮማውያኑ ውስጥ አንድ ብልህ የሆኑ አረጋዊ ሰው ከመቀመጫቸው ተነሱና እንዲህ የሚል ማጠቃለያ ሰጡ፡-

"ክቡር ሆይ! እነዚያ ሰዎች ሌሊታቸውን የሚያሳልፉት ፈጣሪያቸውን በማምለክ ሲሆን ቀን ቀን ደግሞ ጿሚዎች ናቸው። ቃል ኪዳናቸውን አያፈርሱም፣ መልካም ነገርን ለመፈጸምና እኩይ ምግባርን ለማስወገድ እርስበርሳቸው ይረዳዳሉ። ልናሸንፋቸው ያልቻልንበቱ ምስጢር ይህ እንጂ ሌላ አይደለም።"

ይህን የሰማው ሂረቅል እንዲህ አለ፡-

"አንተ እውነቱን ተናግረሃል።"[1]

ለማጠቃለል የሌሊት ሶላት አእምሮን፣ መንፈስንና ልብን ለማስማማት ግንዛቤን፣ ስሜትንና የማስታወስ ኃይልን ለማስላት በጣም ምቹና ተመራጭ ነው። በአካልም ሆነ በመንፈስ ለመጠንከር የሚሻ ሰው የሌሊት ሶላትን ያዘውትር። አላህ ይህን ሁሉ በማወቁ ነው በቁርአን እንደሚከተለው በማለት የሌሊት ሶላትን ትሩፋት (ፈዷኢል) የሚገልጸው

---

[1] ኢብን አሳኪር ታሪኹ ዲመሽቅ

﴿ إِنَّ نَاشِئَةَ ٱلَّيۡلِ هِيَ أَشَدُّ وَطۡـٔٗا وَأَقۡوَمُ قِيلًا ۝٦ ﴾ المزمل: ٦

*“የሌሊት መነሳት እርሷ (ሕዋሳትንና ልብን) ለማስማማት በጣም ብርቱ ናት፡፡ ለማንበብም ትክክለኛ ናት፡፡” (አል-ሙዘሚል፡6)*

ብዙ የአላህ ባሮች በቀን ለሚጠብቃቸው ታላቅ ተልእኮ መንፈሳዊ ኃይልን የሚሞሉትና ብርታትን የሚስሰነቁት በሌሊቱ ሰዓታቸው ነው፡፡ የሌሊትን ሶላት ሳይሰግድና ከዓለማት ጌታ አላህ ጋር በምስጢር ሳያንሾካሹክ የተዋጣለት የሙስሊሞች መሪ መሆን የቻለ ሰው አልታየም በታሪክ ገፆችም ላይ ስሙ አልሰፈረም፡፡

እውነተኛው የሌሊት ሶላት ምስጢር የሚገለጽላቸው እነዚያ በሃቅ የተመሩና የአላህ ወዳጅ ለመሆን የወሰኑ ሲሆኑ ሌሊታቸውን በቁርዓንና በሶላት በማስጌጥ ጠባያቸው ይታወቃሉ፡፡

## መ. ሶላትና ዱዓ (ፀሎት)

አንድ ባሪያ ከአላህ ፊት ሲቆም የአላህን ጽንፍ አልባ ኃያልነት፣ ግርማዊነትና ታላቅነት፣ እንዲሁም የራሱንም ኢምንትነት ማረጋገጥና መቀበል ይኖርበታል፡፡ ከዚያም በሙሉ ተመስጦና ትህትና የአላህን እርዳታና ከእርሱ የሚከጅለውን ማንኛውንም ዓለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ጉዳይ ያቀርባል፡፡ ይህ ነው እንግዲህ ሶላትና ዱዓ የሚባለው፡፡

ዱዓ (ፀሎት) በኃይማኖታችን ውስጥ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን የእኛን የሰው ልጆችን ደካማነትና ረዳት የለሽነት በመለኮታዊው ችሎት ፊት የማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡

አንድ ባሪያ ጉዳዮቹን ይፈጽምለት ዘንድ ወደ ኃያሉ አላህ ፊት ይዞ ሲቀርብ ከቃላት ማነብነብ ባለፈ ልባዊ በመሆንና ጽሞናን ፍጹም ወደ አላህ በማዞር መሆን አለበት፡፡ ይህም ሲሆን ሁልጊዜም ቢሆን አላህን በመፍራትና ምህረቱንም ተስፋ በማድረግ መካከል መሆን የግድ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው አላህ ኃጢአቱን እንዲምረው ከፈለገ በዱዓው (ልመናው) ውስጥ ሙሉ ትኩረት ማድረጉንና ጉዳዩን በሙሉ ልቡ

ለፈጣሪው ማቅረቡን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በፀፀት የተቃጠለ ልብና እንባ የሚያወርዱ ዓይኖች የፈጣሪን ትኩረት የማግኘት እድላቸው ሰፊ ነውና፡፡

በሁሉም አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች አንድ አማኝ የአላህ ባሪያ መሆኑን ከሚያረጋግጥባቸው መስፈርቶች አንዱ ሁልጊዜም እርሱን መለመን መቻሉ ነው፡፡ ባሪያ የመሆን ምስጢሩና የእውነተኛ አምልኮት አስኳል የሚገኘውም አላህን በተከታታይና በዘውታሪነት በመለመን ነው፡፡ ምክንያቱም ሶላትና ዱዓ ወደ አላህ የሚወስዱ ወሳኝ መንፈሳዊ መንገዶች ናቸውና፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِى عَنِّى فَإِنِّى قَرِيبٌ ۖ أُجِيبُ دَعْوَةَ ٱلدَّاعِ إِذَا دَعَانِ ۖ فَلْيَسْتَجِيبُوا۟ لِى وَلْيُؤْمِنُوا۟ بِى لَعَلَّهُمْ يَرْشُدُونَ ﴿١٨٦﴾ ﴾ البقرة: ١٨٦

"ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፡-*"እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ ስለዚህ ለእኔ ይታዘዙ በእኔም ይመኑ እነርሱ ሊምመሩ ይከጀላልና፡፡" (አል-በቀራህ፡186)*

ዱዓ በሚደጋገምበት ጊዜ በአንድ አማኝ መንፈስ ውስጥ ይቀረጻል፡፡ ከዚያም አንዳች ዓለማዊ ወይም መንፈሳዊ እክል ሲገጥመው ያንን በሰገባ ውስጥ እየተቀመጠ የተሳለ ሰይፍ በሕሊናው ማኅደር ቅርጽና መልክ ይዞ የተቀረፀ ዱዓ በማውጣት ሥራ ላይ ያውለዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከሶላታቸው በተጨማሪ እንባቸውን እያፈሰሱና ተረከዛቸው እስኪያብጥ ድረስ አላህን በጽኑ ይማፀኑትና ይለምኑት ነበር፡፡ አጭርና ልባዊ የሆነን ልመና (ዱዓ) የመውደዳቸውን ያክል ከልብ ያልሆነን ማነብነብ ይጠሉ ነበር፡፡ ተከታዮቻቸውንም እንደሚከተለው በማለት ይመክሩሉ፡-

"ባሪያው ወደ ጌታው ይበልጥ ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ ሱጁድ ባደረጋችሁበት ጊዜ ብዙ የምትፈልጉትን ነገር አላህ ያሳካላችሁ ዘንድ ለምኑት፡፡" (ሙስሊም)

አንድ አማኝ ሁልጊዜም በፀሎትና አላህን በመለመን (በዱዓ) መትጋት የሚገባው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በእምነት ወንድሙ የሆነ ሰውም ዱዓ እንዲያደርግለት መጠየቅ ይኖርበታል። ይህ ሰው ምናልባትም ድሃ፣ ደካማ ወይም ችግረኛ ቢሆን እንኳን አላህ የእርሱን ልመና ሊሰማው ይችላል። ምክንያቱም የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"አንድ ሙስሊም ለሌላው ወንድሙ በሌለበት ከሚያደርግለት የበለጠ በፍጥነት ተቀባይነትን የሚያገኝ ዱዓ የለም።" (ቲርሚዚ)

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ጊዜ እንዲህ አሉ፡-

"ሙስሊም ሰው አላህን አንዳች ነገር ከጠየቀ የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ የፈለገውን ነገር ይሰጠዋል ወይም ደግሞ ሊሰጠው በነበረው መልካም ነገር ተመጣጣኝ የሆነ መጥፎ ነገርን ያስወግድለታል። ይህም የሚሆነው ሰውየው የጠየቀው የተከለከለን (ሐራም) ነገር ካልሆነና ዝምድናንም ካልቆረጠ ነው።"

ይህን ያዳመጠ አንድ ባልደረባቸው እንዲህ አለ፡-

"እንደዚያ ከሆነ አላህ ብዙ ነገሮችን እንዲሰጠን እንፈልጋለን። የአላህ መልእክተኛ!"

"የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መለሱ፡-

"የአላህ ፀጋ እናንተ ከምትጠይቁት ነገር ሁሉ በላጭ ነው።" (ቲርሚዚ)

ኃያሉ አላህ ከልብ (በኢኽላስ) የተደረገን ዱዓ ውድቅ አያደርግም። ይሁን እንጂ የተወሰኑ ጉዳዮች ከእርሱ ቅድመ ውሳኔ (ቀደር) ጋር የማይሄዱ ከሆኑ ምንም እንኳን በልባዊነት (ኢኽላስ) የተጠየቁ ቢሆንም ለጊዜው ላይቀበላቸው ይችላል። እንደዚያም ቢሆን የአላህ አገልጋይ የሆነ ባሪያ ምን ጊዜም ቢሆን ተስፋ መቁረጥና እጆቹን ወደ ፈጣሪው ከመዘርጋት መገታት የለበትም። ምክንያቱ በእንዲህ ዓይነት ጊዜ የሚደረግ ዱዓ

ለመጪው ዓለም ከመልካም ሥራ ክምችት ውስጥ ገብቶ ይቀመጣልና፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ አለ፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ يُؤۡتُونَ مَآ ءَاتَواْ وَّقُلُوبُهُمۡ وَجِلَةٌ أَنَّهُمۡ إِلَىٰ رَبِّهِمۡ رَٰجِعُونَ ٦٠ ﴾ المؤمنون: ٦٠

*“ጌታችሁም አለ፡- ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሃነምን በእርግጥ ይገባታል፡፡” (አል-ሙእሚን:60)*

የአላህ ነቢይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“አንድ ባሪያ ወደ ኃጢአት የሚወስደውን ነገር እስካልጠየቀ፣ ዝምድናውን እስካልቆረጠና ውጤቱን ለማየት እስካልቸኮለ ድረስ ዱዓው (ልመናው) ተቀባይነት ሳያገኝ አይቀርም፡፡”

በዚህ ጊዜ እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሆይ፣ ችኮላ ማለት ምንድን ነው?” እንዲህ አሉ፡-

“ባሪያው ይላል፡- “ዱዓ አደርጋለሁ ሆኖም ግን ዱዓዬ ተቀባይነት አላገኘም፡፡” ይህን ካለ በኋላ ዱዓ ማድረጉን ያቆማል፤ ምክንያቱም ወዲያው ተቀባይነት ስላላገኘ፡፡ (ይህ ነው ችኮላ ማለት፡፡) (ሙስሊም)

በተመሳሳይ ሁኔታ ነቢዩ ዘከሪያ (ዐ.ሰ.) እንዲህ በማለት አላህን ለምነዋል፡-

﴿ وَزَكَرِيَّآ إِذۡ نَادَىٰ رَبَّهُۥ رَبِّ لَا تَذَرۡنِي فَرۡدٗا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلۡوَٰرِثِينَ ٨٩ ﴾

*“ዘካሪያም ጌታዬ ሆይ! ብቻዬን አትተወኝ፤ አንተም ከወራሾች ሁሉ በላጭ ነህ ሲል ጌታውን በተጣራ ጊዜ (አስታውስ)፡፡” (አል-አንቢያ:89)*

ይህን የተናገሩት ሃይማኖታቸውን የሚያጠናክር ልጅ እንዲሰጣቸው አላህን በተማፀኑበት ጊዜ ነበር፡፡ ያንን ልመናቸውን የተቀበለው አላህ

ያህያ የሚባል ምርጥ የአላህ ባሪያና ነቢይ በመስጠት ለጥያቄያቸው መልስ ሰጥቷል፡፡

አንድ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው በእርሳቸው ላይ መጀመሪያ ሰለዋትና ሰላምታ ሳያወርድ ዱዓ ሲያደርግ አዩትና እንዲህ አሉ፡-

“ይህ ሰው ትዕግስት የለውም፡፡” ከዚያም ያንን ሰው ጠሩትና ለመላው ሕዝባቸው የሚሆን ማስገንዘቢያ እንዲህ በማለት ሰጡ፡-

“ከእናንተ አንዳችሁ ዱዓ ሲያደርግ በመጀመሪያ አላህን ያመስግን፡፡ ከዚያም በእኔ ላይ ሶለዋትና ሰላምታን ካወረደብኝ በኋላ ሚፈልገውን ነገር ይጠይቅ፡፡” (ቲርሚዚ)

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)፡- ‹‹አንድ አማኝ ሰው የኃይማኖት ወንድሙ ለሆነ ሰው እርሱ ባለበት ወይም እርሱ በሌለበት ዱዓ ያድርግለት›› በማለት መክረዋል፡፡ ኡመር (ረ.ዐ.) ኡምራ ለማድረግ ፈቃድ ይሰጧቸው ዘንድ ሲጠይቋቸው እንዲህ አሏቸው፡-

“ወንድሜ ሆይ! በዱዓህ ውስጥ ጨምረን፡፡ የእኛን ነገር እንዳትዘነጋው፡” (ቲርሚዚ)

ኡመር (ረ.ዐ.) እነዚህን ቃላት ከክቡሩ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) አፍ እንደሰሙ ምን እንደተሰማቸው እንዲህ በማለት ተናገሩ፡-

“መላውን ዓለም ቢሰጡኝ እንኳ እነዚህን ቃላት ስሰማ ካደረብኝ ደስታ የበለጠ አልደሰትም፡፡” (አቡ-ዳውድ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ ሙስሊም በኃይማኖት ወንድሙ ለሆነ ሰው እርሱ በሌለበት ዱዓ ቢያደርግለት ተቀባይነት ያገኛል፡፡ አንድ ሰው ለወንድሙ ዱዓ ባደረገ ቁጥ መልአክ ከጐኑ ይሆንና ለእርሱ እንዲህ እያለ ዱዓ ያደርግለታል፡- “አላህ ያንተንም ዱዓ ይቀበልህ፤ ተመሳሳዩንም ነገር ላንተ ይስጥህ፡፡” (ሙስሊም፣ ኢብኑ ማጀህ)

ስለሆነም እኛ ሁላችን በእምነት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለሆኑት ሁሉ አላህ የዚህንም ሆነ የመጪውን ዓለም መልካም ነገር እንዲለግሳቸው ልንለምንላቸው ይገባናል ማለት ነው።

በዚህች ጠፊ ዓለም ከሁሉም ነገር በላይ ሊኖረን የሚገባው ነገር ተቅዋ (የአላህ ፍራቻ) ነው። ይህን ተቅዋ እንዲሰጠንም ነው በሶላታችን ላይ ሁልጊዜም አላህን የምንጠይቀው። አንድ ሰው ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና እንዲህ አላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ ወደ አንድ ቦታ ልጓዝ ፈልጌያለሁ፤ ዱዓ ያድርጉልኝ።”

እርሳቸውም እንዲህ አሉት፡-

“አላህ ተቅዋ ይስጥህ።” ሰውዬውም “ሌላ ነገርም ይጨምሩልኝ የአላህ መልክተኛ!” አለ።

“አላህ ኃጢአትህን ይማርህ!” አሁንም ይህ ባልደረባቸው እንዲህ አለ፡-

“እናትና አባቴ መስዋእት ይሁኑልዎና አሁንም ይጨምሩልኝ የአላህ መልክተኛ!”

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ የትም ቦታ ብትሆን መልካም ነገርን ለመሥራት ያግራልህ።” (ቲርሙዚ)

አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተሉትን የነቢዩላህ ኢብራሂምን (ዐ.ሰ.) ቃላትና የነቢዩ ዒሣን (ዐ.ሰ.) ዱዓ (ፀሎት) እንዲህ በማለት አነበቡ፡-

“ጌታዬ ሆይ! እነርሱ (ጣኦታት) ከሰዎች ብዙዎችን አሳስተዋልና የተከተለኝም ሰው እርሱ ከእኔ ነው….” (ኢብራሂም፡36)

“ብትቀጣቸው እነርሱ ባሮችህ ናቸው። ብትምራቸውም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ።” (አል-ማኢዳህ፡118)

ከዚያ በኋላ እጆቻቸውን ወደ ላይ አንስተው እያለቀሱ አቤቱታቸውን ለአላህ እንዲህ በማለት አቀረቡ፡-

"አላህ ሆይ! ሕዝቤን (ኡማዬን) ጠብቅልኝ፣ በእነርሱም ላይ እዝነትህን አውርድ።" በዚህ ጊዜ ኃያሉ አላህ እንዲህ አለ፡-

"ጂብሪል ሆይ! ጌታህ ሁሉንም ነገር ጠንቅቆ የሚያውቅ ቢሆንም (ሰዎች ይገነዘቡ ዘንዳ) ወደ ሙሐመድ ሂድና ለምን እንደሚያለቅስ ጠይቀው።"

ጂብሪል (ዐ.ሰ.) ወደ አላህ መልእክተኛ ሲሄድ የሚያለቅሱት የተከታዮቻቸው ሁኔታ አስጨንቋቸው መሆኑን ገለጹለት። ጂብሪል ይህንን ዜና ይዞ ወደላቀው ጌታ ወደ አላህ ሲሄድ እንዲህ አለው፡-

"ጂብሪል ሆይ! ወደ ሙሐመድ ሂድና መልካሙን ዜና ንገረው፤ ተከታዮችህን በተመለከተ አንተን ከምናስደስትህ በስተቀር ሃዘን ፈጽሞ አይነካህም።" (ሙስሊም)

እንግዲህ የእኛ ነቢይ ለተከታዮቻቸው ይህን ያክል አዛኝና ሩህሩህ ነበሩ። ስለዚህ እርሳቸው ላሳዩን ፍቅርና ርህራሄ እኛ የምናሳያቸው አፀፋ ምን ይመስላል? ይህን ሐዲስ በአንክሮ እያስተነተን ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ጥያቄዎች አሉ። ምን ያህሉን የእርሳቸውን ሱና (ፈለገ ሕይወት) ተከትለናል? ምን ያህሉንስ ባሕሪያቸውን ወርሰናል?

በአንድ ወቅት ሰዎች ዝናብ እንዳጡ በማማረር ለተወዳጁ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) አቤት አሉ። በዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሚንበር (የመስበኪያ ሰገነት) እንዲዘጋጅላቸው ጠየቁ። የጠየቁት ነገር ዘወትር የኢድና የጀናዛ ሶላት በሚሰገድበት ቦታ ላይ ተዘጋጀለቸው። እዚያ ቦታ ላይ ሰዎች የሚሰበሰቡበት ቀን ተወሰነ። ፀሃይዋ ከአድማሱ ላይ ቀይ መሆን ስትጀምር ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከመስገጃው ቦታ ደረሱና ሚንበሩ ላይ ወጡ። ከዚያም ተክቢር (አላሁ አክበር) ካሉ በኋላ አላህን አመስግነው የሚከተለውን ተናገሩ፡-

"ሃገራችሁ በድርቅ እንደተጠቃ፣ እንዲሁም ዝናብ በተለመደው ጊዜ እንዳልዘነበና እንደዘገየም ተናግራችኋል። አላህ (ጥራትና ልእልና

ይገባውና) እርሱን እንድትለምኑት አዟችኋል፡፡ ልመናችሁንም እንደሚቀበል ቃል ገብቷል፡፡" ካሉ በኋላ የሚከተለውን ዱዓ አደረጉ፡-

"ምስጋና የሚገባው ለዓለማት ሁሉ ጌታ ነው፡፡ እርሱ እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ ነው፡፡ የፍርዱ ቀን ባለቤት ነው፡፡ ከአላህ በስተቀር ጌታ የለም፡፡ እርሱ የሻውን የሚሰራ ጌታ ነው፡፡ አንተ ጠባቂያችን ሆይ! አንተ አላህ ነህ፡፡ ከአንተም ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንተ ባለፀጋ ነህ፡፡ እኛ ደግሞ ድሃ ነን፡፡ ዝናብ በእኛ ላይ እንዲዘንብ አድርግ፡፡ የምትሰጠንንም ዝናብ ለእኛ ጥንካሬና ጉልበት የሚያላብሰን አድርገው፡፡ ዘላቂና ዘውታሪም አድገው፡፡"

ይህን ካሉ በኋላ እጃቸውን ወደ ላይ አነሱ፡፡ እጆቻቸውን በጣም ከፍ ከማድረጋቸው የተነሣ የብብታቸው ነጩ ክፍል ይታይ ነበር፡፡ ከዚያም ጀርባቸውን ወደሰዎች አዞሩ፡፡ ይህን ሲያደርጉ እጃቸው አሁንም ወደ ላይ እንደተዘረጋ ነበር፡፡ ከዚያም ፊታቸውን ወደ ሰዎች አዞሩ፡፡ በመጨረሻም ከሚንበራቸው ላይ ወርደው ሁለት ረክዓ ሶላት ሰገዱ፡፡ የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ ወዲያውኑ ዳመናዎችን ላከ፡፡ ዳመናው በጉርምርምታና በመብረቅ እየታገዘ ሰማዩን ይገምሰው ጀመር፡፡ በአላህ ፈቃድም ብዙም ሳይቆይ መዝነብ ጀመረ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደመስጊዳቸው የመመለስ እድል እንኳን ሳያገኙ ከሰማይ ላይ እንደጉድ ይቀዳው ጀመር፡ ፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለሶላት የወጣው ሕዝብ ዝናብ ሸሽቶ ሲሮጥ ተመልክተው ፈገግ ካሉ በኋላ እንዲህ አሉ፡-

"አላህ የፈለገውን ነገር ለመስራት እንደሚችል፣ እንዲሁም እኔ ባሪያውና የአላህ መልእክተኛ መሆኔን እመሰክራለሁ፡፡" (አቡዳውድ)

ሰዎች ዝናብን በመከጀላቸው ከላይ በተመለከትነው ሁኔታ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዱዓ ወዲያው ተቀባይነት አግኝቶ ሊዘንብ ችሏል፡፡ ከዚያን ጊዜም አንስቶ ዝናብ ሲጠፋና ድርቅ ሲያይል ይህን ሱና በመከተል አላህን መለመን ተገቢ መሆኑ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቷል፡፡

የነቢዩ ባለቤት ዓኢሻ (ረ.ዐ.) እንዲህ ትላለች፡-

“አንድ ሌሊት ከእንቅልፌ ስነቃ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከጐኔ እንደሌሉ አረጋገጥኩ፡፡ ምናልባት ሌላዋ ሚስታቸው ጋር ሄደው ይሆናል ስልም አሰብኩ፡፡ ዙሪያውን በእጄ እየዳበስኩ መኖራቸውን ለማረጋገጥ ስሞክር እጄ እግራቸውን ነካ፡፡ በዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሱጁድ ላይ መሆናቸውን አወቅኩ፡፡ ከዚያም እያለቀሱ እንደሚከተለው በማለት አላህን ሲማፀኑ ሰማሁ፡፡

“አላህ ሆይ! ከቁጣህ ታርቀኝ ዘንድ ወዳንተ እጠጋለሁ፡፡ ከቅጣትህም አመልጥ ዘንድ ይቅርታህን እሻለሁ፡፡ አላህ ሆይ! አንተኑ ፈርቼ ወዳንተ እንጂ ወደ ሌላ ወደማንም አልሸሽም፡፡ እንደሚገባህ አድርጌም ላመሰግንህ አልችልም፡፡ አንተ በእርግጥም ራስህን እንዳመሰገንከው ነህና!” (ሙስሊም፣ ቲርሚዚ)

ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“በበድር ቀን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የቁረይሽ አጋሪዎችን ሲመለከቱ ወደ አንድ ሺህ የሚጠጋ ቁጥር ነበራቸው፡፡ የእርሳቸው ተዋጊዎች ግን ሶስት መቶ አሥራ ሶስት ብቻ ነበሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ወዲያው ፊታቸውን ወደ ካዕባ (ቂብላ) አዙረው እጆቻቸውን ወደ ላይ በማንሳትና ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ የሚከተለውን ተማጽኖ አቀረቡ፡-

“አላህ ሆይ! ቃል ኪዳን የገባህልኝን ፈጽምልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ድልን አቀዳጀኝ፡፡ አላህ ሆይ! ይህችን የሙስሊም ሰራዊት ካጠፋሃት በምድር ገጽ ላይ አንተን ብቻ የሚያመልክ አንድም ሰው አይኖርም፡፡”

በዚህ ሁኔታ እጆቻቸውን ወደ ላይ እንዳደረጉ ከትከሻቸው ላይ መጐናፀፊያቸው እስኪወድቅ ድረስ ልመናቸውን ቀጠሉ፡፡ ይህን ያስተዋሉት አቡበከር (ረ.ዐ.) ወደርሳቸው በመሄድ መጐናፀፊያቸውን መልሰው ካለበሷቸው በኋላ እንዲህ አሉ፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ለአላህ ያቀረቡት ልመና በቂ ነው፡፡ ልቅና የተገባው ጌታ በእርግጠኝነት ቃል የገባልዎትን ይፈጽምልዎታል፡፡”

በዚያው ቅጽበት ልቅና የተገባው ጌታ እንዲሁም ክቡሩና ልዑሉ ጌታ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አወረደ፡-

﴿ إِذۡ تَسۡتَغِيثُونَ رَبَّكُمۡ فَٱسۡتَجَابَ لَكُمۡ أَنِّي مُمِدُّكُم بِأَلۡفٖ مِّنَ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ مُرۡدِفِينَ ٩ ﴾ الأنفال: ٩

*“ከጌታችሁ እርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ እኔ በሺህ መላእክት ተከታታዮች ሲሆኑ እረዳችኋለሁ ሲል ለእናንተ የተቀበላችሁን (አስታውቅ)፡፡” (አል-አንፋል:9)*

በዚያ እለት አላህ ቃል ኪዳኑን በመሙላት ምእመናንን ለመርዳት መላእክትን አወረደ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

አቡ ማሊክ (ረ.ዐ.) የሚባልና ከሰዎች ጋር በጋራ የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ሶሃባ ነበር፡፡ ይህ ሰው ታማኝና አላህን የሚፈራም ነበር፡፡ በአንድ ወቅት በጉዞ ላይ እያለ አንድ ቀማኛ መንገዱን ቆረጠበትና እንዲህ አለው፡-

“ያለህን ነገር ሁሉ አምጣ፡፡ ከዚያም እገድልሃለሁ፡፡”

“የምትፈልገው ገንዘቤን ከሆነ መውሰድ ትችላለህ፡፡” አለ አቡ ማሊክ፡፡

“እኔ የምፈልገው አንተን መግደል ነው፡፡” አለ ቀማኛው፡፡ በዚህ ጊዜ አቡ ማሊክ (ረ.ዐ.) “እንደዚያ ከሆነ እንድሰግድ ብቻ ፍቀድልኝ፡፡” አለው፡፡

“የፈለግኸውን ያክል መስገድ ትችላለህ፡፡” አለ ቀማኛው፡፡ ሶላቱን ሰግዶ ከጨረሰ በኋላ አቡ ማሊክ የሚከተለውን ዱዓ አደረገ፡-

“አንተ በልቦች ዘንድ የተወደድከው ሆይ! አንተ የታላቁ አርሽ ጌታ ሆይ! አንተ ያ የፈለግከውን የምትሰራ ሆይ! በተባረከውና ማንም በማይወዳደረው ክብርህ እንዲሁም በማይለካው ንግሥናህና ዙፋንህን በሸፈነው ብርሃንህ ከዚህ መጥፎ ቀማኛ ሰው ታድነኝ ዘንድ እጠይቅሃለሁ፡፡ በእርዳታህ ለሁሉም ደራሽ የሆንከው አላህ ሆይ! እባክህን እርዳኝ፡፡”

አቡ ማሊክ (ረ.ዐ.) ይህንን ተማጽኖ ለሶስት ጊዜ ያክል ደጋገመው። ልክ ዱዓውን እንደጨረሰ በእጁ ጦር የጨበጠ ፈረሰኛ ሰው በብርሃን ፍጥነት ከመጣ በኋላ ያንን ቀማኛ ገደለው። በአላህ እዝነት ከመሞት የተረፈው አቡ ማሊክ ፈረሰኛውን እንዲህ አለው፡-

"እኔን እንድትረዳኝ አላህ የላከህ ከቶ አንተ ማን ነህ?"

ፈረሰኛው እንዲህ በማለት መልስ ሰጠው፡-

"እኔ በሰማይ ካሉት የጌታህ ሰራዊቶች መካከል በአራተኛው ሰማይ ላይ የምገኝ መልአክ ነኝ። የመጀመሪያውን ዱዓህን ስታደርግ የሰማያት ደጃፎች ሲሰነጣጠቁ ሰማሁ። በሁለተኛው ዱዓህ የሰማያት ተቀማጮችን ጩኸት ሰማሁ። ሶስተኛውን ተማጽኖህን ስታቀርብ እንዲህ ተባለ "አንድ ችግር የደረሰበት ሰው እርዳታ ይሻል!" ይህን እንደሰማሁ ይህን ዘራፊ እገድለው ዘንድ እንዲልከኝ አላህን ለመንኩት። የልቅናው ጌታ አላህ ፈቀደልኝና መጣሁ። አንድ ማወቅ ያለብህ ማንም ሰው ውዱእ አድርጎ አራት ረከዓ ሶላቶችን ከሰገደ በኋላ ይህን ዱዓ ቢያደርግ በችግር ላይ ቢሆንም ባይሆንም ዱዓው ተቀባይነት ያገኛል።" (ኢብኑ ሐጀር)

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባለቤት የነበሩት ኡሙ ሰለማህ (ረ.ዐ.) እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፡-

"የምእመናን እናት ሆይ! የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከእርስዎ ጋር በሚሆኑበት ጊዜ የሚያዘወትሩት የትኛውን ዱዓ ነው?" ኡሙ ሰለማህ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ፡-

"አላህ ሆይ! አንተ ልቦችን የምትለዋውጠው ጌታ ልቤን (ቀልቤን) በአንተ ኃይማኖት እንዲረጋ አድርግልኝ።" (ቲርሙዚ፣ አህመድ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሕዝባቸውን ወደ እውነተኛው ጎዳና እንዲመራላቸው ብዙ ጊዜ ዱዓ ያደርጉ ነበር። ለአብነት ያክል ለየመን ሕዝቦች የሚከተለውን ዱዓ አድርገዋል፡-

"አላህ ሆይ! ልቦቻቸውን ወደእኛ አዙራቸው።" (ቲርሚዚ)

የጧኢፍ ሰዎች ከከተማቸው ያባረሯቸው ሲሆን በድንጋይ ወግረዋቸዋል፣ የቻሉትን ስድብና በደል ሁሉ አድርገውባቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላም ቢሆን እስከ 9ኛው ዓመተ ሂጅራ ድረስ ሙስሊሞችን በጽኑ ሲከላከሉና ሲያጠቁም ኖረዋል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ሩህሩህ የሆኑት ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) አላህ ለጧኢፍ ሕዝቦች መልካም ነገር እንዲያመጣላቸው እንዲህ እያሉ ይጠይቁ ነበር፡-

"ጌታዬ ሆይ! ሰቂፍን ወደ ቀናው መንገድ ምራት፡፡ ወደእኛ እንዲመጡም አድርጋቸው፡፡"

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አሊን ቃዲ (ዳኛ) አድርገው ወደ የመን ሲልኳቸው በአጐታቸው ልጅ ደረት ላይ በጉጉት እጃቸውን ካስቀመጡ በኋላ የተጣለባቸውን ከባድ ኃላፊነትና ሸክም እያሰቡ የሚከተለውን ዱዓ አደረጉላቸው፡-

"አላህ ሆይ! ልቡን ወደ ሃቅ ምራው፡፡ እንዲሁም ምላሱንም በሃቅ ላይ እንዲፀና አድርገው፡፡"

ዓሊ (ረ.ዐ.) ከጊዜ በኋላ እንዲህ አሉ፡-

"ከዚያ ዱዓ በኋላ በሁለት ሰዎች መካከል አልፈረድኩም፣ ምንም ዓይነት ማመንታት የማይታይብኝ ሆኜ ቢሆን እንጂ፡፡" (ኢብኑ ማጀህ)

በታላቁ ሐጅ መጠናቀቂያ ላይ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ እጃቸውን ከግመላቸው ላይ ሌላኛውን እጃቸውን ደግሞ ከፍ አድርገው ባርነታቸውንና የልባቸውን ረቂቅነት አጉልቶ ያሳየውን ቀጣዩን ረዥም ዱዓ አደረጉ፡፡ የዱዓው የተወሰነው ክፍል ከዚህ በታች ቀርቧል፡-

"አላህ ሆይ! አንተ ራስህን እንዳመሰገንከውና እኛም ምንግዜም ፈጽሞ ልናመሰግንህ በማንችልበት መንገድ የተመሰገንክ ነህ፡፡ አላህ ሆይ ! ሶላቴ፣ አምልኮቴ፣ ሕይወቴም ሆነ ሞቴ የዓለማት ጌታ ለሆንከው ላንተ ነው፡፡ የምመለሰውም ወዳንተ ብቻ ነው፡፡

አላህ ሆይ! ከመቃብር ስቃይ እጠበቅ ዘንድ ወዳንተ እጠጋለሁ፡፡ ልብን ከሚያጥለቀልቀው የሰይጣን ጉትጐታ እንዲሁም ጉዳዮቼን ሁሉ ላንተው

እተዋለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ኃያል አውሎ ነፋስ ከሚያመጣው አስከፊ ውድመት ባንተው እጠበቃለሁ፡፡

አላህ ሆይ! ለዓይኖቼ፣ ለጆሮዎቼና ለልቤ ብርሃንን አድርግልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ከጤነኝነት ወደ ድውይነት አልረማመድ ዘንድ፣ በድንገት የሚይዝ ከሆነው ከቅጣትህ ነጻ እሆን ዘንድም ከቁጣህም እተርፍ ዘንድ አንተኑ እማፀናለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ወደ ቀናው መንገድህ ምራኝ፡፡ ያለፈውንም ሆነ መጪውን ሃጢአቴን ማረኝ፡፡

የሰማያትና የምድር ፈጣሪ የሆንከው አላህ ሆይ! በደረጃዎች ከፍ የምታደርገው፣ ፀጋዎችንም የምታጐናጽፈው በእርግጥ አንተ ነህ፡፡

አላህ ሆይ! ንግግሬን ታዳምጣምለህ፡፡ የት እንዳለሁም ታያለህ፡፡ እኔን የሚመለከት ግልጽም ሆነ ስውር የሆነውን ነገር ሁሉ ታውቃለህ፡፡ ከእኔ ጉዳይ ላንተ የሚሰወርብህ አንዳች ነገር የለም፡፡ እኔም ረዳት የለሽና ድሃ ነኝ፡፡ ትረዳኝና ታዝንልኝ ዘንድ እማፀንሃለሁ፡፡ እኔ ስህተቴን እቀበላለሁ፡፡ ጠባቂዬ ሆይ! ለፀሎቴ መልስ እንዳትነፍገኝ፡፡ ለእኔም ደግና ሩህሩህ ሁንልኝ፡፡ አንተ ከሚልለመኑት ሁሉ ምርጡና ከሰጭዎች ሁሉ በላጬ ሆይ፡፡"[1]

አቡ ኡማማ (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ፡-

"የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ብዙ ዓይነት ዱዓዎችን አንብበውልናል፡፡ ይሁን እንጂ እኛ ልናስታውሳቸው አልቻልንም፡፡ አንድ እለት እንዲህ አልናቸው፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እርስዎ በዙ ዓይነት ዱዓዎችን አነበቡልን፡፡

ይሁን እንጂ እኛ ሁሉንም በቃላችን ልንይዛቸው አልቻልንም፡፡" በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

---

[1] የኢብን ከሲር አል-ቢዳያን እንዲሁም የኢብን ቀይም ዛዱል መዓድን ተመልከት፡፡

“እነዚያን ሁሉ ዱዓዎች የሚያጠቃልል የሆነን ዱዓ አልነግራችሁምን? እንዲህ በሉ፡- “አላህ ሆይ! እኛ ነቢይህ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) የጠየቁህን መልካም ነገሮች ሁሉ ትሰጠን ዘንድ እንጠይቅሃለን፡፡ እንዲሁም ነቢይህ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እነድትጠብቃቸው ከጠየቁህ መጥፎ ነገሮች ሁሉ ትጠብቀን ዘንድ እንጠይቅሃለን፡፡ እርዳታ ሲጠየቅ መስጠት የሚችል ብቸኛው ጌታ አንተ ነህና፡፡ የሰው ልጅ በዚህችም ሆነ በመጪው ዓለም የፈለገውን እንዲያገኝ ማድረግ የምትችለውም አንተ ብቻ ነህና፡፡ ሃጢአትን ለማስወገድ ጥንካሬ ያለው እንዲሁም አምልኮት የሚገባው ከአላህ በስተቀር አንድም የለም፡፡”

አነስ (ረ.ዐ.) የሚከተለውን አስተላልፈዋል፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ጊዜ በህመም ምክንያት ብዙ ክብደት የቀነሰን ሰው ከጠየቁት በኋላ እንዲህ አሉት፡-

“አላህ አንዳች ነገር እንዲያደርግልህ አልፀለይክምን? ወይም አንዳች ነገር ይሰጥህ ዘንድ አልጠየቅከውምን?” ታማሚው ሰውም እንዲህ አለ፡-

“አዎን እንዲህ ብዬ ለምኘው ነበር፡- አላህ ሆይ! ቅጣቴን በዚህችው ዓለም ላይ አድርግልኝ፡፡ ከመጪው ዓለም ቅጣት ግን ነጻ አድርገኝ፡፡”

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ለአላህ ጥራት ይገባው፡፡ ይህንን ለመቋቋም አቅም አይኖርህም፡፡ እንዲህ ብለህ አትለምነም ነበርን?

﴿ وَمِنْهُم مَّن يَقُولُ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِى ٱلْءَاخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿٢٠١﴾ ﴾ البقرة: ٢٠١

*“ጌታችን ሆይ! በዚህች ዓለም ላይ መልካም ነገር ስጠን በቀጣዩም አለም መልካም ነገር ስጠን፡፡ እንዲሁም ከእሳት ቅጣት ጠብቀን፡፡” (በቀራህ፡ 201)*

ሰውየው ይህን ካለ በኋላ ከህመሙ ተፈወሰ፡፡ ስለሆነም አላህን የምንጠይቀውን ጉዳይ በተመለከተ ጠንቃቆች መሆን ይገባናል፡፡ እንዲሁም አላህን ስንበይቅ የዱዓን ሥነ ምግባሮች ማሟላት ይኖርብናል፡ ፡ እኛ እንደምንፈልገውና በመሰለን መልኩ ሳይሆን ሁልጊዜም አላህን ስንጠይቅ መልካም ነገርንና ደህንነትን ነው መጠየቅ ያለብን፡፡ ዱዓችን ይበልጥ እንዲሰምርልን ከሻን ደግሞ የአላህ መልእክተኛ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ነገሮች ያደረጓቸውን ዱዓዎች ማጥናት (መሐፊዝ) ይኖርብናል፡፡ ይህ ነው ፍቱንና ብቸኛ የሆነው መፍትሄ፡፡

ዓሊ (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፉት ሥራ እንዲሰራላቸው የተዋዋሉት አንድ ባሪያ ወደርሳቸው መጣና እንዲህ አላቸው፡-

“እዳዬን መክፈል ስላልቻልኩ እርዳታ አድርግልኝ፡፡” እርሳቸው ግን እንዲህ አሉት፡-

“የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ያስተማሩኝን ነገር ላስተምርህን? ይህንን ዱዓ ማድረግህን እስከቀጠልክ ድረስ ከሁሉም በላይ የሆነው አላህ የእዳህ መጠን የሰቢርን ተራራ ቢያክል እንኳን ይከፍልልሃል፡፡” ይህን ካሉ በኋላ የሚከተለውን ዱዓ አነበቡ፡-

“አላህ ሆይ! የተፈቀደ በሆነው ሲሳይህ አብቃቃኝ፡ እንዲሁም ያልተፈቀደ ከሆነው አርቀኝ (ጠብቀኝ)፡፡ ከአንተ ሌላ በማንም ላይ ጥገኛ እንዳልሆንም እዘንልኝ፡፡” (ቲርሚዚ)

በአንድ ወቅት በባልካን ምድር እንዲህ ሆነ…

የኦቶማን ቱርክ ሱልጣን ሙራድ ቀዳማዊ በኮሶቮ ሜዳዎች ላይ ሲጓዝ ኃያል አውሎ ነፋስ የቀሰቀሰው አቧራ ሰማይ ምድሩን አጨለመው፡፡ በዚህም የተነሣ ምንም ነገር አይታይም ነበር፡፡ ያ ሌሊት ምሕረት የመለመኛ ሌሊት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ሁለት ረክዓ ሶላት ከሰገደ በኋላ ሱልጣን ሙራድ እንባው ከአይኖቹ እየተንከባለለና ወደ ጺሙ እየሰረገ የሚከተለውን ዱዓ አደረገ፡-

“ጌታዬ ሆይ! ይህ ማእበል የተነሳው ደካማና ረዳት የለሽ ጀሆንኩት ባሪያህ ኃጢአት ምክንያት ከሆነ እነዚህን ምስኪን ወታደሮቼን አትቆጣቸው፡፡ እነርሱ ወደዚህ የመጡት የአንተን ስም ከፍ ለማድረግና ኢስላምን ለማስፋፋት ነውና፡፡

“ጌታዬ ሆይ! በዚህ ዓመት ውስጥ አንድም ጊዜ ለሽንፈት አልዳረግሽኝም፡ ፡ ሁልጊዜም ልመናየን ትቀበለኛለህ፡፡ አሁንም ወዳንተ ተመልሼያለሁ፡፡ ልመናየን ተቀበለኝ፡፡ ዝናብ አዝንብልን፡፡ ይህንን አቧራም አስወግድልን፡፡ የከሃዲያኑን ፊት እየተመለከትን ፊት ለፊት እንገጥማቸው ዘንድ አድርግልን፡፡

“ጌታዬ ሆይ! እነዚህ ባሮችህም ሆነ መላው ሃብት ያንተ ነው፡፡ እኔ ደካማና ረዳት የለሽ ባሪያህ ነኝ፡፡ ሃሳቤንና ምስጢሬንም ጠንቅቀህ ታውቀዋለህ፡፡ ዓላማየ ሃብትና ንብረትን መሰብሰብ አይደለም፡፡ እኔ የምሻው ምንጊዜም አንተን ማስደሰት ብቻ ነው፡፡

ጌታዬ ሆይ! እነዚህን አማኝ ወታደሮች በከሃዲያን እጅ እንዲሸነፉ አታድርግ፡፡ ሁሉም ሙስሊሞች ሊያከብሩት በሚችሉት ድል አንበሽብሻቸው፡፡ አንተ ከሻህም እነዚህን ባሮችህን ለዚያ ደስታ ሰማእት እንዲሆኑ አድርጋቸው፡፡

ጌታዬ ሆይ! እኔንም የብዙ ሙስሊሞች ማለቅ ምክንያት አታድርገኝ፡፡ እነርሱን አግዛቸውኝ ድልንም አጐናጽፋቸው፡፡ እኔ ግን ራሴን ላንተ በማቅረብ ሰማእት እንድሆንና ከሰማእታቱ ባሮችህ ጋርም ለመቀላቀል እሻለሁ፡፡ እኔ ለእነዚህ የኢስላም ወታደሮች የሰማእትነትን መንፈስ ልዘራባቸው እሻለሁ፡፡ እባክህ! የሰማእትነትን ደረጃ አጐናጽፈኝ፡፡ የለመንኩህን አሁኑኑ ትሰጠኝ ዘንድ በእዝነትህና በችሮታህ እጠይቅሃለሁ፡፡... አሚን!”

ይህን ልባዊና ከውስጥ ስሜት ፈንቅሎ የወጣ ዱዓ ካደረገ በኋላ ሱልጣኑ ልዩ በሆነ ጽሞና ቁርአን ማንበቡን ቀጠለ፡፡ ከዚያ በኋላ የእዝነት ዳመና ሲያንዣብብ ብዙም አልቆየ፡፡ በኮሶቮ ገላጣ ሥፍራዎች ላይም ከባድ ዝናም ወረደ፡፡ ነፋሳም ፀጥ አለ፡፡ አቧራውም እረጭ አለ፡፡

ከዚያ በኋላ ጠላት በግልጽ ሜዳ ላይ ፊት ለፊት እየታየ ይታጨድ ያዘ፡፡ ስምንት ሰዓት በፈጀ ውጊያም ድሉ የሙስሊሞች ሆነ፡፡ ከጦርነቱ በኋላ ሱልጣን ሙራድ ኻን በቆሰሉትና በተሰውት ወታደሮቹ መካከል በመዘዋወር ላይ ነበር፡፡ አንድ የቆሰለ የሰርቢያ ወታደር እንደምንም ከቆመ በኋላ እንዲህ አለ፡-

"እባካችሁ! ወደ ሱልጣኑ ሄጄ እጃቸውን ከሳምኩኝ በኋላ ሙስሊም ለመሆን እፈልጋለሁ፡፡" ከዚያም ያ ቁስለኛ እንደሆነ የተገመተ ወታደር የሱልጣኑን እጅ ሊስም ተንቀሳቀሰ፡፡ ከዚያም ልክ ሱልጣኑ አጠገብ እንደደረሰ በሚያስደንቅ አኳኋን በክንዱ ውስጥ ደብቆ ያስቀመጠውን ሰይፍ በሱልጣኑ ደረት ላይ ሸቀሸቀው፡፡ እናም የሱልጣኑ ዱዓ መልስ አገኘ፡፡ አዎን! ልመናው ምርጥ በሆነ አኳኋን መልስ አገኘ፡፡ እነሆ ሱልጣን ሙራድ ቀዳማዊ በዚያ ከይሲ ሰው እጅ ሰማእትነቱን ተቀበለ…

ለማጠቃለል ዱዓ (አላህን መለመን) አላህን ከማምለክና የእርሱ ባሪያ ከመሆን አንጻር ማእከላዊ ሥፍራን ይይዛል፡፡ ይህም ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ባሪያው ደካማነቱንና ረዳት የለሽነቱን በመገንዘብ እጆቹን ወደሰማይ ዘርግቶ ፈጣሪውን የሚማፀንበትን ሁኔታ የዓለማቱ ጌታ አላህ ስለሚወደው ነው፡፡

ለዚህም ነው አላህ እርሱን ከመለመን የሚኮሩና የሚብቃቁ ሰዎችን በአሳማሚ ቅጣት እንደሚበቀላቸው በቁርአን የሚገልፀው፡-

﴿ وَقَالَ رَبُّكُمُ ٱدۡعُونِيٓ أَسۡتَجِبۡ لَكُمۡۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَسۡتَكۡبِرُونَ عَنۡ عِبَادَتِي سَيَدۡخُلُونَ جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ ٦٠ ﴾ غافر: ٦٠

*"ጌታችሁም አለ! ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመገዛት (ከመለመን) የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሃነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡" (ጋፊር፡8)*

## ሠ- ትህትና (ተዋዱዕ) እና ኹሹዕ

'ኹሹዕ' የሚለው የአረብኛ ቃል አላህን በጥልቅ ስሜት ማፍቀርና አክብሮት የተመላበት ፍርሃት ማሳደርን ያመለክታል፡፡

የኹሹዕ መንፈስ የሚያድረው በልብ ላይ ይሁን እንጂ የሚገለፀው ግን በሌላው የሰውነት ክፍል ላይ በመሆኑ ሁለት ዓይነት መልክ አለው፡-

ኹሹዕ በልብ ላይ የሚያድር ለፈጣሪ የመተናነስና የርሱን ልእልና የመረዳት ስሜት ነው፡፡ ይህ ስሜት የተሰማት ነፍስ የአላህን ትእዛዛት አሜን ብላ በመቀበል እስከመጨረሻው የችሎታዋ ጠርዝ ድረስ በአክብሮትና በትህትና ትፈጽማለች፡፡

ኹሹዕ በሌላ በኩል በውጫዊው አካል ላይ ይንፀባረቃል ሲባል የባሪያው ውስጥ ማለትም ልቡ (ቀልቡ) እና ነፍሱ አላህን ሲፈሩ ይህ ሁኔታ በውጫዊው የአካል ክፍሎቹ ላይ ክብርን፣ እርጋታን፣ የብርሃን ፀዳልን (ኑር) በማላበስ ተገልፆ ስለሚታይ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ሲሰግድ ዓይኖቹ ወዲያና ወዲህ ሳይቃብዙ ተረጋግተው በአንድ ሥፍራ ላይ የሚያተኩሩ ከሆነ ይህ በራሱ ሰውየው ኹሹዕ እንዳለው ያሳያል፡፡

ኹሹዓ በአንድ ሰው የእለት ተእለት ሕይወትና በአምልኮቱ ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ለማወቅ ቀላሉ ዘዴ የተባረኩትን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እና የባልደረቦቻቸውን ዜና መዋእል መመርመር ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ማንኛውንም የሕይወታቸውን እንቅስቃሴ ከመጪው ዓለም ጋር አስተሳስረው ቢሆን እንጂ አይመለከቱም፡፡ አንድ ሰው ፈጣሪውን በሚያመልክበት ጊዜ ከዚያች ቅጽበት በኋላ የመኖር እድል እንደማያገኝና የመጨረሻ ግንኙነቱ እንደሆነ አድርጐ እንዲያስብ ነበር የሚሹት፡፡

አንድ ጊዜ አንድ ባልደረባቸው ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘንድ መጣና እንዲህ አላቸው፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አጥር ምጥን ያለች ምክር ይስጡኝ፡፡" በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉት፡-

“ሶላትህን ስትሰግድ ከዚህች ዓለም ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚሰናበት ሰው ብጤ እያሰብክ ይሁን፡፡ ቆየት ብለህ ይቅርታ የምትጠይቅበት የሆነን ቃል አትናገር፡፡ በሰዎች እጅ ላይ ባለ ነገር አትቅና፡፡” (ኢብኑ ደጃህ፣ አህመድ)

ሶላት የሚጠቅመውና ተቀባይነትም የሚያገኘው በንቃት፣ በኹሹዕና በተመስጦ ሲሰገድ ነው፡፡ የሶሃቦችና ከእነርሱም በኋላ ፈለጋቸውን የተከተሉ ሰለፍ አባቶች ዋነኛው ፀጋቸው ይህን ባህሪ በልባቸዉ ውስጥ ዘውታሪ ማድረጋቸው ነበር፡፡

አብደላህ ኢብኑ መስዑድ (ረ.ዐ.) ጓደኞቻቸውን እንዲህ እንዳሏቸው ተወስቷል፡-

“እናንተ ከሶሃቦች የበለጠ ትሰግዳላችሁ፡፡ እንዲሁም ትግል ታደርጋላችሁ፡፡ ይሁን እንጂ እነርሱ ከእናንተ ይበልጣሉ፡፡”

“እነርሱ ከእኛ ሊበልጡ የቻሉት በምንድን ምክንያት ነው” ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ አሉ፡-

“እነርሱ ከዚህ ዓለም ጣጣ በመራቅና ስለመጪው ዓለም በመጨነቅ ከእናንተ የተሻሉ ስለነበሩ ነው፡፡” (ኢብኑል-ጅውዚ)

በሶላት ላይ መመሰጥና በኹሹዕ መስገድ በመጪው ዓለም ለስኬት ለመብቃትና መድህን ለማግኘት ወሳኝ ነው፡፡ አላህ ይህን እውነታ በቁርአን እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡-

﴿ قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ۝١ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ۝٢ ﴾ المؤمنون: ١ - ٢

*“ምእመናን ፍላጐታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ)፡፡ እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ውስጥ (አላህን) ፈሪዎች፡፡” (አል-ሙእሚኑን፡1-2)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከአንድ የአላህ ባሪያ መልካም ሥራ ውስጥ በፍርዱ ቀን በመጀመሪያ የሚገመገመው ሶላቱ መሆኑን የተናገሩ ሲሆን አንድ ሰው ሶላቱን ከሰገደ በኋላም የሶላቱ ተቀባይነት የሚመዘነው

ሰውየው ሲሰግድ በነበረው ኹሹዕና ተመስጦ ልክ እንደሆነ እንዲህ በማለት አስቀምጠውታል፡-

“አንድ ባሪያ ሶላት ይሰግዳል። ዳሩ ግን የሚመዘገብለት አንድ አሥረኛው ወይም አንድ ዘጠነኛው፣ ወይም አንድ ስምንተኛው፣ ወይም አንድ ስድስተኛው፣ ወይም አንድ አምስተኛው፣ ወይም አንድ አራተኛው፣ ወይም አንድ ሶስተኛው፣ ወይም ግማሹ ይሆናል።” (አቡዳውድ)

ይህ የሚያሳየን አንድ የአላህ ባሪያ ሶላት ስለሰገደ ብቻ ተቀባይነት ያገኛል ማለት እንዳልሆነና ሶላታችንን ሁልጊዜም አቅማችን በቻለው ያክል ተጠንቅቀን መስገድ ያለብን መሆኑን ነው። ሁኔታው በጣም አሳሳቢ ነው። ማንም ሰው ቢሆን በእርግጠኝነትና አፉን ሞልቶ ሶላቴን አላህን እየፈራሁ ሰግጃለሁ ብሎ ለመናገር አይችልም። የጉዳዩን አሳሳቢነት ይበልጥ የሚያጉላው ደግሞ አላህ እንደሚከተለው ባሉ የቁርአን አንቀፆች የሚሰጣቸው ማስገንዘቢያዎች ናቸው፡-

﴿ وَٱسْتَعِينُوا۟ بِٱلصَّبْرِ وَٱلصَّلَوٰةِ ۚ وَإِنَّهَا لَكَبِيرَةٌ إِلَّا عَلَى ٱلْخَٰشِعِينَ ﴿٤٥﴾ ٱلَّذِينَ يَظُنُّونَ أَنَّهُم
مُّلَٰقُوا۟ رَبِّهِمْ وَأَنَّهُمْ إِلَيْهِ رَٰجِعُونَ ﴿٤٦﴾ ﴾ البقرة: ٤٥ - ٤٦

*“በመታገስና በሶላት ተረዱ። እርሷም (ሶላት) በፈሪዎች ላይ እንጅ በሌላው ላይ በእርግጥ ከባድ ናት። እነዚያ እነርሱ ጌታቸውን የሚገናኙ እነርሱም ወደእርሱ ተመላሾች መሆናቸውን የሚያረጋግጡ በሆኑት (ላይ እንጂ ከባድ ናት።” (አል-በቀራህ: 45-46)*

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለአላህ የነበራቸውን ፍራቻ አብዱላህ ቢን ሺህር (ረ.ዐ.) ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

“አንድ ጊዜ ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ስሄድ እየሰገዱና እያለቀሱም ነበር። ለቅሷቸው የፈጠረውን ድምጽ ሳዳምጠው ደረታቸው የሚፈላ ይመስል ነበር።” (አቡዳውድ፣ አህመድ)

ዓኢሻ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብላለች፡-

“አቡ ጃህም (ረ.ዐ.) በአንድ ወቅት በጥልፍ ያሸበረቀ ቀሚስ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በስጦታ አበረከተላቸው፡፡ እርሳቸውም ለብሰው ሰገዱበት፡፡ ሆኖም ግን ሶላታቸውን እንደጨረሱ እንዲህ አሉ፡-

“ይህን ቀሚስ ለአቡ ጃህም መልሱለት፡፡ ዓይኖቼ በጥልፎቹ ላይ ተማረኩ፡፡ ሶላት ውስጥ መሆኔን እንኳን እስክዘነጋ ድረስ ረበሸኝ፡፡” (ሙወጠእ፣ ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሐጅን ሥርአት ለሕዝባቸው በሚገባ ያስተማሩት በመሰናበቻው ሐጅ ጊዜ ነበር፡፡ ልክ እንደሌሎች የአምልኮት ክፍሎች ሁሉ ሐጅም ጥልቅ ተመስጦና ኹሹዕ እንደሚያስፈልገው በዚያ ጊዜ አብራርተዋል፡፡

በዚያው ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በአረፋ ቀን ከአረፋት ወደ ሙዝደሊፋ እየተመለሱ ሳሉ የተወሰኑ ሰዎች ከኋላቸው እየጮሁና ግመሎቻቸውንም እየደበደቡ ያስጓሯቸው ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደነዚያ ሰዎች በዘንጋቸው እያመለከቱ እንዲህ አሉ፡-

“ሰዎች ሆይ! ረጋ በሉ፡፡ ራሳችሁንም ተቆጣጠሩ፡፡ በመቸኮል የምታገኙት ምንዳ (አጅር) አታገኙም፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም)

ዓሊ (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ፡-

“ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ሶላት ላይ ሆኖ በጺሙ ሲጫወት ተመልክተው እንዲህ አሉ፡-

“ልቡ ውስጥ ኹሹዕ (ለአላህ በአክብሮት መተናነስ) ቢኖረው ኖሮ እጆቹም (አካላቱም) አደብ ይኖራቸው ነበር፡፡”

እናቷ ኡሙ ሩማን (ረ.ዐ.) አንድ ጊዜ እንዲህ እንዳሏት ዓኢሻ (ረ.ዐ.) አስተላልፋለች፡-

“አንድ ጊዜ እየሰገድኩ እያለሁ ወዲያና ወዲህ እወዛወዝ ነበር፡፡ ይህን ሁኔታዬን ያስተዋሉት አቡበክር (ረ.ዐ.) በኃይል የገሰጹኝ ከመሆኑ የተነሳ

ሶላቴን ላቋርጥ ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን ተናግረዋል ብለው ተረኩልኝ፡-

"አንዳችሁ ሶላት ላይ ከቆመ መላ አካላቱ ተረጋግቶና በታላቅ አክብሮት መሆን አለበት፡፡ ልክ እንደ አይሁዳውያን ወደኋላና ወደፊት መወዛወዝ የለበትም፡፡ እግሮችና እጆች አንድ ቦታ ላይ ረግተው መቆማቸው ሶላታችን የተሟላ እንዲሆን ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱ ነው፡፡

ነቢዩ ሱለይማን (ዐ.ሰ.) ምንም እንኳን ስፍር ቁጥር የሌለውን ሃብትና ታላቅ ንግሥና ቢሰጣቸውም ከዚህች ዓለም ውዴታ፣ ከቁሳዊ ፍቅር ራሳቸውን በማራቅ ቀለል ያለ ሕይወትን ይመሩ ነበር፡፡ በዚህ ባህሪያቸውም በመግፋት አላህን የሚፈሩ፣ ትሁትና የማይኮሩ ነበሩ፡፡ የእርሳቸውን ባሕሪ ይበልጥ የሚያንፀባርቅ አባባል ከዚህ በታች ተጠቅሷል፡፡

"ያንን ሁሉ ማለቂያ የሌለው ፀጋ የተሰጡት ሱለይማን (ዐ.ሰ.) አላህን እጅግ ከመፍራታቸው የተነሣ በሕይወታቸው አንድም ጊዜ እንኳን ወደ ሰማይ ተመልክተው አያውቁም፡፡" (ኢብን አቢ ሸይባ)

አብደላህ ቢን አቡ-በከር (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡-

"አቡ ጦልሃ (ረ.ዐ.) አንድ እለት በአትክልት ማሳቸው ውስጥ ይሰግዱ ነበር፡፡ በዚያው ቅጽበት "ዱብሲ" የተባለ ወፍ ከማሳቸው ለመውጣት መንገድ እየፈለገ ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ አቡ ጦልሃን ያስደነቃቸው በመሆኑ ለሰከንዶች ያክል በዓይናቸው ተከተለውት ወዲያና ወዲህ አሉ፡፡ ከዚያም ጽሞናቸውን ወደሶላታቸው ሲመልሱ ስንት ረከዓ እንደሰገዱ ዘነጉት፡፡ ይህ ወፍ ሶላታቸውን በኹሹዕ እንዳይሰግዱ በማድረግ የረበሻቸው በመሆኑ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሄደው የሆነውን ነገር ካጫወቷቸው በኋላ እንዲህ አሉ፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ይህን ወፍ ለእርስዎ በሰደቃ መልክ ሰጥቻለሁ፡፡ እርስዎ ለፈለጉት ጉዳይ ያውሉት ወይም ለፈለጉት ሰው ይስጡት፡፡" (ሙወጣእ)

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች በሶላት ላይ ለአላህ የነበራቸውን ፍራቻና መተናነስ የሚያሳየው የሚከተለው ክስተት ምን ያህል ውብና የሚደንቅ ነው፡፡

“በአንድ ወቅት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከዘመቻ በኋላ ወደ መዲና ሲመለሱ በመንገድ ላይ አረፍ አሉ፡፡ ከዚያም ወደ ባልደረቦቻቸው ዘወር ብለው እንዲህ አሉ፡-

“ዛሬ ሌሊት ሲጠብቀኝ የሚያድር ማን ነው”

አምማር ቢን ያሲር (ረ.ዐ.) ከሙሃጂሮች እንዲሁም አብባድ ቢን ቢሽር (ረ.ዐ.) ደግሞ ከአንሷሮች ወዲያውኑ ተነስተው በመቆም …እኛ እንጠብቅዎታለን የአላህ መልእክተኛ፡፡” አሉ፡፡

አብባድ (ረ.ዐ.) አምማርን (ረ.ዐ.) እንዲህ አለው፡-

“ከሌሊቱ መጀመሪያ ነው ወይስ የመጨረሻ ክፍል ዘብ መቆም የምትፈልገው?” አምማር (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡-

“…እኔ መጠበቅ የምፈልገው በሌሊቱ መጨረሻ ላይ ነው፡፡” ይህን ካለ በኋላ ዘወር ብሎ ጋደም አለ፡፡ አብባድ ከዚያ በኋላ ሶላቱን መስገድ ጀመረ፡፡ በዚያ ሁኔታ ላይ እያለ አንድ አጋሪ መጣ፡፡ ከዚያም አንድ የቆመ የሰው ቅርጽ ጥላ ሲመለከት ይህ ጠባቂ መሆን አለበት በማለት ቀስቱን አልሞ አስወነጨፈ፡፡ ያ የቀስት አረር አብባድን ወጋው፡፡ አብባድ ፍላጻውን ነቅሎ ከጣለ በኋላ መስገዱን ቀጠለ፡፡ አሁንም ያ አጋሪ እንደገና አልሞ በማስወንጨፍ ለሁለተኛና ለሶስተኛ ጊዜ ወጋው፡፡ አብባድም ፍላጻዎቹን እየነቀለ በመጣል መስገዱን ቀጠለ፡፡ ከዚያም ሩኩእ አድርጐ ወደ ሱጁድ ወረደ፡፡ ሶላቱን በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንደጨረሰ ጓደኛውን በመቀስቀስ እንዲህ አለው፡-

“ተነስ በቀስት ፍላጻ ተወግቼ ቆስያለሁ፡፡”

አምማር ወዲያውኑ ተፈናጥሮ ተነሣ፡፡ አጋሪው ሰው ይህን እንዳየ እግሬ አውጪኝ ብሎ ሸመጠጠ፡፡ አምማር (ረ.ዐ.) ከአብባድ ሰውነት ላይ ደም በኃይል ሲፈስ በማየቱ እንዲህ አለ፡-

“ለአላህ ጥራት ይገባው! በመጀመሪያው አረር እንደተወጋህ ለምን አልቀሰቀስከኝም?”

አብባድ (ረ.ዐ.) እንደሚከተለው በማለት ለሶላት ያለውን ጥልቅ ስሜትና ፍላጐት እንዲሁም በሚሰግድበት ጊዜ የሚኖረውን ኹሹዕ ያንፀባረቀ መልስ ሰጠው፡-

“ከቁርአን አንድ ምዕራፍ እያነበብኩኝ ነበር፡፡ የጀመርኩትን የቁርአን ምእራፍ ሳልጨርስ ሶላቴን ለማቆም አልፈለግኩም፡፡ ሆኖም ግን የቀስቶቹ አረሮች ሲደጋገሙብኝ ጊዜ ቁርአን ማንበቤን አቁሜ ሩኩዕ አደረኩ፡፡ በአላህ እምላለሁ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሰጡኝን ይህን የጥበቃ ኃላፊነት ባለማክበር (ለጥቃት አጋልጫቸዋለሁ ብዬ) ባልፈራ ኖሮ ያንን የቁርአን ምእራፍ እያነበብኩ እያለሁ ብገደልና ከዚያ በኂላ ንባቡ ቢቋረጥ እመርጥ ነበር፡፡”

የአቡበከር (ረ.ዐ.) ልጅ የሆነችው አስማ (ረ.ዐ.) አንድ ጊዜ በልጇ ልጅ በአብደላህ የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦላት ነበር፡-

“አያቴ! የነቢዩ ባልደረቦች ቁርዓንን ሲያዳምጡ ምን ያደርጉ ነበር?” አስማ እንዲህ አለች፡-

“ከዓይኖቻቸው እንባ ይፈስሳል፡፡ አንዲሁም በቁርዓን እንደተገለፀው መላ አካላቸው ይንዘፈዘፋል፡፡›› ኃያሉ አላህ ቁርዓንን በጥልቅ ተመስጦ የሚያነቡ ባሮቹ ምን ሁኔታ እንደሚታይባቸው እንዲህ በማለት ገልጿል፡-

﴿ وَيَخِرُّونَ لِلْأَذْقَانِ يَبْكُونَ وَيَزِيدُهُمْ خُشُوعًا ۩ ﴾ الإسراء: ١٠٩

*“…እያለቀሱ በግንባራቸው መሬተ ላይ (በስግደት) ይወድቃሉ፤ ፍርሃትም ይጨምርላቸዋል፡፡” (ኢስራእ:109)*

﴿ ٱللَّهُ نَزَّلَ أَحۡسَنَ ٱلۡحَدِيثِ كِتَٰبٗا مُّتَشَٰبِهٗا مَّثَانِيَ تَقۡشَعِرُّ مِنۡهُ جُلُودُ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُمۡ ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمۡ وَقُلُوبُهُمۡ إِلَىٰ ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ ﴾ الزمر: ٢٣

*"አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን ተመሳሳይ፣ ተደጋጋሚ የሆነን መጽሐፍ አወረደ፡፡ ከርሱ (ግሣጼ) የእነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች ቆዳዎች ይኮማተራሉ፡፡ ከዚያም ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ (ተስፋ) ማስታወስ ይለዝባሉ፡፡" (አዝ-ዙመር፡23)* (በይሃቂ)

በአንድ ጦርነት ላይ በዓሊ (ረ.ዐ.) እግር የቀስት አረር ተሰካባቸው፡፡ ከዚያም ሰዎች ሊያወጡት ሲሞክሩ ከባድ ሕመም ስላስከተለባቸው ዓሊ (ረ..) እንዲህ አሉ፡-

"ሶላት ስሰግድ ያን ጊዜ ታወጡልኛላችሁ፡፡"

ሰዎቹም እንደተባሉት ዓሊ (ረ.ዐ.) ሶላት ላይ በቆሙ ጊዜ ያለምንም ችግር መዝዘው አወጡላቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ምንም ህመም ያልተሰማቸውና ሶላታቸውን ተረጋግተው የጨረሱት ዓሊ (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ፡-

"ምንድን ነው ያደረጋችሁት?"

"የቀስቱን አረር መዘን አወጣንልዎ፡፡"

ፈይሰለ ካራኒ አንድ ጊዜ ከእናቱ እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበለት፡፡

"ልጄ ሆይ! ሌሊቱን ሙሉ እስኪነጋ ድረስ ስትሰግድ የምታድረው እንዴት ነው? እንዴት ድካሙን ሁሉ ተሸከምከው?"

የአላህ ወዳጅ የነበረው ፈይሰል እንዲህ አለ፡-

"የምወድሽ አናቴ! ሶላቴን የምሰግደው በከፍተኛ ጥንቃቄና ንቃት ነው፡፡ በጣም ከመመሰጤና ከሚኖረኝ ኹሹዕ የተነሳ ድካም የሚባለውን ነገር አላውቀውም፡፡ በምሰግድበት ጊዜ ከዚህች ዓለም ጋር የሚያገናኙኝን ነገር ሁሉ እቆርጣለሁ፡፡ እንዲሁም ከሥጋዊ ፍላጐቴ ጋር የሚያስተሳስረኝን

ባሕሪ ሁሉ አስወግዳለሁ፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኜ እየሰገድኩ እያለሁ ምንም ሳላውቀው ንጋቱ ይቀርባል…”

“ለመሆኑ ይህ ኹሹዕ ማለት ምንድን ነው? ውዴ!”

“ኹሹዕ ማለትማ ሌላው ይቅርና የቀስት አረር እንኳን ሰውነትሽን ሲወጋሽ የማይሰማሽ መሆን ማለት ነው፡፡”

ዘይኑል አደዲንን በተመለከተ እንዲህ የሚል ዘገባ ተላልፏል፡-

ዘይኑል አቢዲን ሁልጊዜም ውዱእ ሊያደርጉ ሲዘጋጁ ፊታቸው ይገረጣል፡፡ እንዲሁም ሶላት ሲጀምሩ እግሮቻቸው ይንቀጠቀጣሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የሚታይባቸው ለምን እንደሆነ ተጠይቀው ሲመልሱ እንዲህ አሉ፡-

“ከማን ፊት ለመቆም እየተዘጋጀሁ እንዳለሁ አትገነዘቡምን?” (አቡ ኑዓይም)

በአንድ ወቅት ከቤታቸው ውስጥ ሆነው እየሰገዱ እያሉ ቤታቸው ተቃጠለ፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ሁኔታ እርሳቸው አላወቁም ነበር፡፡ ሶላታቸውን እንደጨረሱ ስለተፈጠረው ሁኔታ ከነገሯቸው በኋላ ሰዎች የሚከተለውን ጥያቄ አቀረቡላቸው፡-

“ቤትዎ በእሳት መያያዙን እንዳይገነዘቡ ያደረገዎት ነገር ምንድን ነው?”

ዘይኑል አቢዲን እንዲህ አሉ፡- “በመጪው ዓለም የሰውን ልጅ የሚጠብቀውና የተደገሰለትን የጀሃነም እሳት ሳስብ የዚህችን ዓለም እሳት እንድዘነጋው አደረገኝ፡፡”

የሙስሊም ቢን ያሲር ሶላትም ተመሳሳይ ሁኔታ ይንፀባረቅበት ነበር፡፡

አንድ ጊዜ በበስራ መስጊድ ውስጥ ይሰግድ ነበር፡፡ በቅጽበት መስጊድ ተደርምሶ መሬት ላይ ወደቀ፡፡ ይሁን እንጂ ሙስሊም ቢን ያሲር ይህን ክስተት ሳይገነዘብ በሶላቱ ላይ እንደተመሰጠ ቀጥሏል፡፡ ሶላቱን እንደጨረሰም ሰዎች ጠየቁት፡-

“መስጊዱ በላይህ ላይ እየተደረመሰ አንተ ግን አንድ ኢንች እንኳን አልተንቀሳቀስክም፡፡ ይህ ሁኔታ ምንድን ነው?”

ሙስሊም ቢን ያሲር በመደነቅ የሚከተለውን ጥያቄ ለጠያቂዎቹ መልሶ አቀረበላቸው፡-

“እንዴ! መስጊዱ ተደርምሷል ነው የምትሉኝ?”

አንድ የአላህ ወዳጅ እንዲህ ይላል፡-

“እኔ የዙህርን ሶላት ከዘኑን መስሪ ኋላ ቆሜ በመስገድ ላይ ነበርኩ፡፡ ያ ብሩክ ሰው “አላሁ አክበር (አላህ ታላቅ ነው) ሲል “አላህ” የሚለው ቃል በእርሱ ላይ የሚፈጥረውን ተጽእኖ ሳስተውል በአካሉ ውስጥ ነፍስ ያለው እስከማይመስል ድረስ ድርቅ ብሎ ነበር የሚቆመው፡፡ “አክበር” የሚለውንም ከአፉ ሲያወጣው ከቃሉ ከባድነት (ባለግርማ መሆን) የተነሣ ልቤ ፍርስ ልትል ምንም አይቀራትም ነበር፡፡”

አምር ኢብን አብዱላህ ሶላት ላይ በሚቆምበት ጊዜ ከውጨኛው ዓለም ጋር የሚያስተሳስረው ነገር ሁሉ ይቆረጥና ከአላህ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያውክ አንዳችም ነገር አይፈጠርበትም ነበር፡፡

ይህንን ሁኔታ ራሱ በአንደበቱ ሲገልጽ እንዲህ ይል ነበር፡-

“እኔ ሶላት ላይ እያለሁ የሰዎችን ድርጊትና ድምጽ ከምከታተል በቀስት ፍላጻ ሰውነቴን ብወጋ ይሻለኛል፡፡”

# ምዕራፍ ሰባት

# ከቅዱስ ቁርዓን ጋር መተሳሰር

ቅዱስ ቁርዓን መታጣት ያልቀደመውና መጥፋትም የማይከተለው የሆነው የዓለማት ጌታ አላህ ለሰው ዘር በሙሉ ያወረደው የመጨረሻው ኪዳን ነው፡፡ ቁርዓን ለምዕመናን እዝነት፣ በልብ ውስጥ ላለ በሽታም መድሃኒት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መለከታዊ ግሳጼና የሰውን ልጅ በሙሉ ከመንፈሳዊ ጽልመት በአላህ ፈቃድ ወደ ብርሃን ስርቀት ጐትቶ የሚያወጣ ተዓምር ነው፡፡

ቅዱስ ቁርዓን መለኮታዊ አዋጅ ሲሆን የሥነ ፍጥረትን ምስጢርና ዓላማ እንዲሁም ምሉእ በኩልሄ የሆነው አላህ ሰውን ራሱን የፈጠረበትን ምክንያት ያስረዳል፡፡ በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ያለውን ሚና እንዲሁም ፈጣሪው ከእርሱ የሚፈልግበትን ደንብና ሥርዓት በምልዓት ያብራራል፡፡

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱللَّهُ نَزَّلَ أَحۡسَنَ ٱلۡحَدِيثِ كِتَٰبٗا مُّتَشَٰبِهٗا مَّثَانِيَ تَقۡشَعِرُّ مِنۡهُ جُلُودُ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُمۡ ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمۡ وَقُلُوبُهُمۡ إِلَىٰ ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ هُدَى ٱللَّهِ يَهۡدِي بِهِۦ مَن يَشَآءُۚ وَمَن يُضۡلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِنۡ هَادٍ ٢٣ ﴾ الزمر: ٢٣

*"አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን ተመሳሳይ፣ ተደጋጋሚ የሆነን መጽሐፍ አወረደ፡፡ ከእርሱ (ግሣጼ) የእነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች ቆዳዎች ይኮማተራሉ፡፡ ከዚያም ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ (ተስፋ) ማስታወስ ይለዝባሉ፡፡ ይህ የአላህ መመሪያ ነው፡፡ በእርሱ የሚሻውን ሰው ይመራበታል፡፡ አላህም የሚያጠመው ሰው ለእርሱ ምንም አቅኚ የለውም፡፡" (አዝ-ዙመር፡ 23)*

ይህ የቁርዓን አንቀጽ የሚያሳየን ልባችን ከቁርዓን ጋር ሊኖረው የሚገባውን ትስስሮሽ ነው፡፡ እኛ ሁላችን የሚኖረን የተቅዋ (አላህን የመፍራትና የመጠንቀቅ) ደረጃ የሚወሰነው ቁርዓን በሕይወታችን ላይ በሚያሳድረው አዎንታዊ ተጽእኖ ልክ ነው፡፡ ይህም የሚገለጸው

በአምልኮታችን (ኢባዳ) ላይ በሚኖረን ኢኽላስ፣ በባሕሪያችን ማማርና በልፋታችን ስፋት ነው፡፡

ቁርዓንን አጥብቆ የያዘና የሰራበት በእርግጥም ለእርሱ መበጠሻ የሌለው የሆነን ዘለበት እንደጨበጠ ነው የሚቆጠረው፡፡ ከሁሉም በላይ የሆነው አላህ የእርሱን ውዴታ ለሚሹና ከጀሃነም ቅጣት ለመዳን ለሚፈልጉ የዘረጋው የእርቅ ሰነድ ነው፡፡ እርሱን ከፍ ከፍ ያደረጉና ሊመሩበት የወደዱ በእውነትም መዳን ተገባቸው፤ ክብራቸውም ተጠበቀ፡፡ እርሱን ያጣጣሉትና በያዛቸው የሥነ ምግባር እሴቶች ለመመራት እንቢኝ ያሉ ኪሣራና ውርደት ተገባቸው፤ መንገድም ሳቱ፡፡

ቅዱስ ቁርአን ጣእሙና ለዛው የማይበላሽና ጊዜ አይሽሬ የሆነ ከአለማት ጌታ ለባሮቹ የተወረደ መንፈሳዊ ድግስ ነው፡፡ በዚህ ግብዣ ለመታደም የፈቀዱ ሰላምን፣ ደስታንና ፍስሃን ገንዘባቸው ያደርጋሉ፡፡

እውነተኛ የሰው ልጆች ክብር ቁርአንን ተቀብለው፣ በእርሱም አምነው ለመስራት ባላቸው ዝግጁነት ላይ ጥገኛ ነው፡፡ ሰው ሕይወቱን በዘፈቀደ ለመምራት ከመረጠ መድሃኒት በማይገኝለት ኃያል ደዌ ተለከፈ ማለት ነው፡፡ የቁርአንን ለዛ፣ ጥፍጥና፣ ጥበብና ግሳፄ የተነፈገ (ያጣ) ሰው በዚህች ዓለም ላይ አለኝ የሚለው ነገር ሁሉ ከንቱ መሆኑን ማወቅ አለበት፡፡ እርሱ በእርግጥም ምንም ነገር የለውምና!

ስለሆነም የመጪውን ዓለም ፀጋና መዳን የምንከጅል ከሆነ ከቁርአን ጋር ያለንን ዝምድና ማሻሻልና ደረጃውን ከፍ ማድረግ አለብን፡፡ ያን ማድረግ ስንችል በእውነትም ትክክለኛ የሆነውን ኢስላማዊ ስብእና ማንፀባረቅ እንችላለን፡፡

በሐዲስ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡-

“ከእናንተ አንዳችሁ ጌታውን መለመንና ከእርሱም ጋር መነጋገር የሚወድ ከሆነ ከልቡና በሙሉ ተመስጦው ቁርአንን ያብብ፡፡” (ሱዩጢ)

“ቁርአንን አንብቡ! ምክንያቱም በፍርዱ ቀን እርሱን በሚገባ ላነበበው ሰው አማላጅ ሆኖ ይመጣልና፡፡” (ሙስሊም)

“ቁርአንን በትክክል ለሚያነብቡና ሲሰሩበት በኖሩ ሰዎች ወላጆች ራስ ላይ በፍርዱ ቀን ዘውድ ይደፋላቸዋል፡፡ በዚህ ዘውድ ላይ ያለው የብርሃን ነፀብራቅ ከፀሐይ ብርሃን ይበልጥ የሚያምር ሲሆን የተቀመጡበት ቤት በብርሃኑ ፀዳል ይሞላዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ቁርዓንን የሚቀራውና በእርሱም የሚሰራው ሰው ብርሃን ምን ሊመስል ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?” (አቡዳውድ)

በሌሊት ሁለት ረከዓ ሶላት እየሰገደ ቁርአን ከሚያነብ ሰው የበለጠ አላህ ማንንም አያዳምጥም፡፡ ባሪያው በሶላት ላይ እስካለ ድረስም የአላህ እዝነት በእርሱ ላይ ይሰፍናል፡፡ ባሪያው አላህን ከምንም በላይ ይበልጥ የሚቀርበው ቁርአንን በሚያነብበት ጊዜ ነው፡፡ “(ቲርሚዚ)

በሐዲስ እንዲህ የሚሉ አባባሎች ተጠቅሰው ይገኛሉ፡-

“ቁርአንን አላህ ካሳወቃቸውና በአእምሯቸውም ከያዙት (ከሃፈዙት) በኋላ ትኩረትና በቂ ጊዜ ሳይሰጡት በመቅረታቸው የሚረሱት ሰዎች ታላቅ ኃጢአት እንደፈጸሙ ይቆጠርባቸዋል፡፡” (አቡዳውድ)

“በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው በልቡ ውስጥ ምንም ዓይነት የቁርአን አንቀጽ የማይገኝ ከሆነ እንደ ወና ቤት ይቆጠራል፡፡ (ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ልብ ብረትን እንደሚያገኘው ዝገት ብጤ ይዝጋል፡፡”

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ይህን ዝገት በምን ማስለቀቅ ይቻላል?” በማለት ባልደረቦቻቸው ጠየቋቸው፡፡

“የአላህን ቁርአን በብዛት በማንበብና አላህንም በብዛት በማውሳት” በማለት መለሱላቸው፡፡ (አሊ አል-ሙተቂ)

በሌላ ቀን ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ተከታዮቻቸውን እንዲህ በማለት መከሩ፡-

“ከአምልኮት ውሰጥ ለዓይናችሁ የሚገባውን አድርጉ!”

“ለዓይናችን የሚገባው አምልኮ ምንድን ነው? የአላህ መልእክተኛ?” ተባሉ፡፡

“የቁርአንን ገጾች ማየት (ማንበብ)፣ በዚያ መሥራት፣ ከግሳጼው መማር” በማለት መልስ ሰጡ፡፡ (ሱዩጢ)

በሌላ ጊዜ ደግሞ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“በእረግጥ ከሰዎች ውስጥ ወደ አላህ የቀረቡ አሉ፡፡”

“የአላህ መልክተኛ ሆይ! እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው?” ተባሉ፡፡

“እነርሱ የቁርአን ሕዝቦች፣ የአላህ ሕዝቦችና የአላህ ልዩ ባሪያዎች ናቸው” አሉ፡፡ (ኢብን ማጃህ)

ሰዎች ተሰባስበው ቁርአንን ለመማርና በውስጡ ያለውንም ምስጢር ለመረዳት ሲሞክሩ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከተመለከቱ በተለየ ሁኔታ ይደሰቱ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰዎችን አስመልክተውም የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

“…ሰዎች ከአላህ ቤቶች በአንዱ ተሰብስበው የአላህን መጽሐፍ በሚያነቡበት (በጋራ በሚያጠኑበት) ወቅት በእነርሱ ላይ እርጋታ ይሰፍናል፡፡ የአላህ እዝነትም ያካብባቸዋል፣ መላእክትም ያጅቧቸዋል፡፡ አላህም ለእርሱ ቅርብ በሆኑ ክፍሎች (መልአኮች ዘንድ) ያወሳቸዋል፡፡ ሥራው (ወደ ኋላ) የሚጐትተው ዘሩ ወደፊት አያስቀድመውም፡፡” (ሙስሊም)

እንግዲህ ሁኔታዎች ይህንን የሚመስሉ ከሆነ በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም የስኬት ባለቤት ለመሆን ቁርአንን አጥብቀን መያዝ፣ በእርሱ መመራትና ከእርሱ ጋር ያለንን ትስስር መጨመር ይኖርብናል፡፡ ስለሆነም በየጊዜው ልናነበው፣ ልንገነዘበውና በልባችን ልናስተነትነው፣ እንዲሁም ሕግጋቱን በሁሉም የሕይወት እንቀስቃሴዎቻችን ልንተገብረው ግድ ይሆንብናል ማለት ነው፡፡

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ቁርአንን ተስማሚ በሆነ ሁኔታ እንዲሁም ትርጉሙንም በጥልቀት በመገንዘብ ትእዛዛቱንም ያለምንም ማስተጓጉል በመተግበር ያነቡት ነበር፡፡ ቁርአንን በሙሉ ልባቸውና ተመስጦአቸው በማንበብ ይኖሩት ነበር፡፡ በሚያነቡት ጊዜም አላህን ከሚያጠራ አንቀጽ ላይ ከደረሱ አላህን ከጉድለት ሁሉ በማጥራት "ሱብሃነኋህ" (ለአላህ ጥራት ተገባው) ይሉ ነበር፡፡ ዱዓ (ተማጽኖ) ማቅረብን ከሚጠይቅ ቦታ ሲደርሱ ደግሞ አላህን ከልብ ይማፀኑ ነበር፡፡ ከአላህ ጥበቃ መሻትን የሚገልጽ አንቀጽ ሲያጋጥማቸውም ወዲያውኑ የአላህን ጥበቃ ይሻሉ፡፡ (ሙስሊም፣ ነሳኢ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በየእለቱ በመደበኛነት ከቁርአን የተወሰነ ክፍልን ያነቡ ነበር፡፡

ከሰቂፍ ጐሣ የሆነውና ወደመዲና የመጣው አውስ ቢን ሁዘይፋ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

"የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ምሽት ከኢሻ ሶላት በኋላ ለረዥም ጊዜ ብቅ ሳይሉ ቆዩ፡፡ እኛም የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ለረዥም ጊዜ ወደእኛ ሳይወጡ የቆዩት ለምንድን? ነው?" አልናቸው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"እኔ በራሴ ላይ በየእለቱ አንድ ሒዝብ[2] የሚሆን የቁርአን ክፍል ለመቅራት ግዴታ አድርጌያለሁ፡፡ ያንን ሳልጨርስ አልወጣም፡፡"

ሲነጋ ባልደረቦቻቸውን ጠየቅናቸው፡-

"ቁርአንን እንዴት ነው የምትከፋፍሉት?" እነርሱም የሚከተለውን መልስ ሰጡን፡-

"የመጀመሪየዎቹን ሶስት ምዕራፎች አንደኛ ሒዝብ እንላቸዋለን፡፡ ከዚያም የሚቀጥሉትን አምስት ምእራፎች ሁለተኛ ሒዝብ፣ ከዚያም ቀጣዮቹን ሰባት ምዕራፎች ሶስተኛ ሒዝብ ከዚያም ቀጣዮቹን ዘጠኝ ምእራፎች፣ ከዚያም ቀጣዮቹን አሥራ አንድ ምእራፎች፣ ከዚያም

ቀጣዮቹን አሥራ ሦስት ምእራፎች፡፡ በመጨረሻም የቃፍ ምእራፍና ከዚያ በኋላ ያሉትን እንደ አንድ ሒዝብ እንቆጥራቸዋለን፡፡ በዚህ ዓይነት ቁርአንን በሰባት ክፍሎች እንከፍለዋለን፡፡" (አህመድ፣ ኢብኑ ማጃህ)

አብደላህ ኢብኑ መስዑድ (ረ.ዐ.) የሚከተለውን ብለዋል፡-

"አንድ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) "ኢብን መስዑድ ሆይ! ቁርአን አንብብልኝ" እኔም "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ቁርአን በእርስዎ ላይ ወርዶ እያለ እንደምን እኔ ላነብልዎት እችላለሁ?" አልኳቸው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"ቁአርንን ሌላ ሰው ሲቀራው (ሲያነበው) ማዳመጥ ደስ ይለኛል፡፡" እኔም በዚህ ጊዜ ከአን-ኒሳእ ምእራፍ ጀምሬ ማንበብ ቀጠልኩኝ፡፡ ከዚያም ከሚከተለው አንቀጽ ላይ ደረስኩ፡-

﴿ فَكَيْفَ إِذَا جِئْنَا مِن كُلِّ أُمَّةٍ بِشَهِيدٍ وَجِئْنَا بِكَ عَلَىٰ هَٰؤُلَاءِ شَهِيدًا ﴿٤١﴾ ﴾

*"ከሕዝቦችም ሁሉ መስካሪን ባመጣን ጊዜ አንተንም በእነዚህ ላይ መስካሪ አድርገን በምናመጣህ ጊዜ (የካሃዲያን ሁኔታ) እንዴት ይሆን?" (አን-ኒሳእ፡ 41)*

ይህን የሰሙት መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"በቃህ!"

በዚያው ቅጽበት ከዓይናቸው ላይ የእንባ ዘለላዎች እንደ ሉል እየተንከባለሉ ሲወርዱ አስተዋልኩ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

አንድ እለት ዓኢሻ (ረ.ዐ.) ወደ ቤት ከመምጣት ዘገየች፡፡ ከዚያም እንደመጣች ምን ችግር አጋጥሟት እንደሆነ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲጠይቋት መስጊድ ውስጥ ቁርአንን እያዳመጠች መሆኑን ከነገረቻቸው በኋላ እንዲህ አለች፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! መስጊድ ውስጥ አንድ ሰው አለ። ከዚህ ሰው የበለጠ ቁርአንን ባማረ ሁኔታ የሚያነብ ሰው ሰምቼ አላውቅም።” በዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ መስጊድ ሄደው ሰውየው ሳሊም (ረ.ዐ.) መሆኑን ከተመለከቱ በኋላ ተመልሰው እንዲህ አሉ፡-

“ከሕዝቤ ውስጥ ይህን የመሰለ ሰው እንዲኖር ላደረገው አላህ ምስጋና ይገባው።” (ኢብኑ ማጃህ፣ አህመድ፣ ሐኪም)

አንድ ጊዜ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ባልደረባቸው እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከሁሉም መልካም ሥራ ይበልጥ አላህን የሚያስደስተው ምንድን ነው?” ተወዳጁ ነቢይም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ሃልና ሙርተሂልን መፈፀም ነው”

“ሃልና ሙርተሂል ምንድን ነው?” አላቸው። እርሳቸውም፡-

“ቁርአንን ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ማንበብና ያንን ከጨረሱ በኋላ እንደገና ከመጀመሪያው መጀመር ነው።” (ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለቁርአን ታላቅ ክብርና ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን ይህንን የሚያደርጉ ባልደረቦቻቸውንም ይወዷቸው ነበር።

አንድ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ቁጥሩ የበዛ ሰራዊት ወደ አንድ ቦታ ሊያዘምቱ ፈልገው እያንዳንዱ ሰው ቁርአንን እንዲቀራ አደረጉ። ሁሉም ሰው በቃሉ ያጠናውን የቁርአን ምእራፍ አነበበ። ከዚያም ከሁሉም ወጣት ወደሆነው ባልደረባቸው ሄዱና እንዲህ በማለት ጠየቁት፡-

“እገሌ ሆይ! ምን የሚባለውን ምእራፍ ነው በቃልህ ያጠናኸው?”

“እኔ ይህንና ይህን እንዲሁም ሱረቱል በቀራህን አጥንቼያለሁ።” አለ።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“ሱራ አል-በቀራህን አጥንተሃል?” መልሱ “አዎን”።

“እንደዚያ ከሆነ መሪያቸው አንተ ነህ። ይህ ምእራፍ ከሞላጐደል ሁሉንም የኃይማኖቱን ጉዳይ ይዟልና።”

ከቡድኑ መሪዎች አንዱ እንዲህ አለ፡-

“በሱራ አል-በቀራህ ላይ ያለውን ነገር ለመተግበር ያደረብኝ ፍራቻ በቃሌ እንዳልይዘው አደረገኝ።”

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን አባባል እንደሰሙ እንዲህ አሉ፡-

“ቁርአዓንን ተማሩ፣ ከዚያም አንብቡት፣ ሌሎችም እንዲያነቡትና እንዲሰሩበትም ገፋፉ። ምክንያቱም ቁርአንን የተማረ፣ ያነበበውና የሰራበት ሰው በጠርሙስ ውስጥ እንደታሸገ ሚስክ መዓዛው ሁሉንም እንደሚያውድ ብጤ ነው። ቁአንን ተምሮ የማይሰራበት የታሸገበት ክዳን ሳልቶ እንደተከደነ ሚስክ ማለት ነው። (ቲርሙዚ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች ከእርሳቸው አስር የሚሆኑ አንቀፆችን ከተማሩ (በቃላቸውም ካጠኑ) በኂላ ሌሎች አስር አንቀፆችን ለማጥናት አይንቀሳቀሱም ነበር። ከዚያ ይልቅ በእነዚያ በመጀመሪያ ባወቋቸው አንቀፆች መሥራትን፣ ለትእዛዛቱ ማደርን፣ ከክልከላዎች መታቀብን፣ ከጥበባቸው መቋደስን እንዲሁም በግሳጼዎቹ መታነጽን ያስቀድሙ ነበር። በዚህ ዓይነት ስብእናቸውን ከቁርአን ሥነ-ምግባርና እሴቶች ጋር ለማስማማት ብዙ ከደከሙና ነፍሳቸውን ከገሩ በኂላ ነው ወደ ሌሎች አንቀፆች የሚረማመዱት። (አህመድ)

ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ፡-

“እኔ ሱራ አል-በቀራህን በአሥራ ሁለት አመቴ አጠናቀቅኩ። ለዚህም ምስጋና ይሆን ዘንድ አንድ ግመል አረድኩ።” (ቁርጡቢ)

አብደላህ ኢብኑ ኡመር (ረ.ዐ.) ሱራ አል-በቀራህን በስምንት ዓመታት አጠናቅቀዋል። (ሙወጠእ)

አንድ ሰው ቁርአንን አጠናቀቀ የሚባለው በሕይወት ሲኖረውና ለሌሎችም ሲያስተምረው መሆኑን ልብ ይሏል።

የሰቂፍ ጐሣ ተወካዮች ነቢዩን ሊያነጋግሩ በመጡ ጊዜ ኡስማን ቢን አቢል-አሰን ወደ ኋላ እንዲቀርና እንስሳዎቻቸውን እንዲጠብቅላቸው አድርገውት ነበር፡፡ ምክንያቱም ከሁሉም የጐሣው አባላት በእድሜ ትንሽ የነበረው እርሱ ስለነበር ነው፡፡ የጐሣው ሰዎች በቀትር ሰዓት ወደማረፊያቸው ሄደው ሲተኙ ኡስማን (ረ.ዐ.) ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በመሄድ ጥያቄዎችን እየጠየቃቸው፣ ስለሃይማኖቱ እየተማረና ቁርአንንም እየቀራ ቆየ፡፡ በዚህ ዓይነት ቁርአንን ማንበብና የተወሰነውንም ክፍል በቃሉ ማጥናት የቻለው በቀጥታ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በመማር ነው፡፡

ኡስማን (ረ.ዐ.) በዚህ ዓይነት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጋር ሲገናኝ ከቆየ በኋላ በምስጢር ኢስላምን ተቀብሎ ከእርሳቸውም ጋር ስምምነት አድርጐ ኃይማኖቱን ሲማር ቆየ፡፡ እርሳቸው በማይገኙ ጊዜም ወደ አቡበከር (ረ.ዐ.) ወይም ኡበይ ኢብን ካእብ (ረ.ዐ.) በመሄድ መጠየቅ የሚገባውን በመጠየቅና መማር የሚገባውን በመማር እውቀቱን አዳበረ፡፡

ይህ የኡስማን (ረ.ዐ.) ድርጊት ያስደሰታቸው ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) በጣም ወደዱት፡፡ የሰቂፍ ሰዎች ወደ ሐገራቸው ለመሄድ ሲነሱ እንዲህ አሉ፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከመካከላችን አንዳችንን መሪ አድርገው አይሾሙልንምን?”

በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ምንም እንኳን ከሁሉም በእድሜ አነስተኛው እርሱ ቢሆንም ኡስማን ቢን አቢል-አስን መሪያቸው እንዲሆን ሾሙላቸው፡፡ (ኢብን ሰዓድ፣ ኢብን ሒሻም፣ አህመድ)

ለዘመናት ሳይቋረጥ፣ አንዱ ሌላውን እየተከተለ ሲወርድ የነበረው ወህይ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እና ለተከታዮቻቸው በቃላት የማይገለጽ ደስታን ሲያጐናጽፋቸው ቆይቷል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ተከታዮቻቸው ለኃይማኖታቸው የነበራቸው ቁርጠኝነት እንዲታደስ ልባቸው ከአላህ ጋር ያለው ትስስት እንዲጠበቅ፣ ተስፋቸው እንዲያበብና በአጠቃላይ የመጽናናታቸው ምንጭ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት በነቢዩ

(ሰ.0.ወ.) መሞት የወህዩ መውረድ ሲቋረጥ በሁሉም ላይ ብርቱ የሃዘን በትር አረፈ፡፡

ሶሐቦች ለወህይ የነበራቸውን ፍቅር ለመረዳት የሚከተለውን ገጠመኝ እንከታተል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ.) ይህችን ዓለም ተሰናብተው ከሄዱ በኋላ አቡበከር (.0.) ኡመርን (ረ.0.) እንዲህ አሏቸው፡-

"ተነስ ወደ ኡሙ አይመን እንሂድ፡፡ እርሷ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ.) በጣም ተወዳጅ ነበረች፡፡ እርሳቸው ይጠይቋት እንደነበረውም እኛም እንጠይቃት፡፡"

ኡሙ አይመን (ረ.0.) ወዳለችበት ሲሄዱ ማልቀስ ጀመረች፡፡ እነርሱም ለምን እንደምታለቅስ ጠየቋት፡፡

"ለምን ታለቅሻለሽ? ከአላህ ዘንድ ያለው ፀጋ ለነቢዩ (ሰ.0.ወ.) የተሻለ እንደሆነ አታውቂምን?"

ኡሙ አይመን (ረ.0.) እንዲህ አለች፡-

"እኔ የማለቅሰው ለዚያ አይደለም፡፡ ብሩክ ለሆኑት ነቢይ ከአላህ ዘንድ ያለው ፀጋ በጣም የተሻለ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ እኔ የማለቅሰው ወህይ መውረዱ በመቋረጡ ነው፡፡"

ይህ ያልተጠበቀና ከዚህች ሴት አፍ ይወጣል ተብሎ ያልተገመተ አባባል ሁለቱንም ሰዎች አስደነቃቸው፡፡ ለወህይ የነበራትን ናፍቆትም በመገንዘባቸው ለቅሶዋ ወደነርሱም ተጋባና አቡበከር (ረ.0.) እና ኡመርም (ረ.0.) ከኡሙ አይመን (ረ.0.) ጋር አብረው ማልቀስ ጀመሩ፡፡ (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ.) ባልደረቦች ቁርአንን በየጊዜው የሚያነቡት ሲሆን ቁርአንን ሳያነቡ ሌላው ቢቀር ገፆቹን እንኳን ሳያዩ አንዲትም ቀን እንድታልፋቸው አይፈልጉም ነበር፡፡ ቀናቸውን በቁርአን የሚጀምሩ

ሲሆን የማየት ችግር ያለባቸው ሰዎችም የቁርአንን ገፆች እንዲመለከቱ ይመከሯቸው ነበር፡፡ (ሃይሰሚ)

ጃሚዑል ቁርአን (የቁርአን ሰብሳቢ) በሚል ማእረግ የሚታወቁት ኡስማን (ረ.ዐ.) ቁርአንን በጣም ከማዘውተራቸው ብዛት ሁለት የቁርአን ቅጅዎችን በእጃቸው ላይ አርጅተው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፡፡ (ካታኒ)

ኡሰይድ ኢብን ሁደይር (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"አንድ ምሽት ላይ የበቀራህን ምእራፍ አነብ ነበር፡፡ ፈረሴ ደግሞ አጠገቤ ታስሯል፡፡ አንድ ቦታ ላይ ስደርስ በኋላ እግሮቹ ቆሞ የፊት እግሮቹን ወደ ላይ አነሣ፡፡ በዚህ ጊዜ መቅራቴን በማቆሜ እርሱም ተረጋጋ፡፡ እንደገና መቅራቴን ስጀምር አሁንም ፈረሴ እግሮቹን ወደ ላይ አቆመ፡፡ በዚህ ጊዜ ፈረሴ ከልጄ ከህያን ላይ እንዳይወጣ ፈራሁ፡፡ ስለሆነም ከአጠገቡ ተቀመጥኩ፡፡ በዚያው ቅጽበት ልክ ወደ ሰማይ ስመለከት የሚያበራ ነገር አስተዋልኩ፡፡ ያ ብርሃንም ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ ተሰወረ፡፡

ከነጋ በኋላ የሆነውን ሁሉ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ስነግራቸው እንዲህ አሉ፡-

"አንብብ! ኡሰይድ ሆይ አንብብ!" … ከዚያም እንዲህ አሉ፡- "ኡሰየድ ሆይ! ያየኸው ነገር ምን እንደሆነ አውቀሃል?"

"አላወቅኩም፡፡" በማለት መለስኩ፡፡

"እነርሱማ አንተ የምትቀራውን ቁርአን ለማዳመጥ የመጡ መላእክት ነበሩ፡፡ ማንበብህን ቀጥለህ ቢሆን ኖሮ እስከንጋት ድረስ ያዳምጡህ ነበር፡፡ እነርሱን ለማየት ብቃት ላላቸው ሰዎች ራሳቸውን ሰውረው አይቆዩም፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም)

አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የቁርአን ወዳጅ በመሆኑ በሰፊው የሚታወቀውን ኡበይ ኢብን ካዕብን እንዲህ በማለት ብስራት ነገሩት፡-

“የልቅና ባለቤት የሆነው አላህ “ለምየኩኒለዚነ ከፈሩ” የሚለውን ምእራፍ ታነብ ዘንድ ለአንተ እንድነግርህ አዝዞኛል፡፡”

ኡበይ ቢን ካእብ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“ከሁሉም በላይ የላቀው አላህ እውን የእኔን ስም ጠቀሰ?”

“እንዴታ!” ነበር የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መልስ፡፡

በዚህ ጊዜ ኡበይ ቢን ካዕብ በዚህ መለኮታዊ ሙገሳ እጅግ ከመነካቱ የተነሣ ከመጠን በላይ ማልቀስ ጀመረ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

እንደሚታወቀው ኡበይ ቢን ካእብ (ረ.ዐ.) ቁርአንን በቃላቸው ካጠኑ ሰዎች መካከል ከመጀመሪያዎቹ የሚሰለፍ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) “ከእነዚህ አራት ሰዎች ቁርአንን ተማሩ፡፡” ብለው ከጠቀሷቸው እድለኛ ሰዎች መካከል ነበር፡፡ ኡበይ (ረ.ዐ.) ቁርአንን አሳምረውና ብዙ አዘውትረው ከሚያነቡ ሰዎች አንዱ ነበር፡፡ እንግዲህ ኡበይ (ረ.ዐ.) ከቁርአን ጋር የነበረው ዝምድናና ትስስር ነበር ይህን ለመሰለ ታላቅ ማእረግ ያበቃው፡፡ ይህን ደረጃ የሚጐናፀፉት ጥቂት እድለኞች ብቻ ናቸው፡፡ ምን ያማረ ክብር፤ ምንስ ያማረ ስጦታ ነው!

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች በአምልኮታቸውና ቁርአንንም የሰብእናቸው አካል በማድረጉ ሂደት የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ፈለግ ይከተሉ ነበር፡፡ ኪሃና አል አደዊ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይላል፡-

“አንድ ጊዜ ኡመር ኢብን አል-ኸጧብ (ረ.ዐ.) ለሰራዊታቸው አዛዦች እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፉላቸው፡-

“ቁርአንን በቃላቸው ያጠኑ ሰዎችን ከመካከላችሁ ለዩልኝና ልወቃቸው፡፡ ከዚያም ቁርአንን ለሰዎች ያስተምሩልኝ ዘንድ ልሾማቸውና በክብር ልልካቸው እፈልጋለሁ፡፡”

በዚሁ የኡመር (ረ.ዐ.) ጥያቄ መሠረት አቡ ሙሳ አል-አሽዓሪ (ረ.ዐ.) በእርሳቸው እዝ ስር ሶስት መቶ የሚሆኑ ቁርአንን በቃላቸው ያጠኑ

(ሃፊዞች) እንዳሉ በመጥቀስ አሳወቁ፡፡ ኡመር (ረ.ዐ.) ለእነዚያ ሃፊዞች ከጻፉላቸው ምክር የተወሰነውን ከዚህ በታች እናቀርባለን፡፡

"ቁርአን የክብራችሁ ምንጭና ከፈጣሪ የተሰጣችሁ ሽልማት እንደሆነ እወቁ፡፡ እርሱን ተከተሉ እንጂ እንዲከተላችሁ አታድርጉ፡፡ ቁርአንን ከኋላው ለማስከተል የሚሞክሩ ጭንቅላታቸው ተዘቅዝቆ ወደ ጀሃነም እሳት እንደሚጣሉ አትዘንጉ፡፡ ለቁርአን ታማኝ የሆነ በላእላይ ጀነት በፊርደውስ እንደሚሰፍር ተስፋ ያድርግ፡፡ ሁላችሁም አቅማችሁ የቻለውን ያክል የቁርአንን ትዳጌ (አማላጅነት) ለማግኘት ጥረት አድርጉ እንጂ በናንተ ላይ መስካሪ አድርጋችሁ አትያዙት፡፡ ምክንያቱም ቁርአን ያማለደው ሰው ጀነት እንደሚገባና በእርሱ ላይ የመሰከረበት ደግሞ ጀሃነም እንደሚወርድ እሙን ነውና፡፡ ቁርአን ወደ ቀናው መንገድ የመመራትና የእውቀት ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ ከአዛኙ ፈጣሪ ወደ ሰብአዊው ፍጡር የተላከ የመጨረሻው መጽሐፍ ነው፡፡ እነሆ የታወሩ አይኖች፣ የተደፈኑ ጆሮዎች፣ የተዘጉ ልቦች በእርሱ ይከፈታሉ…" (አሊ አል-ሙተቂ)

በልጅነታቸው ጊዜ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለረዥም ዘመናት ያገለገሉት አነስ ኢብኑ ማሊክ (ረ.ዐ.) ቁርአንን ባኸተሙ ቁጥር ሁሉ ቤተሰባቸውን በሙሉ ሰብስበው የኸትም ዱዓ (ቁርአን ሲኸተም የሚደረገውን ዱዓ) ያደርጉ ነበር፡፡ (ኢብን አቢ-ሸይባ)

አቡ ሙሣ አል-አሽዓሪ (ረ.ዐ.) መልካም ለዛና የሚያምር ቃና ባለው ድምጽ ቁርአንን ያነቡ ስለነበር በየጊዜው ቁርአን እንዲያነቡላቸው ኡመር ኢብን አል-ኸጧብ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ይጠይቋቸው ነበር፡-

"አቡ ሙሣ ሆይ! እባክህ ጌታችንን እንድናስታውስ አድርገን!" በዚህ ጊዜ አቡ ሙሣ (ረ.ዐ.) ከቁርአን ምእራፎች ውስጥ የተወሰነውን ያነባሉ፡፡ አንድ ጊዜ እንደተለመደው ኡመር (ረ.ዐ.) አቡ ሙሣን (ዐ.ሰ.) እንዲህ አሏቸው፡-

"ወንድሜ ሆይ! ለጌታችን ያለን ፍላጎት ይጨምር ዘንድ አንብብልን!"

አቡ ሙሣም (ረ.ዐ.) ቁርአን ማንበባቸውን ቀጠሉ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ካነበቡ በኋላ ኡመር (ረ.ዐ.) ሶላት እንዲያሰግዱ ተጠሩ፡፡ እጅግ ተመስጠው ሲያዳምጡ የነበሩት ኡመር (ረ.ዐ.) በድንገት ተነሱና እንዲህ አሉ፡-

"እስከአሁን ሶላት ላይ አልነበርንም እንዴ?" (ኢብን ሰዒድ)

ናፊእ የተባለውን የአብደላህ ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) አገልጋይ አንድ ጊዜ ሰዎች እንዲህ በማለት ጠየቁት፡-

"አብደላህ በቤቱ ሲሆን ምንድን ነው የሚያደርገው?"

ናፊእ እንደሚከተለው በማለት መልስ ሰጣቸው፡-

"ሰዎች እርሱ የሚያደርገውን ነገር ማድረግ አይችሉም፡፡ ሁልጊዜም አንድ የሶላት ወቅት ሲመጣ ውዱእ ያደርግና ከሰገደ በኋላ የሚቀጥለው የሶላት ወቅት እስከሚመጣ ድረስ ቁርአን ከፍቶ ሲያነብ ይቆያል፡፡" (ኢብን ሰዓድ)

እውነተኛ የቁርአን ወዳጆችና በቃላቸው ያጠኑ ሰዎች በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም ከጌታቸው ዘንድ ታላላቅ ስጦታዎችን ይስሰጣሉ፡፡ ሙሐመድ ሳሚ ራማዛኖግሉ ስለ አንድ ስለሚያውቀው ሃፊዝ ሰው እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- "ይህ ሰው በአዲና (ቱርክ) ከሰላሳ ዓመታት በፊት ነበር የሞተው፡፡ ከዚያ በኋላ መቃብሩ ያረፈበት ቦታ አዲስ መንገድ ሊሰራበት ስለታሰበ አጽሙ ወደ ሌላ ሥፍራ መዛወር ነበረበት፡፡ መቃብሩ ሲከፈት ሰውነቱ ሊፈራርስ ይቅርና የተገነዘበት ጨርቅ እንኳን አልወየበም፡፡"

በሐዲስ እንደሚከተለው ተብሎ ተጽፏል፡-

"ቁርአንን የሃፈዘ (በቃሉ ያጠና) እንዲሁም በእርሱ ሲሰራበት የቆየ ሰው ሲሞት አላህ ምድርን አካሉን እንዳትበላ ያዛታል፡፡ እርሷም ለትእዛዙ የሚከተለውን መልስ ትሰጣለች፡-

"ጌታዬ ሆይ! በደረቱ ውስጥ ያንተን ንግግር የያዘን ባሪያ እንዴት አድርጌ እበላዋለሁ" (ዳይለሚ፤ አሊ፡ አል-ሙተቂ)

እንግዲህ ተራሮች እንኳን ክብደቱን መሸከም ፈርተው አንቀበልም ያሉትን አደራ (ዲን) እኛ ሰዎች የተሸከምነው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ቁርአንን በተመለከተም ማድረግ የሚገባንን ጥንቃቄና መስጠት የሚገባንን ክብር ሁልጊዜም ማጓደል አይኖርብንም፡፡ ምክንያቱም አሁን እኛ እየኖርን ያለነው ብዙ መንፈሳዊ ፀጋዎችና መልካም ሥራዎች በተጓደሉበት ዘመን ላይ እንደመሆኑ የቁርአንን መንፈሳዊ ፀጋ እየተቋደስን ነው ለማለት ስለማያስደፍር ነው፡፡

ለአብነት ያክል ውዱእ ሳናደርግ ቁርአንን መንካትም ሆነ ማንበብ አይኖርብንም፡፡ የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ በግልጽ የሚነግረን ይህንኑ ነው፡-

﴿ لَّا يَمَسُّهُۥٓ إِلَّا ٱلۡمُطَهَّرُونَ ٧٩ ﴾ الواقعة: ٧٩

*"የተጥራሩት እንጂ ሌላ አይነካውም፡፡" (አል-ዋቂአህ፡ 79)*

ይህ አንቀጽ የሚያስረዳን ውዱእን፣ ከጀናባ መንጻትን፣ ከወር አበባና የወሊድ ደም መንጻትን ሁሉ ነው፡፡ አራቱ የታወቁ የፊቅህ ት/ቤቶች (መዝሃቦች) ቁርአንን ያለ ውዱእ መንካት እንደማይቻል ከሞላ ጐደል ይስማማሉ፡፡ ይህ ደንብ ከ1400 ዓመታት በፊት ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለውም ለዚሁ ነው፡፡ እርግጥ ነው ከፍ ሲል የተጠቀሰውን የቁርአን አንቀጽ በሌላ መንገድ የሚተረጉሙ የኢስላም ምሁራን አሉ፡፡ እንደነርሱ አባባል "የተጥራሩት እንጂ ሌላ አይነካውም" የሚለው አባባል የተጠበቀውን ሰሌዳ (ለውሃል ማህፉዝን) የሚመለከትና `የተጥራሩ` የተባሉትም መላእክት ናቸው፡፡ ይህ አባባል የሚያስኬድ ቢመስልም ብዙ ድጋፍ የሚሰጠው አይደለም፡፡

በተጨማሪም የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አምር ቢን ሃዝምን (ረ.ዐ.) ወደ የመን ሲልኩት አንድ ሰነድ (መግለጫ) አስይዘው ሲሆን በዚያ ሰነድ ላይም ፈርድ (ግዴታ) የሆኑ አምልኮቶች፣ ሱና የሆኑ ነገሮችና ሸሪዓዊ ሕግጋቶች ሁሉ ተጠቅሰዋል፡፡ እንዲሁም በሰነዱ ላይ የተጠቀሰው ሌላው ጉዳይ አምር ሕዝቦቹን ቁርአን እንዲያስተምራቸው፣ ትእዛዛቱንና

ክልከላዎችን፣ በውስጡ የያዛቸውን ጥበባት እንዲሁም ውዱእ ሳያደርጉ እንዳይነኩት ጭምር እንዲነግራቸው ታዟል፡፡ (ሙወጣእ)

የኢማም ማሊክ አቋም በሚከተለው አኳኋን ተገልጿል፡-

ማንም ቢሆን ውዱእ ሳይኖረው ቁርአንን በማንጠልጠያም ቢሆን እንዳይሸከመው፣ ከትራስ ላይ አድርጎም እንዳያነሣው የከለከሉ ሲሆን ይህ ሁሉ የተጠላ ድርጊት ነው ብለዋል፡፡ ይህን ያሉትም ቁርአንን ለማላቅና ከላይ የተሰጠውን ከፍ ያለ ክብር ጠብቀው ለማቆየት በመሻት ነው፡፡

በተጨማሪም ማንም ቢሆን የቁርአንን ክብር በሚዳፈርና ደረጃውን ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ ሊይዘው እንደማይገባ መታወቅ አለበት፡፡ ይህም ከዝቅተኛ ቦታ ላይ ማስቀመጥ፣ መሬት ላይ መጣል፣ ሌሎች መጻህፍትን (ኃይማኖታዊም ቢሆኑ) ከላዩ ላይ መደርደር፣ ቁርአን ወደ ተቀመጠበት ቦታ እግርን መዘርጋት፣ እንደተገለጠ ትቶ ሌላ ሥራ መሥራት ወይም ማውራት፣ ላዩ ላይ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማስቀመጥ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነውና መሆን የሚገባው ልክ እንደ አምልኮት (ኢባዳ) አካል ተቆጥሮ ነው፡፡ ምክንያቱም ቁርአን የአላህ ንግግር ከሆነ እርሱን አከበርን አላቅን ማለት ያወረደውን አካል አከበርን፣ አላቅን ማለት ነውና፡፡ ይህም ስሜትና መንፈስ ከትውልድ ትውልድ መተላለፍ ይኖርበታል፡፡

ኃያሉና ጥበበኛው አላህ የኃይማኖቱን ምልክቶች እንድናከብርና ልቅና እንድንሰጣቸው በግልጽ የረብኛ ቋንቋ ባወረደው ቁርአኑ ላይ እንዲህ በማለት ገልጿል፡-

﴿ ذَٰلِكَ وَمَن يُعَظِّمْ شَعَـٰٓئِرَ ٱللَّهِ فَإِنَّهَا مِن تَقْوَى ٱلْقُلُوبِ ۝٣٢ ﴾ الحج: ٣٢

*"…የአላህን የኃይማኖት ምልክቶች የሚያከብር ሰው እርሷ ከልቦች የሆነች ጥንቃቄ ናት፡፡" (አል-ሐጅ፡32)*

ለቁርአን አካላዊም መንፈሳዊም አክብሮትን እንድናሳይና አጥብቀንም እንድይዘው ለአለማት እዝነት ተደርገው የተላኩት ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ይመክሩናል፡-

“…ቁርአን ልክ እንደ ጠንካራ ገመድ ሆኖ አንዱ ጫፉ ያለው ከአላህ ዘንድ ሲሆን ሌላው ጫፉ ደግሞ በእናንተ እጅ ነው፡፡ ስለሆነም አጥብቃችሁ ያዙት፡፡ እንደዚያ ካደረጋችሁ ጥመት አይነካችሁም፡፡ አትጠፉምም፡፡” (ሃይሰሚ)

ከቁርአን ብዙ መንፈሳዊ ትሩፋቶችንንና ፀጋዎችን ባገኘን ቁጥር እምነታችንም የዚያኑ ያክል እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ እነዚያ ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ለቁርአን የሰጡ በዚህም የአላህንና የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ውዴታ የከጀሉ የኋላ ኋላ መጨረሻቸው የሚያምርና ቃላት ተሰባስበው ሊገልጹት በማይችሉት የድሎት ሃገር (በጀነት) የሚጨጉሉ መሆኑ እውነት ነው፡፡ አላህ ከእነዚህ ሰዎች መካከል ያድርገን፤ አሚን!”

# ምዕራፍ ስምንት

# ዚክር ማድረግና ሰለዋት ማውረድ

‘ኢንሳን’ የሚለው የአረብኛ ቃል ሰው የሚል ትርጓሜን የያዘ ሲሆን ‘ኒስያን’ ከሚለውና ‘መርሳት’ የሚል ትርጉም ካዘለው ሥርወ-ቃል የተገኘ ነው። ይህም ዚክር (ማስታወስ) ከሚለው ቃል ተቃራኒ የሆነና የሰውን ልጅ ከተጠናወቱት ድክመቶች አንዱ ነው። በዚህ ኒስያን (መርሳት) በተባለ አባዜ የሰው ዘር ከሚደርስበት ጉዳት በዚክር (አላህን በማሰታወስ) መድህን ማግኘት ይችላል። ምክንያቱም አንድን ነገር ደጋግሞ ማውሳትና ማስታወስ ለዚያ ነገር ያለንን ትኩረት እንዲጨምር ስለሚያደርገው ነው። በዚሁ መሠረት አላህን ደጋግመን ባስታወስን ቁጥር ከሰብዓዊነታችን ጋር ተያይዘው የሚከሰቱብን ችግሮች ሁሉ ይቀሉልናል፣ ይወገዱልናል።

‘ዚክር’ የሚለው ቃል በቁርአን ውስጥ ከሁለት መቶ ሃምሣ ጊዜ በላይ ተጠቅሷል። አንድ የአላህ ባሪያ እውነተኛ የእርሱ አገልጋይ መሆን የሚችለው ስለ አላህ ተገቢ የሆነ እውቀት ሲኖረውና ሃቆቹንና ከእርሱ የሚጠበቅበትን ግዴታ ሁሉ ለይቶ ሲገነዘብ ብቻ ነው። ይህ ሁሉ የሚገኘው ደግሞ ስለ አላህ በጥልቀት ከማሰብ፣ ቁርአንን ከማንበብና ከማስተንተን እንዲሁም መንፈሳዊ እውቀትን በመሰብሰብ ነው። ይህ ሁሉ ሲጠቃለል ዚክር በሚባል በሰው ልጅ ልቦናና አእምሮ ላይ በሚከናወን የወል ስም ይጠራል። ጌታችን አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱذۡكُر رَّبَّكَ فِي نَفۡسِكَ تَضَرُّعٗا وَخِيفَةٗ وَدُونَ ٱلۡجَهۡرِ مِنَ ٱلۡقَوۡلِ بِٱلۡغُدُوِّ وَٱلۡأٓصَالِ وَلَا تَكُن مِّنَ ٱلۡغَٰفِلِينَ ٢٠٥ ﴾ الأعراف: ٢٠٥

*“ጌታህንም በምስጢር ተዋድቀህና ፈርተህ ከጩኸት በታችም በሆነ ቃል በጧትም በማታም አውሳው። ከዘንጊዎቹም አትሁን።” (አል-አዕራፍ: 205)*

﴿ وَلَذِكۡرُ ٱللَّهِ أَكۡبَرُۗ ﴾ العنكبوت: ٤٥

"…አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው።" (አል-ዐንከቡት፡45)

﴿ ٱلَّذِينَ يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمٗا وَقُعُودٗا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمۡ ﴾ آل عمران: ١٩١

*"(እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጐኖቻቸው ተጋድመውም አላህንየሚያወሱ…"(አሊ-ዒምራን፡191)*

የሰውነታችን ሁሉ ዋነኛ አንቀሳቃሽ የሆነችው ልብ (ቀልብ) አላህን በማስታወስ ሕያው ከሆነች ሃቅንና ባጢልን (ሃሰትን) ለመለየት የሚያስችላት ብርሃን በውስጧ ትምሞላለች። ያን ጊዜ መላውን አካል ወደ እውነትና ወደ ጽድቅም መንገድ እየመራች ትጓዛለች። ለሌሎቹ የአካል ክፍሎችም ተገቢ የሆነውን አመራር እየሰጠች በአጠቃላይ ውጤቱም ሰውየውን አላህ የሚወደውና የሚደሰትበትም ታደርገዋለች ማለት ነው።

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የዚክርን ትሩፋት እንደሚከተለው በማለት ገልፀውታል፡-

"አላህን የሚያስታውስና የማያስታውስ ሰው ምሳሌያቸው ሕያው እንደሆነና እንደሞተ ሰው ብጤ ነው።" (ቡኻሪ)

በተመሳሳይ ሁኔታ አላህን ከማስታወስ የራቁ የእርሱንም ፍቅር ከማግኘት ርቀዋልና በመለኮታዊው ዛቻ ስር ናቸው። ይህን አስመልክቶ በቁርአን እንደሚከተለው ተብሎ ተጽፏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُلۡهِكُمۡ أَمۡوَٰلُكُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُكُمۡ عَن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ وَمَن يَفۡعَلۡ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ٩ ﴾ المنافقون: ٩

*"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ አላህን ከማስታወስ አያታልሏችሁ። ይህንንም የሚሰሩ ሰዎች እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎቹ ናቸው።" (አል-ሙናፊቁን፡9)*

﴿ فَوَيۡلٞ لِّلۡقَٰسِيَةِ قُلُوبُهُم مِّن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ ﴾ الزمر: ٢٢

*"...ልቦቻቸውም ከአላህ መወሳት ለደረቁ ሰዎች ወዮላቸው..." (አዝ-ዙመር:22)*

﴿ وَمَن يَعْشُ عَن ذِكْرِ ٱلرَّحْمَٰنِ نُقَيِّضْ لَهُۥ شَيْطَٰنًا فَهُوَ لَهُۥ قَرِينٌ ﴿٣٦﴾ ﴾ الزخرف: ٣٦

*"ከአር-ራሕማን ግሣጼ (ከቁርአን) የሚደናበርም ሰው ለእርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን:: ስለዚህ እርሱ ለእርሱ ቁራኛ ነው::" (አዝ-ዙኽሩፍ:36)*

﴿ وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِى فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ أَعْمَىٰ ﴾

*"ከግሳጼዬም የዞረ ሰው ለእርሱ ጠባብ ኑሮ አለው:: በትንሳኤም ቀን እውር ሆኖ እንቀሰቅሰዋለን::" (ጣሃ:124)*

የአለማቱ ጌታ አላህን ከማስታወስ ጐናቸውን የሚያጥፉና እርሱ ባወረዳቸው የሥነ ምግባር ደንቦች ለመመራት አሻፈረን ያሉ ተደጋጋሚ ዛቻና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል:: ከእነዚህ ማስጠንቀቂያዎች አንዱ እንዲህ ይላል:-

﴿ أَلَمْ يَأْنِ لِلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَن تَخْشَعَ قُلُوبُهُمْ لِذِكْرِ ٱللَّهِ وَمَا نَزَلَ مِنَ ٱلْحَقِّ وَلَا يَكُونُوا۟ كَٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ مِن قَبْلُ فَطَالَ عَلَيْهِمُ ٱلْأَمَدُ فَقَسَتْ قُلُوبُهُمْ ۖ وَكَثِيرٌ مِّنْهُمْ فَٰسِقُونَ ﴿١٦﴾ ﴾

*"ለእነዚያ ላመኑት ለአላህ ተግሳጽና ልቦቻቸው ሊፈሩ እንደነዚያም በፊት መጽሐፍን እንደተሰጡቶች በእነርሱ ላይ ጊዜ እንደረዘመባቸው ልቦቻቸውም እንደ ደረት ላይሆኑ (ጊዜው) አልቀረበምን? ከእነርሱም ብዙዎቹ አመፀኞች ናቸው::" (አል-ሐዲድ :16)*

ይህ የቁርአን አንቀጽ የወረደው በመካ ስቃይና ሃዘን የሞላበት ሕይወት ሲገፉ ከቆዩ በኋላ ወደመዲና የተሰደዱ ጥቂት ያመኑ ሰዎችን አስመልክቶ ሲሆን እነዚያ ሰዎች መዲና ከደረሱና ብዙ ፀጋዎችን ካገኙ በኋላ የኃይማኖታቸውን ጉዳይ ችላ ማለት በመጀመራቸው ነው:: (ሱዩጢ)

ሙሣና ሃሩን (በሁለቱም ላይ የአላህ ሰላም ይስፈን) ነቢያት ቢሆኑም ኃያሉ አላህ ወደ ፈርኦን ሲልካቸው የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነበር፡-

﴿ ٱذۡهَبۡ أَنتَ وَأَخُوكَ بِـَٔايَٰتِي وَلَا تَنِيَا فِي ذِكۡرِي ۝٤٢ ﴾ طه: ٤٢

*"አንተም ወንድምህም በተዓምራቶቼ ሂዱ፡፡ እኔንም ከማውሳት አትቦዝኑ፡፡" (ጣሃ:42)*

እንግዲህ ጥበበኛው አላህ ነቢያቱን እንኳን እርሱን ከማውሳት እንዳይቦዝኑ የሚያስጠነቅቅ ከሆነ ሌሎች ባሮቹ ከዚህ ተግሳጽ ምን ትምህረት ሊቀስም ይችላል፡፡

ሁልጊዜም አላህን ማስታወሰና ጥንቁቅ የመሆንን (ሙራቀባህ) አስፈላጊነት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

"በማይረባና እንቶ ፈንቶ በሆነ ወሬ ተጠምዳችሁ አላህን አትርሱ፡፡ ምክንያቱም ብዙ ማውራት አላህን ከማስረሳቱም በላይ ቀልብን (ልብን) ያደርቃል፡፡ ከአላህ የራቀ ሰው ማለት የደረቀ ቀልብ (ልብ) ያለው ነው፡፡" (ቲርሚዚ)

እንግዲህ አማኞች ልባቸው አላህን ከመዘንጋትና ከግዴለሽነት እንዲርቅ ለማድረግ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ በተከታታይና በዘውታሪነት አላህን በማስታወስ ነው፡፡ ይህ የአንድ ወቅት ወይም ጊዜያዊ ተግባር መሆን የለበትም፡፡ ዚክር የሕይወት ሙሉ ተግባር ነው፡፡

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባለቤት አዒሻ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብላለች፡-

"እያንዳንዱ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሁኔታና ድርጊታቸው አላህን የሚያስታውስ (ዚክር) ነው፡፡" (ሙስሊም)

ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ ذِكۡرٗا كَثِيرٗا ٤١ ﴾ الأحزاب: ٤١

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት” (አል-አሕዛብ:41)*

“ከሁሉም የበላይ የሆነው አላህ ግዴታ የተደረጉ የአምልኮት ዓይነቶችን ባሪያዎቹ ይፈጽሙ ዘንድ ጊዜንና አሰራርን ገድቧል፡፡ እንዲሁም ጥፋት ላይ ለወደቁት ባሪያዎቹ ደግሞ በንጹህ ልብና በእውነተኛ ንስሃ ወደ እርሱ እስከተመለሱ ድረስ ይቀበላል፡፡ ሆኖም ግን ዚክርን በተመለከተ ምንም ዓይነት ገደብ፣ የጊዜ ምጣኔና ልክ አላደረገም፡፡ ማንኛውም ሰው ነፍሱንና ጽሞናውን ወደፈጣሪው መመለስ በቻለበት በየትኛውም አጋጣሚና ሁኔታ ሁሉ እርሱን እንዲያስታውስ መድረኩን ሁሉ ክፍት አድርጓል፡፡ በመሆኑም ኃያሉ አላህ የሰው ልጅ የትም ሥፍራ፣ ቢሆን በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ያስታውሰው ዘንድ አደራ ብሏል፡፡” (ጦበሪ)

ሰዎች ዚክርን (አላህን ማስታወስን) እንዲያበዙ ለማበረታታት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

“ከኢስማኢል ዘር የሆኑ አራት ባሪያዎችን ነጻ ከማድርግ ይልቅ ከሱብህ (ፈጅር) ሶላት በኋላ ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ አላህን ከሚያስታውሱ ሰዎች ጋር ብሆን የበለጠ ያስደስተኛል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አራት ሰዎችን ከባርነት ነጻ ከማድረግ ይልቅ ከአስር ሶላት በኋላ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ አላህን ከሚያወሱ ሰዎች ጋር ብሆን የበለጠ ያስደስተኛል፡፡” (አቡ ዳውድ)

በተጨማሪም በአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ የምናወርደው ሰለዋትና ሰላምታም አላህን እንደማስታወስ (ዚከር) ይቆጠርልናል፡፡ ኃያሉ አላህ ብርሃን በተሞላው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيۡهِ وَسَلِّمُواْ تَسۡلِيمًا ٥٦ ﴾ الأحزاب: ٥٦

*“አላህና መላእክቱ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ። የማክበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ።” (አል-አሕዛብ:56)*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የዚህን ሰለዋትና ሰላምታ ጥቅም ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ ሰው በእኔ ላይ አንድ ሶለዋት ሲያወርድ ከሁሉም የበላይ የሆነው አላህ በእርሱ ላይ አሥር እጥፍ ያወርድለታል፣ አሥር ኃጢአቶቹን ይሰርዝለታል፣ እንዲሁም አሥር ደረጃዎችን ይጨምርለታል።” (ነሳኢ)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ የሚከተለውን ብለዋል፡-

“በፍርዱ ቀን ከሰዎች ውስጥ ወደእኔ የሚቀርቡት በእኔ ላይ ብዙ ሰለዋትና ሰላምታ ያወረዱብኝ ናቸው።” (ቲርሚዚ)

በመጨረሻም ስለዚክር ስናነሳ ግዴታ የተደረጉ ሶላቶች፣ ፆም፣ የሐጅ ፀሎት፣ ዘካ፣ ተስቢህ (አላህን ማጥራት)[1]፣ ተህሚድ (አላህን ማመስገን)፣ ተክቢር (አላህን ማላቅ ወይም ማወደስ) ወዘተ ዚክር መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርብናል።

እንዲሁም ቁርአንን ማንበብ፣ ማስተንተን (ተደቡር)፣ አንቀፆቹን ለመተግበርና የስብእና ክፍል ለማድረግ መታገል ሁሉ ዚክር ነው።

---

*[1] አላህን ማጥራት (ተስቢህ) ማለት አላህ ጉድለት ኖሮበት ከዚያ ጉድለት ማጥራት ሳይሆን ከጉድለት ሁሉ የጠራ (ምሉእ በኩሉሄ) ለሆነው የዓለማት ጌታ ባሕሪያትና ስሞች እውቅናን መስጠት ነው።*

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

የምእመናን እናት የሆነችው ዓኢሻ (ረ.ዐ.) የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሌሊት ሶላት (ተሃጁድ) ለመስገድ ሲነሱ እያንዳንዱን አሥር አሥር ጊዜ "አላሁ አክበር" (አላህ ታላቅ ነው)፣ "አልሃምዱሊላህ" (ምስጋና ለአላህ ይገባው)፣ "ሱብሃነሏሂ ወቢሃምዲሂ" (ለአላህ ጥራት ይገባው ምስጋና ለአላህ ይገባው)፣ "ሱብሃን አል-መሊኩል ቁዱስ" (ለአላህ ጥራት ይገባው፣ለንጉሱ፣ ቅዱስ ለሆነው)፣ "አስተግፊሩሏህ" (አላህን ምህረት እጠይቃለሁ)፣ "ላኢላሃኢለሏህ" (ከአላህ በስተቀር ጌታ የለም) ካሉ በኋላ አሥር ጊዜ እንዲህ ይላሉ፡-

اللهم إنى أعوذ بك من ضيق الدنيا ومن ضيق الأخرة

"አላህ ሆይ! በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም ከጭንቀትና ጥበት በአንተ እጠበቃለሁ።"

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን ካሉ በኋላ ሶላታቸውን ይጀምራሉ።" (አቡዳውድ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ማድረግ የሚመርጡት አጭር ሆኖም ግን መልእክቱ ጥልቅ የሆነን ዚክር ነው። አንድ እለት ባለቤታቸው ጁዌይሪያ (ረ.ዐ.) የሱብሂን (ፈጅርን) ሶላት ሰግዳ በዚያው በሰገደችበት ቦታ ሳትንቀሳቀስ ተቀምጣ ዚክር ማድረግ ጀመረች። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ግን በጧት ከቤታቸው ወጥተው ከቆዩ በኋላ ሲመለሱ ጁዌይሪያን (ረ.ዐ.) እዚያው ከተቀመጠችበት ቦታ ላይ እንዳለች ሲያገኙዋት እንዲህ በማለት ጠየቋት፡-

"እኔ ትቼሽ ከሄድኩኝ በኋላ እስካሁን ድረስ እዚሁ ሆነሽ ዚክር እያደረግሽ ነበርን?" መልሷ "አዎን" የሚል በሆነ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"እነዚህን ዓረፍተነገሮች ሶስት ሶስት ግዜ ብትይ ኖሮ ከጧት ጀምረሽ እዚህ ቁጭ ብለሽ ካደረግሽው ዚክር ጋር በምንዳ ይመጣጠኑልሽ ነበር።

سبحان الله وبحمده عدد خلقه ورضا نفسه وزنة عرشه ومداد كلماته

*‹‹በፍጡራኑ ልክ የሆነ እርሱን የሚያስደስት፣ ዙፋኑንና የማይነጥፍ ቃሉን የሚመጥን ክብርና ምስጋና ለአላህ ይድረሰው፡፡››*

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"ለምላስ የቀለሉ ለሚዛን የከበዱና አላህን የሚያስደስቱ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች አሉ እነርሱም፡-

**"سبحان الله وبحمده سبحان الله العظيم "**

"ሱብሃነሏህ ወቢሃምዲሂ ሱብሃነሏሂል አዚም" የሚሉት ናቸው፡፡"

ኃያሉ አላህ በእያንዳንዱ ጊዜና በእያንዳንዱም ሁኔታ የባሮቹ ልቦች እርሱን በማውሳት ብቻ እንዲያዙ ይፈልጋል፡፡ በሚቀጥለው የቁርአን አንቀጽ እንደተገለፀውም እንዲህ ዓይነት ባሮቹን አላህ ያወድሳቸዋል፡፡

﴿ ٱلَّذِينَ يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمٗا وَقُعُودٗا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمۡ ﴾ آل عمران: ١٩١

*"(እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጐኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ..." (አሊ-ዒምራን፡191)*

አብዱላህ ቢን በስር (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት አስተላልፏል፡-

"ሁለት የገጠር አእራቦች (በድዊኖች) ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መጡና አንደኛው እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከሰዎች ሁሉ በላጩ ማን ነው?" የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለው መለሱለት፡-

"ረዥም እድሜ ኖሮት ስራው ያማረለት ሰው፡፡" ሌላው ደግሞ እንዲህ በማለት ጥያቄ አቀረበላቸው፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የኢስላም ህግጋት ብዙ ናቸው፡፡ አንድ መልካም ሥራን አጥብቄ እይዝ ዘንድ ይንገሩኝ፡፡"

“ምላስህ ምንግዜም አላህን በማስታወስ የረጠበች ትሁን፡፡” (አህመድ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ስለዚክር ይህን ያክል አጽንኦት ሰጥተው የተናገሩትና ያስተማሩት አማኞች ምንጊዜም ቢሆን በዚክር ላይ ከሆኑ ከቸልተኝነትና ከመርሳት ተወግደው ወደ አላህ ይቀርባሉና ነው፡፡ ዚክር ማድረግ የአላህን ትእዛዝ ለማክበርና ክልከላዎቹንም ለመጠንቀቅ በልብ (ቀልብ) ላይ ተነሳሽነትን ይጨምራል፡፡ ወደ ኃያሉ አላህ ውዴታም ያቃርባል፡፡

አንድ ሰው ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“ታላቅ ምንዳ የሚያስገኘው የትኛው ጅሃድ ነው?” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መለሱለት፡-

“አላህን በብዛት የሚያወሳ ሰው ጅሃድ፡፡” ሰውዬው አሁንም ሌላ ጥያቄ አቀረበላቸው፡-

“የትኛው የፆም ዓይነት ነው ታላቅ ምንዳ የሚያስገኘው?”

“አላህን በብዛት የሚያወሳ ሰው ፆም” በማለት መልስ ሰጡት፡፡ ከዚያ በኋላ ሰውየው ተመሳሳይ የሆነን ጥያቄ ለሶላት፣ ለዘካ፣ ለሐጅና ለሶደቃ ጠየቃቸው፡፡ ለእነዚህ ነገሮች ሁሉ መልሳቸው ተመሳሳይ ነበር፡-

“አላህን በብዛት የሚያወሳ ሰው፡፡”

በዚህ ጊዜ አቡበክር (ረ.ዐ.) ኡመርን (ረ.ዐ.) እንዲህ አሏቸው፡-

“ኡመር ሆይ! አላህን የሚያወሱ ሰዎች ሁሉንም የበጐ ምግባር ድርሻ ወሰዱትኮ!” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ ጊዜ ወደነርሱ ፊታቸውን አዙረው እንዲህ አሉ፡-

“አዎን! ይህ እውነት ነው፡፡” (አህመድ፣ ሃይሰሚ)

ሁልጊዜም ራሳችንን በዚክር ካሰለጠንና ከጠመድን በሁሉም የመልካም ሥራ አትራፊዎች መሆናችን አይቀርም፡፡

ሙዓዝ ኢብን ጀበል (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

“አንድ ጊዜ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አልኳቸው የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ጥቂት ምክር ይስጡኝ፡፡”

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መለሱልኝ፡-

“የቻልከውን ያክል አላህን ፍራ፡፡ ከድንጋይ ወይም ዛፍ አጠገብ ብትሆን የትም ሆነህ አላህን ፍራ፡፡ በድብቅ ለሰራኸው ኃጢአት አላህን በድብቅ ይቅርታ ጠይቀው፡፡ ሆኖም ግን በግልጽ ለሰራኸው ኃጢአት በግልጽ ይቅርታ ጠይቀው፡፡” (ሃይሰሚ)

አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለባልደረቦቻቸው ዚክር ለማድረግ ስለመሰባሰብ ጥቅም እንዲህ በማለት ይነግሯቸው ነበር፡-

“በጀነት ጨፌ አጠገብ ካለፋችሁ አረፍ ብላችሁ ተጠቀሙ፡፡”

“የጀነት ጨፌ ምንድን ነው የአላህ መልእክተኛ” ተብለው ተጠየቁ፡፡

“ዚክር የሚደረግበት (አላህ የሚወሳበት) ቦታ” በማለት መለሱ፡፡

አብደላህ ኢብን ረዋሃ (ረ.ዐ.) አንድ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባ ባገኘ ቁጥር እንዲህ ይል ነበር፡-

“ወንድሜ ሆይ! ለጥቂት ጊዜ አረፍ እንበልና በጌታችን ላይ ያለንን እምነት እናድስ (ዚክር እናድርግ)፡፡”

አንድ ባልደረባቸው ይህ የአብደላህ (ረ.ዐ.) ድርጊት ስላልገባው ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በመሄድ ስለሁኔታው ነገራቸው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጉዳዩን ከሰሙ በኋላ እንዲህ አሉ፡-

“አብደላህ ኢብን ረዋሃ አላህ ይዘንለት፡፡ መላእክት የሚያደንቁትን ለዚክር መሰባሰብ ያፈቅራል፡፡” (አህመድ)

አብደላህ ቢን ሸዳድ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

“ከበኒ ኡዝራ የሆኑ ሶስት ሰዎች ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘንድ ከመጡ በኋላ ኢስላምን ተቀበሉ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ጥያቄ አቀረቡ፡-

“እነዚህን ሰዎች የሚንከባከብልኝ ማን ነው”

ጦልሃ (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡-

“እኔ እንከባከባቸዋለሁ የአላህ መልእክተኛ!”

እነዚህ ሰዎች ከጠለሃ (ረ.ዐ.) ጋር ሳሉ የአላህ መልእክተኛ አነስተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊት ወደ አንድ ቦታ አሰማሩ፡፡ ከሶስቱ ሰዎች አንዱ ከዚያች አነስተኛ ቁጥር ያላት ሰራዊት ጋር አብሮ ከዘመተ በኋላ በዚያ እያለ ተሰዋ (ሸሂድ ሆነ)፡፡ ከዚያም የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሌላ አነስተኛ ሰራዊትን የያዘ ጓድ ለዘመቻ አሰማሩ፡፡ ከእነዚህ ጋር ሁለተኛው ሰው አብሮ ዘመተ፡፡ ሆኖም ግን እርሱም ተሰዋ (ሸሂድ ሆነ)፡፡ ከዚያ በኋላ ሶስተኛው ሰው ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአልጋው ላይ እያለ ሞተ፡፡

ጦልሃ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይላል፡-

“እነዚህን ሶስት ሰዎች በሕልሜ በጀነት ውስጥ አየሁዋቸው፡፡ ከአልጋው ላይ ሆኖ የሞተው የመጀመሪያው ነው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ለዘመቻ በሁለተኛ ዙር ወጥቶ የተሰዋው ሆነ፡፡ የመጨረሻ ደረጃን የያዘው በመጀመሪያው ዙር ዘምቶ የተሰዋው ሆነ፡፡ በዚህ ሁኔታ በጣም ተደንቄና በትንሹም ቢሆን ተናድጄ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በመሄድ ስለሁኔታው ሳጫውታቸው እንዲህ አሉ፡-

“ይህ ሊገርምህ አይገባም፡፡ በአላህ ዓይን ሁልጊዜም በቋሚነት ተስቢህ፣ ተክቢርና ተህሊል ከሚልና ሕይወቱን በኢስላም አስተምህሮቶች ከሚመራ ሰው የበለጠ መልካም ሰሪ የለም፡፡ (አህመድ)

አንድ እለት ኡፍቴድ ወደገጠራማው የቱርክ ግዛት ከተማሪዎቹ (ደረሳዎቹ) ጋር ሄደ፡፡ ከዚያም ውብ በሆነው የገጠር ቀበሌ ሲዘዋወሩ ተማሪዎቹ ማራኪ የሆኑ የአበባ ዝንጣፊዎችን እያመጡ ለመምህራቸው ማበርከት ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ በኋላ ላይ አዚዝ ሙሐመድ ሁደይ በመባል የሚታወቀው ዝነኛ ተማሪያቸው አንዱ ግንዷ የተሰበረና እንደመጠውለግ ያለች አበባ ይዞ በማምጣት ለመምህሩ ከሰጠ በኋላ ጭንቅላቱን አቀረቀረ፡፡ ኡስታዝ ኡፍቴድ ሁኔታውን በጉጉት

በሚከታተሉት ተማሪዎች እንደታጀበ መሐመድን ግንዷ የተሰበረና የጠወለገች አበባ ለምን እንዳበረከተለት በመደነቅ ጠየቀው፡፡

ሙሐመድ ጭንቅላቱን እንዳቀረቀረ የሚከተለውን መልስ ሰጠው፡-

“መምህር ሆይ! ያበረከትኩልህ የአበባ ስጦታ ፈጽሞ አንተን እንደማይመጥንህ አውቃለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዷን የአበባ ግንድ አስጐንብሼ አበባዋን ልቀጥፍ ስል ጌታዋን የምትዘክርና አላህ! አላህ! የምትል መሰለችኝ፡፡ ልቤ ይህን ዚክር ለማቋረጥ አልፈቅድ አለኝ፡፡ ስለሆነም ጨክኜ የምቆርጠው አበባ አጣሁ፡፡ ወዲያው ግን ዘወር ስል ይህች ዚክር ያቆመች አበባ ተሰብራ ግንዷ ተንጠልጥላ በማስተዋሌ እነሆ! እርሷን ይዤ በመምጣት አበረከትኩልህ፡፡››

ልባቸው ለስላሳ የሆኑና እንደ ሙሐመድ ኤፌንዲ ያሉ ሰዎች በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር በዚክር (አላህን በማስታወስ) ላይ መሆኑን የሚያስተውሉበት ውስጣዊ ሕሊና አላቸው፡፡ ሁሉም ሕይወት ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው ፍጡራን በቋሚነት አላህን ይዘክራሉ (ያወድሳሉ)፡፡ የጥበብና የማስተዋል ባለቤት የሆነው አላህ ይህን እውነታ እንደሚከተለው በማለት በክቡር ቃሉ ያረጋግጥልናል፡-

﴿ تُسَبِّحُ لَهُ ٱلسَّمَٰوَٰتُ ٱلسَّبۡعُ وَٱلۡأَرۡضُ وَمَن فِيهِنَّۚ وَإِن مِّن شَيۡءٍ إِلَّا يُسَبِّحُ بِحَمۡدِهِۦ وَلَٰكِن لَّا تَفۡقَهُونَ تَسۡبِيحَهُمۡۚ إِنَّهُۥ كَانَ حَلِيمًا غَفُورٗا ﴿٤٤﴾ ﴾ الإسراء: ٤٤

*“ሰባቱ ሰማያትና ምድርም በውስጣቸውም ያለው ሁሉ እርሱን ያጠራሉ (ያወድሳሉ)፡፡ ከነገርም ሁሉ ከማመስገን ጋር የሚያጠራው እንጂ አንድም የለም፡፡ ግን ማጥራታቸውን አታውቁም፡፡ እርሱ ታጋሽ መሐሪ ነው፡፡” (አል-ኢስራእ፡ 44)*

የሰውም ልጅ እንግዲህ ይህን ሁሉ በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ የሚገኝ ህልቆ መሳፍርት የሌለው አስደናቂ ትእይንት እያየና እየሰማ ፊቱን ማዞሩ ተገቢ አይሆንም፡፡ ስለሆነም የፈጣሪውን ታላቅነት ማወጅና በጧትም ሆነ በማታ ሊያወድሰው፣ ሊያስታውሰውና ሊያጠራው ይገባል፡፡

ከምናደርጋቸው ዚክሮች ሁሉ በላጬ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ ሰለዋትና ሰላምታን ማውረድ ነው። አንድ ሰው በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ ሰለዋትና ሰላም ባወረደ ቁጥር መንፈሳዊ ደረጃው ከፍ እያለና ከአላህ ዘንድ ያለው ቀረቤታም ከፍ እያለ ይሄዳል። ምክንያቱም በአላህ አይን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያላቸው ሥፍራ እጅግ ከፍ ያለና የተከበሩም ስለሆኑ ነው።

ኡበይ ቢን ካእብ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

“አንድ ጊዜ የሌሊት አንድ ሶስተኛ እንዳለፈ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከእንቅልፋቸው ከነቁ በኋላ ተነስተው እንዲህ አሉ፡-

“ሰዎች ሆይ! አላህን አስታውሱ! አላህን አስታውሱ! የመጀመሪያው መለከት ይንነፋና ምድርን ከዳር እስከዳር ያናውጻታል። ከዚያም የሚቀጥለው መለከት ይንነፋል። ከዚያም ሞት ይመጣና ባለው ኃይል ፍጡሩን ሁሉ ይጠራርገዋል።”

በዚህ ጊዜ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ጠየቅኳቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔ በእርስዎ ላይ ብዙ ሰለዋትና ሰላምታ አወረድኩብዎ። አሁንም ልጨምር እንዴ? ምን ያህል ባወርድ ይበቃኛል”

“የፈለግከውን ያክል ማውረድ ትችላለህ” አሉኝ።

“ለዚክር ከመደብኩት ጊዜዬ አንድ አራተኛ የሚሆነው በእርስዎ ላይ ሰለዋትና ሰላምታ ባወርድበት አይበቃኝምን?” በማለት ጠየቅኳቸው።

“የፈለግከውን ያክል ጊዜ መድብ። ሆኖም ግን ብትጨምር ላንተ የተሻለ ይሆናል” አሉኝ።

“እንደዚያ ከሆነ ሁሉንም ጊዜዬን ሰለዋትና ሰላምታ በእርስዎ ላይ ለማውረድ አውለዋለሁ።” አልኳቸው እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡-

“እንደዚ ካደረግክ አላህ ሁሉንም ጭንቀትህን በማስወገድ ኃጢአትህን በሙሉ ይምርሃል።” (ቲርሚዚ)

አንድ ጊዜ የሆነ ባልደረባቸው (ራቅ ብሎ እያለ) አላህን በማመስገን ከጀመረ በኋላ በእርሳቸው ላይ ሰለዋት አውርዶ ዱዓ ሲያደረግ ሰምተው ካመሰገኑት በኋላ እንዲህ አሉ፡-

“አንተ ዱዓ የምታደርግ ሰው! ጠይቅ የጠየቅከው ሁሉ ተቀባይነት ያገኛልና፡፡” (ቲርሚዚ)

ኡመር ቢን አል-ኸጧብ (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ፡-

“የምታደርጉት ዱዓ ብቻውን በሰማይና በምድር መካከል ይንጠለጠላል፡፡ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ ሰለዋት እስካላወረዳችሁ ድረስወደ ወደ አላህ አይወጣም፡፡” (ቲርሚዚ)

ካዕብ ቢን ኡጅራ (ረ.ዐ.) ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእርስዎ ላይ ሰላምታ ማውረድን ተማርን፡፡ ሆኖም ግን ሰለዋት እንዴት እንደምናወርድልዎት አልተማርንም፡፡” የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡- “እንደዚህ በሉ፡-

اللهم صلى على محمد وعلى أل محمد كما صليت على إبراهيم وعلى أل إبراهيم إنك حميد مجيد, وبارك على محمد وعلى أل محمد كما باركت على إبراهيم وعلى أل إبراهيم أنك حميد مجيد.

“አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በቤተሰባቸው ላይ እዝነትህን እንዳወረድክላቸው በሙሐመድና በቤተሰባቸውም ላይ እዝነትህን አውርድላቸው፡፡ በእርግጥም አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡ አላህ ሆይ! ለኢብራሂምና ለቤተሰባቸው ርህራሄና ቸርነትህን እንዳደረግህላቸው ለሙሐመድና ለቤተሰባቸውም ርናራሄና ቸርነትህን አድርግላቸው፡፡ በእርግጥ አንተ ምስጉንና እጅግ የላቅክ ነህና፡፡” (ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ማለታቸው ተወስቷል፡-

“ከሁሉም ቀናት ውስጥ የተባረከው ቀናችሁ የጁምዓ ቀን ነው፡፡ …ስለሆነም በዚያ ቀን ብዙ ሰለዋትና ሰላምታን አውርዱብኝ፡፡ ያኔ

(ከሞትኩ በኋላ) ይደርሰኛል፡፡ በዚህ ጊዜ ባልደረቦቻቸው እንዲህ በማለት ጠየቁ፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እርሰዎ ከሞቱና ፋናዎ ከጠፋ በኋላ የእኛ ሰለዋትና ሰላምታ እንደምን ሊደርስዎት ይችላል?”

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለው መለሱ፡- “ልቅና የእርሱ የሆነው ጌታ የነቢያትን አካል እንዳትበላ ምድርን እርም አድርጕባታል፡፡” (አቡዳውድ)

ዓሊ (ረ.ዐ.) በእለተ ጁምዓ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ ሶለዋትና ሰላምታ ማውረድ ያለውን ትሩፋት ሲገልጹ እንዲህ አሉ፡-

“በእለተ ጁሙዓ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ላይ መቶ ጊዜ ሶለዋትና ሰላምታን ያወረደ በፍርዱ ቀን የሚያምርና አንፀባራቂ ፊት ኖሮት ይቀሰቀሳል፡፡ ከዚያም ሰዎች በጉጉት እርስበርሳቸው እንዲህ እየተባባሉ ይጠያየቃሉ፡- “ይህ ሰው ምን ዓይነት ሥራ ሰርቶ ይሆን እንዲህ ፊቱ የሚያበራው” (ቡኻሪ)

ከዓብ ቢን ኡጅራ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብሏል፡-

“አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደ ሚንበራቸው (መስበኪያ ሰገነት) እንድንሰባሰብ ነገሩን፡፡ ያዘዙንን አደረግን፡፡ ከዚያም የመጀመሪያውን ደረጃ ሲወጡ “አሚን!” አሉ፡፡ ከዚያም ሁለተኛውን ደረጃ ሲወጡም “አሚን!” አሉ፡፡ ሶስተኛውንም ደረጃ ሲወጡ እንዲሁ “አሚን!” አሉ፡፡

ከሚንበሩ ላይ ንግግራቸውን ጨርሰው እንደወረዱ ጠየቅናቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከዚህ በፊት ሰምተነው የማናውቀውን ነገር ዛሬ ሲናገሩ ሰማን፡፡ ይህ “አሚን” ያሉት ነገር ምንድን ነው?” እንዲህም ብለው መለሱልን፡-

“ጂብሪል (ዐ.ሰ.) ወደ እኔ መጣና እንዲህ አለኝ፡- “ረመዳን መጥቶ ሃጢአቱ ሳይማርለት የቀረን ሰው (ከአላህ እዝነት) መራቅ ይገባው!” አለኝ እኔም “አሚን!” አልኩ፡፡ ሁለተኛውን ደረጃ ስወጣ፣ “ያንተ ስም

ሲነሳ ሰምቶ ሰለዋት የማያወርድብህ ሰው (ከአላህ እዝነት) መራቅ ይገባው!” አለኝ፡፡ እኔም “አሚን!” አልኩት፡፡ ሶስተኛውን ደረጃ ስወጣ፡- “አንዳቸው ወይም ሁለቱንም ወላጆቹን በእርጅና ጊዜያቸው ደርሶባቸው እነርሱን በማስደሰት ጀነት መግባት ያልቻለ ሰው (ከአላህ እዝነት) መራቅ ይገባው!” አለኝ ፡፡ እኔም “አሚን!” አልኩት፡፡” (ሐኪም፣ ቲርሚዚ)

አንድ የአላህ አገልጋይ እንዲህ አለ፡-

“የተለያዩ ሙስሊም ምሁራንን መጽሐፍት እየገለበጠ (እያበዛ) የሚያስቀምጥ አንድ ጐረቤት ነበረኝ፡፡ ሲሞት በሕልሜ አየሁትና እንዲህ ስል ጠየቅኩት፡-

“ልቅና የተገባው ጌታ እንዴት ያለ አቀባበል አደረገልህ?”

“ይቅርታ አድርጐልኛል፡፡” አለኝ፡፡

“የትኛው መልካም ሥራህ ይሆን ለዚህ ያበቃህ?” በማለት ጠየቅኩት፡፡

“በምጽፋቸው መጽሐፍት ላይ ምንጊዜም የክቡሩን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) ስም በጠቀስኩ ቁጥር ሰለዋት ሳላወርድባቸው ቀርቼ አላውቅም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ጌታዬ ምህረትን አድርጐልኝ ዓይኖች አይተውት የማያውቁት፣ ጆሮዎችም ሰምተውት የማያውቁት እንዲሁም ማንም ቢሆን እንዲህ ይሆናል ብሎ ገምቶት የማያውቅ የሆነን ጀነት ሰጥቶኛል፡፡” (ነባሃኒ)

የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ባህሪያትና ሱናቸውንም መተግበር ያልቻለ ሰው አንድ ጊዜ በሕልሙ አያቸው፡፡ ሳያናግሩት ቀሩ፡፡ በጣም ተከፍቶ እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

“የአላህ መልክተኛ ሆይ! ተቀይመውኛል ማለት ነው?”

“እንዲያውም!”

“ታዲያ ለምን ይሆን ሳያናግሩኝ የቀሩት?”

“ማን እንደሆንክ ስላላወቅኩህ ነው፡፡”

“ይህ እንዴት ይሆናል የአላህ መልእክተኛ! እኔ ከእርስዎ ኡማ (ሕዝብ) ውስጥ አንዱ ነኝ። የእውቀት ባለቤቶች (ዓሊሞች) እንደነገሩን እርስዎ ተከታዮችዎን እናት ልጇን ከምታውቀው በበለጠ ለይተው ያውቃሉ…”

“ይህ እውነት ነው። ይሁን እንጂ ባንተ ላይ አንድም የእኔን ፈለግ አላየሁብህም። በተጨማሪም አንድም ጊዜ በእኔ ላይ ሰለዋትና ሶላምታ አውርደህብኝ ደርሶኝ አያውቅም። እኔ ተከታዮቼን የማውቀው የእኔን ሱና አጥብቀው በመያዛቸውና ፈለጌንም ስለሚከተሉ ነው።”

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከእንቅልፉ የባነነው ያ ሰው እጅግ በጣም አዘነ። ከዚያም በጣም ተጸጽቶ ተውበት ካደረገ በኋላ ምስጉን የሆነውን የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ.) ባሕሪ ማጥናትና መተግበር ጀመረ። አብዛኛውን ጊዜውንም በእርሳቸው ላይ ሰለዋትና ሰላምታ በማውረድ ያሳልፍ ነበር። ከጊዜ በኋላ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደገና በሕልሙ ተገልፀውለት እንዲህ አሉት፡-

“አሁን አውቄሃለሁ፤ አማላጅም (ሸፊዓ) እሆንሃለሁ።

በአጭሩ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

“ሰው ከሚወደው ጋር ይሆናል።” (ቡኻሪ)

በዚህ አባባል መሠረት አንድ አፍቃሪ የተፈቃሪውን ሁሉንም ነገሩን ይወዳል። ስለሆነም እኛ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በድርጊታችንም ሆነ በሁሉም ሁኔታችን ልንከተላቸው ይገባናል። ለእርሳቸው ያለን ውዴታና የፍቅር ግለት አላህን የመውደዳችንና ለእርሱ የምናሳየው ፍቅር ልማድ ነው። ከዚህ የሚቃረን ማንኛውም ፍቅር በቁርአንም ሆነ በሱና የተወገዘ ነው።

ወደ አላህ ለመቃረብና ቀናውን መንገድ ለመመራት ብቸኛው መንገድ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከምንምና ከማንም በላይ ማፍቀር ነው። ማፍቀር ማለት ደግሞ ያፈቀሩትን በእርእያነት መከተልና እርሱ የወደደውን መውደድ፣ የጠላውንም መጥላት ማለት እንጂ ሌላ አይደለም። ኃያሉ ጌታችን አላህም እንዲህ ብሏል፡-

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾ آل عمران: ٣١

*"በላቸው! አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ:: አላህ ይወዳችኋልና:: ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምራልና:: አላህም መሐሪ አዛኝ ነው::" (አሊ-ዒምራን:31)*

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

*"ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አላችሁ::" (አል-አሕዛብ:21)*

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ለሞትና ለመጪው ዓለም መዘጋጀት

አንድ ሰው የዚህን አጽናፈ ዓለም አጠቃላይ አወቃቀርና የሚተዳደርበትን ሥርአት ካስተዋለ ሞት ከተባለ አይቀሬ እዳ ጋር መፋጠጡ የግድ ነው፡፡ ለመሆኑ ሞት ምንድን ነው? ሰዎች ዘላለማዊ ሥጋ ለብሰው እንዳይኖሩ፣ ከሚወዱት ሰው፣ ከቤታቸው፣ ከንብረታቸውና ከብዙ ውብ ነገሮች በግድ ተመንጭቀው ወደ ሞት የሚወሰዱት ለምንድን ነው? ከሞት ጀርባ ያለውስ ጥበብ ምን ይሆን

ኃያሉ አላህ ሕይወትና ሞት ከጀርባቸው የያዙትን ጥበብ በሁለት መስመር ቃላት ውብ አድርጎ ሲገልፀው እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ﴿٢﴾ ﴾ الملك: ٢

*“ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፡፡ እርሱም አሸናፊው መሀሪው ነው፡፡” (አል-ሙልክ:2)*

የተፈጠርንበትና የምንሞትበት ዋነኛ ግብ ይኸው ነው፡፡ እናም ሰው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ሕይወት ያለው ፍጥረት በውድም ሆነ በግድ ሞትን ይቀምሳል፡፡

ይህን አንኳር ሃቅ አላህ በቁርአን እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡-

﴿ كُلُّ مَنْ عَلَيْهَا فَانٍ ﴿٢٦﴾ ﴾ الرحمن: ٢٦

*“በርሷ (በምድር) ያለው ሁሉ ጠፊ ነው፡፡” (አር-ራሕማን:26)*

﴿ كُلُّ نَفْسٍ ذَآئِقَةُ ٱلْمَوْتِ ۗ وَنَبْلُوكُم بِٱلشَّرِّ وَٱلْخَيْرِ فِتْنَةً ۖ وَإِلَيْنَا تُرْجَعُونَ ﴿٣٥﴾ ﴾

*“ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን፡፡ ወደ እኛም ትመለሳላችሁ፡፡” (አንቢያእ: 35)*

ረንደዚያም ሆኖ ብዙ ሰዎች አሁንም ቢሆን በከንቱ መታለል ሆነው መታየታቸው ያስደንቃል፡፡ በየእለቱ የሞትን ትእይንት እዚህም እዚያም እያዩ ሆኖም ግን አንድ ቀን ወደ እነርሱ እንደሚመጣ የማይገምቱ ከንቱዎች ብዙ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እውነታው አንድ ሰው ወደዚህች ዓለም ከመጣበት ቅጽበት ጀምሮ ወደ ሞት የሚወስደውንም ጉዳና የሚያያዘው መሆኑ ነው፡፡ ነፍስ እያወቀ ከመጣ ጀምሮ የሚያስተውለው ሃቅ ለሞት ዝግጅት ማድረግ መጀመር እንዳለበት ያሳስበዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ቢወድም ቢጠላም አንድ እለት ባልታሰበ ሁኔታ ሞት ደጁን ያንኳኳል፡፡ ሞት ወደ መጪው ዓለም የሚወስድ የመሸጋገሪያ ሂደት ሲሆን ታላቅ ለሆነ ጉዞ የመግቢያ በርም ነው፡፡

ከሁሉ የበላይ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن نُّعَمِّرْهُ نُنَكِّسْهُ فِى ٱلْخَلْقِ ۖ أَفَلَا يَعْقِلُونَ ﴿٦٨﴾ ﴾ يس: ٦٨

*“እድሜውንም የምናረዝመውን ሰው በፍጥረቱ (ወደ ደካማነት) እንመልሰዋለን፡፡ አያውቁምን” (ያሲን፡68)*

እንግዲህ የሰው ልጅ በዚህች ጠፊ ዓለም ለተወሰኑ ዘመናት የመገኘቱ ምስጢር አላህን የሚያደስቱ መልካም ተግባራትን ፈጽሞ ዘላለማዊ ተድላን ማግኘት ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አዋቂና ብልህ ሰው ማለት ሥጋዊ ፍላጐቱንና ስሜታዊ ዝንባሌውን ተቆጣጥሮ ከሞት በኋላ ላለው ዓለም የሰራ ነው፡፡ ሞኝ ተላላና ደካማ ሰው ማለት ደግሞ በከንቱ ስሜቱ ቁጥጥር ስር ራሱን አውሎ የአላህን ምህረትና ፀጋውን በባዶ ተምኔት የሚጠባበቅ ሰው ነው፡፡” (ቲርሚዚ)

ነጂብ ፋዚል የተባለው ገጣሚ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የሚከተሉትን ስንኞች ቋጥሯል፡-

አንተ በየሥፍራው የምትኳትን ነጋዴ

ፈረንካ ፍለጋ የምትባዝን መደዴ

እስቲ ስማኝ ምክር ብጤ ላካፍልህ

ቀብር ስትገባ የምትሆንህ ለነገህ

ቆጥረህ አስቀምጥ ቀነስ አርግና ከትርፍህ!

ሕይወት በአንድ ብርጭቆ ላይ እየተንጠባጠበ በሚሞላ ውሃ ልትመሰል ትችላለች፡፡ የብርጭቆው ንጹህ መሆን ጥገኛ የሆነው በነጠብጣቦቹ ውሃዎች ንጹህ መሆን ላይ ነው፡፡ የመጨረሻዋ ጠብታ የሰው ልጅ የመጨረሻ እስትንፋስ ስትሆን ከዚያ በኋላ በሕይወት አውድ በአጸደ ነፍስ የመኖሩ ጉዳይ ያልቅለታል ማለት ነው፡፡

በአንድ ሐዲስ ላይ እንዲህ የሚል ተጽፎ እናገኛለን፡-

“የመጨረሻ ቃሉ ‘ላኢላሃኢለሏህ’ የሆነ ሰው ጀነት ይገባል፡፡” (አቡዳውድ፣ሐኪም)

ይህ አባባል በጣም አስፈሪና እጅግም የሚያሳስብ ነው፡፡ ለመሆኑ ስንቱ ነው የመጨረሻ ቃሉ “ላኢላሃኢለሏህ” ሆና ከዚህች ዓለም የሚወጣው? ይህን ለማድረግ ሁሉም ሰው በነፍስ ወከፍ ልቡን ከተለያዩ በካይ ነገሮችና ይህችን ከሊማ ብሎ እንዳይወጣ ከሚያግዱት ደራሽ ፍላጐቶች፣ ሥጋዊ አምሮቶች፣ ከንቱ ምኞቶችና ሞኛሞኝ አስተሳሰቦች ሁልጊዜም ማጽዳት ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ከዚህ የተለየ ሕይወት ሲገፋ ለኖረ ሰው በመጨረሻዋ ስቅታው “ላኢላሃ ኢለሏህ” የምትለዋን ቃል (ከሊማ) ከአንደበቱ ለማውጣት ያስቸግረዋልና ነው፡፡ የእውነት ነቢይ የሆኑት ሙሐመድ ቢን አብዱላህ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ሰዎች እንደአኗኗራቸው ይሞታሉ፡፡ እንዳሟሟታቸውም ይቀሰቀሳሉ፡፡” (ሙስሊም)

የሰው ልጅ የመጨረሻ እስትንፋስ በጭጋግ እንዳልተሸፈነ መስታወት ናት፡፡ የሰው ልጆች በመጨረሻው ሰዓታቸው ሁሉንም እውነታ ያለምንም ግርዶሽ ይመለከታሉ፡፡ በክፉም ሆነ በበጐ ሁኔታ ያሳለፉት ሕይወታቸው ነፀብራቅ በልባቸውና በዓይናቸው ላይ ቁልጭ ብሎ እንዲታያቸው ይደረጋሉ፡፡ ስለሆነም ከሞት የበለጠ መካሪና ገሳጭ የለም ማለት ነው፡፡ በእውነቱ ለሰው ልጅ ከሞት የበለጠ መካሪ ከየት ይመጣለታል? የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"*ሥራ* መቃብር አንድም የጀነት ጨፌ ነው አለያም ደግሞ የጀሃነም ጉድጓድ ነው፡፡" (ቲርሚዚ)

ስለዚህም ነው እኛ ሁላችንም በዚህች ምድር ላይ የምንኖርባቸውን የተቆጠሩ ዓመታትና ቀናት ነፍሳችን ከሥጋችን ስትለይ ለጥሩ ባሪያ የሚደረገው መስተንግዶ ይደረግላት ዘንድ መልፋት ያለብን፡፡ ይህንን ስንፈጽምም ወደ መጪው ዓለም በሚያሸጋግረን የመጀመሪያው በር በመቃብራችን የጀነት ጨፌና ማራኪ ሽታዋ ይጠብቀናል፡፡ በቀብሩ የተሳካለት ሰው በመጪው ዓለምም ለስኬት እንደሚበቃ አይጠረጠርም፡፡

ኃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَٱعۡبُدۡ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأۡتِيَكَ ٱلۡيَقِينُ ٩٩ ﴾ الحجر: ٩٩

*"እውነቱም (ሞት) እስከመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ" (አል-ሒጅር፡99)*

እንግዲህ ሕይወታቸውን በሙሉ የአላህንና የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ትእዛዛት በመጠበቅና ክልከላዎቻቸውንም በመጠንቀቅ የኖሩ የሰሪን ሥራ የማያጠፋው አላህ በመጨረሻ ይክሳቸዋል፡፡ ይህም ነፍሳቸው ከጉሮሮአቸው ከመውጣቷ በፊት ይህን ከሊመቱ ጠይባ (ላኢላሃኢለሏህ ሙሐመዱን ረሱሉላህ) በአንደበታቸው በማረጋገጥ ወደዘንታለማዊ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ጉዞው ምንኛ ያማረ አቀባበሉስ ምንኛ የሰመረ ነው!

የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"ከሞት በኋላ ፀፀት የማይዘው አንድም ሰው የለም፡፡"

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ፀፀቱ ከምን የተነሳ ነው?” የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው። እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡-

“መልካም ሥራዎችን ሰርቶ በመልካም ሁኔታ የሞተ ለምን ከበጐ ምግባሬ ጨመር አድርጌ አልሰራሁም? በማለት የሚፀፀት ሲሆን በመጥፎ ሥራዎች ጌታውን የተገናኘ ደግሞ እኩይ ድርጊቱን ትቶ ፈጣሪውን ባለመገናኘቱ ይፀፀታል።” (ቲርሚዚ)

ኃያሉ አላህ ባሪያዎቹን እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تُلْهِكُمْ أَمْوَٰلُكُمْ وَلَآ أَوْلَٰدُكُمْ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ ۚ وَمَن يَفْعَلْ
ذَٰلِكَ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَٰسِرُونَ ﴿٩﴾ وَأَنفِقُوا۟ مِن مَّا رَزَقْنَٰكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِىَ أَحَدَكُمُ
ٱلْمَوْتُ فَيَقُولَ رَبِّ لَوْلَآ أَخَّرْتَنِىٓ إِلَىٰٓ أَجَلٍ قَرِيبٍ فَأَصَّدَّقَ وَأَكُن مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿١٠﴾ وَلَن
يُؤَخِّرَ ٱللَّهُ نَفْسًا إِذَا جَآءَ أَجَلُهَا ۚ وَٱللَّهُ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿١١﴾ ﴾ المنافقون: ٩ - ١١

*“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ አላህን ከማስታወስ አያታልሏችሁ። ይህንንም የሚሰሩ ሰዎች እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎቹ ናቸው። አንዳችሁንም ሞት ሳይመጣውና ጌታዬ ሆይ! እንድመፀውትና ከደጋጐቹም ሰዎች እንድሆን ወደ ጥቂት ጊዜ ብታቆየኝ እመኛለሁ።” በማለት በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ ለግሱ። ማንኛይቱንም ነፍስ (የሞት) ጊዜዋ በመጣበት ጊዜ አላህ በፍጹም አያቆያትም። አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጥ አዋቂ ነው።” (አል-ሙናፊቁን፡9-11)*

ለማጠቃለል ሞታችንም ሆነ በመቃብር ውስጥ እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ የሚገጥመን ሁኔታ የሚቀረጸው በዚህች ዓለም ላይ ባሳለፍነው የሕይወት ዘይቤና በሰራናቸው መልካምም ሆነ እኩይ ተግባራት ነው።

## የሰናይ ምግባራት ገጽታዎች

አብደላህ ኢብኑ ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አንድ ጊዜ ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ጋር እያለሁ አንድ የአንሷር ሰው መጣና ሰላምታ ካቀረበላቸው በኋላ እንዲህ አለ፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከአማኞች ሁሉ በላጩ ማን ነው”

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መለሱለት፡-

“ከሁሉም የበለጠ ጥሩ ፀባይ ያለው፡፡” በዚህ ጊዜ ሰውየው ሌላ ጥያቄ አነሳ፡፡

“መልካም! ከአማኞች ሁሉ ብልሁስ ማን ነው” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ለዚህም እንዲህ የሚል መልስ ሰጡት፡-

“ከሁሉም የበለጠ ሞትን የሚያስታውስና ከእርሱም (ከሞት) በኋላ ለሚመጣው ነገር የበለጠ የሚዘጋጅ ነው፡፡ እርሱ ነው እውነተኛ ብልህ የሚባለው፡፡” (ኢብኑ ማጃህ)

በራዕ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት አስተላልፏል፡-

“በአንድ የመቃብር ቦታ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጋር አብረን ነበርን፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከመቃብሩ አጠገብ ቁጭ አሉና በዙሪያቸው ያለው መሬት በእንባ እስኪርስ ድረስ ማልቀስ ጀመሩ፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡-

“ወንድሞቼ (በሁላችንም ላይ ወዳቂ ለሆነው) ሞት በሚገባ ተዘጋጁ፡፡” (ኢብኑ ማጃህ)

ኡመር (ረ.ዐ.) በአንድ ወቅት አንዱን አገልጋያቸውን በየእለቱ የሚከተለውን አረፍተ ነገር እንዲደግምላቸው አዝዘውት ነበር፡-

“ኡመር ሆይ! ሞትን አትርሳ!” ይሁን እንጂ በጺማቸው ላይ የተወሰኑ ነጫጭ ጸጉሮች መታየት ከጀመሩ በኋላ አገልጋያቸውን እንዲህ አሉት፡-

“ከእንግዲህ ይበቃሃል፡፡ እነዚህ በጺሜ ላይ የበቀሉት ነጫጭ ፀጉሮች በያንዳንዱ ቅጽበት ሞትን ያስታውሱኛልና፡፡”

የአላህ ነቢይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ከቀብር ትእይንቶች ውስጥ የተወሰነውን ሲገልጹልን ከሞት በኋላና በመጪውም ዓለም ከሚጠብቀን አደጋ እንድንጠበቅ በመሻታቸው እንጂ ለሌላ አይደለም፡፡ ከእነዚያ ትእይንቶች የተወሰኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

“ሙስሊም ሰው የሞት ጭንቀት (ጣእር) ሲይዘው ነጫጭ ሐር የለበሱ የእዝነት መላእክት ይወርዱና እንዲህ ይላሉ፡-

“አንች አማኝ ነፍስ ሆይ! ጌታሽ የሚሰጥሽን የወደድሽ ስትሆኝና ጌታሽም ካንቺ የወደደ ሲሆን ከዚህ አካል ውጪ፡፡ ወደ ጌታሽም ተመለሺ፡፡ ጣፋጭ በሆነ መዓዛ ታውደሽ የጌታሽ ቁጣ የሌለብሽ ስትሆኝ ተመለሺ፡፡

ከዚያም ነፍሱ በጣም አስደሳች በሆነ የሚስክ ሽታ እየታወደች ከአካሉ ተለይታ መላእክት ይዘዋት ወደ ሰማይ ደጃፍ ይወጣሉ፡፡ እዚያ ያሉ መላእክትም ይላሉ፡-

“ከምድር ይዛችኋት የመጣችሁት ይህች ምን አስደሳች መዓዛ ያላት ነፍስ ናት! ከዚያም ከእርሱ በፊት ከሞቱ አማኝ ሰዎች ነፍሳት ጋር ትቀላቀላለች፡፡ አንዳችሁ እጅግ የሚወደው ነገር ጠፍቶት ሲያገኘው ከሚደሰተው የበለጠ እነዚያ አማኝ ነፍሶች በእርሱ መምጣት ይደሰታሉ፡፡ ከዚያም እንዲህ በማለት ይጠይቁታል፡- “እገሌ እንዴት ሆነ? እገሌስ እንዴት ሆነ?” ይህም በምድር ዓለም የሚያውቁትን ሰው ሁኔታ ለማወቅ ጥረት ሲያደርጉ (ከመካከላቸው የተወሰኑት እንዲህ ይላሉ)፡-

“ኧረ እርሱን ተውት፡፡ እርሱ ኮ እዚያው በጭንቅ ተይዟል፡፡” በዚህ ጊዜ አዲስ የመጣው እንዲህ ይላል፡- “እንዴ! እገሌኮ ሞቷል፡፡ ወደዚህ አልመጣም እንዴ?” እነርሱም ይመልሳሉ፡-

“እንደዚያ ነው? እንደርሱ ከሆነማ መሄድ ወዳለበት ቦታ ሄዷል ማለማት ነው፡፡ ወደ ጀሃነም ተወስዷል ማለት ነው፡፡”

አማኝ ያልሆነ ሰው በሞት ጭንቅ በሚያዝበት ጊዜ የቅጣት መላእክት አስቀያሚ መልክ ያለውና ከሻካራ ነገር የተሰራ ልብስ ለብሰው በመምጣት እንዲህ ይላሉ፡-

“አንቺ ከሃዲ ነፍስ ሆይ! ይህን አካል በግድ ለቅቀሽ ውጪ፡፡ የአላህ ቁጣ ባንቺ ላይ ሰፍኗል፡፡ ወደ ቅጣቱም ተመላሽ ሆነሽ ውጪ፡፡ ከዚያም ያቺ ነፍስ እጅግ የሚገማ ሽታ ኖሯት አካሉን ለቅቃ ትወጣለች፡፡ ከዚያም መላእክቱ ይዘዋት ወደ ሰማይ ይወጣሉ፡፡ የሰማይ ነዋሪዎችም ይላሉ -

"ይህች እጅግ የምትገማ ነፍስ የማን ናት?" "የእገሌ" ይባላሉ፡፡ "እርሷ የጌታዋ ቁጣ ያለባት ስትሆን የሰማይ ደጃፎች አይከፈቱላትም!" ይላሉ፡፡ ከእዚያም መላእክቱ ወደ ምድር ይመለሱና ከሌሎች ከሃዲያን ነፍሳት ጋር እንድትቀላቀል ያደርጓታል፡፡ (ነሳኢ)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"በፍርዱ ቀን የአደም ልጅ እንደ በግ እየተነዳ ወደ አላህ ፊት ይቀርብና ልቅና የተገባው አላህ እንዲህ ይለዋል፡-

"ብዙ ሃብትንና ንብረትም ሰጥቼህ ነበር፡፡ እንዲሁም ብዙ ውለታዎችንና ፀጋዬንም አፍስሸልህ ነበር፡፡ ለዚህ ውለታዬ ምንድን ነው የሰጠኸኝ ምላሽ?" ሰውየው ይላል፡-

"ጌታዬ ሆይ! አከማችቼዋለሁ፡፡ አካብቼዋለሁ፤ ዱሮ ከነበረው እጅግ ብዙ እንዲሆን አድርጌዋለሁ፡፡ ወደ ምድርአለም ልሂድና አምጥቼ ላስረክብህ፡፡"

ይህ ባሪያ ለዚህ ነው ምንም መልካም ነገር ለመጪው ሕይወቱ ሳያሳልፍ የቀረው፡፡ ለዚህም ነው ወደ ጀሃነም እሳት የሚጣለው፡፡" (ቲርሚዚ)

በዚህ ዓለም ሳሉ ለመጪውና ከሞት በኋላ ላለው ዓለም የማይዘጋጁና ሕይወታቸውን በግዴለሽነት የሚመሩ መሪር የሆነ ፍጻሜ ይጠብቃቸዋል፡፡ ጥርስ ከማፋጨትና የጣትን አጽቆች በቁጭት ከመንከስ በቀር ሌላ ምንም መልካም ሥራ የመስሪያ ጊዜና እድል አይገኝም፡፡ ጥበበኛውና ኃያሉ አላህ የእውነት ብርሃን በተሞላው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَمَّا مَنْ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهْرِهِۦ ﴿١٠﴾ فَسَوْفَ يَدْعُوا۟ ثُبُورًا ﴿١١﴾ وَيَصْلَىٰ سَعِيرًا ﴿١٢﴾ إِنَّهُۥ كَانَ فِىٓ
أَهْلِهِۦ مَسْرُورًا ﴿١٣﴾ إِنَّهُۥ ظَنَّ أَن لَّن يَحُورَ ﴿١٤﴾ ﴾ الانشقاق: ١٠ ـ ١٤

*"መጽሐፉን በጀርባው ኋላ የተሰጠ ሰውማ (ዋ ጥፋቴ! በማለት) ጥፋቱን በእርግጥ ይጠራል፡፡ የተጋጋመች እሳትንም ይገባል፡፡ እርሱ በቤተሰቡ*

*ውስጥ ተደሳች ነበርና፡፡ እርሱ (ወደ አላህ) የማይመለስ መሆኑን አስቧልና፡፡" (አል-ኢንሺቃቅ:10-14)*

**በምድራዊ ፀጋና ብልጭልጭ በሆነው የዚህች ዓለም ከንቱ ሃብት እጅጉን የተሞኘ፣ ከዚያም የውድቀቱን ጉድጓድ በገዛ እጁ እጅግ አድርጎ በማራቅ የቆፈረ ከንቱ ሰው ቃሩን ነው፡፡ ይህ ሰው ከበኒ ኢስራኢል የካህናት ወገን ነበር፡፡ ሆኖም ግን በኋለኞቹ የሕይወት ዘመናቱ እጅግ የናጠጠ ባለፀጋ እንዲሆን ያስቻለውን የቅመማ (ኬሚስትሪ) እውቀት ከኃያሉ አላህ (ለፈተና) ተሰጠ፡፡ ቃሩን ፈተናውን ማለፍ አልቻለም፡፡ ኮራ፣ ተኮፈሰ፣ ሕዝቦቹንና የአላህንም ሕግጋት አጣጣለ፡፡ ነቢያቱን ገላመጠ፡፡ ከእምነትም ዞረ፤ ካደ፡፡ በመጨረሻም በሕይወት እያለ ምድር ከነሃብቱና መላ ቤተሰቡ እንዲሁም ከነ አሽከሮቹና ግሳንግሱ ዋጠችው፡፡ በመጪው ዓለምም ፈርኦንንና ሃማንን ከመሳሰሉት ቀንደኛ ከሃዲያን ጋር በመሆን ወደ ጀሃነም አዘቅቶች ይጣላል፡፡ ቁርአን ይህንን እውነታ እንደሚከተለው ይዳስሰዋል፡-**

﴿ إِنَّ قَٰرُونَ كَانَ مِن قَوۡمِ مُوسَىٰ فَبَغَىٰ عَلَيۡهِمۡۖ وَءَاتَيۡنَٰهُ مِنَ ٱلۡكُنُوزِ مَآ إِنَّ مَفَاتِحَهُۥ لَتَنُوٓأُ
بِٱلۡعُصۡبَةِ أُوْلِي ٱلۡقُوَّةِ إِذۡ قَالَ لَهُۥ قَوۡمُهُۥ لَا تَفۡرَحۡۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلۡفَرِحِينَ ٧٦ وَٱبۡتَغِ فِيمَآ
ءَاتَىٰكَ ٱللَّهُ ٱلدَّارَ ٱلۡأٓخِرَةَۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ ٱلدُّنۡيَاۖ وَأَحۡسِن كَمَآ أَحۡسَنَ ٱللَّهُ
إِلَيۡكَۖ وَلَا تَبۡغِ ٱلۡفَسَادَ فِي ٱلۡأَرۡضِۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ٧٧ قَالَ إِنَّمَآ أُوتِيتُهُۥ عَلَىٰ عِلۡمٍ
عِندِيٓۚ أَوَلَمۡ يَعۡلَمۡ أَنَّ ٱللَّهَ قَدۡ أَهۡلَكَ مِن قَبۡلِهِۦ مِنَ ٱلۡقُرُونِ مَنۡ هُوَ أَشَدُّ مِنۡهُ قُوَّةٗ وَأَكۡثَرُ
جَمۡعٗاۚ وَلَا يُسۡـَٔلُ عَن ذُنُوبِهِمُ ٱلۡمُجۡرِمُونَ ٧٨ فَخَرَجَ عَلَىٰ قَوۡمِهِۦ فِي زِينَتِهِۦۖ قَالَ ٱلَّذِينَ
يُرِيدُونَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا يَٰلَيۡتَ لَنَا مِثۡلَ مَآ أُوتِيَ قَٰرُونُ إِنَّهُۥ لَذُو حَظٍّ عَظِيمٖ ٧٩
وَقَالَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡعِلۡمَ وَيۡلَكُمۡ ثَوَابُ ٱللَّهِ خَيۡرٞ لِّمَنۡ ءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحٗا وَلَا
يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ٱلصَّٰبِرُونَ ٨٠ فَخَسَفۡنَا بِهِۦ وَبِدَارِهِ ٱلۡأَرۡضَ فَمَا كَانَ لَهُۥ مِن فِئَةٖ يَنصُرُونَهُۥ
مِن دُونِ ٱللَّهِ وَمَا كَانَ مِنَ ٱلۡمُنتَصِرِينَ ٨١ ﴾ القصص: ٧٦ - ٨١

*“ቃሩን ከሙሳ ነገዶች ነበር። በእነርሱም ላይ አመፀ ከድልቦችም ያንን መክፈቻዎቹ ብቻ የኃይል ባለቤቶች የሆኑ ጭፍሮችን (ሸክሙ) የሚከብድን ሰጠነው። ወገኖቹ ለእርሱ አትኩራ፤ አላህ ኩራተኞችን አይወድምና ባሉት ጊዜ (አስታውስ)። አላህም በሰጠህ ሃብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ። ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን አትርሳ። አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ። በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ። አላህ አጥፊዎችን አይወድና (አሉት)። (ሃብቱን) የተሰጠሁት እኔ ዘንድ ባለው እውቀት ብቻ ነው አለ። አላህ ከርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ሰዎች በኃይል ከርሱ ይበልጥ የበረቱትን (ሃብትን) በመሰብሰብም ይበልጥ የበዙትን በእርግጥ ያጠፋ መሆኑን አያውቅምን? አመፀኞችም ከኃጢአቶቻቸው (ምንረት የሚከተለውን ጥያቄ) አይጠይቁም። በሕዝቦቹም ላይ በጌጡ ውስጥ ሆኖ ወጣ። እነዚያ ቅርቢቱን ሕይወት የሚፈልጉት ወይ ምኞታችን! ቃሩን የተሰጠው ብጤ ምነው ለእኛ በኖረን እርሱ የታላቅ እድል ባለቤት ነውና አሉ። እነዚያም እውቀትን የተሰጡት ወዮላችሁ! የአላህ ምንዳ ላመነ ሰው መልካምንም ለሰራ በላጭ ነው። ታጋሾችም እንጂ ሌላው አያገኛትም አሉ። በርሱም በቤቱም ምድርን ደረብን። ለእርሱም ከአላህ ሌላ የሚረዱት ጭፍሮች ምንም አልነበሩትም። ከሚርረዱትም አልነበረም።” (አል-ቀሶስ:76:81)*

አንድ እለት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡-

“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በፍርዱ ቀን ጌታችንን እናየዋለን?” ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ሰዎቹን ጠየቋቸው፡-

“በቀትር ላይ ወይም ዳመና በሌለበት ቀን ፀሐይን ለማየት አንዳች የሚያግዳችሁ ነገር አለን? የሰዎቹ መልስ አሉታዊ በሆነ ጊዜ እንደገና ሌላ ጥያቄ አቀረቡላቸው፡-

“ዳመና በሌለበት ምሽት ጨረቃን ለማየት እርስ በርሳችሁ ትጋፋላችሁን?”

የባልደረቦቻቸው መልስ አሁንም "አንጋፋም" የሚል በሆነ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

"ነፍሴ በእጆቹ በሆነችው ጌታዬ እምላለሁ! ፀሐይንና ጨረቃን ለማየት እንደማትጋፉ ሁሉ ጌታችሁንም ለማየት እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ አትጋፉም፡፡››

በዚህ ዓይነት መልኩ ባሪያው ከጌታው ጋር ፊት ለፊት ይሆናል፡፡ አላህም እንዲህ በማለት ይጠይቀዋል፡-

"እገሌ ሆይ! ውለታ አልዋልኩልህምን? በብዙ ሰዎችስ ላይ አልሾምኩህምን? ሚስት አልሰጠሁህምን? ፈረስንና ግመልን እንዲያገለግሉህ አልገራሁልህምን? መሪ እንድትሆን በማድረግ ከሚገኘው ምርኮ አንድ አራተኛውን እንድትወስድ አላደረኩህምን?" ባሪያው እንዲህ ይላል፡-

"አዎን! ጌታዬ ሆይ"

ከሁሉም በላይ የላቀው አላህ አሁንም ይጠይቃል፡-

"ታዲያ የማንገናኝ መስሎህ ነበርን?"

"ባሪያው ይላል፡- "አይደለም ጌታዬ ሆይ!" አላህም ይላል፡-

"እንደዚያ ከሆነ ያኔ ረስተኸኝ እንደነበረው ዛሬ በተራዬ እኔ እረሳሃለሁ፡፡"

ከዚያም ሁለተኛው ባሪያ ከአላህ ፊት ይቀርባል፡፡ ከሁሉም በላይ የሆነው አላህ ይህንንም ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠይቀዋል፡፡ ከዚያም ሶስተኛውን ባሪያ እንዲህ በማለት ይጠይቀዋል፡-

"የማንገናኝ መሆናችንን ጠርጥረህ ነበርን?" ባሪያው ይመልሳል፡-

"ጌታዬ ሆይ! እኔ ባንተ አምኛለሁ፡፡ በመጽሐፍትህም፣ በነቢያትህም አምኛለሁ፡፡ እሰግድ ነበር፣ እፆምም ነበር፣ ዘካም አወጣ ነበር፡፡" ይህን ካለ በኋላ የልቅና ጌታ የሆነውን አላህን የቻለውን ያክል ያወድሰውና ያመስግነው ጀመር፡፡ ልእልናና ኃያልነት የተገባው አላህ እንዲህ ይላል፡-

“በል ይበቃሃል! ከዚህ በኋላ መስካሪ ይመጣና ይመሰክርብሃል፡፡” በዚህ ጊዜ ባሪያው እንዲህ እያለ ያስባል፡-

“ማን ነው በእኔ ላይ ምስክርነቱን የሚሰጠው?” ከዚያም አፉ ይታሸጋል፡፡ “ኑና ምስክርነታችሁን ስጡ” ይባላሉ፡፡ እነርሱም ድርጊቶቹን በሙሉ ይዘረዝራሉ፡፡ በዚህም የተነሣ ባሪያው ምንም ዓይነት ይቅርታ አይደረግለትም፡፡ ይህ ሰው መናፍቅ ሲሆን የአላህ ቁጣም ይሰፍንበታል፡፡ ” (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው አሉ፡-

“አንድ ባሪያ መቃብሩ ውስጥ እንደተከተተና ዘመዶቹና ቀባሪዎቹ ከእርሱ ርቀው የጫማቸውን ኮቴ እንደሰማ መላእክት ከሰማይ ወርደው ፊት ለፊቱ ይገኛሉ፡፡ ከዚያም ቁጭ እንዲል ካደረጉት በኋላ እንደሚከተለው በማለት ይጠይቁታል፡-

“ስለሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ምን ታስባለህ? የተጠየቀው ሰው አማኝ ከሆነ የሚከተለውን መልስ ይሰጣል፡-

“እርሳቸው የአላህ ባሪያና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡” ከዚያም እንዲህ በማለት ይጠይቁታል፡-

“በጀሃነም የነበረህን ቦታ ተመልከት፡፡ አላህ ይህንን በጀነት መናፈሻዎች ቀይሮልሃል፡፡››

ሰውየው ሁለቱንም ቦታዎች ይመለከታል፡፡ ከዚያም አላህ በመቃብሩ ውስጥ ጀነትን የሚመለከትበት መስኮት ያደርግለታል፡፡

የሚጠየቀው ሰው ከሃዲ ወይም መናፍቅ ከሆነ ለመላእክቱ ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ይሰጣል፡-

“እኔ ስለዚህ ስለምትሉት ሰው የማውቀው ነገር የለም፡፡ ሌሎች ሰዎች ሲሉ የምሰማውን ዝም ብዬ ስደጋግም ነበር፡፡” ከዚያም እንዲህ ይባላል፡-

“ምንም የምታውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ስለዚህ አልተከተልካቸውም፡፡”

ከዚያ በብረት ዘንግ በሁለት ጆሮዎቹ መካከል ይመታል፡፡ በዚህ ጊዜ ታላቅ ጮኸትን ይጮሃል፡፡ ከሰውና ከጂን በስተቀር ይህን ጩኸቱን ሌሎች ፍጡራን ሁሉ ይሰሙታል፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም)

የነቢዩላህ ዳውድ (ዐ.ሰ.) ልጅ የሆኑት ነቢዩ ሱለይማን (ዐ.ሰ.)መሬቱን እያረሰ በነበረ አንድ ገበሬ አጠገብ ሲያልፉ ገበሬው እንዲህ አለ፡- "ያለምንም ጥርጣሬ የዳውድ ቤተሰቦች ታላቅ ንግስናን ተሰጥተዋል፡፡"

ይህን የገበሬውን ንግግር ነፋስ ለነቢዩ ሱለይማን (ዐ.ሰ.) ወስዶ ስላሰማቸው ከሚጓዙበት እንስሳ ላይ ወርደው ወደ ገበሬው አመሩና እንዲህ አሉት፡-

"ወዳንተ የመጣሁት የማይገባህን (ልትሸከመው የማትችለውን) ነገር እንዳትመኝ ላሳስብህ ነው፡፡" ይህን ካሉ በኋላ ቀጠል አድርገው እንዲህ አሉት፡-

"አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው አንድ ተስቢህ (አላህን ማጥራትና ማላቅ) ያለምንም ጥርጥር ዳውድና ቤተሰቡ ከተሰጡት ሃብትና ንግሥና ሁሉ ይበልጣል፡፡"

እውነቱን ለማየት ከቻልን በዚህች ዓለም ላይ በፍጹም ኢኽላስ የሰራናቸው መልካም ሥራዎች በመጪውና ዘላለማዊ በሆነው ዓለም ለሚኖረን የደስታና የስኬት ሕይወት ምክንያቶች ይሆኑልናል፡፡ በቁርአን እንደሚከተለው ተብሎ ተጽፏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَلۡتَنظُرۡ نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ لِغَدٖۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ
بِمَا تَعۡمَلُونَ ١٨ ﴾ الحشر: ١٨

*"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ማንኛይቱም ነፍስ ለነገ ያስቀደመችውን ትመልከት፡፡ አላህንም ፍሩ! አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው፡፡" (አል-ሐሽር፡18)*

ከሞት የምናመልጥበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡ ያለን ብቸኛና የሚያዋጣ አማራጭ ለእርሱ በቂ ዝግጅት አድርጎ መጠበቅ ብቻ ነው፡፡ የአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) እነዲህ ብለዋል፡-

“ነቢዩ ዳውድ (ዐ.ሰ.) ሃይማኖታቸውን በተመለከተ ልዩ ትኩረት የሚያደርጉና በጥልቀት የሚያስተውሉ ለክብራቸውም በጣም የሚጠነቀቁ ሰው ነበሩ፡፡ ምንጊዜም ከቤታቸው ሲወጡ የቤታቸውን በር ማንም ሊከፍተው በማይችል ሁኔታ የሚቆልፉ ሲሆን እስኪመለሱ ድረስ ማንም አይደፍራቸውም ነበር፡፡ አንድ እለትም እንደተለመደው ቤታቸውን ቆልፈው ወጡ፡፡ …ሲመለሱ ግን አንድ ሰው በቤታቸው ውስጥ ተቀምጦ ተመለከቱ፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉት፡-

“አንተ ማን ነህ?” ሰውዬው እንዲህ ሲል መለሰ፡-

“እኔ ማንንም ሌላው ቀርቶ ንጉስም ቢሆን የማልፈራ፣ ምንም ዓይነት ግርዶ የማይመልሰኝ ነኝ፡፡” ይህን አንደሰሙ ዳውድ (ዐ.ሰ.) እንዲህ አሉ፡-

“እንደዚያ ከሆነ በአላህ! አንተ የሞት መልአክ መሆን አለብህ፡፡ በአላህ ፈቃድ እንኳን ደህና መጣህ፡፡”

ይህ ከሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መልአኩ ነፍሳቸውን ይዞ ወደ ሰማየ ሰማያት መጠቀ…” (አህመድ)

ለሞት የተዘጋጁ ሰዎች ሞት በሚመጣበት ጊዜ የሚያሳዩት ሁኔታ ይህ ነው ፡፡

የሚከተለው ብልህነት የተሞላበት የአቡ ዘር (ረ.ዐ.) አባባል ለሞትና ከዚያም በኋላ ለሚጠብቁን የተለያዩ ፈተናዎች እንዴት መዘጋጀት እንዳለብን የሚያሳየን ግሩም ምሳሌ ነው፡-

“በማንኛውም ንብረትህ (ሃብትህ) ይገባኛል ባዮች የሆኑ ሶስት አካላት አሉ፡፡ የመጀመሪያው አንተ ራስህ ነህ፡፡ ሁለተኛው እድልህ ወይም እጣህ ነው፡፡ ይህም ጥሩ ይሁን መጥፎ፣ መከራ ወይም ሞት አንተን ሳያማክር ከች የሚል ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ወራሽህ ሲሆን ባፍጢምህ እስክትደፋና ውርስ እስኪያገኝ ድረስ ትእግስት በማጣት የሚጠባበቅህ

ነው፡፡ ከሞትክለት ወዲያውኑ አንተ የምትጠየቅበትን ሃብትህን መንትፎ ዘወር ነው፡፡ ስለሆነም አቅምህ ከቻለ በእነዚህ ሶስት ባለጋራዎችህ ላይ ክንድህ እንዳይዝል፡ (ቶሎ ቶሎ ብለህ ገንዘብህን ለመጪው ዓለም ሕይወትህ አሻግር)፡፡

ከሁሉም በላይ ልቅና የተገባው ጌታ እንዲህ ይላል፡-

﴿لَن تَنَالُواْ ٱلْبِرَّ حَتَّىٰ تُنفِقُواْ مِمَّا تُحِبُّونَۚ وَمَا تُنفِقُواْ مِن شَيْءٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٌ ٩٢﴾

*“የምትወዱትን እስከምትለግሱ ድረስ በጐን ሥራ (ዋጋውን) አታገኙም…” (አሊ-ዒምራን:92)*

“በዚህ ዓለም ላይ ምርጥ የሆነው ንብረቴ ይህ ግመል ነው፡፡ በጀነት እንደገና እንዳገኘው ስለምፈልግ አሁኑኑ ሰደቃ በመስጠት ወደዚያው ላሸጋግረው እፈልጋለሁ፡፡” (አቡ ኑአይም)

በኦቶማን ቱርኮች ወርቃማ ዘመን ይኖር የነበረ ኡቅባስ ኑረዲን ሐምዛ ኤፈንዲ የሚባል የታወቀ ምሁር ነበር፡፡ ይህ ሰው ገንዘቡን ከሞላ ጐደል ሁሉንም ያጠራቅም ነበር፡፡ ምክንያቱም ማውጣት ስለማይወድ ነው፡፡ ፈረስ አይጋልብም፣ አዲስ ልብስ ከመግዛት ይልቅ ያረጁ ልብሶችንና አሮጌ ጫማዎችን ማድረግን ይመርጥ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ገንዘቡን ዝም ብሎ ያጠራቅም ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ ሰዎች ዘንድ ኡቅባስ “ገንዘብ የሚያፈቅረው›› የሚል ቅጽል ስም ወጣለት፡፡

በኋላ ላይ መድረሳ አሳነጸ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ መስጊድ አስገነባ፡፡ ሁለቱንም ያስገነባው ሁሉ እየተዘባበተበት ባጠራቀመው ገንዘቡ ነበር፡፡ መስጊዱ ልዩ የሆነና ለምሁራን (ኡለማዎች) እና ለድሆች ሰዎችም ማረፊያ ያለው ሲሆን ለእነዚህ ሰዎችም መተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ ተቆርጦላቸው ነበር፡፡ ይህን ሁሉ በጐ ምግባር እንደሰራ የሰሙ ሰዎች በጣም የተደነቁና የተገረሙ ከመሆኑ የተነሣ በእርሱ ላይ እንዲህ እያሉ መቀለድ አመጡ፡-

“ያን ያክል ስትንገበገብለት የኖርከውን ገንዘብ መለየቱ እንዴት አስቻለህ?”

እርሱም የሚከተለውን ቁምነገርና ቀልድ የተቀላቀለበት መልስ ይሰጣቸው ነበር፦

“ውድ ጓደኞቼ! የተናገራችሁት ትክክል ነው፡፡ እንዳላችሁት ገንዘቤን በጣም እወደዋለሁ፡፡ ለዚህም ነው በዚህ ዓለም ላይ ጥየው ላለመሄድ የወሰንኩት፡፡ አዎን! እዚህ ተለይቶኝ እንዳይቀርና በመጪው ዓለምም አብሮኝ እንዲሆን አስቀድሜ ወደዚያው ማሻገሬ ነው (መድረሳና መስጊድ መስራቴ)፡፡››

አሊ (ረ.ዐ.) እንዲህ ይሉ ነበር፦

“ይህች ዓለም ጀርባዋን እየሰጠችንና እያለፈች ነው፡፡ መጪው ዓለም ደግሞ ከፊት ለፊታችን ሆኖ ይጠብቀናል፡፡ ሁለቱም የየራሳቸው ልጆች (ተከታዮች) አሏቸው፡፡ እናንተ የመጪው ዓለም ልጆች (ተከታዮች) እንጂ የዚህች ዓለም ተከታዮች አትሁኑ፡፡ ዛሬ የሥራ ጊዜ ሲሆን ሒሳብ የለም፡፡ ነገ ደግሞ ሂሳብ እንጂ ለሥራ የሚሆን ጊዜ የለም፡፡” (ቡኻሪ)

ይህን አባባል ፈተናውን ጨርሶ ከአዳራሽ ከሚወጣ ተማሪ ሁኔታ ጋር ማነጻጸር እንችላለን፡፡ ይህ ተማሪ ከዚያ በኋላ ጥያቄ ለመመለስ ወይም ውጤቱን ለማሻሻል ፈጽሞ አይችልም፡፡

ከዓሊ (ረ.ዐ.) ንግግር ተጠቃሚ የሆኑ የአላህ ወዳጆች የሚከተለውን ተናግረዋል፦

“ይህች ዓለም ጀርባዋን አቀብላን ስትሄድ መጪው ዓለም (አኺራ) ደግሞ ፊት ለፊታችን እየተጠባበቀን ይገኛል፡፡ ጀርባዋን ወደሰጠችው ጠፊ ዓለም ፊቱን ያዞረና አይቀሬ ለሆነው መጪ ዓለም (አኺራ) ደግሞ ጀርባውን የሰጠ ሰው አይደንቅምን?”

አቡ ደርዳእ (ረ.ዐ.) እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፦

“እኔ የምፈራላችሁ በዚህች ዓለም ፀጋዎች ትታለሉና በከንቱ ስሜቶቻችሁ ተጠርጋችሁ ትወሰደላችሁ ብዬ ነው፡፡ እነዚህ ፍላጐታችሁ የሚቀሰቀሱት እውቀትን ስትራቡ ነው፡፡ ያኔ ሆዳችሁን በምግብ ትሞላላችሁ (መንፈሳችሁ ግን ባዶ ይሆናል)፡፡ መጥፎ ጓደኛ እንዲህ ሲል ባልንጀራውን ይመክራል፡-

“ወንድሜ ሆይ! ና ከመሞታችን በፊት እንደሰት፡፡ እንብላ፣ እንጠጣ እንዲሁም የቻልነውን ያክል ነፍሳችንን እናስደስታት፡፡” (አቡ ኑዓይም)

ሱፍያን አስ-ሰውሪ ገና በወጣትነት እድሜያቸው ጀርባቸው ጉብጧል፡፡ ይህ ለምን ሊሆን እንደቻለ ተጠይቀው ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል፡-

“ብዙ እውቀት ያስገበየኝ አንድ መምህር (ኡስታዝ) ነበረኝ፡፡ ሊሞት በጣእር ላይ እያለ የእምነት ማረጋገጫ የሆነውን ከሊማ እንዲል ደጋግሜ ብወተውተውም ያንን ከሊማ ከአንደበቱ ሊያወጣ ሳይችል ሞተ፡፡ ይህን ክስተት ካየሁ በኋላ በሃሳብ ጉበጥኩ፡፡››

ከነቢያት ውጪ ያለ ማንንም ሰው ቢሆን ስለፍጻሜው (ሑስነል ኻቲማው) መስጋቱ ተገቢ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የአላህ ነቢይ የነበሩት ዩሱፍ (ዐ.ሰ.) እንኳን የሚከተለውን ዱዓ ማድረጋቸው በቁርዓን ተጠቅሷል፡-

﴿ فَاطِرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ أَنتَ وَلِىِّۦ فِى ٱلدُّنْيَا وَٱلْءَاخِرَةِ ۖ تَوَفَّنِى مُسْلِمًا وَأَلْحِقْنِى
بِٱلصَّٰلِحِينَ ﴿١٠١﴾ ﴾ يوسف: ١٠١

*“...የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ! ...ሙስሊም ሆኜ ግደለኝ፣ ከመልካሞቹም አስጠጋኝ (አለ)፡፡” (ዩሱፍ፡101)*

እንግዲህ በየጊዜው ወህይ (ራዕይ) የሚወርድለትና የመለኮት ምስጢር የሚገለጽለት ነቢይ ይህን ያክል ለፍጻሜው ከሰጋ እኛማ እንዴት! ለዚህም ነው ምእመናን ሁልጊዜም አላህን በመፍራትና የእርሱንም ምኅረት በመከጀል መካከል ሆነው ፈጣሪያቸውን እንዲያመልኩ የሚመከሩት፡፡

ሸይኽ በልሂ አንድ ጊዜ በአንድ መቃብር አጠገብ ሲያልፉ በጥንቃቄ ያስተውሉ ጀመር፡፡ ከዚያም አብረዋቸው ለነበሩት ሰዎች እንዲህ አሉ፡-

“እዚህ ከተቀበሩት አብዛኞቹ ይህች ዓለም እንዳታለለቻቸው በአሁኑ ጊዜ ተገንዝበዋል፡፡”

“ለምን?” የሚል ጥያቄ ሲቀርብላቸው እንዲህ በማለት መለሱ፡-

“በዙዎቹ በሕይወት በነበሩ ጊዜ ንብረት፣ ሃብት፣ ቤት፣ የመጓጓዣ እንስሳ፣ ቤተሰብ፣ የአትክልት ቦታ (ማሳ) እንዲኖራቸው ጧት ማታ ይደክሙ አልነበረምን? ሆኖም ግን አሁን እንደምታዩት ያንን ሁሉ ነገር ጥሰው ከአፈር ውስጥ በስብሰዋል፡፡…”

የአላህ ወዳጅ የነበሩት የረቢእ ኢብን ሃይሰም (አላህ ይዘንላቸውና) ንግግርና ተግባር አንድ ሰው ለሞትና ለመጪው ዓለም ሕይወቱ ምን ያክል ማሰብና መጨነቅ እንዳለበት ያስገነዝባል፡-

ረቢእ ኢብን ሃይሰም አንድ ጊዜ ከቤታቸው ጓሮ የመቃብር ጉድጓድ ቆፈሩ፡፡ ከዚያ በኋላ ቀልባቸው የደረቀና ከአላህ የራቁ በመሰላቸው ጊዜ ሁሉ እዚያ ጉድጓድ ውስጥ እየሄዱ በመጋደም ፍጻሜያቸውን ያስታውሱ ነበር፡፡ ይህን የሚያደርጉት አንድ ወቅት የሚገቡበት ቤታቸው ስለሚሆነው ቀብር እያሰቡ ሥራቸውን ለማስተንተንና አካሄዳቸውን ለማሳመር በማሰብ ነው፡፡ እዚያ ውስጥ ገብተውም እያለቀሱ አላህን ምሕረት ይጠይቁት ነበር፡፡ የሚከተለውንም የቁርአን አንቀጽ ያነብባሉ፡-

﴿ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَ أَحَدَهُمُ ٱلۡمَوۡتُ قَالَ رَبِّ ٱرۡجِعُونِ ﴿٩٩﴾ لَعَلِّيٓ أَعۡمَلُ صَٰلِحٗا فِيمَا تَرَكۡتُۚ ﴾

*“አንዳቸውም ሞት በመጣበት ጊዜ እንዲህ ይላል ጌታዬ ሆይ! (ወደ ምድረ ዓለም) መልሰኝ፡፡ በተውኩት ነገር በጐን ሥራ ልሰራ እከጅላለሁና፡፡” (አል-ሙእሚኑን 99-100)*

ከዚያ ራሳቸው ከማሱት የቀብር ጉድጓዳቸው ሲወጡም እንዲህ ይሉ ነበር፡-

“ረቢእ ሆይ! ተመልከት፤ ዛሬ ወደ ሕይወት የመመለስ እድል አግኝተሃል። ሆኖም ግን ይህ ምኞትህ ፈጽሞ ተቀባይነት የማያገኝበት የምር ቀን ይመጣል። ስለዚህ ግሳቤህን ያዝ። ከዚያም መልካም ሥራዎችህን ለማብዛት ተጣደፍ። በአላህ መንገድ የምታደርገውን ትግልህንና ለሞት የምታደርገውንም ዝግጅት አጧጡፍ።”…”

የኢማም አል-ገዛሊ ቀጣዩ ምክር ምንኛ የሚያምር ነው። እንዲህ ይላሉ፦

“ዘወትር የሱብሂ (ፈጅርን) ሶላት ከሰገደ በኋላ እያንዳንዱ አማኝ ከነፍሱ ጋር ፊት ለፊት ይፋጠጥና የተወሰነ ውል ይዋዋላል። ይህም ውል (ኮንትራክት) ልክ አንድ ነጋዴ ለሸሪኩ (ባልደረባው) የመነገጃ ወረቱን (ካፒታሉን) ሲያስረክበው አብሮ ማስጠንቀቂያም እንደሚሰጠው ብጤ ነው። የሰውም ልጅ በየእለቱ ነፍሱን እንዲህ እያለ ከማስጠንቀቅ ወደ ኋላ ማለት የለበትም።

“የእኔ ወረቴ (ካፒታሌ) ሕይወቴ ነው። ሕይወቴ አበቃ ማለት ወረቴ (ካፒታሌ) ከሰረ፣ ትርፍና ጥቅማጥቅም አበቃለት ማለት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ቀን አዲስ ቀን ነው። ከሁሉም የበላይ የሆነው ጌታዬ አላህ ይህን ቀን እኖርበት ዘንድ ፈቃዱ ሆኖ እነሆ ሰጥቶኛል። ጌታዬ ነፍሴን ወስዷት ቢሆን ኖሮ ያልቅልኝ ነበር። እኔ አሁንም ቢሆን ይህንን እድል የምመለከተው ጌታዬ ነፍሴን ከወሰዳት በኋላ ለአንድ ቀን መልካም ሥራ እሰራ ዘንድ ፈቃዱ ሆኖ እንደለቀቀልኝ ነው። እንበልና ነፍሳችሁ ከወጣች በኋላ ተመልሳ እንድትገባ ተደረገች። ከዚያ እለት በኋላ ለቅጽበት እንኳን ኃጢአት ትፈጽማላችሁን? ከጊዜያችሁ ውስጥስ አንድ ሰከንድ እንኳን ያለአግባብ ታባክናላችሁን?

“ልብ አድርጉ። አንድ ቀን ከነሌሊቱ 24 ሰዓታት ያሉት መሆኑ ይታወቃል። በፍርዱ ቀን 24 የሚሆኑ ያታሸጉ ሳጥኖች በሰው ልጅ ፊት በእያንዳንዱ እለት ይቀርቡለታል። ከእነዚያ ሳጥኖች መካከል አንዱ ይቀርብና ይከፈታል። ባሪያው በውስጡ ያለውን ብርሃን ያያል። ይህም ሊሆን የቻለው በዚያ ሰዓት በሰራው መልካም ሥራ ምክንያት ሽልማት (ምንዳ) ስለተጻፈለት ነው። አላህ የሰጠውንም ፀጋ ሲመለከት በጣም

ይደሰታል፡፡ በዚያች አንድ ሰዓት ውስጥ በሰራው መልካም ሥራ ያገኘው ደስታ ጀሃነም ውስጥ ላሉ ሰዎች ቢካፈል ስቃያቸውን ያስረሳቸው ነበር፡፡ ሁለተኛው ሳጥን ሲከፈት ውስጡ ጨለማና በአስቀያሚ ሽታ የተሞላ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው በዚያ ሰዓት ባሪያው አላህን በማመጽ በማሳለፉ ምክንያት ነው፡፡ ከዚያም ባሪያው በዚህ ሁኔታ በጣም ይከፋል፡፡ ይህ ሃዘኑ ጀነት ውስጥ ለሚቀማጠሉት አማኝ ነፍሳት ቢካፈል ደስታቸውን ማጣጣም እንዳይችሉ ያደርጋቸው ነበር፡፡ ሶስተኛው ሳጥን ይከፈታል፡፡ በሚያስደንቅ አኳኋን ባዶ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህ የሚያሳየው በዚያ ሰዓት ባሪያው በእንቅልፍ በመወሰዱ ምክንያት ነበር፡፡ ይህም የተፈቀደ (ሐላል) ድርጊት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሥራ በሚመዘንበት ጊዜና ባሪያው ትንሽም ብትሆን መልካም ሥራ በጣም በሚፈልግበት ሰዓት ያችን ሰዓት በእንቅልፍ በማሳለፉ በፀፀት ይቃጠላል፡፡…

እንግዲህ ጉዳዩ ይህን የሚመስል ከሆነ አንቺ ሁልጊዜም በመጥፎ የምታዝኝ ነፍሴ ሆይ? መልካም ሥራ የመሥራት እድሉ አሁን በእጅሽ ይገኛልና ሳጥኑን በእኩይ ወይም በጨለማ ከመሙላት ተቆጠቢ፡፡ ባዶ ሆኖ እንዳያሳፍረኝም አትጉትጉቺኝ፡፡ ሰነፍና ደካማ እንድሆን አታድርጊኝ፡፡ እንደዛ ከሆንኩ ከታላቅ የተራራ አናት ቁልቁል ወርጄ በእሳት ወለል ላይ መደፋቴ አይቀርምና፡፡

ኻሊድ ባግዳዲ በተለያዩ የሳይንስ ዘርፎች ጫፍ ላይ የደረሰ ጠቢብ ቢሆንም የፍጻሜው ነገር ሁልጊዜም የሚያስጨንቀው ሰው ነበር፡፡ መክተባት በተባለው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፡-

“ከሁሉም በላይ በላቀው ጌታዬ አላህ እምላለሁ! እኔ በእርሱ ዓይን መልካምና ተቀባይነት አለው ብዬ የምተማመንበት አንድም ሥራ የለኝም፡፡ መልካም ሥራን በተመለከተ ዋጋ ቢስ መሆኗን እስካላሰባችሁ ድረስኮ ታላቅ ኪሳራ ላይ ወድቃችኋል፡፡ ይህም የመሃይምነት ጫፍ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡….”

ከዚህ በመቀጠል የሚቀርበው ደግሞ ኻሊድ ለጓደኛው ከጻፈው ረዘም ያለ ደብዳቤ የተወሰደ ሲሆን ለመጨረሻው እስትንፋሱ ምን ያህል ይዘጋጅ እንደነበር ያሳያል፡-

"…ራስህን በመጪው ዓለም ለሚጠቅምህና ነፍስህ አካልህን ተለይታ ስትወጣ በሚያገለግልህ ተግባር ላይ እንደጠመድክ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እንዲሁም የዚህችን ጠፊ ዓለም አታላይ አካሄድ ወደ ጐን ብለህ የታላቁን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሱናዎች በክራንቻ ጥርስህ እንደያዝክ እገምታለሁ፡፡ ምስኪን ለሆነው ወንድምህ ለኻሊድ ዱዓ ማድረግህን አትዘንጋ፡፡ አላህን ሲገናኝ መጨረሻው ያማረና በመልካም ሁኔታ ተሰንቆ እንዲሄድ በዱዓህ አስታውሰው፡፡" (መክተባት ኻሊድ ፡ ገጽ፡ 175)

ታላላቅ የሚባሉት የአላህ ወዳጆች በሰሩት መልካም ሥራ ያን ያክል የማይመኩና የአላህን እዝነት ብቻ የሚሹ መሆኑን ከዚህ ትረካ መረዳት አይገድም፡፡

በአንድ ወቅት በአንድ ከተማ መውጫ በኩል የሸቀጣሸቀጥ መደብር ያለው ሰው ይኖር ነበር፡፡ የመቃብሩ ስፍራ የሚገኘው በእርሱ ሱቅ በኩል ስለነበር ሰዎች አስከሬን ተሸክመው ሲሄዱ በተመለከቱ ቁጥር ከአጠገቡ በሚገኝ ሳጥን ውስጥ አንድ ጠጠር ያስገባል፡፡ በመጨረሻም በወሩ መጨረሻ ላይ ሳጥኑን ይከፍትና ጠጠሮቹን በመቁጠር ስንት ሰው በአንድ ወር ውስጥ ብቻ እንደሞተ ይናገራል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም ይህ ሰው በዝንጋቴ ውስጥ ተውጦ እያለ እርሱንም ሞት ጐበኘው፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጓደኛው ይህንን ዜና ሳይሰማ ሊጠይቀው ሲመጣ ሱቁ ተዘግቷል፡፡ ጐረቤቶቹን ሲጠይቅ የመሞቱን ዜና አረዱት፡፡

ብዙ ሰዎች ይህ ሰው ያሳየውን የቂልነት ባሕሪ ሲያንፀባርቁ ይታያሉ፡፡ በእነርሱ እምነት ሁልጊዜም የሚሞቱት ሌሎች ብቻ ናቸው፡፡ ሞት እነርሱንም አንድ ቀን እንደሚጐበኛቸው ቢያውቁም በጣም ሩቅ በሆነ ጊዜ እንደሚሆን ራሳቸውን በማሳመን ዝም ብለው ይቀመጣሉ፡፡

የኦቶማ ቱርክ መሪ የነበረው የቡዝ ሱልጣን ሳሊም ኻን አገልጋይ ሐሰን ቃን እንዲህ ይላል፡-

“አንድ ጊዜ በሱልጣን የቡስ ጀርባ ላይ እባጭ ወጣበት፡፡ ያ እባጭ በአጭር ጊዜ እያደገ ሄዶ በጀርባው ላይ ትልቅ ክፍተት ፈጠረ፡፡ የሱልጣኑን ጉበትና ውስጣዊ አካላት በዚያ እባጭ ውስጥ አሾልከን ማየት ጀመርን፡፡ በዚሁ እባጭ የተነሳም በጣም በመታመሙ ልክ እንደቆሰለ አንበሳ ሆነ፡፡ እንደዚያም ሆኖ ያጋጠመውን ድክመት ለመቀበል ባለመፈለግ የጦር አዛዥነቱን ሚና ለመጫወት ሲሞክር ይታይ ነበር፡፡ ከዚያም እኔ ጠጋ ብዬ ያለበትን ሁኔታ በለዘብታ አስረዳሁት፡፡ እርሱም እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፡-

“ሃሰን ቃን ሆይ! ይህ ያለሁበት ሁኔታ ምንድን ነው?”

እኔም ሁኔታውን ሳጤነው የመጨረሻው ሰዓት መቃረቡንና ወደ መጪው ዓለም ሊሽጋገር መሆኑን በማወቁ የመለያየታችን ነገር ልቤን እየበላውና በሃዘን ተውጬ እንዲህ አልኩት፡-

“የእኔ ሱልጣን ሆይ! ወደ ልቅናው ባለቤት አላህ የምትሄድበት ጊዜ የተቃረበ ይመስላል፡፡”

ያ ባለግርማ ሱልጣን ፊቱን ወደእኔ ካዞረ በኋላ በመደነቅ እንዲህ አለ፡-

“ሃሰን! እስከዚህች ሰዓት ድረስ ስለእኔ ምንድን ነው የገመትከው? ከኃያሉ አላህ ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ አንዳች ችግር አይተህብኛልን?”

በዚህ አነጋገሩ ሃፍረት ስለያዘኝ እንዲህ አልኩት፡-

“አላህ ይቅር ይበልህ ሱልጣን ሆይ! እኔ ለማለት የፈለግኩት እንደዚያ አይደለም፡፡ እኔ ልገልጽልህ የፈለግኩት ከእንግዲህ እየተዳከምክ በመሆኑ እረፍት ያስፈልግሃል፡፡ ይህ ሰዓት እንደሌላው ጊዜ አይደለምና ጥንቃቄ አድርግ ነው፡፡”

ያ ታላቅ ሱልጣን ከዚያ በኋላ ለረዥም ጊዜ በሃሳብ ሰምጦ ከቆየ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ እንዲህ አለኝ፡-

“ሃሰን ሆይ! ሱራ ያሲንን አንብብልኝ፡፡”

ዓይኖቹ በእንባ ጭጋግ እንደተጋረዱ የያሲንን ምዕራፍ ማንበቤን ቀጥየ “ሰላም” ከሚለው ላይ ስደርስ ነፍሱን ለጌታው ሰጥቶ ፀጥ አለ፡፡

ጠቅለል ባለ አገላለጽ ሕይወታቸውን በሙሉ አላህን ሲያመልኩና ከእርሱ ጋር የነበራቸው ግንኙነት መልካም ያልነበረ ሰዎች ይህን ዓይነት ፍጻሜ አያገኙም፡፡

ሱልጣን ሙራድ ሁለተኛ (ዳግማዊ ሙራድ) የራሱን ምቾት ለማደላደል እምብዛም የሚጨነቅ ሰው አልነበረም፡፡ የእርሱ የጧትና የማታ ጭንቀት የአላህን ውዴታ ለማግኘት ነበር፡፡ ይህንን ለመጐናፀፍም የራሱን ነፍስ አሳልፎ ለመስጠት ቁርጠኛና ለእምነቱ የጠነከረ ሰው ነበር፡፡ የእርሱ የመጨረሻ ምኞት ከአላህ ጋር ሲገናኝ በልቡ ውስጥ የጋለ እምነት እንደጨበጠና በፍርዱም ቀን ኃጢአት የሌለበትና የማይወቀስም መሆን ነው፡፡ ወንዱንና ሴቷን ልጁን ከዳረ በኋላ ሚኒስትሩ ለነበረው ጋንዳርሊ ኢብራሂም ፓሻ እንዲህ አለው፡-

“ጋንዳርሊ ሆይ! ለአላህ ምስጋና ይድረሰው፡፡ በዚህ ዓለም ላይ ለልጆቻችን ያለብንን ኃላፊነት በእርሱ መልካም ፈቃድ እነሆ ፈፅምን፡፡ ከዚህ በኋላ የሚቀረን በልባችን ሙሉ እምነት እንደጨበጥን ወደርሱ መሄድ ብቻ ነው…”

ሙዛፊር የተባለው የቱርኮች ወታደራዊ መኮንን በዳርዳኔል ጦርነት ታላቅ ጀብዱ የፈፀመ ነው፡፡ ከዚያም ወደምስራቁ አቅጣጫ ተዛውሮ በታላቅ ጀግንነት ሲዋጋ ክፉኛ ቆስሎ ወደቀ፡፡ ነፍሱ ልትወጣ በተቃረበችበት የመጨረሻ ሰዓት በምላሱም ሆነ በዓይኑ የፈለገውን ነገር መግለጽ አይችልም ነበር፡፡ ከዚያም ከኪሱ ውስጥ አንድ ፖስታ አወጣና ከመሬት ላይ ከተንጣለለው ደሙ በእንጨት እያጠቀሰ እንደሚከተለው በማለት ጻፈ፡-

“ቂብላ በየት በኩል ነው?”

መሞቻው መቃረቡን ያወቁት በዙሪያው ያሉ ባልደረቦቹ ጥያቄውን በማሟላት ወደቂብላ አዙረው አጋደሙት፡፡ በዚያ ባለበት ሁኔታ በአንድ በኩል ሰማእት (ሸሂድ) ሆኖ የመሞቱ ነገር ቢያስደስተውም በሌላ በኩል ደግሞ ሃገሩን ከጠላት የማዳኑ ግዳጅ ውስጡን እያብከነከነው ስለነበር በዚያ ፖስታ ላይ አሁንም በደሙ እያጠቀሰ የሚከተለውን ጻፈ፡-

“ተዋጊ ኃይላችን ለአላህ ብሎ የጀመረውን ጅሃድ በእኔ መሞት ታውኮ እንዳይቋረጥ አደራ፡፡”

ሶስተኛውን መልእክቱን ለመጻፍ ሞክሮ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሰዓቱ አልቃበት ነበር፡፡ እናም ወደ ፈጣሪው ተጓዘ፡፡

እንዲህ ዓይነት መልካም ፍጻሜ የታደሉ ሰዎችን ኃያሉ አላህ በሚከተለው የቁርአን አንቀጽ እንዲህ ሲል አብስሯቸዋል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ قَالُواْ رَبُّنَا ٱللَّهُ ثُمَّ ٱسۡتَقَٰمُواْ تَتَنَزَّلُ عَلَيۡهِمُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ أَلَّا تَخَافُواْ وَلَا تَحۡزَنُواْ وَأَبۡشِرُواْ بِٱلۡجَنَّةِ ٱلَّتِي كُنتُمۡ تُوعَدُونَ ٣٠ نَحۡنُ أَوۡلِيَآؤُكُمۡ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِۖ وَلَكُمۡ فِيهَا مَا تَشۡتَهِيٓ أَنفُسُكُمۡ وَلَكُمۡ فِيهَا مَا تَدَّعُونَ ٣١ نُزُلٗا مِّنۡ غَفُورٖ رَّحِيمٖ ٣٢ ﴾ فصلت: ٣٠ - ٣٢

*“እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉ፣ ከዚያም ቀጥ ያሉ አትፍሩ አትዘኑም በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ፤ በማለት በእነርሱ ላይ መልአክት ይወርዳሉ፡፡ እኛ በቅርቡሙም ሕይወት በመጨረሻይቱም ረዳቶቻችሁ ነን፡፡ ለእናንተም በእርሷ ውስጥ ነፍሶቻችሁ የሚሹት ሁሉ አላችሁ፡፡ ለእናንተም በእርሷ ውስጥ የምትፈልጉት ሁሉ አላችሁ፡፡ መሀሪ አዛኝ ከኾነው አላህ መስተንግዶ ሲሆን (ይባላሉ)፡፡” (ፉሲለት፡30-32)*

የዚህ ታላቅ ብስራት ተቋዳሾች በማድረግ ይባርከን ዘንድ አላህን እንለምናለን፡፡ አሚን፣

***=ተፈጸመ=***